# ክፍል አንድ

# አጠቃላይ

## 1. መግቢያ

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችሉ ፓሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባትና በአግባቡ በማጤን እንዲሁም በአምስት ዓመቱ (2003-2007) የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተመለከቱትን ሃገራዊ አቅጣጫዎችና ግቦች መሠረት በማድረግ የተዘጋጀውን የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድን መሠረት በማድረግ ይህ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የ2005 በጀት ዓመት መሪ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

ይህ ዕቅድ በአጠቃላይ **አስራ ሁለት ዋና ዋና ሥራዎችን** ያካተተ ነው፡፡ ዕቅዱ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ደረጃ የቅርብ ክትትል የሚደረግባቸው ቁልፍና ዋና ዋና ሥራዎች ላይ በማተኮር፣ መነሻ ሁኔታዎችን በመዳሰስ፣ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን በመለየት እና የአፈጻጸም አቅጣጫዎችን በማመለላከት የተዘጋጀ ነው፡፡ እነዚህ ዋና ዋና ሥራዎች አፈጻጸማቸውን መመዘን ይቻል ዘንድ በግቦች ተከፋፍለው ከነክብደታቸው፣ የአፈጻጸም መለኪያዎቻቸውና ኢላማዎቻቸው በድርጊት መርሃ-ግብር ውስጥ በግልጽና በዝርዝር ተቀርጸዋል፡፡ በአፈጻጸሙ ሂደት በማስፈጸም አቅም ግንባታ፣ በሚዛናዊ ውጤት ተኮር ሥርዓት ዝርጋታ ሂደት የትኩረት መስኮች፣ በለውጥና በልማት ሠራዊት ግንባታ ሥራዎች እንዲሁም በዕቅድ ዝግጅት፣ በአፈጻጸም ክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስ ሥራዎች ላይ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡

ዕቅዱ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በየደረጃው የውስጥ ውይይት ተካሂዶበት እንዲዳብር የተደረገ ሲሆን በተጨማሪም ከግንቦት 9 - 10 ቀን 2004 በተካሄደው የክልሎች፣ የከተማ አስተዳደሮች እና የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተቋማት የሚገኙበት የሴክተር ጉባዔ ላይ ቀርቦ የዳበረ እና የጋራ መግባባት ላይ የተደረሰበት ነው፡፡ በመሆኑም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥር የተደራጁ ቢሮዎች፣ ተጠሪ ተቋማት፣ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ይህንን መሪ ዕቅድ መሰረት በማድረግ እንዲሁም ሌሎች መደበኛ ሥራዎቻቸውን አካተው ዝርዝር ዕቅዳቸውን እንደሚያዘጋጁ ይጠበቃል፡፡ የእነዚህ ተቋማት ዕቅድ በለውጥና የልማት ሠራዊት ግንባታ እንዲሁም በዘርፉ የልማት ሥራዎች ዋና ዋና ግቦች እና ተግባራት ላይ ያተኮሩ ሆነው ይዘጋጃሉ፡፡

የዕቅድ ሰነዱ **በስድስት ክፍሎች** የተደራጀ ነው፡፡ **በክፍል አንድ** አጠቃላይ በሚለው ምዕራፍ ሥር መግቢያውን ጨምሮ የሚኒስቴር መ/ቤቱን ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴት፣ በሴክተሩ የተለዩ የትኩረት

መስኮች እና ተግባርና ኃላፊነት የቀረበበት ነው፡፡ **በክፍል ሁለት** የዕቅዱ መነሻ ሁኔታዎች የተገለጸበት ሲሆን በዚህ ርዕስ ሥር የዘርፉ የ2004 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ተገምግሞ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ተቀምጠዋል፡፡ **በክፍል ሦስት** የ2005 በጀት ዓመት ዕቅድ በዋና ዋና ሥራዎች ተከፋፍሎ የቀረበ ሲሆን የእያንዳንዱ ዋና ዋና ሥራዎች ዓላማዎች፣ ግቦችና ዝርዝር ተግባራት ተዘርዝረው የፕሮግራም በጀትም ቀርቧል፡፡ **በክፍል አራት** ስጋቶችና የመፍትሔ አቅጣጫዎች የተመላከቱ ሲሆን **በክፍል አምስት** ደግሞ የዕቅድ አፈጻጸማችንን ለመከታተል የሚያስችል የአመራር፣ የክትትል፣ የግምገማና ግብረ-መልስ ሥርዓታችንን አካቷል፡፡ በመጨረሻም **በክፍል ስድስት** የዕቅድ ማጠቃለያ ተቀምጧል፡፡

## 2. ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴቶች እና ሥልጣንና ኃላፊነት

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የአመራር ሚና የሚጀምረው ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ሥልጣንና ኃላፊነት እንዲሁም በሥሩ ካሉ የቢሮዎች/ተቋማት የሥራ ባህሪና አሁን ከሚሰራበት ነባራዊ ሁኔታ ሲሆን የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ራዕይና ተልዕኮ ደግሞ ከአጠቃይ ሃገራዊ እና ክፍለ-ኢኮኖሚያዊ ራዕይ የሚመነጭ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ ከዚህ በታች በቀረበው ሁኔታ ተቀርቧል፡፡

### 2.1. ራዕይ

**"ለኑሮ ምቹና ተወዳዳሪ የሆኑ ከተሞች እና ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በ2012 ተፈጥሮ ማየት"፡፡**

### 2.2. ተልዕኮ

የተቋሙን ተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላትን በማስተባበርና በማቀናጀት ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት በከተሞች እንዲቀርብ በማድረግ ከተሞች የልማት ማዕከላት እንዲሆኑና ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በመገንባት ዜጎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ነው፡፡

### 2.3. እሴቶች

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ያስቀመጠውን ራዕይ፣ ተልዕኮና ዓላማ ለማሳካትና በተሰጠው ሥልጣንና ተግባራት መሠረት ሃላፊነቱን ለመወጣት የሚከተሉት መሰረታዊ እሴቶች ሆነው ተቀምጠዋል፡፡

**የተቋም የጋራ እሴቶች፡-**

1) ግልጸኝነት፤ዕውነተኝነትና፣ተጠያቂነት አሠራር መርህን ተከትዬ እሠራለሁ፣
2) ለውጤታማነትና ለቅልጥፍና ዘወትር እተጋለሁ፣
3) ሁሌም በማያቋርጥ የመማርና የመማማር ሂደት ላይ መሆኔን እገነዘባለሁ፣

**ከጋራዎቹ በተጨማሪ የአመራር እሴቶች ደግሞ፡-**

4) ለህዝብ ጥቅም ቅድሚያ መስጠት እንዳለብኝ አምናለሁ፣

5) ሁሉን ሰው እኩል ማየትና የተለያዩ ሃሳቦችን በአግባቡ ማስተናገድ የኃላፊነት ግዴታዬ መሆኑን እገነዘባለሁ፡፡

## 2.4. የመሥሪያ ቤታችን የትኩረት መስኮች

1) ቀልጣፋና ውጤታማ አሠራርና አመራር ማረጋገጥ፣
2) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የተወዳዳሪነት አቅም ግንባታ፣
3) የላቀ የካዳስተር አፈጻጸም፣
4) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የተወዳዳሪነት አቅም ግንባታ፣ እና
5) የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶችን ማብቃት ናቸው፡፡

## 2.5. የመሥሪያ ቤታችን አበይት ዋና ዋና ተግባራት እና የትኩረት ቅደም ተከተላቸው

1) የሥራ ዕድል ፈጠራና የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራዞች ልማትን ማስፋፋት፣
2) የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ሥርዓት ማዘመን፣
3) የከተማ የመኖሪያ ቤቶች አቅርቦት ማመቻቸት፣
4) የከተሞች መልካም አስተዳደር ማጠናከርና የማስፈጸም አቅም ግንባታን ማፋጠን፣
5) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ማጠናከር፣
6) የከተሞች መሠረተ-ልማት ማስፋፋት፣ እና
7) የከተሞች ጽዳትና አረንጓዴ ልማት ማጠናከር ናቸው፡፡

## 2.6. የሥልጣንና ኃላፊነት ትንተና (Mandate Analysis)

ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በአዋጅ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በሦስት በመክፈል እንደሚከተለው ለማየት ተሞክሯል፡፡ ይኸውም ለተቋሙ ብቻ የተሰጠ ሥልጣን፣ ከሌሎች ተቋማት ጋር በጋራ የተሰጠ ሥልጣን እና ለተቋሙ የተሰጡ ሥልጣንና ኃላፊነቶችን ሆነው ወደታችኛው ተቋማዊ እርከኖች በማውረድ የሚከናወኑ ናቸው፡፡ እነዚህም በአብዛኛው በደንብና መመሪያዎች የታገዘ ክትትል፣ ሙያዊና ሌሎች ከፈቃድ ጋር የተገናኙ አገልግሎቶችን መስጠትና የመሳሰሉትን ተግባራት ማከናወንን የሚመለከቱ ናቸው፡፡

### 2.6.1. ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በወል የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት

የሚኒስቴር መ/ቤቱ በ1998 በአዋጅ ቁጥር 471/98 እና በ2003 በአዲስ መልክ በአዋጅ ቁጥር 691/2003 ሲዋቀር የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባራት እንዲያከናውን ኃላፊነት ተጥሎበታል፡፡

1) የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፣
2) ፖሊሲዎችንና ሕጎችን ያመነጫል፣ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣
3) የፌዴራል መንግሥቱ ሕጎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጠል፣

4) የጥናትና ምርምር ተግባሮችን ያከናውናል፣ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያቀናብራል፣ ያሰራጫል፣
5) ለክልሎች እንደአስፈላጊነቱ ድጋፍና ምክር ይሰጣል፣ እንዲሁም ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር አስተባባሪነት የተቀናጀ ድጋፍ ያደርጋል፣
6) በሕግ መሠረት ውሎችንና ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ያደርጋል የሚሉ ናቸው።

### 2.6.2. ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ብቻ የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት

እነዚህ በአዋጅ ቁጥር 471/1998 ለቀድሞው ሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባሮች እና በአዋጅ ቁጥር 691/2003 ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራትን ያካትታል። እነዚህም፡-

1) አከታተምን በሚመለከት ጥናት ያካሂዳል፣ የከተሞችን ደረጃ መመዘኛ ያወጣል፣
2) ከተሞች የአካባቢያቸው የልማት ማዕከል እንዲሆኑ ሁለገብና የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል፣
3) ከተሞች የአገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ የአቅም ግንባታ እገዛ ያደርጋል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በከተሞች ልማት መሰረት የማሰልጠኛና የምርምር ተቋሞችን ያቋቁማል፣ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ለኮንስትራክሽንና ለከተማ ልማት ዘርፍ የሚያስፈልገውን የሠው ሃይል እንዲሰለጥን ያደርጋል፣ እንደአስፈላጊነቱም የማሰልጠኛ ተቋሞችን ያቋቁማል፣
4) ከክልሎች ጋር በመተባበር የከተሞች ልማት ከገጠር ልማት ጋር በተቀናጀ መንገድ የሚከናወንበትን ሁኔታ በሚመለከት ጥናት ያደርጋል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ያግዛል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣
5) ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ የሆኑ የከተማ አስተዳደሮችን የሥራ እንቅስቃሴዎች ይከታተላል፣
6) በፌዴራል መንግሥት ሆነ በክልል በጀት የሚከናወን የመንግሥት ኮንስትራክሽን በሚመለከት የዲዛይን፣ የኮንስትራክሽንና የቁጥጥር ሥራዎች በዓለም አቀፍ ጨረታ ለውጪ ሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የሚሰጡበትን ሁኔታ ይወስናል፣
7) የጥቃቅንና የአነስተኛ ተቋማት ልማት እንዲስፋፉ ያደርጋል፣
8) የከተማ ልማት ሥራ ከድህነት ቅነሳ ጋር የተቀናጀ እንዲሆን ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ለተግባራዊነታቸውም ድጋፍ ይሰጣል፣
9) ለሌሎች አካላት በሕግ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የኮንስትራክሽን ሥራ ደረጃዎች ያወጣል፤ መከበራቸውን ይከታተላል።
10) ዓለም አቀፍ የተወዳዳሪነት ብቃት ያለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለመገንባት የሚያስችሉ የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፣
11) በፌዴራል መንግስት በጀት ለሚሰሩ ሕንፃዎች ዲዛይኖችና የግንባታ ውሎች እንዲዘጋጁ በማድረግና የግንባታ ሥራዎችን በመቆጣጠር ረገድ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣

12) መሐንዲሶችና አርክቴክቶችን ይመዘግባል፣ የሙያ ችሎታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ የሥራ ተቋራጮችንና የአማካሪዎችን ደረጃ ይወስናል፣ ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ውስጥ መሥራት የሚችሉ ሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የሥራ ተቋራጮችና የአማካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣

13) በአገር ውስጥ የሚመረቱ የኮንስትራክሽን እቃዎችን ዓይነትና ጥራት ለማሻሻል የሚረዳ ምርምር ያካሂዳል፣

14) ለሌላ የመንግሥት አካል በህግ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት ሥር የሚገኙ ቤቶች አስተዳደር በአግባቡ እንዲከናወን መደረጉን ያረጋግጣል፣

15) ከክልሎች በሚቀርብለት ጥያቄና በሚያወጣው ቅደም ተከተል መሠረት የከተሞች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሌሎች ሁኔታዎች ተጠንተው መሪ ኘላኖች እንዲዘጋጁላቸው ያደርጋል፣ አፈፃፀማቸው በሚመለከት ለክልል መስተዳደሮች የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፣

16) በፌዴራል መንግሥት የሚከናወን የኮንስትራክሽን ሥራ በተገባለት ውል መሠረት የጥራት ደረጃው፣ የጊዜና የዋጋ ሂደቱ ተጠብቆ መሠራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል ቁጥጥር አንዲኖር ያደርጋል፣ በበላይነትም ይቆጣጠራል፣

17) የከተማ ነዋሪው ሕዝብ ከአቅሙ ጋር የተመጣጠኑ መኖሪያ ቤት እንዲሰራ አጠቃላይ አቅጣጫ ለመቀየስ የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል ለተግባራዊነታቸውም ለከተሞች የአቅም ግንባታ ድጋፍ ይሰጣል፣

18) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሥልጣኑ በከፊል ለሌላ የፌዴራል መንግሥት አካል በውክልና መስጠት ይችላል፣

19) የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ ድጋፍ የሚያገኙበትን መንገድ ይቀይሳል፡፡

20) በፌደራል መንግስት ባለቤትነት ስር የሚገኙ ቤቶች አስተዳደር በአግባቡ እንዲከናወን መደረጉን ያረጋገጣል፡፡

21) የከተማ ቦታ ሊዝ አዎጁን ለማስፈጸም ለከተማ አስተዳደሮች የቴክኒክና አቅም ግንባታ ድጋፍ የማድረግ፣ የመሬትና መሬት ነክ መረጃዎችን በቴክኖሎጅ የማዘመን እና የማስፈጸሚያ ስታንዳርዶችን፣ ሞዴል ደንቦችን፣ መመሪያዎችንና ማንዋሎችን በማዘጋጀት አጠቃላይ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፡፡

በአጠቃላይ ተቋሙ ከላይ የተዘረዘሩትን ሥልጣንና ተግባራትን መሠረት በማድረግ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ኘሮግራሞችን እና ሕጎችን የሚያወጣ ሲሆን አፈጻጸማቸውንም በተመለከተ ለክልሎችና ከተሞች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡ ሃገር አቀፍ የልማት ፕሮግራሞችን አፈጻጸም አስመልክቶም የአስተባባሪነትና ተሳታፊነት ሚና ያለው ሲሆን ለአጋር መንግስታዊ ተቋማት፣ የግል

ሴክተርና የሲቪክ ማህበረሰብ የቴክኒክ ድጋፎችን የሚሰጥ እና ተልዕኮውም በእነዚህ ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው፡፡

# ክፍል ሁለት

# የከተማ ልማት ዘርፍ እና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የ2005 ዕቅድ መነሻ ሁኔታዎች

## 1. የዘርፉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞች

1.1. የከተማ ልማት ፖሊሲው እና ፖሊሲዉን መነሻ ተደርገው የወጡ ሌሎች ፖሊሲዎች፣

1.2. አገራዊው የ5 ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ፣

1.3. የዘርፉ የ5 ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ፣ እና

1.4. በየፕሮግራሞቹ የተዘጋጁ ስትራቴጂዎች እና የ3 ዓመታት የፕሮግራም ሰነዶች ናቸው።

## 2. የ2004 በጀት ዓመት የተከናወኑ ዋና ዋና ሥራዎች እና የተገኙ ውጤቶች

### 2.1. የለውጥና የልማት ሠራዊት ለመገንባት የተከናወኑ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች

የለውጥ እና የልማት ሠራዊት ግንባታ ቅድመ ዝግጅት ሥራ እንደ ቁልፍ ሥራችን አድረጎ በመውሰድ በርካታ ውጤታማ ተግባራትን ማከናወን ችለናል። በዚህም ሂደት በተዋረድ ባለው የአደረጃጀት እርከን በዕቅድ ዝግጅት፣ በሰው ኃይል ዝግጅትና ስልጠና በአደረጃጀትና የአሠራር ሥርዓት ማስተካከል፣ እንዲሁም በለውጥ መሣሪያዎች ትግበራ በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ ለማስፈጸም የሚያስችል ያልተቆራረጠ የክትትል፣ የግምገማ እና ግብረ-መልስ ሥራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል።

ሴክተሩ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዳችን ላይ ከተሰጠው ተልዕኮና ዓላማ አንፃር የ2004 በጀት ዓመት ዕቅድ በዝርዝር መንደፉ ይታወቃል። ከዚህም በመነሳት በዘርፉ የሚታየውን የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር ለመድፈቅ እና የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን ለማሳካት የሚያስችሉ አደረጃጀቶችን በማሻሻልና በመፍጠር፤ የሰው ኃይል በማሟላት፣ የወጡ ስትራቴጂዎችን በመዘርዘር፣ የህግ ማዕቀፎችን እና የማስፈጸሚያ ማኑዋሎችን በማዘጋጀት እና ሥልጠና በመሥጠት ወደ ተሟላ ትግበራ ለመግባት የሚያስችል ዝግጅቶች ተደርገዋል። በተጨማሪም ክልሎችንና ከተሞችን በማሳተፍ የክፍለ ኢኮኖሚውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተዘጋጅቶ እንዲናበብ ተደርጓል። በመጨረሻም ከክልሎች ጋር የመግባቢያ ሠነድ በመፈራረም ወደ ተግባር ተገብቷል።

የ2004 በጀት ዓመት የተናበበውን የክፍለ ኢኮኖሚውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እና በለውጥ ትግበራው የአፈጻጸም ክትትልና ድጋፍ የተካሄደ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ቼክ ሊስት በማዘጋጀት በሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ በተጠሪ ተቋማት፣ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ ተቋማት የዕቅድ አፈጻጸም ምዘና ተካሂዶ ያሉበት ደረጃ የሚያስገነዝብ የጽሑፍ ግብረመልስ ለእያንዳንዱ የሥራ ክፍል፣

ተቋማትና ክልሎች በተከታታይ ተሰጥቷል፡፡ በዕቅዱ አፈፃፀም ረገድም ተስፋ ሰጪ ጅምር ውጤቶች በመታየት ላይ ይገኛሉ፡፡

በሌላ በኩል በመሥሪያ ቤታችን የውጤት ተኮር ምዘና ሥርዓት ግንባታ አምስት የትኩረት መስኮች ማለትም ቀልጣፋና ውጤታማ አሠራርና አመራር ማረጋገጥ፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የተወዳዳሪነት አቅም ግንባታ፣ የላቀ የካዳስተር አፈጻጸም ማስተግበር፣ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ተወዳዳሪነት አቅም ግንባታ እና የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶችን ማብቃት የትኩረት መስኮች በመለየት ትግበራው ተጀምሯል፡፡ በመቀጠልም በሚ/ር መ/ቤቱ የተቀናጀ የውጤት ተኮር የዕቅድ አፈጻጸም የትግበራ ምዕራፍ ማስፈጸሚያ ማኑዋል በማዘጋጀትና በማጸደቅ ለሁሉም የሚ/ር መ/ቤቱ ሠራተኞችና ኃላፊዎች ከውጤት ተኮር ዕቅድ ዝግጅት ሥልጠና ጋር አብሮ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ ስትራቴጂያዊ ግቦች በውጤት ተኮር ተግባራት በመመንዘር እስከ ግለሰብ ፈፃሚ የማውረድ ሥራው ተጠናቆ ከጥር 1 ቀን 2004 ጀምሮ በተሟላ መንገድ ወደ ትግበራ ተገብቷል፡፡ ለውጤት ተኮር ሥርዓቱ ግንባታ መጠናከር በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ሬጉላቶሪ ቢሮ ቀደም ብሎ የተከናወነው የሙከራ ትግበራ በግብዓትነት ተወስዷል፡፡ በመሆኑም በሚ/ር መ/ቤቱ ያሉ አመራሮችና ፈጻሚዎች በተዘጋጀው የሥራ አፈጻጸም መገምገሚያ ማንዋል መሠረት የበጀት ዓመቱ የግማሽ ዓመት የሥራ አፈፃፀም ግምገማ በውጤት ተኮር ዕቅድ አፈጻጸም፣በዙሪያ መለስ ግምገማና ራስን የማብቃት ዕቅድ ዝግጅት ግምገማ እንዲካሄድ ሥልጠና በመስጠት ግምገማ እና ምዘናው እንዲከናወን ተደርጓል፡፡ በዚህም ምዘና ወደፊት የወጡ፣ በመሃል ያሉና ወደ ኋላ የቀሩ ሠራተኞች መለየት ተጀምሯል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከሚያዚያ ወር 2004 ጀምሮ በየወሩ የአመራሩና የሠራተኞች ወርሃዊ የሴክተሩ የGTP ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በተያያዘም የመሠረታዊ የአሰራር ሂደት ለውጥ እና የውጤት ተኮር ምዘና ሥርዓትን በዘመናዊ የኢንፎረሜሽን ቴክኖሎጂ ተደግፎ ለመተግበር የሚያስችል ዌብ ቤዝድ የሆነ የኦቶሜሽን ሲስተም ለመዘርጋት ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ (INSA) ጋር ጥናቱ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ ስራው ሲጠናቀቅ ለሀገር አቀፍ ትግበራ ፋይዳ ይኖረዋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ጥናቱ እስኪጠናቀቅ በኤክሴል (የመከታተያ ቅጾች) በመታገዝ ዕለታዊና ሳምታዊ የአፈፃፀም መረጃዎች እንዲያዙ በመደረግ ላይ ነው፡፡

በመ/ቤታችን ባሉ ቡድኖችና ኬዝ ቲሞች የእርስ በእርስ መገማገምና መማማር በሳምንት ሁለት ቀን እንዲካሄድ ሥርዓቱ ተዘርግቷል፡፡ የእርስ በርስ መማማሩ የአመለካከት ለውጥ ማምጣት ወይም መፍጠር፣ የአመራር ዘይቤ ማሻሻል፣ የክህሎት ማሻሻል፣ ግልፅ እቅድ እና ደረጃውን የጠበቀ ሪፖርት ስለማዘጋጀት፣ የግብዓት አጠቃቀም የማንዋል ዝግጅትና ትግበራ፣ የክትትልና ድጋፍ ሥራው ማነቆዎችን በመፍታት እንዲያተኩር በማድረግ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀምና አዳዲስ ሀሳቦች መጠቀምን፣ ተሞክሮዎችን መቀመርና ማስፋፋት፣ ግምገማና ግብረ-መልስን እና እንደቢሮው ተጨባጭ

ሁኔታ ሌሎች ርዕሰ ጉዳዮችን በማንሳት ይካሄዳል። በየወሩ በሚካሄደው በGTP ዕቅድ የአፈጻጸም ግምገማ መድረክ የተቀመጡ አቅጣጫዎች በመውሰድ ለቀጣይ አፈፃፀም መሻሻል እንደ ግብዓት ጥቅም ላይ ለማዋል አስችሏል።

የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አመራርና ሠራተኞች በዘርፉ የወጡ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ እና ፕሮግራሞች ላይ የጠራ ግንዛቤ ጨብጠው እንዲተገብሩት ለማድረግና የጋራ ራዕይ ለመፍጠር ከመጋቢት 3 እስከ 22 ቀን 2004 በተለያዩ 13 ከዘርፉ ጋር የተያያዙ ረቂቅ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ዕቅዶች ላይ በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ማዕከል በማድረግ ስልጠና ተሰጥቷል። ስልጠናው በአግባቡ እንዲጨበጥ በንባብ፣ በኃይል መድረክ፣ በቡድን ውይይት፣ በአሀድ ግምገማና በፅሁፍ ምዘና እና ፈተና ጭምር ተደግፎ ተከናውኗል።

በተጠሪ ተቋማት፣ በክልል የዘርፉ መ/ቤቶችና በ19 ከተሞች ከፌደራል ጋር በማናበብ የተዘጋጀው ዕቅድ የሚገመገሙበት ሥርዓት ተዘርግቷል። በክልሎች የሦስት ወር የአፈጻጸም ሪፖርት ላይ ለየክልሎቹ የጽሑፍ ግብረ-መልስ ይሰጣል። በየስድስት ወሩ ደግሞ ከክልሎች ከራሳቸው በተውጣጣ ገምጋሚ ግብረ-ኃይል ተመዝነው የአፈጻጸም ደረጃ ይወጣላቸዋል። በውጤቱም ላይ የሴክተር ጉባዔ ተጠርቶ ውይይት ይደረግበታል። ከዕቅድ አፈጻጸማችን ጥንካሬ ትምህርት የሚወሰድበትና ከድክመቶቻችንም የምንማርበት መድረክ ለማድረግ እየተሞከረ ነው። ከተሞችን ደግሞ በተደራጀ መንገድ በአመት አንድ ጊዜ በመሠረተ ልማት ማስፋፋት እና በአገልግሎት አቅርቦት አፈጻጸማቸው ይገመገማሉ። በየዓመቱ በሚካሄደው የከተሞች ሣምንት ውጤቱ ለህዝብ የሚገለጽበት ሥርዓትም እየተዘረጋ ነው።

## 2.2. የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ሥራዎች

### 2.2.1. የአስፈጻሚና ፈጻሚ አካላት አቅም ግንባታ ሥራችን

የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ አዲሱን የዘርፉን ስትራቴጂ ለማስፈጸም የሚያስችል አቅም እንዲኖረው ተደርጎ የተደራጀ ሲሆን አደረጃጀቱ ሙሉ በሙሉ በሰው ኃይል ተሟልቶ ወደ ሥራ እንዲገባ ተደርጓል። በፌደራል፣ በክልሎችና በከተሞች በሚገኙ አስፈጻሚ አካላት እና በኢንተርፕራይዞች የሚታየውን የኪራይ ሰብሳቢነት የአመለካከትና የተግባር ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂ በተመረጡ 7 ዘርፎች ተለይተው በተዘጋጁ ማኑዋሎች ዙሪያ ከየክፍሉ ለተውጣጡ አመራር አካላትና ባለሙያዎች በተለያዩ ዙሮች በፌዴራል ደረጃ ሥልጠናዎች ተሰጥተዋል። በክልል ደረጃም እንዲሁ ማኑዋሎቹን በየክልሉ ቋንቋ በመተርጎም በተዋረድ በርካታ ሥልጠናዎች የተሠጠ ሲሆን በየደረጃው የሚገኘውን ነባሩን የሰው ኃይል በጥልቀት የመገምገም፣ የማጥራትና መልሶ ማደራጀት ሥራዎች ተከናውነዋል። በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ በግምገማዊ ሥልጠናው ሂደት ከ15,106 አመራሮችና አስፈጻሚ ባለሙያዎች የአሰልጣኞች

ሥልጠና የተሰጣቸው ሲሆን የተዘጋጁት ማንዋሎችም ሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ የእቅዱ አፈጻጸሙም 149 ከመቶ ነው፡፡ በተመሳሳይ ለ735,025 ለሚሆኑ የነባርና አዳዲስ አንቀሳቃሾች የአመለካከትና የክህሎት ችግሮቻቸውን ለመፍታት መነሻ የሚሆን በገጽ ለገጽ እና በፐላዝማ ሥልጠና ለመስጠት ተችሏል፡፡

የዘርፉን ልማት በተቀናጀ ሁኔታ ለመምራት ከፌዴራል ጀምሮ በየደረጃው እስከ ከተሞች ድረስ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ምክር ቤት ተቋቁሞ የተደራጀ ሥራ መጀመሩ የማስፈጸም አቅምን ከማጠናከር እና ባለሚናዎችን ከማሳተፍ አንጻር የበኩሉን ድርሻ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በየደረጃው ከሚገኙ የዘርፉ አስፈጻሚ አካላት ጋር በመቀናጀት የሚተገበሩ ሥራዎችን በመለየት በፌዴራል ደረጃ የዘጠኝ ሴክተሮች የሥራ ዕድል ፈጠራ ዕቅድ ለየብቻው አዘጋጅተው ወደ ትግበራ የገቡ ሲሆን የጋራ ዕቅድ አፈጻጸምን የበለጠ ለማሳለጥ በፌዴራል የዘርፉ ምክር ቤት የኮንስትራክሽን፣ የብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ፣ የጨርቃ ጨርቅና ቆዳ፣ የንግድ አገልግሎት እና የፋይናንስ ጉዳዮች የስቲሪንግ ኮሚቴ ተቋቁሞ የዕለት ተዕለት ክትትልና ድጋፍ በማድረግ አፈጻጸሙን ለመ/ቤቱ የበላይ አመራር አቅርቦ የሚገመገምበት ሥርዓትም ተዘርግቷል፡፡ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማትን በተደራጀና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመምራት እና ለኢንዱስትሪው ልማት ሰፊ መሠረት ለመጣል እንዲቻል የዘርፉን የተቀናጀ የልማት ፕሮግራም በመዘጋጀት ላይ ነው፡፡

### 2.2.2. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት እና የሥራ ዕድል ፈጠራው ሥራችን

ባሳለፍነው በጀት ዓመት በመደበኛ የሥራ ዘርፎች ለ554,622 ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ433,274 ቋሚና 226,547 ጊዜያዊ በድምሩ ለ659,821 (119%) ዜጎች አዲስ የሥራ ዕድል የተፈጠረ ሲሆን በዘርፍ ሲታይም በማኑፋክቸሪንግ 107,058፣ በኮንስትራክሽን ሥራዎች 236,768፣ በአገልግሎት 128,133፣ በከተማ ግብርና 72,144 እና በንግድ 115,718 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ክልላዊ ስርጭቱም በትግራይ 82,680፣ አማራ 101,720፣ አዲስ አበባ 99,899፣ ኦሮሚያ 230,849፣ በደቡብ 127,112፣ በጋምቤላ 1,401፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ 1010፣ በሐረሪ ህዝብ 3,224፣ በድሬዳዋ 8,623 እና በሶማሌ 3,303 ሲሆን አጠቃላይ ከተፈጠረው የሥራ ዕድል ውስጥ የሴቶች ድርሻ 40.6 በመቶ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች ለ226,536 ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ488,179 (215%) ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡ ይህም በዝርዝር ሲታይ የቤቶች ልማት ፕሮግራም (185,980)፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስፋፊያ ፕሮግራም (10,510)፣ የውሃና መስኖ ልማት ፕሮግራም (3,280)፣ የመንገድ ዘርፍ ፕሮግራም (170,452)፣ የባቡር ዘርፍ ፕሮግራም (874) እና የኮብል ስቶንና የከተማ መሠረተ ልማት ፕሮግራም (117,163) ነው፡፡

በአጠቃላይ በ2004 በጀት ዓመት በመደበኛ የሥራ ዘርፎች እና በመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች ከታቀደው 781,158 ውስጥ የተፈጠረው የሥራ ዕድል 1,148,080 ሲሆን የሴቶች ድርሻ 40 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ፋሲሊቴሽንና ድጋፍ ሥራዎች

የአንድ ማዕከል አገልግሎት ጣቢያዎችን ከማስፋፋት አንጻር በያዝነው ዓመት ማዕከላቱን ከ825 ወደ 925 ለማድረስ ታቅዶ ነበር፡፡ በአሁን ጊዜ ተጨማሪ አዳዲስ 212 የአንድ ማዕከል አገልግሎት ጣቢያዎችን በማቋቋም በጠቅላላው 1,037 ማዕከላት አገልግሎት እየሠጡ ይገኛሉ፡፡ ክልላዊ ስርጭቱም በትግራይ 81፣ በአማራ 238፣ በኦሮሚያ 442፣ በደቡብ 141፣ በድሬዳዋ 9፣ በሐረሪ 6፣ በሶማሌ 4፣ በአዲስ አበባ 116 ነው፡፡

ከዚህ በፊት በማዕከላቱ ይሰጡ የነበሩት አገልግሎቶች እንዳሉ ሆነው የTIN ቁጥር አሰጣጥ አገልግሎትን ተደራሽ ለማድረግ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጋር በመነጋገር የባለስልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሚገኙባቸው ከተሞች አገልግሎቱ እንዲሰጥ ስምምነት ላይ ተደርሶና ለቅ/ጽ/ቤቶች ህጋዊ ውክልና ተሰጥቷቸው ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ከፌዴራል የኅብረት ሥራ ማህበራት ኤጀንሲና ከንግድ ሚኒስቴርም ጋር በተመሳሳይ በመግባባት የፍቃድ አሰጣጥ ውክልና ለክልሎች እንዲሰጡ በማድረግ አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከንግድ ሚኒስቴር የአመራር አካላት ጋር በተደረገ ተከታታይ ውይይት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የንግድ ስም ስያሜ አገልግሎት ለመስጠት ከፍተኛ መዘግየትና መጉላላት ስለነበር ይህንን ችግር ለማቃለል በንግድ ሚኒስቴር አማካይነት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ብቻ አገልግሎት የሚሰጥ የተለየ መስኮት፣ ፋክስና፣ የሰው ኃይል በማደራጀት በቀን እስከ 250 ተገልጋዮች መስተናገድ በመቻሉ በተወሰነ ደረጃ ችግሩ እንዲቃለል ተደርጓል፡፡ በቀጣይም አገልግሎቱን ወደ ወረዳ ለማውረድ የአውቶሜሽን ስራ እየተሠራ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል በዘርፉ እንደ አጠቃላይ በተለዩና በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች በWide - Area Network (WAN) ለመጠቀም የሚያስችል ምቹ ሁኔታዎች መኖራቸውን ለማረጋገጥ የመረጃ አሰባሰብ፣ አያያዝና አደረጃጀት በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ የቅድመ ዝግጅት ጥናት ተከናውኗል፡፡

በበጀት ዓመቱ የቴክኒክ ክህሎት ክፍተት ማሟያ ሥልጠና ለ389,919 አንቀሳቃሾችን ለመስጠት ታቅዶ ለ225,873 (58%) ለመስጠት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በኢንተርፕርነርሺፕና በንግድ ሥራ አመራር 680,810 አንቀሳቃሾችን ለማሰልጠን ታቅዶ 733,703 (108%) አንቀሳቃሾች ሥልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም የካይዘን ተግባራዊ ሥልጠና ለኢንተርፕራይዞች እንዲሰጥ በማድረግ በመጀመሪያ ዙር ከአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች፣ በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በትግራይ እና በደብብ ክልሎች ከሚገኙ ዋና ከተሞች ከእያንዳንዱ 10 ኢንተርፕራይዞችን በድምሩ 60 በመምረጥ የማምረቻ ቦታ፣

የገንዘብ፣ የጥሬ ዕቃና ብክነትን ማዳን ያስቻለ ተግባራዊ ስልጠናና ልምድ እንዲያገኙ ተደርጓል። በሁለተኛው ዙር ከአዲስ አበባ ከተማ 192 እና ከትግራይ ክልል 200 ኢንተርፕራይዞችን የትግበራ ሥልጠናውን አግኝተዋል። በአጠቃላይ በፌደራል ደረጃ በተሠጠ ስልጠና 452 በተለያየ ዘርፍ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች የካይዘን ሥርዓት ስልጠና እንዲያገኙ ለማድረግ ተችሏል። ይህን ተከትሎና ክልሎች ለበርካታ ኢንተርፕራይዞች የካይዘን ሥርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ስልጠና ሰጥተዋል (ለምሳሌ የትግራይ ክልል ለ1,600 ለሚሆኑ ኢንተርፕራይዞች ስልጠናውን በራሳቸው የሰጡ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል)። በተጨማሪም ለሶስቱ የዘርፉ አስፈጻሚ አካላት በንግድ ልማት ምክር አገልግሎት ፣ በእሴት ሰንሰለት ጽንሰ ሃሳብና አተገባበር እና በክላስተር ልማትና አመራር የሥልጠና ርዕሶች ላይ ከሁሉም ክልሎችና ከሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች ለተውጣጡ 458 ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ሥልጠና ተሰጥቷል።

ከቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ጋር በመቀናጀት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ምርታማነትን የሚያግዙ የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚካሄድባቸው 229 ፕሮቶታይፖችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 285 ፕሮቶታይፖች የተዘጋጁ ሲሆን አፈጻጸሙ 124 በመቶ ነው። በተጨማሪም ከህንድ አገር በተገኘ ተሞክሮ የአነስተኛ ኢንዱስትሪዎች የተሟላ ሞዴል ቴክኖሎጂዎች ለቴክኒክ እና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ተሰራጭቶ በየተቋማቱ የተመረጡ ቴክኖሎጂዎች ፕሮቶታይፕ እየተሠራ ይገኛል። የተሠራጨት ዋና ዋና ቴክኖሎጂዎቹ ከብሎኬት ማምረቻ፣ ከምግብ ማብሰያና ማምረቻ፣ የላሜራና የእብነ በረድ መቁረጫ፣ ብረት መጠቅለያ እና የልብስ ስፌት ማሽን ናቸው።

በከተሞች የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ቀጣይነት ያለውን ልማት ለማረጋገጥ የሚያስችል ሀገራዊና ወጥ የሆነ ማምረቻና መሸጫ ማዕከላት ዲዛይን ዝግጅት በ19 አይነት ታይፖሎጂዎች ተጠናቆ ተሰራጭቷል። በአሁኑ ወቅት አብዛኞቹ ክልሎች ወደ ግንባታ ስራ በመግባት ላይ ይገኛሉ። በዘጠኝ ክልሎችና በሁለት ከተማ አስተዳደሮች ወደ ሥራ ለሚገቡ 250,000 አንቀሳቃሾች አገልግሎት የሚውል 615 ሄክታር ቦታ በማዘጋጀት 3,248 ሼዶች እና 100 ህንፃዎች በብር 1ቢሊየን በመገንባት ላይ ነው። የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕይዞች ተደራጅተው ማምረትና መሸጥ እንዲችሉ ለማድረግ በታቀደው መሠረት የክላስተሮቹ ግንባታ በኦሮሚያ በጨረታ ሂደት ላይ፣ ደቡብ ክልል አዲስ የሚጀምሩት አምስት ከተሞች በመሬት ርክክብ ላይ፣ አማራ ክልል 23ቱ ብሎኮች ጨረታ ተከፍቶ አሸናፊ መታወቁና 13ቱ ብሎክ ድጋሚ ጨረታ ሂደት ላይ፣ በትግራይ ክልል በ12 ከተሞች የ120 ሄክታር የመሬት ዝግጅትና 186 ሚሊየን ብር በጀት ተይዞ ግንባታ ላይ፣ ሐረሪ ክልል ገና የበጀት ማስፈቀድና የቦታ መረጣ ሂደት ላይ፣ ድሬደዋ ጨረታ ወጥቶ አሸናፊው ታውቆ የቦታ ርክክብ የተደረገ መሆኑ ተረጋግጧል። ከእነዚህ ውስጥ 13 ህንፃዎችና 175 ሼዶች ግንባታቸው ተጠናቋል። ባሳለፍነው በጀት ዓመት ለ575,965 አንቀሳቃሾች ብር 1,776,393,643 ብድር ለማመቻቸት ታቅዶ ለ81,926 የብድር አቅርቦት ሊታሰብበት የሚገባ መሆኑን ያስገንዝባል። የብድር ማስመለስን በተመለከተ ተሰራጭቶ የመመለሻ ጊዜ የደረሰውን

ብድር 100% ለማስመለስ ታቅዶ ብር 702,557,720 /80%/ ተሰብስቧል፡፡ እንዲሁም የቁጠባ ባህልን ከማሳደግ አኳይ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕይዝ አንቀሳቃሾች ግንዛቤ በማስጨበጥ ብር 1,154,655,868 ለማስቆጠብ ታቅዶ ብር 1,448,650,248 ተቆጥቧል፡፡ አፈፃፀሙ 114 በመቶ ሲሆን ይህም በነባር አንቀሳቃሾች ላይ አበረታች የቁጠባ ባህል እየመጣ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ አዲስ ተበዳሪዎች 20 በመቶ ቆጥበው እንዲበደሩ በስትራቴጂው በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ተግባራዊ ለማድረግ በአስፈፃሚዎች፣ በተጠቃሚዎችና በህብረተሰቡም ዘንድ አሁንም የጋራ መግባባት ላይ ክፍተት የሚታይ በመሆኑ ይህን ለማስተካከል የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች በመሰራት ላይ ይገኛሉ፡፡

የዘርፉን ልማት በቅርበት በመከታተልና በመደገፍ ውጤታማ ለማድረግ የኢንተርፕራይዞችን መልካም ተሞክሮ ቀምሮ ለማስፋፋት እንዲቻል በክልሎችና ከተሞች ሁለት ቡድን ተሰማርቶ በኮንስትራክሽን /7/፣ በብረታ ብረት /3/፣ ቆዳና ቆዳ ውጤቶች /1/፣ ከተማ ግብርና /2/፣ አገልግሎት ዘርፍ /2/፣ በጠቅላላው የ15 ኢንተርፕይዞች ምርጥ ተሞክሮ መረጃው ተሰብስቦ ለሁሉም ክፍሎች ለማስፋፋት ቅመራው በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

### 2.2.3. አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ከመንግስት የልማት ተቋማትና ከግል ኢንዱስትሪዎች ጋር የማስተሳሰር ሥራችን

በመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች የሚፈጠሩ የሥራ ዕድሎችን አሟጦ ለመጠቀም እንዲቻል ከብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ጋር በስድስት ፕሮጀክቶች ዙሪያ ዝርዝር ዕቅድ በማዘጋጀት ወደ ትግበራ እንዲሸጋገር ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ሌሎች የባለድርሻ አካላት ማለትም ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ ከሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር፣ ከመስሪያ ቤታችን ኮንስትራክሽን ዘርፍ፣ ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ፣ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ፣ ከብሔራዊ ባንክና ከአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ማኅበር አስፈፃሚ መ/ቤቶች ጋር የጋራ ዕቅድ በማዘጋጀት ወደ ትግበራ እንዲሸጋገር እየተደረገ ነው፡፡ በመ/ቤቱም አማካይነት አፈፃፀሙ በመደበኛነት ክትትልና ድጋፍ ይደረግበታል፡፡

### 2.2.4. በትግራይ ክልልና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተገኙ የተሻሉ ልምዶች ቅመራና ማስፋፋት ሥራችን

በትግራይ ክልልና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዘርፉን ልማት በተቀናጀ አመራር በመከታተል በመደገፍና ተጨባጭ ውጤት በማስገኘት ውጤቱን ወደ ሌሎች ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ለማስፋት እንዲቻል የዘርፉ አስፈፃሚ አካላትና ባለሙያዎች በማደራጀት የተሻለ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ በዚህም መሠረት በትግራይ ክልል ከቅድመ ዝግጅት ሥራና የግንዛቤ ፈጠራ እንቅስቃሴ ጀምሮ አስፈፃሚ አካላት፣ ባለሙያውን፣ ተጠቃሚዎች እንዲሁም ህብረተሰቡን በማንቀሳቀስ በተለይ

በዩኒቨርሲቲ እና በቴክኒክና ሙያ ምሩቃን ስራ ፈላጊዎች ላይ በማተኮር የተሻለ የማሳመን ሥራ ተሰርቷል፡፡ በክልሉ 72,618 /ወንድ 42,606 እና ሴት 30,012/ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ተችሏል፡፡ ከዚህ ውስጥ 30,886 የሚሆኑት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና የቴክኒክና ሙያ ምሩቃን የሆኑ ወጣቶች ናቸው፡፡ በክልሉ በዘርፉ ልማት የተገኘው ውጤት ተቀምሮ ለሁሉም ክልል/ከተማ አስተዳደር አመራሮች መግለጫ የተሰጠበት ሲሆን፣ ሰነዱም እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ከኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቭዥን ጋር በመተባበር ሂደቱ በዶክሜንተሪ ፊልም እንዲሰራና በቀጣይ ለክልሎች እንዲሰራጭ ይደረጋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉለሌ ክፍለ ከተማ ላይ በማተኮር በ10 ወረዳዎች አመራርና ባለሙያዎች ተመድበው ሙሉ የሥራ ጊዜንና በእረፍት ጊዜያቸውም ጭምር ከሥራ ፈላጊዎች ምዝገባ ጀምሮ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ፣ የሥራ ዕድል የሚፈጠርባቸውን ዘርፎች በመለየት፣ በሚሰጡ ድጋፎች ላይ ማለትም ዲዛይን በማዘጋጀት መሠረተ ልማት እንዲሟላ በማድረግ፣ ስልጠና በመስጠት በተደራጀ ሁኔታ ወደ ስራ ለማስገባት በቅንጅት እየተሠራ ነው፡፡ በዚህም ሂደት በክፍለ ከተማው በተለያዩ ዘርፎች ባለፉት ሶስት ወራት ብቻ በጠቅላላው 9,114 ለሚሆኑ ስራ ፈላጊ ዜጐች የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡ በዚህ መሠረት የተከናወነውን የዘርፉን የልማት እንቅስቃሴ ከመነሻው እስከ ውጤቱ ድረስ የነበረው የማነቆ አፈታት ልምድ ተቀምሮ ለሌሎች ክፍለ ከተሞች እና ክልሎች/ከተሞች ለማስፋፋት እንዲቻል በሰነድ፣ በኦዲዮ ቪዥዋልና በፎቶ ለማዘጋጀት እንዲቻል አንድ ቡድን ተቋቁሞ እየሰራ ይገኛል፡፡

## 2.3. የከተማ መሬት አጠቃቀም ፕላን፣ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ሥራዎች

### 2.3.1. የከተማ መሬት አጠቃቀም ፕላን ፖሊሲ፣ የሕግ ማዕቀፍ፣ አደርጃጀትና አሠራር ማስተካከል ሥራችን

በበጀት ዓመቱ የከተማ ፕላን ዝግጅት ሥራዎች በተሟሉ የአሰራር ማኑዋሎች መሠረት እንዲከናወን ለማድረግ የተለያዩ የጥናት ሰነዶች በመዘጋጀት ላይ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ ውስጥ የከተሞች የሰው ኃይል ልማት ጥናት ፣ ላንድ ስኬፕ ዲዛይን ዝግጅት፣ የህንፃ ስታንዳርድ ጥናት እና የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አስተዳደር ሥርዓት ጥናት ለማካሄድ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ እንዲሁም ለከተማ ፕላን ዝግጅትና አተገባበር የሚያግዙ የኢትዮጵያ ከተሞችን ደረጃ ለመወሰን የሚያስችል ስታንዳርድ ሰነድ ዝግጅት፣ የከተማ ግብርና ማስፋፊያ ጥናት፣ የአየር ንብረት ለውጥ በኢትዮጵያ ከተሞች ላይ ያለው ተጽዕኖ ጥናት ፣ የከተማ መሬት ማደራጀትና ማልማት አሰራር የዳሰሳ ጥናት ፣ የደረቅ ወደብ ምስረታ የከተሞች ዕድገት ላይ ያለው ተጽእኖ ጥናት እና የተቀናጀ የከተማ መሰረተ ልማት ፕላን አዘጋጃጀት ማንዋልን የማሻሻልና የማዘጋጀት ሥራ ተጠናቀዋል፡፡

የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም በከተማ ፕላን አዋጅ መሠረት ስለመሆኑና የፕላን ጥሰትን አስመልክቶ በተለያዩ ክልሎች ክትትልና ግምገማ ተጀምሯል፡፡ በአሁኑ ወቅት በ12 ከተሞች በኦዲዮ ቪዥዋል የተደገፈ መረጃ በማሰባሰብ የክትትልና የግምገማ ሥራ ተከናውኖ ለከተማ አስተዳደሮቹ ግብረ-መልስ በጹሑፍ ተሰጥቷል፡፡ በከተማ ፕላን ልዩ ድጋፍ የሚሹ ክልሎችን ከመደገፍ አኳያ በጋምቤላና አፋር ክልሎች የከተማ ፕላን አሃዶች እንዲደራጁ የተደረገ ሲሆን በሌሎች ክልሎች ደግሞ አደረጃጀቱን የማናበብ ሥራ ተከናውኗል፡፡

## 1) የአነስተኛ ከተሞች ፕላን ዝግጅት

የ150 አነሰተኛ ከተሞች የመሠረታዊ ካርታና መሠረታዊ የከተማ ፕላን ዝግጅትን በተመለከተ የ114 ከተሞች መሠረታዊ ካርታ እንዲሁም ለ143 ለከተሞች መሠረታዊ ፕላን የተዘጋጀ ሲሆን የጹሁፍ ግብረ-መልስም ለየክልሎቹ ፕላን ተቋማት ተሰጥቷል፡፡

በበጀት ዓመቱ የክልሎችን የከተማ ፕላን አዘገጃጀትና አተገባበር አቅም ከማጎልበት አኳያ በሁሉም ክልሎች ለሚገኙ 430 የከተማ ከንቲባዎች ፣ ሥራ አስኪያጆች፣ ባለሙያዎች ስለ ከተማ ፕላን አዘገጃጀትና አተገባበር የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተስጥቷል፡፡ እንዲሁም ለ139 ባለሙያዎች በማህበራዊ ፣ ፊዚካላዊና ስፓሻል ሙያ ላይ ተጨማሪ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በከተሞች የአካባቢ ልማት ፕላን /LDP/ ዝግጅትና ትግበራ ዙሪያ፣ LDP ያስፈለገበትን አካባቢ በመለየት ላይ እና LDP ሲዘጋጅ መከተል ስለሚገባው ቴክኒካዊ ጉዳዮች የሚያመለክት ማኑዋል በማዘጋጀት ለክልሎች ተልኳል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የመሠረታዊ ካርታ የማዘጋጀት አቅምን በአገር አቀፍ ደረጃ ለማሳደግ እንዲቻል የሃርድዌር፣ የሶፍትዌር እና ፍቶግራሜትሪ መሳሪያዎች ተገዝተው የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ኤጀንሲን ጨምሮ ለአራቱ አበይት ክልሎች እንዲሰራጩ ተደርጓል፡፡

## 2) የመንግስት ግዙፍ እና ተያያዥ ፕሮጀክቶች የመዋቅራዊና የአካባቢ ልማት ፕላን ዝግጅት

በበጀት ዓመቱ የመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ በ11 ዩኒቨርሲቲዎች ፣ በ10 ስኳር ልማት ፕሮጀክቶች እና በማዳበሪያ ፕሮጀክቶች የሚሰፍረውን ህዝብና ልማት መሸከም የሚችሉ ከተሞችን ለመፍጠር ወይም ለማስፋፋት እንዲቻል ዩኒቨርሲቲዎቹ የመሠረታዊ ካርታና ፕላን ያላቸው በመሆኑ ፕላናቸው በየከተሞቹ መዋቅራዊ ፕላን ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአካባቢ ልማት ፕላን /LDP/ ከሚያስፈልጋቸው ውስጥ የአምቦ፣ ወልቂጤ፣ ጅጅጋ፣ አቃቂ ቃሊቲ፣ ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ተጠናቋል፡፡ የቡሌ ሆራ፣ የመቱ፣ የአዲግራት፣ የደብረ-ታቦርና የአሶሳ ዩኒቨርሲቲዎች በቅድመ ዝግጅት ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

የስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክቶችን በተመለከተም የኩራዝ እና የከሰም መሠረታዊ ካርታ ዝግጅት በኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ኤጀንሲ አማካይነት በመዘጋጀት ላይ ሲሆን የጃዊ ተጠናቆ ለመዋቅራዊ ፕላን ዝግጅት

መረጃ የመሰብሰብ ስራ ተጀምሯል፡፡ በወልቃይት የሁለት መንደሮች /የማግባ እና የመጉዕ/ መሠረታዊ ካርታ ቅየሳ የተካሄደ ስሆን የመጉዕ ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል፡፡ በኦሮሚያ ክልል የአጋምሶ ፊንጫ የመሠረታዊ ፕላን ዝግጅት ተጠናቋል፡፡ የማዳበሪያ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ የያዩና የቢቂላ የመወቅራዊ ፕላን ዝግጅት የተጠናቀቀ ሲሆን ለቢቂላ የመሠረታዊ ፕላን ተዘጋጅቷል፡፡

## 2.3.2. የከተማ መሬት ልማት፣ ዘመናዊ የአመራር ስርዓት የመዘርጋትና የማስፈጸም አቅም የመገንባት ሥራችን

በበጀት ዓመቱ የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ሥራዎቻችንን ግልጸኝነትና ተጠያቂነት ባለው መንገድ ለመምራት እና የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር ለመድፈቅ እንዲሁም የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዳችንን ለማሳካት የሚስችሉ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ዘርፉን ውጤታማ በሆነ ስርዓት ለመምራት የሚያስችል ፖሊሲ እና ስትራቴጂ እንዲሁም የፕሮግራም ሰነድ ዝግጅት በተሟላ መንገድ በማጠናቀቅ በዘርፉ ውስጥ ለሚገኙ ፈጻሚዎች እና አመራሮች እንዲሁም ለሚመለከታቸው አካላት የተሻለ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የሚያስችል ተከታታይ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ ዘርፉ የሚጠበቅበትን ተልዕኮ ለመወጣት እና የተዘረጋውን አዲስ የአሠራር ሥርዓት ለመሸከም የሚችል አደረጃጀት የመቅረጽ ሥራ በማጠናቀቅ በፌዴራል ደረጃ የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ፣ የፌዴራል የተቀናጀ የመሬትና የመሬት ነክ መረጃ ፕሮጀክት ጽ/ቤት እና የመሬትና መሬት ነክ ቋሚ ንብረት ምዝገባ ኤጀንሲ በአዲስ መልክ የተደራጁ ሲሆን አደረጃጀቱ ከክልል እስከ ከተሞች ተዘርግቶ እንዲናበብ እና ወደ ሥራ እንዲገቡ ከሠፊ ውጣ ውረድ በኃላ ማስፈጸም ተችሏል፡፡

ዘርፉን በአዲስ መልከ ከማደራጀት ጎን ለጎን ፖሊሲውን መሰረት በማድረግ የዘርፉን የአሰራር ስርዓት ግልጸኝነት እና ተጠያቂነት ባለው ሥርዓት ለመምራት የሚያስችሉ የህግ ማዕቀፎች ለማዘጋጀት ተችሏል፡፡ በዚሁ መሠረት የሊዝ አዋጁ የተሻሻለ ሲሆን አዋጁን ተከትሎ ለማስፈጸም የሚያገለግል ሞዴል ደንብ በተለያዩ መድረኮች ሰፊ ውይይት ተካሄዶበት ለክልሎች እና ለከተሞች አስተዳደር እንደተጨባጭ ሁኔታቸው እንዲያጸድቁት ተልኳል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ፖሊሲውን እና አዋጁን ተከትሎ ለዘርፉ አስፈላጊ የሆኑ ረቂቅ መመሪያዎች፣ የአሰራር ስታንዳርዶች እና ማኑዋሎች ተዘጋጅተዋል፡፡ የዘርፉን ፈጻሚ እና አመራር ለመሬት ልማት እና ማኔጅመንት አሠራር በወጡ የህግ ማዕቀፎች፣ የአሰራር ስታንዳርዶች እና ማኑዋሎች ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግ እንዲቻል ለ60,000 ባለሙያዎች እና አመራር አካላት የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረክ ተመቻችቷል፡፡ የክህሎት ክፍተቱን ለማሟላትም እንዲቻል የመረጃ ሥርዓት ትግበራ ከሚጀመርባቸው ከተሞች ለተውጣጡ 253 ባለሙያዎች በመረጃ አያያዝና በካዳስተር ላይ ያተኮር ወደ ሥራው የሚያስገባ ስልጠና በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ሥልጠናው በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ ይህም ተግባር በተጠናከረ መልኩ የሚቀጥል ይሆናል፡፡ በዘርፉ ላይ ተሰማርቶ የሚገኘውን የሰው ኃይል ክህሎት በመመዘን ብቃቱን ማረጋገጥ እና የዘርፉን ውጤታማነት ማሳደግን በተመለከተ ከትምህርት ሚኒስቴርና ከቴክኒክና ሙያ

ትምህርት እና ሥልጠና ተቋም ጋር በመሆን ከደረጃ ሁለት እስከ ደረጃ አምስት የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ሥልጠና ዓይነቶች ተለይተው የሙያ ብቃት መመዘኛ ተዘጋጅቶላቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ ከመሬትና መሬት ነክ ጋር ተዛማጅ የሆነ የትምህርት ዝግጅትና የሥራ ልምድ ያላቸው 500 ባለሙያዎች ብቃት በማረጋገጥ የመረጃ ሥርዓት ትግበራውን የሚቀላቀሉበት መንገድ ለማመቻቸት በተያዘው ግብ መሰረት ከየክልሉ የብቃት ማዕከላት /Center of competence/ ጋር ምዘናው በሚካሄድበት አግባብ ላይ ቅድመ ዝግጅት በመካሄድ ላይ ነው፡፡ ለዘርፉ የተዘጋጁ የሙያ ደረጃዎችን /Occupational Standard/ በመፈተሽ ምዘና ሊካሄድባቸው የሚችሉትንና ተዛማጅ የትምህርትና የሥራ ልምዶች ተለይተዋል፡፡

የብቃት ምዘና መሣሪያዎችን /Assessment tool/ የማዘጋጀቱ ተግባርን አስመልክቶ አስፈላጊ ግብአቶችን ለማሟላት የሚያስችል ዝክረ-ሐሳብ /proposal/ ተዘጋጅቶ ለ13ቱም የሙያ ደረጃዎች የምዘና መሳሪያዎች ተዘጋጅቷል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ የክልል ፕሮጀክት ጽ/ቤት፣ የቴክኒክና ሙያ /TVET/ ተቋማት እና የብቃት /COC/ ማዕከላት ሥልጠናና ምዘና ለመጀመር ቅድመ ዝግጅት በማካሄድ ላይ ይገኛሉ፡፡ እንደ የክልሎቹ ተጨባጭ ሁኔታ ምዘና ሊካሄድባቸው የሚችሉትን የሙያ ደረጃዎችና ተዛማጅ የትምህርትና የሥራ ልምዶችን የመለየትም ሥራዎች በመካሄድ ላይ ይገኛሉ፡፡ በካርታ ሥራ ላይ እርሾ ሊሆኑ የሚችሉ ከተለያዩ ክልሎች የተውጣጡ 19 ባለሙያዎች ከህንድ ሀገር በመጡ ከፍተኛ ባለሙያዎች ሰልጥነው ሰርቴፋይ የሚደረጉበት ሁኔታ ለመፍጠር እየተሠራ ነው፡፡ የዘርፉን የሰው ኃይል ልማት በረዥም ጊዜ ስልጠናዎች በዘላቂነት ለማረጋገጥም በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ለመስጠት የካሪኩለም ዝግጅት ተጠናቋል፡፡ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሚመራው የረዥም ጊዜ የትምህርት ፕሮግራም ተጠናክሮ እንዲቀጥልና ወደ ሌሎች ዩኒቨርሲቲዎችም እንዲሰፋ አቅጣጫ ተቀምጦ እየተሠራ ይገኛል፡፡

የዘርፉን አሰራር ስርዓት ለማዘመን እንዲቻልም በበጀት ዓመቱ ውስጥ በዘርፉ የተከናወነው በአዲስ አበባ በሁለት ወረዳዎች የሲስተም ሙከራ ትግበራ ለማድረግ የአፈጻጸም ዕቅድ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን እየተዘጋጀ ነው፡፡ በተያያዥ ደረጃውን የጠበቀ፣ ደህንነቱ፣ የተረጋገጠ፣ የሚያድግ /Scalable/ የመረጃ ማዕከል እንዲኖር ለማድረግ በአገር አቀፍ ደረጃ ለመንግስት ተቋማት የተዘረጋውን ኢንፍራስትራክቸር /Nationa Data center Infrastructure/ ጥራት እና አቅም በማጥናት በክልሎችና ፌደራል ደረጃ ለሚዘረጋው ኔትወርክ እና ዳታ ሴንተር ግብዓት በሚሆን መልኩ ተዘጋጅቷል፡፡

በሀገሪቱ 23 ከተሞች የይዞታዎች ፋይል የማደራጀት እና የዲጅታይዜሽን የዳሰሳ ጥናት ተካሄዷል፡፡ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ተከላና ማባዛት ሥራም በመካሄድ ላይ ነው፡፡ እንዲሁም የመቆጣጠሪያ ነጥቦች የመረጃ አያያዝና ጥበቃ ሥርዓት ለመዘርጋት ይረዳ ዘንድ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ እና

የነጥቦቹን አቀማመጥና አጠባበቅ ፎርማት እና የናሙና ዳታቤዝ በማዘጋጀት ለክልሎች ተላልፈዋል፡፡ ለዚህ ሥራ የሚያግዙ 83 ባለሙያዎች ከየክልሉ ተውጣጥተው በአዲስ አበባ በተግባር ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጎ ወደ ሥራ ተሰማርተዋል፡፡ በእነዚሁ ከተሞች የመሬት መረጃ ስርዓቱ ግብአት የሚሆን የአየር ፎቶግራፍ ማንሳት ሥራ (በረራውን) ከሚያካሂድ ድርጅት /INSA/ ጋር ውል ተፈጽሞ የአየር ፎቶግራፍ ማንሳት ሥራው በ12 ከተሞች ተከናውኗል፡፡ የ11 በክረምቱ ምክንያት ማካሄድ አልተቻለም፡፡

የመሬት ልማት እና ማኔጅመንት አሰራር ስርዓቱን ወደላቀ ደረጃ ለማሳደግም እንዲቻል የቅየሳ፣ ቤዝማፕና ካዳስተር ካርታ ስታንዳርድ እንዲጸድቅ ለማድረግ ከካርታ ሥራ ኤጀንሲ ጋር የጋራ መርሃ-ግብር ተዘጋጅቷል፡፡ በዚሁ መሠረትም ከሶስቱ ስታንዳርዶች መካከል ሁለቱ ተከናውነዋል፡፡

በ14 ከተሞች የመሬት ግብይትና አሰጣጥ አገልግሎትን ለማሻሻል የአሰራር ስታንዳርድ በማዘጋጀት ለመተግበር የተቻለ ሲሆን የጨረታ ግብይት እና መረጃ ሶፍትዌር ተዘጋጅቶ በሙከራ ፍተሻ ላይ ይገኛል፡፡ በከተሞች የመሬት ሀብት ምዝገባ አሰራር በመዘርጋት መረጃውን በመሰረታዊ ካርታ ላይ በማመላከት እና በመረጃ ቋት ለማደራጀትም ከተያዘው ዕቅድ አኳያ መረጃውን በዲጂታል ፎርማት ለማደራጀት የሚያስችል ጊዜያዊ ዳታ ቤዝ በማዘጋጀት አጠቃቀሙ በመፈተሽ ላይ ሲሆን በ33 ከተሞች ላይ 17,000 ሄክታር መሬት ለመመዝገብ ተችሏል፡፡ በአንድ ክልል የይዞታ ማህደርን በቀላሉ ለመፈለግ የሚያስችል (Automated Data Base) ሶፍትዌር እና የአድራሻ ስርዓት ዝርጋታ ጋር ተያይዞ የተዘጋጀውና የእያንዳንዱን ነዋሪ የተሟላ አድራሻ የያዘና ከGIS ጋር በማገናኘት የተሻለ መረጃ ሊሰጥ የሚችል ሶፍትዌር የተዘጋጀ ሲሆን አጠቃቀሙ ተፈትሾ የማሳደግ እና የማስፋት ስራ በቀጣይነት የሚከናወን ይሆናል፡፡

የመሬት ልማት እና ማኔጅመንት የማስፈጸም አቅም ለመገንባት ህብረተሰቡ እና የሚመለከታቸው አካላት ተገቢውን ግንዛቤ ለማስጨበጥ በተያዘው ግብ በፖሊሲው፣ በሊዝ አዋጅ እና በሞዴል ደንቡ የግንዛቤ መፍጠሪያ ፕሮግራሞች እና መድረኮች በመፍጠር የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ተከናውኗል፡፡ በቀጣይም በምናከናውናቸው ተግባራት የፈጻሚውን፣ የአመራሩን እንዲሁም የህብረተሰቡን ተሳትፎ ለማሳደግ የሚያስችሉ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ተከታታይ በሆነ አግባብ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

### 2.3.3. የመሬት ዝግጅት፣ አቅርቦት እና ይዞታ አስተዳደር ሥራችን

በበጀት ዓመቱ 10,188.8 ሄክታር መሬት ለተለያዩ አገልግሎቶች ለማቅረብ ታቅዶ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች በአጠቃላይ 16,924.03 ሄክታር መሬት ተዘጋጅቷል፡፡ ከዚህ ውስጥ 994.25 ሄክታር ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የማምረቻና መሸጫ ማዕከላት ግንባታ የሚሆን እና 1,294.87 ሄክታር ለኢንዱስትሪ አገልግሎት የሚውል ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር

በመተባበር ልዩ የኢንዱስትሪ ዞኖች በሚገነቡባቸው ከተሞች ማለትም በድሬደዋ 1,200 ሄክታር፣ በሐዋሳ 1,000 ሄክታር፣ በሰንዳፋ 1,400 ሄክታር እና በኮምቦልቻ 1,123 ሄክታር በጠቅላላው 4,723 ሄክታር መሬት በመከለል እና ሳይት ፕላን በማዘጋጀት ርክክብ የተፈጸመ ሲሆን ተዘጋጅቶ ወደ ከተማ መሬት ባንክ ከገባው የመሬት መጠን 15,631.6 ሄክታር ውስጥ 3,645.07 ሄክታር በጨረታ፣ በምደባ እና በድርድር ተላልፏል፡፡

የመሬት ይዞታ አስተዳደሩን ስርዓት ለማስያዝ ከተያዘው ግብ አኳያ በሊዝ ውል አፈጻጸም ላይ በተደረገው ክትትል በውላቸው መሰረት ካልፈጸሙ ከ158 ውል ፈጻሚዎች 259 ሄከታር መሬት በህጉ መሰረት ተመላሽ ለማድረግ የተቻለ ሲሆን ለ1,258 ውል ፈጻሚዎች ደግሞ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል፡፡ በ59 ከተማ አስተዳደሮች ድንበር ውስጥ ተከልሎ ለሚገኙ የገጠር ይዞታዎች እንዲሁም በከተሞች በጊዜያዊነት ለተያዙ ቦታዎች 15,062 የመሬት መጠቀሚያ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡ በህገ-ወጥነት የተያዙ ይዞታዎችን መረጃ በማደራጀት ስርዓት ለማስያዝ በተደረገው ጥረት በበጀት ዓመቱ 63,871 ቦታዎች መረጃ በማደራጀት ስርዓት ለማስያዝ የሚያስችል ጥናት እየተደረገ ሲሆን በ4,461 ቦታዎች ላይ የማፍረስ እርምጃ ተወስዷል፡፡ የሰነድ አልባ ይዞታዎችን መረጃ በማደራጀት ሰነድ እንዲያገኙ በታቀደው መሠረት 33,564 ሰነድ አልባ ይዞታዎች መረጃ ለማደራጀት ተችሏል፡፡ በዚሁ ጊዜ ውስጥ ለ26,447 ሰነድ አልባ ይዞታዎች ተገቢው ማጣራት ተደርጎ ሰነድ እንዲሰጣቸው ተደርጓል፡፡

ከተሞች የመሬት ሃብታቸውን በአግባቡ ለማስተዳደር እንዲችሉ የአስተዳደር ወሰን በመከለል፣ የከተሞች መሬት ሃብት ምዝገባ አሰራር በመዘርጋት፣ መረጃውን በመሠረታዊ ካርታ ላይ በማመላከት እና በመረጃ ቋት መደራጀቱን ለማረጋገጥ ከተያዘው ዕቅድ አኳያ 22 ከተሞች የአስተዳደር ወሰን ከልለው መረጃውን በዲጂታል ፎርማት በ33 ከተሞች /የአዲስ አበባ 10 ክፍለ ከተሞችን እንደ አንድ ከተማ በመውሰድ/ 24,653.56 ሄክታር መሬት በመመዝገብ ለማራጀት የሚያስችል ጊዜያዊ ዳታ ቤዝ የተዘጋጀ ሲሆን ተግባራዊ አጠቃቀሙም በመፈተሽ ላይ ይገኛል፡፡

## 2.4. የመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመንግስት ህንፃዎች ግንባታ ሥራዎች

### 2.4.1. የቤቶች ልማት የሕግ ጉዳይ ሥራችን

በከተሞች በመኖሪያ ቤት አቅርቦት ዙሪያ ያሉ ዘርፈ ብዙ ችግሮች በመፍታትና ቀደም ሲል የተጀመሩ የቤት ልማት ሥራዎች በተለይም በአዲስ አበባ በስፋት ለማስቀጠል እንዲሁም በክልሎች የተለያዩ የቤት አማራጮች ለማቅረብ እንዲቻል የከተማ ቤት ፖሊሲና የስትራቴጂ ማዕቀፍ ረቂቅ ሠነድ ተዘጋጅቷል፡፡ ሠነዱ በቀጣይ በስትራቴጂ፣ ፕሮግራምና የህግ ማዕቀፍ በዝርዝር ታይቶ የሚፈፀም ሆኖ ረቂቁ ለመንግሥት ከመቅረቡ በፊት ለአስተያየት ለክልሎች ተልኮ ምላሽ/ ግብረ-መልስ እየተሰጠበት ይገኛል፡፡ በከተሞች በሚታየው የቤት ችግር ግንባር ቀደም ተጎጂ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን የቤት ፍላጎት

ከቁጠባ ጋር አስተሳስሮ ለመፍታት እንዲያስችል የአነስተኛ ገቢ ያላቸው ነዋሪዎች የቤት ልማት ፕሮግራም ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ተዘጋጅቶ በመንግሥት ጸድቋል፡፡ በተመሳሳይ የ40/60 ቁጠባ ቤቶች ልማት ፕሮግራም ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ተዘጋጅቶ በመንግስት ጸድቋል፡፡ ሁለቱም ፕሮግራሞች ወደ ተግባር ለማሸጋገር ቅድመ ዝግጅቱ በማጠናቀቅ ላይ ነው፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ ያለ በቂ የሕግ ሽፋንና ወጥነት በጐደለው መንገድ ሲካሄድ የነበረውን የሪል ስቴት ልማት በአግባቡ በመምራት የተጠቃሚዎችን (የደንበኞችን) ፍላጎትና መብት ያስጠብቃል ተብሎ የሚታሰበው የሪል ስቴት ልማትና ግብይት አዋጅ ረቂቅ ተዘጋጅቶ አስተያየት እየተሰጠበት ይገኛል፡፡

### 2.4.2. በመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች የሕንፃ ዲዛይን ዝግጅትና ትግበራ ሥራዎች

ከቤቶችና ሕንፃ ዲዛይን ዝግጅትና ትግበራ ክትትል ጋር በተያያዘ ለ2004 በጀት ዓመት ከታቀዱት ሥራዎች መካከል የህብረተሰቡን የቁጠባ ባህል በማዳበርና 40% የቤቱን ወጪ እስከ 5 ዓመት በሚደርስ ጊዜ እንዲቆጥቡ በማድረግ ሊገነቡ የሚችሉ 5 የተለያዩ ስታንዳርድ ዲዛይኖች /የG+2 እና G+4 G+7, G+9 እና G+12/ ከመሠራታቸውም በላይ የተለያዩ ባለሙያዎችና ባለድርሻዎች አስተያየት ተሰጥቶበት እንዲጠናቀቅ ተደርጐ G+12 በመንግስት ከፀደቀ በኋላ ለትግበራ ተልኳል፡፡ በተጨማሪም ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የከተማ ነዋሪዎች ተደራሽና ወጪ ቆጣቢ የሆነ የአርክቴክቸራል፣ የስትራክቸራል፣ የኤሌክትሪካልና የሳኒተሪ ዲዛይን በአማካሪዎች ተዘጋጅቶና በባለሙያዎችና ከፍተኛ ኃላፊዎች በተሰጡ አስተያየቶች መሠረት ተስተካክሎ ሥራ ላይ እንዲውል እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል፡፡

ከመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ በግማሽ ዓመቱ ለስኳር ልማት የሚውሉ 17 የሚሆኑ የጋራዥና ለመኖሪያ ያልሆኑ የተለያዩ አገልግሎቶች ዲዛይኖች ተዘጋጅተው ለትግበራ ተልኳል፡፡ እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል ለሚገነባው የማዳበሪያ ፋብሪካ 8 ዓይነት የመኖሪያ ቤቶች እና 13 ለመኖሪያ ያልሆኑ አገልግሎቶች መስጫ ተቋማት ዲዛይኖችን ለማዘጋጀት አማካሪ ተመርጦ ወደ ሥራ ከመገባቱም በላይ አማካሪ ድርጅቱ ያዘጋጀውን የመጀመሪያ /ረቂቅ/ ዲዛይን አቅርቦ አስተያየት እየተሰጠበት ይገኛል፡፡ በተጓዳኝም ከብረታ ብረት ኮርፖሬሽን ጋር በመሆን ፋብሪካው የሚገነባባቸው ቦታዎች ተለይተዋል፡፡

በመጀመሪያ ምዕራፍ በአዲስ አበባ /ቦሌ ለሚና ቅሊንጦ አካባቢዎች/ በመቀጠልም በኮምቦልቻ፣ በድሬዳዋ እና በሐዋሳ ለሚካሄዱ የኢንዱስትሪ ዞኖች ግንባታ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና በሚኒስቴር መ/ቤታችን በጋራ የኢንዱስትሪ ዞን ልማት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ በቦሌ-ለሚ አካባቢ የፋብሪካ ሼዶች፣ የመኖሪያና መኖሪያ ያልሆኑ ግንባታዎች አስፈላጊው ዲዛይን በአማካሪ ኩባንያ ተዘጋጅቶ ለግንባታው የሥራ ተቋራጮች ተለይተዋል፡፡ ግንባታውም በአጭር ጊዜ እንደሚጠናቀቅ ይጠበቃል፡፡ ለቦሌ ለሚ የሚዘጋጀው ስታንዳርድ ዲዛይን በመጀመሪያው ምዕራፍ በአዲስ አበባ ቅሊንጦ አካባቢ፣ በመቀጠልም በኮምቦልቻ፣ በድሬዳዋ እና በሐዋሳ  የኢንዱስትሪ መንደሮች

ሊያገለግል ስለሚችል በዚህ ስታንዳርድ ዲዛይን መሠረት ዝርዝር ጥናትና ዲዛይን አማካሪዎች ለመቅጠር የሚያስችል ዝግጅት ተደርጓል፡፡

ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ማስፋፊያ የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት የሚውሉ 17 የተለያዩ ስታንዳርድ ዲዛይኖች በዚህ ግማሽ ዓመት ተዘጋጅቶ ርክክብ ተፈጽሟል፡፡ በተመሳሳይ 2 ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የንግድና አገልግሎት ማዕከላት ስታንዳርድ ዲዛይኖች ለማዘጋጀት በታቀደው መሠረት ለንግድ ማዕከላት የሚሆኑ ሁለት ዓይነት ዲዛይኖች /G+1 እና G+2/ በቅድሚያ በአዲስ አበባ በተለያዩ አካባቢዎች ለመንገባት እንዲቻል የዲዛይን ዝግጅት ተጠናቆ ለትግበራ ተልኳል፡፡ የንግድ ማዕከላት ግንባታው የአካባቢ ግብዓት የሚጠቀም፣ በፍጥነት ሊገነባ የሚችል፣ ሰፊ የሥራ ዕድል የሚፈጥር፣ ጥራቱን የጠበቀና አስተማማኝና አዳዲስ ቴክኖሎጂ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን የቴክኖሎጂ መረጣው በአዲስ አበባ አስተዳደር ዲዛይንና ግንባታ አስተዳደር ልማት ቢሮ በኩል ጨረታ ወጥቶ ሠነዱን የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚ/ርን ጨምሮ ከተለያዩ አካላት በተውጣጡ የባለሙያዎች ኮሚቴ እየተገመገመ ይገኛል፡፡ ውጤቱ ታይቶ ወደ ክልሎችም እንዲስፋፋ ይደረጋል፡፡

### 2.4.3. የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም አፈጻጸም

የአገር አቀፍ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድን ከማሳካት አንጻርና ያረጁና የተጎሳቆሉ አካባቢዎችን ለማሻሻልና የመኖሪያ ቤት እጥረትን ለመቅረፍ በመካሄድ ላይ የሚገኘው የአገር አቀፍ የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም ከአዲስ አበባና ሐረሪ ክልል በስተቀር በሌሎቹ ክልሎች እንዲቆሙ መደረጉ የሚታወስ ነው ፡፡ በዚሁ መሠረት በ2000 በጀት ዓመት በክልሎች ግንባታቸው ከ80 በመቶ በታች የሆኑት የየራሳቸው አማራጮች በማፈላለግ እንዲያስተላልፉ፣ ከ80% በላይ የደረሱት ደግሞ ለአፈጻጸሙ በተዘረጋው ስረዓት መሠረት ተጠቃሚዎችን ለይተው ከባንክ ጋር እንዲያስተሳስሩ አቅጣጫ የተቀመጠ ቢሆንም እስካሁን ሥራው እልባት እንዲያገኝ አልተደረገም፡፡

በክልሎች በ2000 የተጀመሩት 39,328 ቤቶች የበጀት ዓመቱ የግንባታ አፈጻጸም ሲታይ ኦሮሚያ 97.7 በመቶ፣ አማራ 92.1 በመቶ፣ ትግራይ 77.9 በመቶ፣ ደቡብ 97.23 በመቶ፣ ድሬዳዋ 86 በመቶ ሲሆን በሐረሪ ክልል በህብረተሰቡ የፋይናንስ ቁጠባ እየተካሄደ የሚገኘው የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ አፈጻጸም 89 በመቶ ነው፡፡ በአዲስ አበባ የነባር ሳይቶች 18 ሺህ ቤቶች አፈጻጸም 99.53 በመቶ ሲሆን በልደታ መልሶ ማልማት የተገነቡ 1,985 ቤቶች አፈጻጸም 98.0 በመቶ ደርሰዋል፡፡ በ2003 በጀት ዓመት የተጀመሩ 17,171 ቤቶች አማካይ የግንባታ አፈጻጸም 47.84 በመቶ የደረሱ ሲሆን በ2003 መጀመር ከነበረባቸው ቀሪዎቹን ከ2004 በጀት ዓመት ከተያዘ ዕቅድ ጋር በማጣመር ግንባታቸው በመጀመር ላይ ይገኛል፡፡ በ2004 በጀት ዓመት በዕቅዱ መሠረት ግንባታቸው መጀመር የነበረባቸው ሙሉ በሙሉ የተጀመሩ ሲሆን በአጠቃላይ ለ42,829 ቤቶች ግንባታ የመሬትና የዲዛይን ዝግጅት፣ የመሠረተ ልማት

አቅርቦት እና የስራ ተቋራጮች የሥራ ትስስር በመፍጠር ግንባታው ተጀምሮ አፈጻጸሙ 17.85% ለማድረስ ተችሏል፡፡ በሚቀጥለው ዓመት ከሚገነቡ ቤቶች ለአነስተኛ ገቢ ላለው ነዋሪና የ40/60 ጨምሮ የ35,000 ቤቶች ግንባታ በመጀመር ላይ ነው፡፡ በዚህ ዓመት በተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም፣ በስኳር ልማት ቤቶች ግንባታ እና በ10 አዲስ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ 4,306 የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች 2,000 ሥራ ተቋራጮች እና 42 አማካሪ ኢንተርፕራይዞች የተፈጠሩትን ጨምሮ በአጠቃላይ ለ183,980 ዜጎች የሥራ ዕድል ፈጥሯል፡፡

## 2.5. የከተሞች መሠረተ ልማት ማስፋፍያ ሥራዎች

የከተሞች መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮጀክት (Urban Local Government Development Project - ULGDP) በመንግስት ፀድቆ ተፈጻሚ እየተደረገ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህ ፕሮጀክት ከተሞች ለመሠረተ ልማት ማስፋፍያ፣ ለተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ እና አቅም ግንባታ፣ ለቄራ፣ ለገበያ ቦታዎች ማስፋፍያ፣ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ክላስተር ግንባታ እና ለሌሎች የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶችን ማጠናከሪያ እንዲውል ተደርጎ የተቀረጸ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

በያዝነው የበጀት ዓመት በፕሮጀክቱ ድጋፍ በ27 ከተሞች 245.5 ኪ.ሜ የድንጋይ ንጣፍ መንገድ 102 ኪ.ሜ የጎርፍ ማስወገጃ ቦይ፣ 194 ኪ.ሜ የጠጠር መንገድ፣ 5 አነስተኛ ገቢ ላላቸው የህብረተሰብ ክፍል አገልግሎት የሚውሉ የገበያ ማዕከላት፣ 56 የክላሰተር ሼድ፣ 29 የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶችና 5 የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ፕሮጀክቶች የዲዛይን፣ የኮንትራት አስተዳደርና ፕሮጀክቶቹ እንዲገነቡና አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ መንግስት ከዓለም ባንክ ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት የሚሰጠው ድጋፍ ከ19 ከተሞች በተጨማሪ 18 ከተሞች እንዲካተቱ እየተደረገ ነው፡፡ ለዚህ ሥራ የተመደበው በጀት ለሶስት ዓመት ከ150 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ያላነሰ ነው፡፡ በጀቱም የሚመደበው በፕሮጀክቶቹ የአፈጻጸም ደረጃ፣ ክልሎች ለከተሞቹ በሚሰጡት የማቺንግ ፈንድና የከተሞቹ ከዕቅድ ዝግጅትና የፋይናንስ አያያዝ ጋር በተያያዘ ተገምግመው በሚገኘው ውጤት መሠረት ነው፡፡ የዘርፉ የክልል አመራሮች ይህንን ሥራ ትኩረት ሰጥተው እየመሩት አይደለም፡፡ በተወሰነ ደረጃ በአንዳንድ ክልሎች ከሚደረገው ጥረት በስተቀር በአብዛኛው ክልሎቻችን በአግባቡ ባለመመራቱ በፕሮጀክቱ ቀጣይነት ላይ የራሱ ስጋት እየፈጠረ ነው፡፡

## 2.6. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ሬጉላቶሪ ሥራዎች

### 2.6.1. የኮንስትራክሽን ሕግ ዝግጅትና ማስፈጸም ሥራችን

በኮንስትራክሽን ዘርፍ ሊከናወኑ ከሚገባቸው ሥራዎች መካከል የኢትዮጵያ የሕንፃ አዋጅን ለማስፈጸም የሚያስችሉ ማስፈጸሚያ ሰነዶችን ማዘጋጀትና ያሉትንም ማሻሻል፣ አዋጁ ተፈጻሚ በሚሆንባቸው ከተሞች የሕንፃ ሹም እንዲመደብ እና ተጓዳኝ አደረጃጀቶችን (በሰው ኃይል፣ በቁሳቁስ እና በሥልጠና) ማሟላት ነበሩ፡፡ በዚሁ መሠረት የኢትዮጵያ የሕንፃ ደንብ ተዘጋጅቶ በሚኒስትሮች ም/ቤት የፀደቀ

ሲሆን የኢትዮጵያ የሕንፃ መመሪያ ተዘጋጅቶ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዲፀድቅ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም የሥራ ተቋራጮች የአፈጻጸም ደረጃ መመሪያ እና የአማካሪ ድርጅቶች የአፈጻጸም ደረጃ መመሪያ (Performance Ranking Guidelines)፣ የኢትዮጵያ የእሳት አደጋ መከላከያ መመሪያ (የሕንፃ)፣ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የብቃት ማረጋገጫ በሚሰጥባቸው የንግድ ሥራ መስኮች የንግድ ፈቃድ የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶችን ለመወሰን የተዘጋጀ መመሪያ፣ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ጤናና ደህንነት መመሪያ እና የመኖሪያ ሕንፃዎች ዲዛይን ማንዋል ተዘጋጅተዋል፡፡ በተጨማሪም በሥራ ላይ የሚገኙትን 11ዱን የሕንፃ ኮድ ስታንዳርዶችን ለማሻሻል እና ሶስት አዳዲስ ኮዶችን (የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የጤናና ደህንነት ኮድ፣ የአርክቴክቸራል ዲዛይን ኮድና የእሳት አደጋ መከላከያ ኮድ) ለማዘጋጀት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ጋር የውል ስምምነት ተፈጽሞ ሥራው ለዩኒቨርስቲው እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ የሥራ ተቋራጮች፣ የአማካሪ ድርጅቶችና የባለሙያ የምዝገባ መመሪያዎች ከወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ለማጣጣም ነባር መመሪያዎች በመፈተሽ መለወጥና መጨመር ያለባቸውን በመለየት ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት በማድረግ እና አስተያየት በማሰባሰብ መመሪያዎቹ ተዘጋጅተዋል፡፡ የመሠረተ ልማት ግንባታ ቅንጅታዊ አሰራር ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቷል፡፡

በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚሳተፉ አነስተኛና መካከለኛ ሥራ ተቋራጮች እና አማካሪዎች የፋይናንስና የመሣሪያ አቅማቸውን ለማሳደግ የአሰሪ፣ ተቋራጭና ፋይናንስ ተቋማት ለፕሮጀክት የብድር አሰጣጥ እና አመላለስ የሶስትዮሽ የብድር አሰጣጥ መመሪያ በመዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡ በአገሪቱ ያለው የግንባታ ግዥ አፈጻጸም ሥርዓት ወጥ እንዲሆን ለማድረግ ከመንግስት የግዢ ኤጀንሲ ጋር በመሆን የየክልሎችን የግዥ ሥርዓት በማጥናት ያሉትን ልዩነቶች ለማውጣት እና ልዩነቶችን ለማጥበብ የሚያስችሉ አማራጮችን ለማዘጋጀት ከኤጀንሲው ጋር በቅንጅት እየተሰራ ነው፡፡ እንዲሁም የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት አባል የሆኑበት ብሔራዊ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ም/ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ተዘጋጅቷል፡፡

የሕንፃ ሹም አሿሿምና ተጓዳኝ አደረጃጀቶችን በተመለከተ በሕንፃ አዋጁ እና በሕንፃ ኢንዱስትሪ ስትራቴጂ ላይ በፌዴራልና በየክልሎቹ ሥልጠና እንዲካሄድ የተደረገ ሲሆን የሕንፃ አዋጁ ተግባራዊ የሚሆንባቸው ከተሞች እንዲለዩ ተደርጓል፡፡ በዚህ በጀት ዓመት አዋጁ ተፈጻሚ ከሚሆንባቸው 271 ከተሞች ውስጥ በ99ኙ የማስፈጸሚያ መዋቅር እንዲዘረጋ ለማድረግ የተቻለ ሲሆን 33 ከተሞች ጽ/ቤቱን አደራጅተው በቋሚነትትና በጊዜያዊነት የሕንፃ ሹም መሰየማቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙ እጅግ መዘግየት የሚታይበት ነው፡፡

### 2.6.2. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሰው ኃይል ልማት፣ የደረጃዎች ዝግጅትና ትግበራ ሥራችን

በኮንስትራክሽን ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሙያዎች በዚህ ዓመት በTVET አማካይነት ለማካሄድ የሙያ ዓይነቶችና ደረጃዎች መለየት፣ የምዘና መሳሪያዎች (Assesment tools) እና ካሪኩለም የማዘጋጀት ስራዎች ተከናውነዋል፡፡

በመሆኑም በተለዩት 5 ደረጃዎች ውስጥ ለተካተቱ 18 የሙያ ዓይነቶች እና 54 የምዘና መሳሪያዎች የተዘጋጁ ሲሆን የተለያዩ የምዘና ማስፈጸሚያ ሰነዶችን እና ምዘናውን የሚያካሄዱ አካላትን በመለየትና የጋራ ዕቅድ በማዘጋጀት ምዘናው እየተካሄደ ይገኛል፡፡ የምዘና ስራው በሙከራ ደረጃ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሚገነቡ የመንግስት ሕንፃዎች ማለትም በቤቶች ልማት ፕሮጀክቶች በሚሰሩ የጋራ መኖሪያ ቤቶች እና የተለያዩ የመንግስት ግንባታዎች ላይ በተሰማሩ ባለሙያዎች ከነሐሴ ወር 2003 ጀምሮ ስራው ቢጀመርም የመሪ መዛኞችን አስቀድሞ ማፍራት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የመሪ መዛኞች ምዘና ከጥር ወር 2004 ጀምሮ በተጠናከረ መልኩ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ በበጀት ዓመቱ በአጠቃላይ 10 ዙር የግንዛቤ ማስጨበጫ ለስትሪንግ ኮሚቴ አባላት እና ለባለሙያዎች የተሰጠ ሲሆን በስልጠናው ላይ በአጠቃላይ በአራት ዙር በድምሩ 1,841 ባለሙያዎች ተገኝተው መሪ መዛኝ ለመሆን ማሟላት ያለባቸውን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ወስደዋል፡፡ በወጣውም የምዘና መርሃ-ግብር መሰረት ተመዝግበው ለምዘና ጥሪ ከተደረገላቸው 647 ባለሙያዎች መካከል 607 ባለሙያዎች ቀርበው ተመዝነዋል፡፡ ከተመዘገቡት መካከል በምዘና መርሃ-ግብሩ መሠረት ከተፈተኑት ውስጥ 382 ብቁ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ ከእነዚህ መካከል 63ቱ በመሪ መዛኝነት ተመርጠዋል፡፡ በተጨማሪም ያለውን የመሪ መዛኝ ክፍተት ለመሙላት አስፈላጊውን መስፈርት አሟልተው ከሰኔ 26 እስከ 30 ቀን 2004 ድረስ የምዘና መርሃ ግብር ወጥቶላቸው የሚጠባበቁ 158 ባለሙያዎች ይገኛሉ፡፡

## 2.7. የከተሞች ያልተማከለ አስተዳደር፣ የሕዝብ ተሳትፎ እና የአቅም ግንባታ ሥራዎች

### 2.7.1. ያልተማከለ አስተዳደር እና የሕዝብ ተሳትፎ ማሻሻያና ማጠናከሪያ ሥራችን

የከተሞች የሕዝብ ንቅናቄ ረቂቅ እስትራቴጂ ተዘጋጅቷል፡፡ በአራት አጀንዳዎች ላይም ለሕዝብ ውይይት መነሻ የሚሆኑ ሰነዶችም ተዘጋጅተው ከእስትራቴጂው ጋር ለከተሞቹና ለክልል የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ስልጠና መስጠት ተጀምሯል፡፡ በመጀመሪያ ዙር ለ57 ፈጻሚና አመራሮች የተሰጠ ሲሆን በተከታታይ ለ160 ፈጻሚዎችና አመራሮች ይሰጣል፡፡ ያልተማከ አስተዳደር ለመዘርጋትና ለማጠናከር የሚያስችል የስትራቴጂ ረቂቅ ተዘጋጅቶ ውይይት እየተደረገበት ነው፡፡

### 2.7.2. ለከተሞች የሚሆን የፈጻሚና የአመራር የሰው ኃይል ልማትና ዝግጅት ሥራችን

በተመረጡ 10 የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች የሙያ ደረጃና ስታንዳርድ ለማዘጋጀት ፕሮፖዛል ቀርቦ ፀድቋል፡፡ በፀደቀው ፕሮፖዛል መሠረት በደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ፣ በዘላቂ ማረፊያና መዝናኛ፣ በውበትና መናፈሻ፣ በጥልቅ የጉድጓድ ውሃ ሥራዎች፣ የውሃ ሂሳብ ክፍያ ሥራ፣ በእሳትና ድንገተኛ አደጋዎች

መከላከልን መቆጣጠር፣ በሲቪል ምዝገባና ዋና ዋና ኩነቶች ስታቲስቲካዊ መረጃዎች፣ በደንብ ማስከበር፣ በሕዝብ ተሳትፎ እና ንቅናቄ በመሬት የካዳስተር ቅየሳ እና የከተማ ፕላን ዝግጅት ላይ የሙያ ደረጃና የብቃት ምዘና መስፈርት ተዘጋጅቷል፡፡ ይህን መስፈርት መሠረት በማድረግ ከደረጃ አንድ እስከ አምስት የተዘጋጁ 45 ሙያዎች ተቀርጸዋል፡፡ በሙያ ደረጃዎቹ ላይ ከክልል ከተማ ልማት ቢሮዎች፣ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲዎች እና ከክልል የምዘና ተቋማት ለተውጣጡ 27 ባለሙያዎች ግንዛቤ እንዲጨብጡ ተደርጓል፡፡ ለተቀረጹት የሙያ ደረጃዎች፣ ለስምንቱ ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በተደረገ ስምምነት እና አገልግሎቶቹን ከሚሰጡ መስሪያ ቤቶች ጋር በመሆን በ45ቱ ሙያዎች ላይ ስርዓተ ትምህርት ተዘጋጅቷል፡፡ እንዲሁም አገልግሎቱን የሚሰጡ ባለሙያዎችን ለመመዘን የብቃት ምዘና መሳሪያዎች /Assesement tool/ ተዘጋጅቷል፡፡

ባለፈው በጀት ዓመት ውስጥ በተመረጡ የከተማ ልማትና አገልግሎት መስኮች የከተማ ልማትን ሊያጠናክሩ በሚችሉ ስፔሻላይዝድ ዘርፎች (በከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት፣ በከተማ ፕላንና ልማት፣ በከተማ ሥራ አመራር፣ በከተማ መሠረተ ልማት አቅርቦትና ማኔጅመንት እና በከተማ አካባቢና የአየር ለውጥ ማኔጅመንት) ላይ 210 ሰልጣኞች በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ የድህረ ምረቃ ስልጠና እየተከታተሉ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በፕሮጀክቱ በየደረጃው ያለውን የፈጻሚ አቅም ለማጎልበት የሚያስችል ከላይ በተዘረዘሩት ስፔሻላይዜሽን ዙሪያ 250 ሰልጣኞችን ለማሰልጠን የሚያስችል የገንዘብ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ባሳለፍነው በጀት ዓመት ከክልሎች ለተውጣጡ 84 ባለሙያዎች በመሬት ልማትና ማኔጅመንት ዙሪያ የ11 ወራት ስልጠና ተሰጥቷቸው ወደ ክልሎቻቸው ተመልሰዋል፡፡ በተጨማሪም ከ6 የከተማ አስተዳደሮች ለተውጣጡ ባለሙያዎች በULGDP (ከዓለም ባንክ ጋራ የሚሰራ) ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ማንዋሎች ማለትም በአካባቢና ማኅበራዊ ደህንነት አጠባበቅ ማኔጅመንት እና በመልሶ የማስፈር ሥርዓት ላይ በፕሮጀክቱ ከሚደገፉ 19 ከተሞች እንዲሁም ከክልል የአካባቢ ጥበቃ ለተውጣጡ 72 ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በግዥ፣ በኮብልስቶን እና ኮንትራት አስተዳደር ላይ ለ30 ባለሙያዎች እንዲሁም በካፒታል ኢንቨስትመንት ፕላን (CIP) ላይ ለ48 ባለሙያዎች እንደዚሁ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

### 2.7.3. የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ስታንዳርድ ማሻሻልና የአፈጻጸም ምዘና ሥራችን

የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ስታንዳርዳይዜሽንና የአፈጻጸም ምዘና ሥርዓት ለመዘርጋት እንዲቻል ረቂቅ የማስፈጸሚያ የስትራቴጂ ሰነድ ተዘጋጅቶ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መግባባት የተፈጠረ ሲሆን ስርዓቱን ለመዘርጋት የሚያስችል መሪ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተሻለና ምርጥ ተሞክሮ ያላቸውን ከተሞች መነሻ በማድረግና የተገኘውን ምርጥ ተሞክሮ በመቀመር ስታንዳርድ ማዘጋጀት እንዲቻል ስታንዳርድ የሚዘጋጅላቸውን አገልግሎቶች

የመለየትና የስታንዳርድ ግኘሮዎችን የማካሄድ ሥራ እየተከናወነ ነው፡፡ በተጨማሪም የሁለት ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች ማለትም የኮንትራክተር፣ አማካሪዎች፣ ባለሙያዎችና የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ምዝገባ አገልግሎት እና የእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር አገልግሎት ስታንዳርድ ዝግጅት ተከናውኗል፡፡ በቅርቡም ስልጠና ተሰጥቶ ወደ ተግባር ይገባል፡፡

### 2.8. የከተሞች ጽዳትና ውበት ሥራዎች

የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሸ አያያዝና አወጋገድን ለማሻሻል የከተሞች ጽዳትና ውበት ማረጋገጥ እና የሥራ ዕድል ፈጠራ ስልትና አተገባበር ጥናት፣ ዘመናዊ የቀልዝ (composting) አዘገጃጀትና አተገባበር ዘዴ ማንዋል፣ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ዕቅድ አዘገጃጀት ማንዋል ተጠናቀዋል፡፡ የተቀናጀ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሥርዓት ስታንዳርድ እና አራት የውበትና አረንጓዴ ልማት ጥናቶች በመካሄድ ላይ ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም ንጹህና አረንጓዴ የወንዝ ዳርቻ ቦታዎች አያያዝ ማንዋል ዝግጅት ጥናት በመጠናቀቅ ላይ የሚገኝ ሲሆን በከተሞች የእግረኞች መንገድ ላንድስኬፕ ዲዛይን ስታንዳርድ ማንዋል ዝግጅት በመካሄድ ላይ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በከተሞች ጽዳትና ውበት አገልግሎት ዘርፍ ለ224 ዜጎች በቴክኒክና ሙያ በከተሞች ጽዳትና ውበት ቢሮ አገልግሎት ዘርፍ ስልጠና እንዲሰጥ የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት ተጠናቋል፡፡ በዚህ ረገድ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት በኩል ሊተኮርባቸው የሚገቡ ርዕሰ ጉዳዮች የሚያሳይ ጠቋሚ የጥናት ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡ በዘርፉ ስልጠና ለሚሰጥባቸው የሙያ ዓይነቶች እና የሙያ ደረጃዎችን የሚያመላክት ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡ የሥርዓተ ትምህርት ቀረጻውም ተካሄዷል፡፡ በተጨማሪም የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እንዲሁም የከተሞች ፍሳሽ ቆሻሻ ማኔጅመንት ስትራቴጂ ረቂቅ ተዘጋጅቶ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት እየተደረገበት ነው፡፡

## 3. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ የ2005 ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገቡ ሥራዎች

### 3.1. የለውጥና የልማት ሥራ አመራርና የሠራዊት ግንባታ ሥራዎች

በ2004 የተጀመሩ የለውጥ መሳሪያዎች ትግበራ ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ በስራ ዕድል ፈጠራ የልማት ሰራዊት ግንባታ ቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ወደ ተሟላ ትግበራ እንዲሸጋገሩ ይደረጋል፡፡ በመሬት ልማትና ማኔጅመንትና በቤቶች ግንባታ ሥራዎች ለሰራዊት ግንባታ በቅድመ ዝግጅት ደረጃ መሠረት ያለው ሥራም ይሰራል፡፡ ይህንኑ ይዘን የመልካም ልምድ ቅመራና የማስፋት ስራም እንሰራለን፡፡ እነዚህን ሥራዎች የጋራ ራዕይ እና ተልዕኮ ጨብጦ ወደ ተግባር መግባት መሠረታዊ ጉዳይ በመሆኑ ከሴክተሩ ሥራዎች ጋር በቀጥታ በተያያዙ (tailor-made) እና የተዘረዘሩ የስትራቴጂ ሰነዶች ላይ በመጀመሪያ የአሰልጣኞች ስልጠና በመስጠት በተዋረድ እስከ እያንዳንዱ ፈጻሚ የሚወርድበት ዕቅድ ተዘጋጅቶ ይተገበራል፡፡ ሰነዶቹም፡-

ሀ. የከተማ ሥራችን የአመራር ጥበብ፣

ለ. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂና ተያያዥ ሰነዶች፣

ሐ. የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ፖሊሲ እና ተያያዥ ሰነዶች፣

መ. የከተማ ቤት ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ፣

ሠ. የከተሞች የተቀናጀ የመሠረተ ልማት አቅርቦት ፖሊሲ እና የአፈጻጸም ስልቶች፣

ረ. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ፣

ሰ. የከተሞች ያልተማከለ አስተዳደርና የሕዝብ ተሳትፎ ስትራቴጂ

ሸ. የከተሞች የአረንጓዴ ልማትና የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ስትራቴጂ፣ እና

ቀ. በከተማ ሥራችን የትምህርታዊ እና የልማታዊ ኮሚዩኒኬሽን ስትራቴጂ ናቸው፡፡

ለልማትና የለውጥ ሰራዊት ለመገንባት በተቋማት፣ በቡድንና በመምሪያ የሚፈጠር ህዋስ በከተማ አስተዳደሮች ደግሞ በሰፈር የሚፈጠር ህዋስ ወሳኝ የትግል አውድማ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ ለዚህም የሚያግዝ አደረጃጀትና አሰራር ይፈጠራል፡፡ በተቋማት ከፌደራል እስከ ከተማ አስተዳደሮች በእያንዳንዱ መዋቅር መምሪያ ወይም ቡድን ወይም ዴስክ ደረጃ የህዋስ አደረጃጀት በመፍጠር በአሰራርና በተግባር አፈጻጸም ሂደት ለሚፈጠሩ ማነቆዎች መፍትሔ እንዴት እንደሚሰጥ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ በዚህ ሂደትም ግንባር ቀደሞች የሚለዩበት መድረክ እንዲሆን ተደርጎ ይመራል፡፡ የከተማ ነዋሪውም በተለይ በአዲስ አበባ ከወረዳ በታች ባለው የቀጠና እና የሰፈር አደረጀጀት ሕዝቡ በራሱ ነፃ አገልግሎት የሚሰጡትን ነዋሪዎች በመምረጥ ምክር ቤት እንዲኖረው በትርፍ ጊዜ የሚያገለግሉ አስፈጻሚዎች እንዲኖሩትና በተለይ በቀጠና ደረጃ አንድ የጽ/ቤት ኃላፊና ረዳቱ በቋሚነት እንዲመደቡ ይደረጋል፡፡ በዚሁ የሕዝብ አደረጃጀት አማካይነት መሠረታዊ ድርጅትና የህዋስ አደረጃጀት በመፍጠር ሕዝቡ በአካባቢው ልማትና መልካም አስተዳደር ተሳታፊ እና ባለቤት የሚሆንበት ሁኔታ እንፈጥራለን፡፡ በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ በአካባቢ ልማት፣ በመሬት ጥበቃና የመረጃ ማጥራት፣ በቁጠባ እና በጋራ ቤቶች አቅርቦት ዕድል አጠቃቀም፣ በመሠረተ ልማት አቅርቦትና አጠባበቅ፣ በጋራ ቤቶቹ አስተዳደር ሥርዓት፣ በአካባቢ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና የአረንጓዴ ልማት ወዘተ ሕብረተሰቡ በባለቤትነት በየወሩ መጨረሻ ቅዳሜ ከ3፡00 - 7፡00 ባለው ጊዜ ተሰብስቦ ዕቅድ ይገመግማል፣ መፍትሔ ያስቀምጣል የቀጣይ አቅጣጫ የሚያስቀምጥበት ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

በፌደራል መ/ቤታችን የተቀናጀ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማትና የልማታዊ ድጋፍን በላቀ ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ የሥራ ክፍሎች የማስፈጸም አቅም ጋር በተያያዘ የሚያጋጥማቸውን ችግር መፍታት የሚያስችሉ የለውጥ መሳሪዎቹን በኦቶሜሽን በመደገፍ ስራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ በተለይ የተቋማዊ የስራ ምዘና በፌደራል ደረጃ ተጠናቆ ወደ ክልሎችም እንዲስፋፋ ይሞክራል፡፡

### 3.2. የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የማስፋፋት ሥራዎች

በያዝነው በጀት ዓመት የመጀመሪያው ትኩረታችን የሥራ ዕድል ፈጠራ ሆኖ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ በመደበኛ የድጋፍ አሰጣጥና በዋነኛነት በዜጎች ጥረት በድምሩ ወደ 618,832 የሥራ ዕድል ይፈጠራል፡፡ የሥራ ዘርፎቹም ከጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ዝግጅት 72,592፣ ከእንጨትና ብረታ ብረት ሥራ 53,338፣ ከምግብ ዝግጅት እና አግሮ ፕሮሰሲንግ 70,329፣ ከመንግስት ትላልቅ ፕሮጀክቶች ውጭ ካለው ኮንስትራክሽን 181,288፣ ከከተማ ግብርና 71,202፣ ከንግድ ሥራ 37,418፣ ከአገልግሎቶች አቅርቦት ሥራ 132,665 እንደሚፈጠር ታቅዷል፡፡ በመንግስት ትላልቅ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ፕሮጀክቶች ደግሞ በድምሩ 1.1 ሚሊዮን የሚሆን የሥራ ዕድል ይፈጠራል፡፡ ይህም ከቤቶች ልማት 182,335፣ ከኃይል ግንባታና ልማት 121,114፣ ከመስኖና ግድቦች 48,662፣ ከገጠር መንገዶች ልማት 382,713፣ ከባቡር ግንባታ 131,040፣ ከኮብል እስቶን መንገድ ግንባታ 120,662፣ ከማዳበሪያና ኢንዱስትሪ ዞን ልማት 37,077 እና ከስኳር ፕሮጀክቶች 48,662 የሥራ ዕድል ይፈጠራል፡፡ አጠቃላይ የዓመቱ ዕቅዳችንም 1.7 ሚሊዮን ይሆናል ማለት ነው፡፡ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ከፀደቀው 600,000 ዕቅዳችን ሶስት እጥፍ መሆኑ ነው፡፡

ከሥራ ዕድል ፈጠራና የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ከማስፋፋት አኳያ ሁለተኛው ሥራችን በታቀደው ልክ የሥራ ዕድሉ እንዲፈጠር እና ለልማት ሠራዊት ግንባታ መሠረት ለመጣል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ አቅም የማጠናከር ሥራ ነው፡፡ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የማስፋፋት የመሪነት ሚና መጫወት ያለበት ከፌደራል ጀምሮ በክልል፣ በዞን፣ በከተማ፣ በወረዳና በአንድ ማዕከል ደረጃ የተደራጀው ኤጀንሲ መሆን አለበት፡፡ ተቋሙን ለሰራዊት ግንባታ ተልዕኮ ለማዘጋጀት በተለይ ከሰው ኃይል የአስተሳሰብና የተግባር ዝንባሌ አንጻር ተገምግሞ የተልዕኮ ዝግጁነት ደረጃው የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡ በተለይ ለለውጡና ልማት ሰራዊት ትግበራ መነሻ እንዲሆን የተዘጋጀው ጋይድ ላይን በምን ደረጃ አስተግባሪ ባለቤት እንዳገኘ መፈተሽ አለበት፡፡ የድጋፍ ማዕቀፎቹም በምን ደረጃ እየተተገበሩ መሆኑንም በዝርዝረ አይቶ በተሟላ መልኩ እንዲተገብሩ መደረግ አለበት፡፡ የአነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ልማት ም/ቤትም በአግባቡ ተደራጅቶ ስብሰባዎቹ ሳያቆራርጡ መካሄድ ይኖርባቸዋል፡፡ እያንዳንዱ የም/ቤት አባልም የዓመት የሥራ ድርሻውን በዝርዝር አቅዶ ለም/ቤቱ አቅርቦ ማፀደቅ አለበት፡፡ አፈጻጸሙንም በመደበኛነት በተከታታይ እየተገመገመ ግብረ መልስ መሰጠት አለበት፡፡ ሥራው ከሚኖረው ፋይዳ አንጻር የሥራው ባለሙያዎች (Subject Matter Experts —SME) ያሉበት የተለያዩ ቴክኒካል ኮሚቴዎች በም/ቤቱ ስር ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡ ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት መስፋፋት ዋናው አንጓ (node) የአንድ ማዕከል አገልግሎት በመሆኑ በአገልግሎት አቅርቦት ተነሳሽነቱ፣ በግብዓትና በሰው ኃይል ማደራጀት በኩል የተሻለ ትኩረት ሰጥቶ በፍጥነት ማጠናቀቅና ወደ ተግባር በተሟላ መልኩ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡

በሶስተኛ ደረጃ የድጋፉ አደረጃጀቶችን የማጠናከርና ወደ ተሟላ ትግበራ የማስገባት ስራ ነው፡፡ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት በአሰራርና በክህሎት ትራንስፎርም ከማድረግ አንጻር ተልዕኮ ከተሰጣቸው ተቋማት የቴክኒክና ሙያ ተቋም አንዱ ነው፡፡ የኦፕሬተሮቹ የአስተሳሰብና የተግባር ዝንባሌያቸውን ከማስተካከል አንጻር ትልቅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡ የአገልግሎትና የምርት በቀጣይነት የማሻሻል አስተሳሰብ እንዲገነቡ የሚያስችል አቅምና ዝግጁነት እንዲፈጠርላቸው ያስፈልጋል፡፡ ይህ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ተልዕኮ ከካይዘን ጋር አያይዘው በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት ውስጥ እንዲያስተገብሩት ዕቅድ ተይዞ እየተሰራ ነው፡፡ ኦፕሬተሮቹ ለተሰማሩበት ስራም በቂ ክህሎት እንዲኖራቸውም የማድረግ ተልዕኮ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ነው፡፡ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና የኤክስቴንሽን አገልግሎት የመስጠት ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው፡፡ የልህቀት ማዕከላቱም የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የመስጠት አቅማቸው አጠናክረው በስፋት መሄድ የሚችሉበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡ በምዘና የሚወድቁትንም በተከታታይ ስልጠና ዳግም ተመዝነው የሚያልፉበት ሥርዓትም መዘርጋት ይኖርበታል፡፡ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ራሳቸውን በካይዘን አሰራር አደራጅተውና ቀጣይነት ያለው የመሻሻል ምህዋር ውስጥ በመግባት የአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማትን የካይዘን አሰራር እንዲረዱት በማድረግ የምርትና የአገልግሎት አቅርቦታቸውን በቀጣይነት የሚያሻሽሉበት አቅም መፍጠር ይጠበቅበታል፡፡ የአነስተኛ ብድር ተቋማትም ሕብረተሰቡን ለቁጠባ ማነሳሳት ላይ ሰፊ ሥራ እንዲሰሩ ይጠበቅባቸዋል፡፡ መዋቅራቸውንም እስከ አርሶ አደሩ በማድረስና የቁጠባና ብድር ኤጀንት በማሰማራት እስከ አሁን ከነበራቸው ቁጠባ በእጥፍ የማሳደግ ዕቅድ ይዘው መረባረብ አለባቸው፡፡ ለአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋማት ለማምረቻ የሚሆኑ ቦታዎች ይዘጋጁ ዘንድ ለክልሎች ዲዛይን ተዘጋጅቶ ተልኳል፡፡ በዚሁ መሠረት የክላስተር ግንባታዎች እየተካሄዱ ነው፡፡ ከዚህ በፊት የተካሄዱም አሉ፡፡ ግንባታዎቹ በፍጥነት ተካሄደው አብዛኛዎቹ ከየካቲት በፊት ለአገልግሎት መብቃት አለባቸው፡፡ ለአገልግሎት እና ንግድ የሚሆን ሕንፃ አቅርቦት የሚሆኑ ቦታዎች ዲዛይንም በፌደራል ተዘጋጅቶ ለክልሎች እንዲላክ ይደረጋል፡፡ በዲዛይኑ መሠረት ከተሞች የንግድና የአገልግሎት ማዕከላት እንዲፈጠሩ ግንባታውን አካሂደው ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ማዘጋጀት አለባቸው፡፡ የማምረቻና የመሸጫ ሕንጻዎች፣ ክላስተሮችና ሼዶች ብዛት በማገናዘብ በቀጣይም የኢንዱስትሪ ዞኖች ሼድ ግንባታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህንን ሀብት የሚያስተዳድር ኢንተርፕራይዝ መፍጠር ያስፈልግ ይሆናል፡፡ ኢንተርፕራይዙ ከመሳሪያና መሸጫ ቦታዎቹ የሚሰበሰበው ገንዘብ መልሶ በቀጣይነት በገቢው በቀጣይነት ለአነስተኛና ጥቃቅን ኦፕሬተሮች መስሪያና መሸጫ ግንባታ እያካሄደ እንዲሄድ እና የንብረቶቹም አስተዳደር ውጤታማ እንዲሆን ሊያግዘን ይችላል፡፡

ለአራተኛው ለአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃቸውን መሠረት ያደረገ ልማታዊ ድጋፍ የመስጠት ሥራችን ነው፡፡ በስትራቴጂው ላይ በግልጽ እንደተመለከተው ለአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ድጋፍ ስንሰጥ ዕድገታቸውንና የዕድገት ደረጃቸውን ባገናዘበ መልኩ መሆን

እንደሚኖርበት ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም ኦፕሬተሮቹን በሶስቱ ደረጃዎች በመለየት ትኩረት ሰጥተን መስራት ይኖርብናል፡፡

በምስረታ ደረጃ ላይ ያሉ ስራ ፈላጊዎች የሚያጋጥማቸው መሠረታዊ ችግር ወደ ስራ የሚያስገባቸው የብድር ገንዘብ ማግኘትና የክህሎት ማነስ በመሆኑ ያለምንም ገንዘብ ባላቸው ጉልበትና ክህሎት በቀጥታ ወደ ተግባር የሚያስገባቸው የኮብልስቶን፣ የከተማ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣ የከተማ አረንጓዴ ልማት፣ የኮንስትራክሽን፣ የማዕድን (ወርቅ፣ ኦፓል፣ ድንጋይ፣ አሸዋ)… ወዘተ ስራዎች ላይ አሳምኖና አደራጅቶ ማሰማራት ወሳኝ ተግባር ተደርጎ መወሰድ ይኖርበታል፡፡ የክህሎት ስልጠናውም በቴክኒክና ሙያ ተቋማት አማካይነት በስልጠና ጥራት ላይ ምንም ዓይነት መንጓደል እንዳይኖር በማድረግ ማካሄድ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ዓይነት ጀማሪ ኢንተርፕራይዞች መነሻ ገንዘብና ብድር ሳያስፈልጋቸው ወደ ስራ እንዲሰማሩ ማድረግ ይቻላል፡፡ ገቢ ማግኘት ሲጀምሩ ከገቢያቸው የተወሰነውን እንዲቆጥቡ የሚያስገድድ አሰራር እና በቀጣይነት እንዲያድጉ እና እንዲሻሻሉ የሚያስችላቸው አስተሳሰብ እንዲይዙ ስልጠና የሚያገኙበት አሰራር መፈጠር ይኖርበታል፡፡ በስራ የተሰማሩ ዜጎች በቆጠቡት ገንዘብ አማካይነት የተወሰነ ብድር እንዲያገኙ በማድረግ ኢንተርፕራይዝ እንዲመሰርቱና ወደ ታዳጊ ደረጃ ኢንተርፕራይዝ እንዲሸጋገሩ ዝርዝር ዕቅድ ከእነሱም ጋር ሆኖ በማዘጋጀት ማስፈጸም ይገባል፡፡ ለዚሁ አፈጻጸም ያግዝ ዘንድ በአንድ ማዕከል የሚሰጡ አገልግሎቶችም የቁጥጥር (Regulatory) ባህርይ ያላቸው ሳይሆን የተወዳዳሪነት አቀም የመፍጠር (Facilitaton role) ሚና እንዲኖራቸው ማድረግና በዚሁ ልክ መምራት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም የምዝገባ፣ የግብር ከፋይነት ቁጥር፣ የስልጠና፣ የሥራ፣ የመስሪያ ቦታ በፍጥነት እንዲጠናቀቁላቸው የሚያስችል አሰራር የመዘርጋትና የአፈጻጸሙ የክትትልና ድጋፍ አግባቡ ተጠናክሮ መቀጠል ይጠበቅበታል፡፡

በታዳጊ ደረጃ ያሉ ኢንተርፕራይዞችን በተመለከተ የሚሰጡ ድጋፎች ኢንተርፕራይዞቹ የካይዘን አሰራር እንዲለመዱ እና የኢንተርፕሬነርሽፕ ባህሪ እንዲላበሱ የሚያስችላቸው የተለያዩ ስልጠናዎችና ልማታዊ ድጋፎች እንዲያገኙ ፋሲሊቴት ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ በንግድ ዘርፍ ተዋናይነታቸው የኮርፖሬት ባህርይ ለምሳሌ ብድር የመመለስ እምነት (value) እንዲይዙ፣ በተሰማሩበት ስራ የድጋፍ የአስተሳብ ዝንባሌ ሳይሆን የተወዳደሪነት የአስተሳሰብ ዝንባሌ የሚያላብስ ባህርያት እንዲያጎለብቱና በራሳቸው ምርት እና አገልግሎት ተማምነው ወደ ገበያ መግባት የሚያስችላቸው ስልጠናዎች በቂ ዝግጅት ተደርጎ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ የመስሪያና የመሸጫ ቦታዎቹን በአግባቡ እንዲጠቀሙበት እንዲሁም ብድር በአግባቡ እየመለሱ፣ ገቢ ሲኖራቸውም ያለግዳጅ መቆጠብ የሚችሉና በቀጣይነትም ለሥራዎቻቸው ከተለያዩ ባንኮች በሕጋዊ መንገድ እና የብድር መስፈርቶችን አሟልተው መበደር የሚችሉ ተቋሞች እንዲሆን ማስቻል ያስፈልጋል፡፡

ለገበያ ተወዳዳሪነት የበቁና ታዳጊ መካከለኛ ደረጃ ያሉ የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞችን በተመለከተ የሚሰጡ ድጋፎች ደግሞ በዋነኛነት የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም የሚያስችላቸው አሰራር በመዘርጋት ተጠቃሚ ስለመሆናቸው ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የወሰዱትን ብድር ውጤታማ በሆነ መንገድ ተጠቅመው እና በገቡት ውል መሠረት ወቅቱን ጠብቀው የሚመልሱ መሆናቸው በማረጋገጥ ይህንኑ የሚገልጽ ዕውቅና የሚያገኙበትና የበለጠ የሚበረታቱበት ሥርዓት መዘረጋት ጠቃሚ ነው፡፡ ተቋማቸውን በካይዘን አሰራር በማያቋረጥ የዋጋና የጥራት መሻሻል እንቅስቃሴ ውስጥ ለማስገባት የሚያደርጉት ጥረት መከታተልና መደገፍ ያስፈልጋል፡፡ ብድር ከትልልቅ ባንኮች መበደር የሚያስችላቸው ቅድመ ሁኔታ ያላቸው መሆናቸውን የሚያረጋግጥ እና ተወዳዳሪ ቁመና የያዙ መሆናቸውን ሲረጋገጥ የመስሪያ ቦታና ብድር አግኝተው ከአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋምነት ወደ መካከለኛ ተቋምነት የሚሸጋገሩበትና የሚመረቁት ሥነ-ሥርዓት መካሄድ ይኖርበታል፡፡ የሚሰጡ ድጋፎችም ይህንኑ ታሳቢ ያደረጉ መሆን አለባቸው፡፡ በየክልሉ እነዚህን ሶስት ደረጃዎች ታሳቢ ያደረገ የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞችን ያሉቡት ደረጃ የሚዳስስ ጥናት በማካሄድ ከዚህ በፊት በተቀመጠውና ከላይም በድጋሚ በተዘረዘረው መሠረት ለየደረጃዎቹ ተስማሚ የሆነ የድጋፍ መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ መረባረብ ተገቢ ነው፡፡

አምስተኛውና ዋነኛ ሥራ የአነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞችን ለማስፋፋት መዋቅራችን የትኛውም ዓይነት ድጋፍ ቢያደርግላቸው ተቋማቶቹ ራሳቸው ተደራጅተውና ሕብረተሰቡ በየአካባቢው ተደራጅቶ በሥራ ዕድል ፈጠራውና ውጤታማነት ላይ ካልተሳተፉበት ዘርፉን ለማጠናከር የሚደረገው እንቅስቃሴ መሠረታዊ ለውጥ የሚያመጣ አይሆንም፡፡ በመሆኑም በከተሞች በሚኖሩ የሰፈር እና የቀጠና አደረጃጀቶች ዜጎች ለስራ ዕድል ፈጠራው አጀንዳ አድርገው እየተወያዩ ስራ አጥ ነዋሪዎች ወደ ስራ የሚሰማሩበት ሁኔታ መፍጠር አለባቸው፡፡ ኢንተርፕራይዞቹም በአምራች የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እና በንግድና የዘርፍ ምክር ቤት ወይም በራሳቸው የአነስተኛና ጥቃቅን ጠቃሚ የሆነ ለዘወትር መሻሻል ገንቢ ሚና የሚጫወት ተልዕኮ የሚወስድ አደረጃጀት በመፍጠር መንቀሳቀስ አለባቸው፡፡ ባለፈው ሁለት እና ሶስት ዓመታት በተጀመረው መልኩ የአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት በራሳቸው አሀድ ተደራጅተው እርስ በእርሳቸው እየተገማገሙ ለቀጣይ መሻሻል (Continuous improvement) መትጋት አለባቸው፡፡ በመዋቅራችን ውስጥ እየተከሰተ ያለው የኪራይ ሰብሳቢነት የአመለካከትና የተግባር ዝንባሌን መታገል የሚያስችላቸው ፖለቲካዊ መድረክና ከባቢያዊ ሁኔታ መፍጠር መቻል አለብን፡፡ ይህንን ሥራ በአግባቡ ከሰራነው ከፍተኛ ውጤት ማምጣት እንደሚቻል ከትግራይ እና ከአዲስ አበባ አስተዳደር ጉለሌ ክፍለ ከተማ ከሰራነው ስራ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በጥርብ ድንጋይ ብዙ የተማረ ሰው መሰማራት ጀምሯል፡፡ ቁጠባም በተሻለ ደረጃ ላይ ነው፡፡ ሥራን ሳያማርጡ መሰማራት ላይም መልካም ጅምር የምንለው እንቅስቃሴ የታየበት እና በአርዓያነት ሊጠቀስ የሚችል ተግባር እየሆነ ነው፡፡ እስከአሁን ከሚታወቁት የሥራ ዕድል ፈጠራ በተጨማሪ የከተሞች አረንጓዴ ልማት ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠር

የሚችል ነው። የሕዝብ መናፈሻ አካባቢዎች፣ የመንገድ አካፋዮች፣ የሃይማኖትና ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጡ የመንግስት መ/ቤቶች ግቢዎች፣ የጤና እና የትምህርት ቤት ግቢዎች በአረንጓዴ እናልማቸው ካልን በጣም ብዙ የሥራ ዕድል ይፈጥራሉ። በየከተሞቹ ያሉ የተፋሰስ ጥበቃዎች ደግሞ የአትክልት ልማት ቤት (Green house) በመገንባት ለከተሞችም የምግብ ዋስትና ከማረጋገጥ አንጻር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው ስለሆነ በፍጥነት ልናስፋፋው የሚገባ ስራ ነው። በከተሞች የጋራ የከብት እርባታ ሼድ በመስራት የወተት አቅርቦት ማስፋፋትም ይቻላል። ትንንሽ የጫጩት መፈልፈያ ኢንኩቤተር በየቤቱ በማሰራጨትም ቀላል የማይባል የሥራ ዕድልና ለምግብ ዋስትና አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ የሚችሉ ሥራዎች መስራት ይቻላል። እነዚህና ተመሳሳይ ሥራዎች ለማቀጣጠል የሥራ አጥ ዜጎች የአስተሳሰብ ዝንባሌአቸውን የማስተካከል፣ የሕብረተሰቡ ተሳትፎ የማጠናከር እና ከየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚሄዱ ዝርዝር የሥራ ዕድል ፈጠራ ዕቅድ አዘጋጅቶ መንቀሳቀስ ይጠይቃል። የተሟላ ጤንነት ኖሯቸው በየከተሞቹ ጐዳናዎች የሚለምኑና የሚተኙ ዜጎች ሊፈቀድላቸው አይገባም። በዚህ ዓይነት ተሰማርተው ሲገኙ ማረፍያ ተዘጋጅቶላቸው አስተሳሰባቸውን የሚያስተካክል ስልጠና ተሰጥቷቸው ወደተፈጠሩት ሥራዎች የሚሰማሩበት ሥርዓት በየከተሞቹ መዘርጋት አለበት። በተጀማመሩ ሥራዎች አመርቂ ውጤት ተገኝቷል። ይህ የሕግ ማዕቀፍም ተዘጋጅቶለት ሥርዓት ማስያዝ አለብን። ከሕብረተሰቡም ጋር ውይይት ተደርጎ መግባባት ላይ መድረስ ያስፈልጋል። የጐዳና ሕይወት ቀደም ሲል እንደተቀመጠው አማራጭ መሆን የለበትም።

በአምስተኛ ደረጃ በአነስተኛ እና በጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ማስፋፋት ዘርፍ እንድናስፈጽም የተቀመጠው ሥራ በዘርፉ ከተሰማሩ ኦፕሬተሮች በካይዘን አሰራር የበቁ፣ በተጨባጭ በሚያመርቱት ምርትና አገልግሎት በዋጋና በጥራት የተወዳዳሪነት አቅም ያዳበሩና ለዘወትር መሻሻል የሚተጉ ኦፕሬተሮች ተሞክሮዎች የመቀመር ጉዳይ ነው። ማነቆዎቹን በኦፕሬተሮችም ይሁን በደጋፊ ተቋማት የተፈቱበት ልምድ መቀመርና ማስፋት ያስፈልጋል። በዶክመንተሪ ፊልም ጭምር የታገዘ ተደርጎ መቀመር አለበት። በአካል ጉብኝት የሚደረግበት ሥርዓትም ተፈጥሮ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልገናል። በዚህ ዓመት የትግራይ ልምድ ተቀምሯል። የአዲስ አበባ ደግሞ የተሻለ የአፈጻጸም ተሞክሮ ለመፍጠር ጥረት እየተደረገ ሲሆን ከተሳካ ይቀመራል። በየክልሎቹም ተመሳሳይ ጥረት መደረግ ይኖርበታል።

### 3.3. የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ሥራዎች

የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ሥራችን ከተሞች የመሬት ሀብታቸውን ልማታችንን በሚያፋጥን እና አሰራሩም ግልጽነት፣ ተጠያቂነት፣ ፍትሃዊነት እና ዘመናዊነት በተላበሰ መንገድ የመጠቀም ዓላማ በመያዝ የሚከናወን መሆኑ ይታወቃል። ይህ ስራ በዋነኛነት የሚከናወነው በክልሎችና በከተሞች በመሆኑ በዚህ ስራ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድርሻ ሀገር አቀፍ ዕቅዶችን፣ ስትራቴጂዎች እና የሕግ

ማዕቀፎች እንዲዘጋጁና በሚመለከታቸው አካል እንዲፀድቁ ማድረግ እንዲሁም በትክክል መተግበራቸውን መከታተልና ማረጋገጥ በቀጣይነት የሚሰራ ሥራ ይሆናል፡፡

በዚሁ መሠረት የመጀመሪያው ስራ የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ሥርዓቱን ለማስተካከል መሠረታዊ የሆነውን የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ፖሊሲ እና የሊዝ አዋጅ ለማስፈጸም እንዲያግዙ የተቀረጹ የሕግ ማዕቀፎች እንዲተገበሩ ለክልሎችና ለከተሞች ድጋፍ ይሰጣል፡፡ እየተዘጋጁ ያሉ የመሬት አጠቃቀም ፕላን ስትራቴጂ፣ የመሬት አጠቃቀም ፕላን አዋጅ ማሻሻያ፣ የመሬትና መሬት ነክ ቋሚ ንብረት ምዝገባ አዋጅ እና ተያያዥ የሕግ ማዕቀፎች በሚመለከተው አካል ተሳትፎና ይሁንታ ሲያገኙ በአተገባበራቸው ላይ ተገቢው ክትትል ይደረጋል፡፡ ከተሞቻችን ዘመናዊና ለኑሮ የተመቹ እና ለአካባቢ ጥበቃ ትኩረት የሰጡ ይሆኑ ዘንድ የከተማ መሬት መዋቅራዊ ፕላንና የአካባቢ ልማት ፕላን እንዲሁም የአካባቢ ልማት ዲዛይን ሥራዎች በከፍተኛ አመራሩ ጭምር ትኩረት ተሰጥቷቸው ልማታችን በዚሁ መሠረት ይፈጸም ዘንድ ተገቢው ግንዛቤ ለመፍጠር ጥረት ይደረጋል፡፡

የከተማ መሬት ዝግጅትና መልሶ ማልማት ሥራችን ሌላው ትኩረት ተሰጥቶት መሰራት ያለበት ሥራ ነው፡፡ የከተማ መሬትና ከተማ ማደስ ሥራዎች ግልጽ፣ ተጠያቂነት የሰፈነበት፣ ፍትሃዊና ወጪ ቆጣቢ በሆነ አግባብ እንዲከናወን ይደረጋል፡፡ የከተሞች አስተዳደር ወሰን በመከለል እና በካርታ በማመላከት፣ ተገቢው የመሬት ሃብት ኢንቨንተሪና ምዝገባ እንዲኖር እንዲሁም መሬቱም በመሬት መረጃ ባንክ የሚመዘገብበት ሥርዓት ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ በወረቀት ላይ የሚገኙ የወረቀት መረጃዎችን ዲጂታላይዝ በማድረግ፣ የመረጃ ጥራትና ደህንነት በተጠበቀ ሁኔታ በመሬትና በመሬት ነክ ተቋማት መካከል የመረጃ ቅብብሎሽ እና አጠቃቀም ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ የተጀመረው የኢንዱስትሪ ዞን ልማት ሥራ በዓመቱ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ስራ ይሆናል፡፡ የመልሶ ማልማት ስራ ሲከናወን የአካባቢው ነዋሪ በቀጣይነት ወደ ሌላ ቦታ ሳይፈናቀል በቅርብ አካባቢ የሚስተናገድበት ስትራቴጂ ተነድፎ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

በመሬት ልማትና ማኔጅመንት ሶስተኛው ሥራችን በወጡ ሕጎች መሠረት የመሬት ግብይት፣ አሰጣጥና አስተዳደር ሥርዓቱ ቀልጣፋና ውጤታማ የማድረግ ሥራ ነው፡፡ የመሬት ግብይት ሥርዓቱ ግልጽነት ያለው፣ ተጠያቂነት የሰፈነበትና ልማታዊ በሆነ መንገድ የሚሰራ እንዲሆን ሥርዓቱ ይጠናከራል፡፡ ለተለያዩ አገልግሎቶች የመሬት አቅርቦቱ በተለይ የዋጋ መረጋጋት በሚፈጥር ልክ እንዲቀርብ እና ስብጥሩም የተጠበቀ እንዲሆን ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፡፡ መሬት የተረከበውም አካል በፍጥነት ወደ ልማት እንዲገባም ይደረጋል፡፡ የከተማ መሬት አስተዳደር ዋነኛው የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብና ተግባር መገለጫ በመሆኑ የትግል መድረኮች አደረጃጀትና ሥርዓት የበለጠ እየጠራ እንዲሄድ ይደረጋል፡፡ ከመደበኛው የመንግስት መዋቅር በታች የቀጠና፣ የሰፈር እና የብሎክ አደረጃጀት በከተሞች

በጥናትና መዋቅራዊ ፕላኑ ተደግፎ ይዘረጋል፡፡ በዚህ መዋቅር አማካይነት የነዋሪው፣ የሴቶች፣ የወጣቶች፣ የሕፃናት፣ የባለሀብቶች፣ የሃይማኖት ተቋማትና ሌሎችም ኢንዲደራጁና መሬት የመንግስትና የሕዝብ የጋራ ሀብት መሆኑን በማስገንዘብ በጋራ እንዲጠብቁት ይደረጋል፡፡ የመሬት እና የመሬት ነክ ንብረት ምዝገባም ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዲኖራቸው የሕግ ማዕቀፍ ይዘጋጅና ይተገበራል፡፡

በመሬት ልማትና ማኔጅመንት አራተኛው ሥራ ደግሞ በከተሞች ካርታ ሳይሰጣቸው ሕጋዊ መሠረት ኖሯቸው የተያዙ ይዞታዎች ጉዳይና የሕገ-ወጥ ይዞታዎች ጉዳይ በፍጥነት እልባት እንዲያገኝ አቅጣጫ መቀመጡ ይታወቃል፡፡ ይህ ሥራ በ4 ዓመት ጊዜ ውስጥ መጠናቀቅ እንዳለበትም በአዋጅ ተደንግጓል፡፡ አንድ ዓመት አልፏል፡፡ 2005 የአካባቢ ምርጫ አለ፡፡ 2007 የሀገር አቀፍ ምርጫ አለ፡፡ በመሆኑም ያለን ጊዜ በዚህ ዓመት የሚሞከረውን ሞክሮ በ2006 ይህ ጉዳይ ካላጠናቀቅን ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ መሆኑ አይቀርም፡፡ በዚህ ረገድ የተሳካ ሥራ የሰሩ ክልሎች እንዳሉም ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባ ነው፡፡ ይህ ሥራ በአግባቡ ከተሰራ በመዋቅራዊ ፕላን ዝግጅትና ለከተሞች የመሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ እንደቅድመ ሁኔታ ስለሚቀመጥ ትልቅ አጋዥ ሥራ ይሆናል፡፡

አምስተኛ እና ለፖለቲካል ኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን መሰረት የሚጥለው ስራ የመሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ ሥራችን ነው፡፡ በዚህ ረገድ ግዙፍ የሚባሉ ሁለት ሥራዎች አሉ፡፡ አንዱ የዲጂታል ካርታ ሥራ ነው፡፡ በ23 ከተሞች ማንሳት የተጀመረው የአየር ካርታ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ እያንዳንዱ ይዞታ በቁራሽ መሬት መለየት (parcel identification)፣ በጎዳና የመለየት (Street Addresing)፣ በብሎክ የመለየት (Block identification) ተግባር ትልቅ ስራ ይሆናል፡፡ ይህንን አጠናክረን እንቀጥላለን፡፡ ሁለተኛው ሥራ የይዞታ ማረጋገጥ ሥራ ነው፡፡ በየከተሞቹ በመደዳ እያጠሩ በመሄድ ሥርዓት (systemic method) እያንዳንዱ ባለይዞታ ምን ያህል መሬት ይዟል፣ አገልግሎቱ ምንድነው፣ በምን ዓይነት ሕጋዊ አግባብ ይዞታል፣ ይዞታው አሁን ሕጋዊ ተደርጎ መመዝገብ አለበት ወይ (ሕገ-ወጥ ይዞታ ከሆነ)፣ ይህ ይዞታ በካርታ ላይ የት ነው የሚገኘው፣ በዚህ ይዞታ ላይ ባለመብቶቹ እነማን ናቸው፣ የይዞታው የመጠቀም መብቱ እስከምን ድረስ ነው የሚሉ ጥያቄዎች እየተነሱ ትክክለኛ ውሳኔ የሕዝቡ ተሳትፎ ታክሎበት የሚሰጥበትና ትክክለኛ መረጃ የመመዝገብ ስራ ነው፡፡ ይህ ስራ ፖለቲካዊ ውሳኔ የሚፈልግም ስራ በመሆኑ በአመራሩ በቅርብ ክትትል መፈጸም ያለበት ስራ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይህም አሁን በጀመርነው ፍጥነትና አካሄድ መሄድ ስለማይቻል ሥራችንን በዝርዝር ገምግመን ዕቅዳችንን በመከለስ በፍጥነት የምንምዘገዝግበት ስትራቴጂ ነድፈን መንቀሳቀስ ይጠበቅብናል፡፡ ከእነዚህ ሁለት ሥራዎች ጋር የሚያያዙ ፈርጀ ብዙ ተግባራት በዝርዝር ዕቅዱ ውስጥ የተካተቱ በመሆኑ እዚህ ለማንሳት አልተሞከረም፡፡

የመጨረሻ ግን ቁልፍ ስራ በመሬት ልማትና ማኔጅመንት ስራችን የሰው ኃይል ዝግጅታችን ነው፡፡ አሁን እየተደራጁ ባሉ መዋቅሮች የዘርፉ እውቀትና ክህሎት ያለው ሰው ወሳኝ ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ስራውን መስራት ሲያቅተው በንትርክ ብዙ ዓመታት ያስቆጥራል፡፡ እውቀትና ክህሎቱ ብቻም የትም አያደርስም ስራው በፍጥነት እንዲሄድ ተነሳሽነት ያለው ሰው ያስፈልገናል፡፡ በተለይ በመጀመሪያዎቹ ሥራዎች በሕግ ብቻ ሊገደቡ የማይቻሉ በየመድረኩ የሚወሰኑ በጣም ብዙ ጉዳዮች ስለሚኖሩ የውግንና ጥያቄም ጎልቶ ይመጣል፡፡ በመሆኑም የሰው ኃይል ዝግጅት ቁልፍ ተደርጎ መወሰድ እና መመራት አለበት ማለት ነው፡፡

### 3.4. የመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመንግስት ሕንፃዎች ግንባታ ሥራዎች

በሀገራችን የመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመንግስት ሕንፃዎች ግንባታ ሥራዎችን ሰፊ የሥራ ዕድል ለመፍጠር፣ የመኖሪያ ቤት እጥረት ለማቃለል፣ ዜጎች በተለይ ሴቶችና አነስተኛ ገቢ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ቋሚ ንብረት በማፍራት የፍትሃዊ የሀገር ሀብት ልማታዊ በሆነ መንገድ ተጋሪ እንዲሆኑ ለማድረግ፣ የከተሞቻችን የተጎዱ አካባቢዎች መልሶ ለማደስና ለማሻሻል እንዲሁም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን አቅም በአሰራር፣ በቴክኖሎጂና በክህሎት ለማሻሻልና ለማጠናከር ታሳቢ በማድረግ የተቀረጸ ፕሮግራም ነው፡፡

በዚህ ስራ ቁልፍ ችግራችን ከፍጥነት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የዓመቱ ርብርብ በዘርፉ የለውጥና የልማት ሰራዊት ከካይዘን ጋር አያይዞ የመተግበር ሥራ ነው፡፡ አሁን ያለውን በየፕሮጀክቶች ከ2 እስከ 3 ከመቶ ያልበለጠ አፈጻጸም ከ10 በመቶ ያላነሰ አፈጻጸም እንዲኖረው እንረባረባለን፡፡ በስራው የሚሰማሩ የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች፣ ኮንትራክተሮች፣ አማካሪዎች፣ ፈጻሚ መዋቅራችን እና የግብዓት አቅራቢዎች የተቀናጀ ተልዕኮ ወስደው የሚንቀሳቀሱበትና አፈጻጸሙ በተከታታይ እየተገመገመ ለባለሚናዎች ደረጃ የሚሰጥበት ሥርዓት ይፈጠራል፡፡ ይህ በአዲስ አበባ ላይ የተሻለ ስራ ከሰሩ ተቋማት ልምድ ተወስዶ (ሱር) በተወሰኑ ፕሮጀክቶች ላይ እየተሞከረ ስለሆነ ውጤቱም ተቀምሮ እንዲሰፋ ይደረጋል፡፡

ሁለተኛው ስራ የተጀመሩ የቤቶች ግንባታ የማጠናቀቅ ስራ ነው፡፡ አዲስ አበባ ላይ በአሁኑ ጊዜ ከ100 ሺህ በላይ ቤቶች በግንባታ ሂደት ላይ ናቸው፡፡ እነዚህን ከምርጫ በፊት ማጠናቀቅ ትኩረት ይሰጠዋል፡፡ በክልሎችም ያልተጠናቀቁ ቤቶች ጉዳይ እልባት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ የማዳበሪያና የስኳር ቤቶች ግንባታ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ የዩኒቨርስቲ ግንባታዎችም በተመሳሳይ ተጠናክረው ይቀጥላሉ፡፡ የ40 ከመቶ ቁጠባና የ60 ከመቶ በአዲስ አበባ 10,000 ቤቶች በዚህ ዓመት ግንባታው ይጀመራል፡፡ የክልሎች በሚቀርበው ጥናት መሠረት ወደፊት የሚወሰን ይሆናል፡፡ አነስተኛ ገቢ ላለው ህብረተሰብ አዲስ አበባ ላይ 35,000 ቤቶች ይገነባሉ፡፡ የክልል ከተሞች ዝርዝር ጥናት ተካሄዶ የሚወሰን ይሆናል፡፡

በሪል እስቴት የሚገነቡ ቤቶች መሬት በጨረታ እየቀረበላቸው ተወዳድረው የሚወስዱበት ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ ከዜጎች ጋር የገቡት ውልም ሕጋዊ ድጋፍና አስገዳጅነት እንዲኖረው የሚያደርግ የሕግ ማዕቀፍም ይዘጋጃል፡፡ ለግል ቤት ሰራዎች መሬት በሊዝ ማቅረቡ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

በዚህ ዘርፍ ሶስተኛው ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ቀልጣፋ የሎጅስቲክስ ሥርዓት የመዘርጋት እና የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን በማቅረብ የሕንፃ ግንባታ አፈጻጸማችን ውጤታማና ቀልጣፋ የማድረግ ስራ ነው፡፡ ከውጭ የሚገቡ የብረት፣ ማግኒዝየም ክሎራይድ፣ የሴራሚክስ፣ የኤሌክትሪክ እና የፒቪሲ ግብዓቶች በቅድሚያ በመተንበይ በቂ ክምችት እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል፡ በአካባቢ የሚመረቱ አሸዋ፣ ጠጠር፣ ድንጋይ፣ ማግኒዢየም ኦክሳይድ... ወዘተ በቂ ክምችት የሚያዝበት ሥርዓት መፍጠር መቻል አለብን፡፡ ለኮንትራክተሮች፣ ለአማካሪዎች እና ለአነስተኛና ጥቃቅን የሚያስፈልጉ ማሽነሪዎች በብድር ሊዝ ሥርዓቱ እንዲተገበር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በማስፈጸም አቅም በኩል ያለው የተነሳሽነት፣ የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብና ተግባር ዝንባሌ እንዲሁም የባለቤትነት መጓደል ችግሮች በቁልፍ ተግባሩ ላይ እንዳስቀመጥነው የሚፈታበት ሥርዓት አያይዘን ማየት ይኖርብናል፡፡ የክህሎት ስልጠናም ለሁሉም ባለሚናዎች ዝርዝር ኦፐሬሽናል ፕላንና የተሻሻለ ሰነድ አዘጋጅተን ቀደም ሲል የነበረው አሰራር አጠናክረን መቀጠል አለብን፡፡ እየተዘጋጁ ያሉ ስትራቴጂዎችና የሕግ ማዕቀፎችም ፀድቀው ወደ ተግባር ይሸጋገራሉ፡፡

### 3.5. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ሬጉላቶሪ ሥራዎች

በሀገራችን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ተወዳዳሪ የሆኑ የሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች፣ የኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዞችና የትምህርት ተቋማት እንዲፈጠሩ በዘርፉ የሚገኙትን ተዋንያን አቅም የመገንባት፣ ደረጃቸውን የማሳደግና ምቹ የአሰራር ሥርዓት የመገንባት ተልዕኮ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ተሰጥቶታል፡፡ የግንባታ አቅም ለማጎልበት የሚያግዙ የተሻሻሉና ወጪ ቆጣቢ የሆኑ ግብዓቶችንና ቴክኖሎጂዎችን ለመለየት ምርምር የሚያደርጉትን የማበረታት፣ ለምርምር ውጤቶቹ ደረጃ የማሰጠት፣ የማስፋፋትና የግንባታ መሳሪያዎችን ምዝገባ መስፈርት በማሻሻልና በመመዝገብ የመሳሪያዎች አቅርቦት አማራጮች /የማሽነሪ ሊዝንም ጨምሮ/ የማሻሻል ስራዎች መስራት አንዱ ስራ ይሆናል፡፡

ሁለተኛው ስራ የኮንስትራክሽን ሴክተር የሰው ኃይል የማልማት ስራው አፈጻጸም ባለቤት ሆኖ የመከታተል ጉዳይ ነው፡፡ በዩኒቨርስቲዎች በዘርፉ የሚሰጡ ትምህርቶች ጥራት፣ የተመራቂዎች የመረጃ ቅብብሎሽ፣ የሰልጣኝ ብዛትና ስምሪቱ፣ በዲግሪ ደረጃ በዘርፉ የሚመረቁ ምሩቃን የምዝና ሥርዓት መዘርጋትና መጀመር ትኩረት የሚሰጠው ስራ ይሆናል፡፡ በቴክኒክና ሙያ ደረጃም የተዘጋጁትን የሙያ ደረጃዎች የምዝና ሥርዓቱ የማስፋትና የማቀላጠፍ እንዲሁም የኩባንያዎች የትብብር ስልጠና እና ምዘና

አጠናክሮ ማስቀጠል ያስፈልጋል፡፡ አዳዲስ ምሩቃንም እያደራጁ አሰልጥኖ ማሰማራትም ትኩረት ይሰጠዋል፡፡

በሕንፃ አዋጁ መሠረት በየከተሞቹ የሚካሄዱ የሕንፃ ግንባታዎች በተፈቀደላቸው ዲዛይንና የጥራት ደረጃ እንዲገነቡ መከታተልና መደገፍ እንዲሁም ሕንፃዎቹ ተገንብተው ሲጠናቀቁ አስተማማኝ አገልግሎት እንደሚሰጡ ማረጋገጥ ሶስተኛው ስራ ይሆናል፡፡ በወጡት የሕንፃ የሕግ ማዕቀፎች አማካይነት እነዚህ ጉዳዮች የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ይደረግባቸዋል፡፡ ይህ ብቃት፣ ተነሳሽነትና መልካም ሥነ-ምግባር የሚፈልግ ስራ ለመሆኑ በሰው ኃይል ምደባው ላይ የአመራሩ የቅርብ ክትትል የሚፈልግ ስራ ነው፡፡ በሀገራችን በስራ ላይ እየዋለ ያለው የሕንፃ ግንባታ ስታንዳርዶች ከ20 ዓመት በላይ ያስቆጠሩ ስለሆኑ ከፍተኛ ወጪ ተደርጎ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አማካይነት ወደ 13 ዓይነት የስታንዳርዶቹ ማሻሻያ በመጠናት ላይ ነው፡፡ ተገቢው ክትትል ተደርጎ ሲፀድቅ ለክልሎቹ የመላክና ሰፊ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ይሰራል፡፡

አራተኛው ስራ በኮንስትራክሽን ዘርፍ ያሉ ባለሚናዎች ተቋራጮች፣ አማካሪዎች፣ ባለሙያዎች፣ የማሽነሪ አከራዮች፣ የማሽነሪ አቅራቢዎች ምዝገባና ፍቃድ አደሳ ዘመናዊ የማድረግ ስራ ነው፡፡ ይህ ስራ የሌሎች ሀገሮች ልምድም በመውሰድ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ከሙስና ነፃ የሆነ አገልግሎት ለማድረግ ጥረት ይደረጋል፡፡ የመረጃ ሥርዓቱም ለተገልጋዮች ተደራሽ ለማድረግና እንዲሁም ከዩኒቨርስቲዎችና ክልሎች የሚናበብበት ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ በተዋናዮቹ የልማታዊ አስተሳሰብና ተግባር እንዲኖር የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ ካውንስልም እንዲቋቋም እናደርጋለን፡፡

አምስተኛው የዘርፉ ስራ በመንግስት የሚካሄዱ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ውጤታማነት መገምገም የመጀመር ስራ ነው፡፡ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ተቋም በመንግስት የሚካሄዱ ግንባታዎች የኮንትራት አስተዳደር ውጤታማነት እንዲያረጋግጥ ኃላፊነት የተሰጠው ቢሆንም የሚወጣው በጀትና የሚሰራው ስራ አዋጪነት የሚገመገምበት ሥርዓት አልዘረጋም፡፡ ከዚህ የበጀት ዓመት በመጀመር የመንግስት ፕሮጀክቶች የአፈጻጸም ውጤታማነት እየተገመገመ ለቦርዶችና ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣናት ግብረ-መልስ የሚሰጥበት ሥርዓት ይጀመራል፡፡

### 3.6. የከተሞች የተቀናጀ የመሠረተ ልማት አቅርቦት ሥራዎች

በሀገራችን እየተመዘገበ ያለው ፈጣን ልማትና ዕቅድ እያስፈጸምን ያለው ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረገው የፖለቲካል ኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን በከተሞች ሰፊ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ስራ ይጠይቃል፡፡ የሀገራችን ጠቅላላ ምርት አብዛኛው ምንጩ ወይም ዋነኛው ሞተር ኢንዱስትሪ ሲሆን አብዛኛዎቹ ማዕከላቱ ከተሞች እንደሚሆኑ ይጠበቃል፡፡

የአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋማት፣ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችና የንግድና የአገልግሎት ተቋማት ተወዳዳሪ ሆነው እንዲቀጥሉ የተሳለጠ የመሠረተ ልማት የማይተካ ሚና አለው። በመሆኑም በአቅርቦቱ ለሶስት ሥራዎች ትኩረት ተሰጥቶ መሰራት አለበት።

በመጀመሪያ ደረጃ በከተሞች የሚካሄዱ መሠረተ ልማቶች ሰፊ የስራ ዕድል እንዲፈጠሩ ተደርገው መቀረጽ አለባቸው። የውስጥ ለውስጥ መንገድ ግንባታ፣ የጐርፍ መፋሰሻ ቦዮች፣ የፍሳሽ ቆሻሻ መስመሮች፣ የውሃ አቅርቦት መስመሮች ግንባታና ዕድሳት፣ የደረቅ ቆሻሻ ማስተናገጃ ቦታዎች ልማት፣ የሕዝብ ሽንት ቤቶች፣ የመናፈሻ ቦታዎች ልማትና አያያዝ፣ የንግድና የአገልግሎት አቅርቦት ቦታዎች ዝግጅት፣ የክላስተር ቦታዎች ዝግጅት፣ የቄራ ልማት... ወዘተ ሥራዎች ከአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋማት ልማት ጋር ተያይዘው እንዲቀረጹ መደረግ አለበት። ከዚህ ጋር በተያያዘ ለእነዚህ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም መንግስት ከዓለም ባንክ ጋር ተዋውሎ በሥራ ላይ እየዋለ ያለው ገንዘብ ለከተሞች በጀት ተመድቦላቸው በአመራሩ ድክመት ምክንያት የልማት ዕድሉ እያመለጣቸው ነው። አንዳንዶቹ ከዕድሉ ሊሰረዙ ቋፍ ላይ ያሉም ከተሞች አሉ። ስለዚህ ይህ ስራ ከከተሞች ልማት ጋር ያለው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

ሁለተኛው ከመሠረተ ልማት ጋር አያይዘን ትኩረት መስጠት ያለብን መናበብ በመፍጠር ተደማሪ ልማት የማምጣት ስራ ነው። በከተሞች የሚካሄዱ ስራዎች በከፍተኛ ደረጃ መስተጋብር ይፈልጋሉ። ከተሞቻችን ስናለማ ሁለቱ አማራጮች ሚዛን ሰጥተን መምራት ይኖርብናል። አንዱ በከተማው መሀል መልሶ የማልማትና የማሻሻል ጉዳይ ነው። በዚህ ወቅት የመሠረተ ልማት አንስቶ መልሶ ማልማት ይጠይቃል። ይህ ደግሞ በተጨባጭ ከሚገመተው እጅግ የበዛ ጊዜ እየወሰደ በመሆኑና ልማቱን እያስተጓጐለ በመሆኑ ከመጀመሪያው የቅንጅት መድረክ በመፍጠር ዝርዝር ዕቅድ አዘጋጅቶ አፈጻጸሙን በጋራ እየገመገሙ መሄድ ይጠይቃል። ሁለተኛው በመስፋፍያ አካባቢ የሚካሄደውን ልማት ነው። ይህ ትልቅ የፖለቲካ ውሳኔ መሆኑን ተገንዝቦ በአግባቡ መምራት ያስፈልጋል። የመስፋፍያ ልማት እንዲካሄድበት በተወሰነበት ቦታ በአንድ ቀን ልዩነት የመሬትና የንብረት ዋጋ እንደ መሠረተ ልማቱ ዓይነት እስከ 100 እጥፍ የዋጋ ልዩነት ያመጣል። የመደበኛ እርሻ መሬት የነበረ ቦታ የባቡር መስመር ያልፍበታል፣ ዩኒቨርስቲ ይገነባበታል፣ ዋና መንገድ ያልፍበታል፣ የኢንዱስትሪ መንደር ይገነባበታል፣ 40 ሺህ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ይገነባበታል፣ የስኳር ፋብሪካ ይገነባበታል ተብሎ ሲወሰን በአንድ ቀን ልዩነት በዚያ አካባቢ ባለው ቋሚ ንብረት ላይ ከፍተኛ የንብረት ዋጋ ልዩነት ይፈጠራል። የመሬትና መሬት ነክ ቋሚ ንብረት ዋጋ ይጨምራል። በመሆኑም ይህ ስራ በተለይ የመሠረተ ልማቶቹ በተቀናጀ መንገድ እንዲፈጸምና ከልማቱ የሚመጣውም የዋጋ ልዩነት ለመንግስትና ለሕዝብ የጋራ ተጠቃሚነት እንዲውል አቅዶ መስራት ይጠይቃል። መሠረተ ልማቶቹ ከመምጣታቸው በፊት መሬቶቹ ባይተላለፉና

ከዚያ በኋላ እንዲተሳሰሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የተቀናጀና የተደራጀ የከተማ ማስፋፊያ ዕቅድ አዘጋጅቶ መምራት ያስፈልጋል፡፡

ሶስተኛው በከተሞች የሚካሄደው የመሠረተ ልማት ግንባታ የማቀናጀት ጉዳይ ነው፡፡ ውሃ፣ መብራት፣ ስልክ፣ የፈሳሽ መስመር፣ የጐርፍ መስመር፣ የመንገድ ግንባታ እና የመሬት ልማት ሥራዎች ተቀናጅተው መፈጸም አለባቸው፡፡ መንገድ የሁሉም ልማት መሪ ሆኖ ሌሎቹ ከመንገድ ጋር ተያይዘው የሚለሙበት ሥርዓት መዘርጋት አለብን፡፡ ይህንን ለማስፈጸም የተዘጋጀ እስትራቴጂና የሕግ ማዕቀፍ ስላለ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅ ተቀናጅተን ማስፈጸምና አፈጻጸሙንም መከታተል ያስፈልጋል፡፡

### 3.7. የከተሞች ያልተማከለ አስተዳደር፣ የሕዝብ ተሳትፎና የማስፈጸም አቅም ግንባታ ሥራዎች

ከተሞቻችን የልማትና የመልካም አስተዳደር ስራዎቻቸውን በራሳቸው ለማስፈጸም ሲፍጨረጨሩ ይስተዋላሉ፡፡ እነዚህ ሥራዎች በመዋቅራችን ብቻ ብናስፈጽማቸው የሕዝቡ ተሳትፎ ካልታከለበት ነዋሪው ባለቤት አይሆንም፡፡ የሕዝብ ባለቤትነት ካልታከለበት ደግሞ የልማትና የመልካም አስተዳደር ሥራዎች ምንም ያህል ብንረባረብ ማሳለጥ አይቻልም፡፡ መዋቅራችን ስለህዝብ ተሳትፎ አስፈላጊነት በአግባቡ ባለመጨበጡ ወይም የአስተሳሰቡና የተግባሩ አካል ባለማድረጉ በተጨባጭ ይሄ ነው የሚባል ስራ እየተሰራ አይደለም፡፡ በተወሰነ ደረጃ አዲስ አበባ የተሞካከረ ነገር ስላለ የዚህ ልምድና የሩዋንዳ ልምድ ተቀምሮ ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል፡፡ ሲፀድቅም ተቀናጅተን የምንተገብረው ይሆናል፡፡ ከመደበኛ የከተማ አስተዳደር መዋቅራችን በታች ለሕዝብ አደረጃጀት ልዩ ትኩረት መስጠት ይኖርብናል፡፡ ሕዝብ አደራጅተን ለማንቀሳቀስ የቀጠና (Sector)፣ የሰፈር (Village) እና የመንደር (Block) አደረጃጀት ፈጥረን ሕዝቡን በልማትና መልካም አስተዳደር ሥራዎች ላይ በፍጥነት ማንቀሳቀስ አለብን፡፡ በቀጠና ደረጃ የጽ/ቤት ኃላፊና ረዳት መመደብ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ ውጭ ያለውን ግን ሕዝቡ በነፃ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት ሥርዓት ብንፈጥር የሚል ዕቅድ እየተዘጋጀ ነው፡፡ ለሥራ ዕድል ፈጠራ፣ ለመሬት አስተዳደር፣ ቁጠባን መሰረት ያደረገ የቤት አቅርቦት፣ ለድሃ ተኮርና የጋራ መኖሪያ ቤቶች ፍትሃዊ አቅርቦት፣ የከተሞቹ ፅዳትና አረንጓዴ ልማት፣ ለመሠረተ ልማት… ወዘተ ሥራዎች ሕዝቡን በላቀ ደረጃ አደራጅተን ማንቀሳቀስ እንችላለን፡፡

በዚህ ዘርፍ ሁለተኛ ትኩረት መስጠት ያለብን ስራ ከማዘጋጃ ቤቶች አገልግሎት ጋር ያለው ችግር መፍታት ነው፡፡ የአገልግሎት አቅርቦት ችግር በመፈታት እረገድ መዋቅራችን ሽባ እየሆነ ነው፡፡ አቤቱታ ቀርቦለት መልስ የሚሰጥ (Responsive) መዋቅር መቶ በመቶ የለም ብለን መደምደም በሚቻልበት ደረጃ እየተደረሰ ነው፡፡ በመሆኑም ነባራዊ ሁኔታውን ፈትሾ ይህንን ማስተካከል የሚያስችል ዕቅድ አዘጋጅቶ ወደተግባር መግባት ይጠይቃል፡፡ የማዘጋጃ ቤቶች አገልግሎት በተለይ ከመሬት ጋር የተያያዘው አሳሳቢ ነው፡፡ በዝርዝር ፈትሾ ማስተካከል ይጠይቃል፡፡ መሠረታዊ ለውጥም በተለይ

ከአስተሳሰብ /አገልጋይነት ጋር አያይዞ ለየት ባለ መንገድ መስራት ይጠበቅብናል፡፡ በፌደራል ደረጃም ስታንዳርዶች እየተዘጋጁ ለከተሞቹ የሚወርዱበት ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ ስልጠናም ይሰጣል፡፡

ሶስተኛው በዚህ ዘርፍ መሰራት ያለበት ስራ የሰው ኃይል ልማትና ስምሪት ስራ ነው፡፡ ለከተማ ስራችን ተብለው ከሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ የሚሰለጥኑ አመራሮችና ባለሙያዎች ስምሪት ችግር ያለበት ነው፡፡ በየክልሉ ተመርቀው የወጡ ሰልጣኞች ዝርዝር ለይቶ ስምሪታቸውን እንደገና ማጣጣም ይጠይቃል፡፡ ለማዘጋጀ ቤት አገልግሎት የሙያ ደረጃ ወጥቶላቸው ወደ ተግባር ለመግባት ቅድመ ዝግጅት የተጠናቀቀላቸው የሙያ ዓይነቶችና ደረጃዎች በፍጥነት ወደ ምዘና መግባትና ስልጠና ያልተጀመረባቸውን ስልጠና ማስጀመር ያስፈልጋል፡፡ በተለይ ከመሬት ጋር የተያያዘው ዩኒቨርስቲዎች አዳዲስ የትምህርት ዓይነት መጀመር ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም ለአፈጻጸሙ የአመራሩ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ያስፈልጋል፡፡

## 3.8. የከተሞች የፅዳትና የአረንጓዴ ልማት ሥራዎች

የከተሞቻችን የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና የአረንጓዴ ልማት ሥራ በአመራር ደረጃ ወይይት ተካሂዶበት አያውቅም፡፡ በየደረጃው ያለው አመራር በዚህ ጉዳይ ላይ አጀንዳ አድርጎ የሚወያይበት መድረክ የለም፡፡ በዘርፉ የሚመደቡ አመራሮችም እንደማቆያ ቦታ እንጂ የከተሞች ደረጃ መገለጫ የሆነውን የከተሞች ገፅታ ግንባታ ለመቀየር ተልዕኮ የሚሰጣቸው አመራሮች የሚመደቡበት ሥራ አይደለም፡፡ በመሆኑም ከአመራሩ ጀምሮ በከተሞች ፅዳትና አረንጓዴ ልማት ላይ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ሥራዎች ጋር አጣጥሞ ድርብ ስኬት ማስመዝገብ የሚቻልበት ዘዴ በመቀየስ መምራት ይጠበቅበታል፡፡

ከዚህ አንፃር የመጀመሪያ ሥራ መሆን ያለበት ከፅዳት ጋር ያለው የአስተሳሰብና የተግባር ዝንባሌ ለመቀየር ሰፊ ሥራ መስራት ነው፡፡ በከተማ ያለው ዜጋ የግሉና የአካባቢው ንፅህና ቢጠብቅ ለቤተሰቡ ለህክምና የሚያወጣው ወጪ በምን ያህል እንደሚቀንስ ማስገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ጤንነቱ የተሟላ ቤተሰብ የተሻለ ኑሮ እንደሚኖርም ማስገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

እያንዳንዱ ቤተሰብና ዜጋ ቆሻሻ ከተጠየፈና በሥርዓቱ ከያዘ ከተሞቻችን እንዴት ሊፀዱ እንደሚችሉ ማሳየት ተገቢ ነው፡፡ ይህ ሥራ በት/ቤት፣ በኃይማኖት ተቋማት፣ በገበያ፣ በብዙሃን መገናኛ፣ በስብሰባና በተለያዩ መድረኮች የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም የግንዛቤ መፍጠሪያ ሥራው መሠራት አለበት፡፡ ንፅህና ስልጣኔ መሆኑን ማስገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የደረቅ ቆሻሻ በመሰብሰብ፣ ወደ ቀልዝ በመቀየር፣ መልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉ ውዳቂዎች በመሰብሰብ፣ በማጓጓዝ ሥራ ላይ ሰፊ የሥራ ዕድል እንዲፈጠርበት አድርገንም ተግባራዊ ማድረግ ይኖርብናል፡፡ እንቅስቃሴው ዘላቂ እንዲሆን ለደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አስፈላጊ የሆኑ የመሬት ዝግጅት፣ የገንዳ ግዢ፣ የማጓጓዣ ቀላል መኪናዎች (ባለሞተርና ባለሶስት እግር)፣ የደህንነት መጠበቂያዎች ማሟላትም ላይ ትኩረት ተሰጥቶ መሠራት አለበት፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ከደረቅ ቆሻሻ የላቀ ዝግጅትና ሙያ የሚጠይቀው የከተሞች የአረንጓዴ ልማት ሥራ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በአረንጓዴነት የሚለሙት አካባቢዎች መጀመሪያ መለየት፣ በአገልግሎታቸው ዓይነት ተስማሚ ዲዛይን የማዘጋጀትና ለልማቱ ተገቢው የቅድመ ዝግጅት ሥራዎቹ መሠራት አለባቸው፡፡ ለአካባቢው የሚስማማ የሚተከለው ተክል ዓይነት በጥናት መወሰንና ችግኙን አፈላልጎ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡ ችግኙ ከተተከለ በኋላ ዘላቂ እንክብካቤ የሚያደርግ ሰው መመደብ፣ ኮንትራት መግባትና አሰልጥኖ ማሰማራት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ሥራ በህዝብ መናፈሻ አካባቢዎች፣ በመንገድ አካፋይ፣ በትምህርት ቤት፣ በጤና ተቋም ግቢ፣ በኃይማኖት ተቋማት ግቢ፣ በመንግስት መ/ቤቶች ግቢ፣ በግለሰብ መኖሪያ ቤት ግቢ የአረንጓዴ ልማት ማካሄድ ይቻላል፡፡ በዚው ልክ ሰፊ የማነሳሳት ሥራ ከሠራንበት ከመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች የላቀ የሥራ ዕድል መፍጠር ይችላል፡፡ በሌላ በኩል በወንዝ ዳርቻዎች፣ በኃይማኖትና በት/ቤት ግቢዎች፣ በቀብር ቦታዎች፣ በተዳፋት ቦታዎች በግሪን ሃውስ አትክልት ማልማት ቢጀመር በዓመት 3 እና 4 ጊዜ በማምረት የምግብ ዋስትና በማረጋገጥ በኩል የሚኖረውም ፋይዳ ቀላል አይደለም፡፡ በዚህ ረገድም ቋሚ ገቢ የሚገኝበት የሥራ ዕድል መፍጠርም ይቻላል፡፡ ከተሞቻችንም በእርግጥም ውብና የተስተካከለ ገጽታም ይኖራቸዋል፡፡

በሦስተኛ ደረጃ የፅዳትና የአረንጓዴ ልማት ሥራ የተሳካ ለማድረግ የአስተሳሰብ ማስተካከል ስራ ብቻ ውጤታማ ሊያደርገው አይችልም፡፡ ሕዝቡ ከመንግስት መደበኛ አደረጃጀት በታች እራሱን አደራጅቶ መንቀሳቀስ የሚያስችለው አሠራር መዘርጋት አለበት፡፡ ይህንኑ የሚያጠናክር የህግ ማዕቀፍ አዘጋጅቶ ማስፈጸምም ያስፈልጋል፡፡ እነዚህን ሥራዎች ለማስፈጸም የሚያግዙ የከተሞች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ስትራቴጂና የከተሞች የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ ረቂቅ ተዘጋጅተው ለክልሎች ተልኳል፡፡ ሲፀድቁ በቂ ስልጠና ተሰጥቶባቸው ይተገበራሉ፡፡

### 3.9. የጥናትና ምርምር ሥራዎች

በከተሞች የምሰራቸው የልማትና የመልካም አስተዳደር ሥራዎች መነሻቸውና መድረሻቸውን ተገንዝበን መምራት የሚያስችሉን ጥናቶች በመካሄድ ላይ ናቸው፡፡ በከተሞች የሚሰጡ አገልግሎቶች የመሠረታዊ መረጃዎች መነሻ (Base-line survey) እየተዘጋጀ ሲሆን በመቀጠል መድረሻ (Bench mark) ግቦች በማስቀመጥ የከተሞች የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዳይዝ የሚያደርግ ሥርዓት ይቀየሳል፡፡ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለኢኮኖሚው የሚያበረክተው አስተዋፅኦና የሚገላበጠው ሀብት መጠን ከማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለስልጣን ጋር በመሆን ለመጀመሪያ ጊዜ ጥናት እየተካሄደ ነው፡፡ በተከታታይም በየዓመቱ በቀጣይነት እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የተሰማሩበት የሥራ ዓይነት፣ የሚፈጥሩት ሀብት መጠን እና ለኢኮኖሚው የሚያበረክቱት አስተዋፅኦም በመጠናት ላይ ሲሆን እንደ መነሻ መረጃው ከተቀመጠ በኋላ በተከታታይ የሚጠናበት እና ዝንባሌው

የሚገመገምበት ሥርዓትም ይዘረጋል፡፡ መረጃዎቹ ከክልሎች ከሚመለከታቸው ሴክተሮች ጋር ተያይዞ የሚሰራበት ሥርዓትም በቀጣይ የሚታይ ይሆናል፡፡

የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ በስፋት ለመጠቀም የሚያስችሉ መሠረተ ልማቶችም በመዘጋጀት ላይ ናቸው፡፡ በተለይ የመሬትና መሬት ነክ መረጃ፣ የቤቶች ኢንቨንተሪ መረጃ፣ የሥራ ዕድል ፈጠራ መረጃ፣ የኮንስትራክሽን ምዝገባና የግንባታ ፍቃድ መረጃ፣ የዕቅድ አፈጻጸም ክትትል (BSC) መረጃ በቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን የፊዚካልና የኔትወርክ እንዲሁም የሶፍትዌር ዝግጅቶች በመካሄድ ላይ ናቸው፡፡

በመንግስት ቤቶች አስተዳደር በኩል ያለው መዝረክረክ ለማስተካል ያሉትን ችግሮች በጥናት ለመለየት ግብረ- ኃይል ተደራጅቶ እየሠራ ነው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ከአዲስ አበባ ከተማ ጋር በቅንጅት በመሆን የንብረት ባለቤትነት ይዞታውም እየተወሰደ ነው፡፡ በቀጣይ በኦዲተሮች ለመመርመር የማይቻል የተባለውን ሀብትና ንብረት አስተዳደሩ የንብረትና ቤት ምዝገባው በሥርዓት ተካሄዶ የሚስተካከልበት ሥርዓት ለመፍጠር እየታሰበ ነው፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ሳይሟሉ የለውጥ መሣሪያዎች ለመተግበር መጣጣር ምንም ውጤት አያመጣም የሚል እሳቤ እየተወሰደ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት በኤጀንሲው የተያዙ መሬቶችና ቤቶች በአግባቡ ተመዝግበውና ተተምነው የሚታወቁበት ሥርዓት ይፈጠራል፡፡ የንብረት አስተዳደሩን ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው አሰራር እንዲመራ ይደረጋል፡፡

### 3.10. የትምህርታዊና የልማታዊ ኮሙዩኒኬሽን ሥራዎች

በከተሞች ያሉ የኪራይ ሰብሳቢነት የአመለካከትና የተግባር ዝንባሌዎች ወደ ልማታዊ የአስተሳሰብ እና የተግባር ዝንባሌ ለመቀየር ከትግበራ ጐን ለጐን የልማታዊ ኮሙዩኒኬሽን ሰፊ ሥራ መሰራት ይጠይቃል፡፡ ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ ለሴክተሩ ተስማሚ የሆነ የትምህርታዊና ልማታዊ የኮሙዩኒኬሽን ስትራቴጂ ረቂቅ ተዘጋጅቶ ለትችት ለሚመለከታቸው ባለሚናዎች ተሠራጭቷል፡፡ ዳብሮ ሲፀድቅ የመልካም አስተዳደርና የልማት እንቅስቃሴአችን እንዲሁም የህዝቡን የተደራጀ የልማት ተሳትፎ በማጀብ በኩል ሰፊ አስተዋፆ ይኖረዋል ተብሎ ታስቧል፡፡ በዚሁ ልክ ባለሚናዎቹን የሚያሳትፍ ዝርዝር ዕቅድ አዘጋጀተንና ስልጠና ሰጥተን የምንሠራው ሥራ ይሆናል፡፡ በከተሞች የህዳሴ ጉዞአችን ያመጣው ለውጥ በልማትና መልካም አስተዳደር የተደማሪ ዕድገት ወይም የመሻሻል ዝንባሌ (trend) ትንታኔ የታጀበ እናደርገዋለን፡፡

# ክፍል ሦስት

# የ2005 በጀት አመት ዕቅድ

## 1. በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ የለውጥና የልማት ሠራዊት ግንባታ ሥራዎች

**ጥቅል ዓላማ፡** በዘርፉ የተናበበ አደረጃጀት በመፍጠርና የዓለም አቀፍ ልምድ በመነሻ በማድረግ እያደገ የሚሄድ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት፣ የአመለካከት ለውጥ በማምጣት፣ የለውጥ ሠራዊት በመገንባትና የአገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻል የዘርፉን ተልዕኮ ማሳካት ነው፡፡ በምክንያታዊ ትንታኔ የሚያምንና ለልማቱ ቁርጠኛ አቋም ያለው ፈጻሚና አመራር በመፍጠር ተልዕኮዎቹን በጊዜ የለንም መንፈስ ለማስፈጸም በጋራ ተረባርቦ ዜጎችን ተጠቃሚ የማድረግ ውጤት ማስመዝገብ ነው፡፡

**ጥቅል ግብ፡** በዘርፉ የለውጥ መሣሪያዎቹ ተናበው እንዲተገበሩ በማድረግ፣ የተጠናከረ የክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስ ሥርዓት በመዘርጋት፣ የከተማ የልማት ሠራዊት በመገንባት እና የጥራት ሥራ አመራር ሥርዓትን በመዘርጋት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን በስኬት ጎዳና እየተጓዘ መሆኑን በማረጋገጥ ለዓመቱ የተጣሉ ግቦችን ማሳካት ነው፡፡

### 1.1. የወሳኝ አቅም፣ የለውጥ ባለሙያና አመራር ግንባታ ሥራ (የአመራሩና የፈጻሚው የምክንያታዊ ትንተና /Rational Thinking/ አቅም ግንባታ ሥራ)

**ዓላማ፡** አመራሩና ፈፃሚው አቋም ለሚወሰድባቸው የአስተሳሰብ ዝንባሌና የተግባር አፈጻጸሙ በተተነተነ ምክንየት መነሻነት እንዲሆን የሚያስችለውን አቅም በመፍጠር ለሀገሩ ግንባታና ለተለዕኮው የሚቆጥበው ጉልበትና አቅም እንዳይኖር ለማድረግ ነው፡፡

**ጥቅል ግብ፡** የአመራሩንና ፈፃሚውን የአስተሳሰብ ዝንባሌ በመቀየር ዓመታዊ አፈጻጸማችን እስከ አሁን ካስመዘገብናቸው ውጤቶች ተጨማሪ 50 ከመቶ ይመዘገባል፡፡

**ዝርዝር ግቦችና ተግባራት**

**ግብ አንድ፡** ልማታዊ አመለካከት እና የአመራርና የፈጻሚ የመፈጸም እና የማስፈጸም ክህሎት በማሳደግ የመንግስትን ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ፕሮግራሞችን በዕውቀት እና በእምነት ተቀብሎ ለተፈፃሚነታቸው የሚጥር ልማታዊ አመለካከት የያዘ (በገንቢ ምክንያታዊ ትንታኔ የዳበረ አቅም) እና የመፈጸምና የማስፈጸም አቅሙ የጎለበተ የከተሞች የልማት ሠራዊት ይገነባል፡፡

**ተግባር 1፡** በዘርፉ አስፈጻሚ ተቋማት የሚስተዋሉ የአመለካከት ክፍተቶችን እና ምንጮቻቸውን ለመለየት የሚያስችል ጥናት በበጀት ዓመቱ አንድ ጊዜ ከዘርፉ የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ጋር አቀናጅቶ በማከናወንና በመተግበር አፈጻጸሙን ተከታትሎ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 2፡** በሥነ ምግባርና ዲሲኘሊን መመሪያና ደንቦች፣ (የጋራ እሴቶቻችን ላይ ትኩረት በማድረግ) በተቀናጀ ውጤት ተኮር ሥርዓት ትግበራ አውቶሜሽን አጠቃቀም፣ በዙሪያ መለስና የራስ ማሻሻል ዕቅድ ዝግጅት፣ በአፈጻጸም እና ግምገማ ውጤት ምዝገባ ላይ ለሁሉም አመራሮችና ፈጻሚዎች በበጀት ዓመቱ አንድ ጊዜ ሥልጠና መስጠት፣

**ተግባር 3፡** ለሁሉም አመራርና ፈጻሚዎች በግብዓት አቅርቦትና አጠቃቀም ላይ የሚታዩ የአመለካከት ክፍተቶችን የሚሞላ ሥልጠና በበጀት ዓመቱ 5 ጊዜ ማካሄድ፣

**ተግባር 4፡** በዘርፉ አስፈጻሚ ተቋማት የልማት ሠራዊት ግንባታን ለማሳካት በአመራሩና በባለሙያ የሚስተዋሉ ወሳኝ የክህሎት ክፍተቶችን እና ምንጮቻቸውን ለመለየት የሚያስችል ጥናት በበጀት ዓመቱ አንድ ጊዜ ከዘርፉ የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ጋር በማቀናጀት ማካሄድ፣

**ተግባር 5፡** የዙሪያ መለስ እና የግል ዕቅድ ዝግጅት፣ የአፈጻጸም የክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስ መረጃዎች አያያዝና ልውውጥ የሚያግዝ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ /ICT/ አጠቃቀም፤ የሚዛናዊ ውጤት ተኮር፣ የልማትና የለውጥ ቡድን፣ የርስ በርስ መማማር፣ ዙሪያ መለስ፣ ራስን የማብቃት ዕቅድ እና የአፈጻጸም ምዝገባ፣ ግምገማና ምዘና፤ በጥራት ሥራ አመራር /ISO/ ሥርዓት ዝርጋታ ጽንሰ ሐሳብ አስፈላጊነትና ፋይዳ ላይ ለሁሉም የዘርፉ አመራሮችና ፈጻሚዎች የ6 ዙር ሥልጠና መስጠት፣

**ተግባር 6፡** በተቀናጀ ውጤት ተኮር ሥርዓት ደረጃ ዘጠኝ ውስጥ የዙሪያ መለስና የግል ማሻሻል ዕቅድ እና አፈጻጸም ምዘና ላይ በሚዘጋጁ መመሪያዎችና ማኑዋሎች ላይ ለሁሉም የዘርፉ አመራሮች የአሰልጣኞች ሥልጠና በበጀት ዓመቱ አንድ ጊዜ ማካሄድ፣

**ተግባር 7፡** በዘርፉ ለሚገኙ ለሁሉም አመራሮች በውጤታማ አመራር እና ምክንያታዊ ትንተና /Rational Thinking/፣ የልማት ሠራዊት ግንባታን የሚያግዝ የአዲስ ቅጥር ሠራተኞች የክትትልና ምክር ድጋፍ /ሜንቶሪንግ/ እና ተነሳሽነትን ማጎልበት /Motivation/ ላይ በበጀት ዓመቱ 2 ጊዜ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ማካሄድ፣

**ተግባር 8፡** የልማትና የለውጥ ቡድን/አሃድን ብዙ ግንባር ቀደም ፈጻሚዎችን ማፍራት የሚያስችለው አቅም ለመፍጠር እና ለማጠናከር የሚረዳ ድጋፍ በየሩብ ዓመቱ ማካሄድ፣

**ተግባር 9፡** በዘርፉ የከተማ ልማትና የከተማ ቤት ፖሊሲዎች፣ የከተማ የልማት ሠራዊት ግንባታ፣ የኮንስትራክሽን ኢዱስትሪ ልማትና የማስፈጸም አቅም ግንባታ ስትራቴጂ፣ የከተሞች የማስፈጸም አቅም ግንባታና የህዝብ ንቅናቄ ስትራቴጂዎችን ዓላማ ይዘትና ፋይዳ የመሳሰሉትን በአጭሩ አጠቃለው የሚይዙ እና ባለቤትነትን የሚፈጥሩ 5 ጽሁፎችን ማዘጋጀት፣

**ተግባር 10፡** በዘርፉ የተመዘገቡ ውጤታማ ሥራዎችን የተቋሙ አመራርና ፈጻሚዎችን አንድ ጊዜ በማስጎብኘት የአመራሩና ፈጻሚው እምነት እና ተነሳሽነት እንዲጎለብት ማድረግ፣

ተግባር 11፡ የምክንያታዊ ትንተና /Rational Thinking/ እና የባለቤትነት የአስተሳሰብ ዝንባሌ መፍጠሪያ የሥልጠና ዝግጅት እና የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ማንዋል እና የልማት ሠራዊት ግንባታ አፈጻጸም፣ የትግበራ ክትትል እና ግምገማ ማንዋል ማዘጋጀት፡፡

**ግብ ሁለት፡ አመራሩ እና ፈጻሚው በውጤት ተኮርና በራስን የማብቃት ዕቅድ እና በዙሪያ መለስ ግምገማና ምዘና መስፈርቶች እንዲመዘን በማድረግ 13 ታታሪዎችን ለይቶ ዕውቅና እና ማበረታቻ በመስጠት እንዲሁም ተሞክሮዎችን በመቀመር የዘርፉ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ግቦች አፈጻጸም እንዲጎለብት ይደረጋል፡፡**

ተግባር 1፡ የ2004 በጀት ዓመት የአመራርና ፈፃሚ የውጤት ተኮር፣ የዙሪያ መለስና ራስን የማብቃት ዕቅድ አፈፃፀም ምዘና እንዲካሄድ ማድረግ፣

ተግባር 2፡ የ2004 በጀት ዓመት ውጤት ተኮር ዕቅድ፣ የዙሪያ መለስ እና ራስን የማብቃት ግምገማና ምዘና መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ 13 ታታሪዎችን መለየትና ዕውቅና መስጠት፣

ተግባር 3፡ በየወሩ፣ በየሩብ ዓመቱ እና በግማሽ ዓመት በሚደረጉ የግምገማና ምዘና መረጃዎችን በመሰብሰብ የችግር አፈታት ክህሎት (Problem solving skills) ክፍተቶች ላይ ዝንባሌያዊ ትንተና ማካሄድ፣

ተግባር 4፡ በየወሩ፣ በየሩብ ዓመቱ እና በግማሽ ዓመት የሚደረጉ የግምገማና ምዘና መረጃዎችን በመሰብሰብ የአስተሳሰብ ዝንባሌና የተግባር አፈጻጸም ዝንባሌ ላይ ምክንያታዊ ትንተና ማካሄድ፣

ተግባር 5፡ በዘርፉ በበጀት ዓመቱ አንድ ጊዜ የሞዴል አመራርና ሠራተኞች ምርጥ ተሞክሮ ቀምሮ ሰነድ ማዘጋጀት፡፡

## 1.2. የለውጥ መሣሪያዎች ትግበራ ክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስ ሥራ

**ዓላማ፡** **በመስሪያ ቤታችን እየተተገበረ ያሉ የመሠረታዊ የአሠራር ሥርዓት ለውጥ (BPR)፣ የሚዛናዊ የውጤት ተኮር ምዘና (BSC)፣ የዙሪያ መለስ ግምገማ (360% degree evaluation)፣ ግብ ተኮር አመራር (ABM)፣ የግል አቅም ማሻሻል (SDP)፣ የፕሮግራም በጀት አፈጻጸም (Program budgeting) እና የጥራት ሥራ አመራር (ISO 9001:2008) በተቀናጀ መንገድ እንዲፈጸምና በዓመቱ ለተያዘው ዕቅድ አፈጻጸም ቅልጥፍና እና ውጤታማነት አጋዥ እንዲሆን ለማድረግ ነው፡፡**

**ጥቅል ግብ፡** በ2005 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ ከላይ የተዘረዘሩ የለውጥ መሣሪያዎች አንዱ ከሌላው መለየት በማይቻል መልኩ የመ/ቤታችን የዕለት ተዕለት አሠራር እስከሚሆኑ ድረስ በክትትልና ድጋፍ እንዲሁም የክህሎት ክፍተቱን ለይቶ በስልጠና በመሙላት ቋሚ ሥርዓት ይደረጋል፡፡

**ዝርዝር ግቦችና ተግባራት**

**ግብ አንድ፡ የአደረጃጀትና የአሠራር ሥርዓቶችን በየወቅቱ በማሻሻል (BPR - calibration) የዘርፉን የልማት አፈፃፀም ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ የተገልጋይ እርካታን 95% በማድረስ የተገልጋይ ተጠቃሚነት እንዲያድግ ይደረጋል፡፡**

**ተግባር 1፡** የተቋሙን የአመራር፣ የአሰራርና የተግባር አፈጻጸም መመሪያ መከለስና አፅድቆ ተግባራዊ በማድረግ አፈጻጸሙ ላይ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

**ተግባር 2፡** በየደረጃው በቢሮ እና በመምሪያ ደረጃ ላሉ ኃላፊዎችና ፈጻሚዎች የበጀት አጠቃቀምን ጨምሮ የመወሰን ኃላፊነት ከተጠያቂነት ጋር ለመስጠት የሚያስችል ማንዋል በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ፣

**ተግባር 3፡** በተቋሙ የተገልጋዮች መድረክ (በየዘርፉ የተደራጁ በማድረግ) በዓመት ሁለት ጊዜ በማካሄድ የአገልግሎት ዕርካታ 95 በመቶ መድረሱን ማረጋገጥ፣

**ተግባር 4፡** የምርጥ ተሞክሮ ቅመራ ማንዋል ማዘጋጀት፣ የተሻለ ውጤትና የአመራር ብቃት በተለይ የችግር አፈታት ተሞክሮ መቀመርና ማስፋት፣

**ተግባር 5፡** በዘርፉ በ2004 ተቀናጅተው በተተገበሩ የለውጥ መሳሪያዎች አማካኝነት የተገኙ የልማት ስራዎች አፈጻጸም ምርጥ ተሞክሮ በመቀመር በዶክመንተሪ ፊልም አስደግፎ እንዲስፋፋ ማድረግ፤

**ተግባር 6፡** የግለሰብ የተቀናጀ የውጤት ተኮር ሥርዓት ትግበራ በኦቶሜሽን ታግዞ መተግበር፤

**ተግባር 7፡** የአዲስ ቅጥር ሠራተኞች የክትትልና ምክር ድጋፍ /የሜንቶሪንግ ሥራዎች ማንዋል ማዘጋጀት፣

**ተግባር 8፡** በለውጥ መሣሪያዎች አፈፃፀም በሚገኙ መረጃዎች መሰረት የአገልግሎት ስታንዳርዶችና ደረጃዎችን ማሻሻል (calibration)፡፡

**ግብ ሁለት፡ የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲን አደረጃጀትና የአሠራር ሥርዓቶችን በማሻሻል (BPR - calibration & BSC) የተገልጋይ እርካታን 100% በማድረስ የተገልጋይ ተጠቃሚነት እንዲያድግ ይደረጋል፡፡**

**ተግባር 1፡** የሚኒስቴር መ/ቤቱን ተሞክሮ መነሻ በማድረግ የኤጀንሲውን አደረጃጀትና አሠራር (BPR) እንዲጠና በማድረግና ተግባራዊነቱ ላይ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

**ተግባር 2፡** የሚኒስቴር መ/ቤቱን ተሞክሮ መነሻ በማድረግ በኤጀንሲውን በየደረጃው በቢሮ እና በመምሪያ ደረጃ የመሠረታዊ ውጤት ተኮር (BSC) ሥርዓት እንዲጠና በማድረግ ተግባራዊነት ላይ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

**ተግባር 3፡** መላ የኤጀንሲው ሠራተኞች የዘርፉን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ላይ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ለማድረግ ሥልጠና በመስጠት የለውጥ ሠራዊት መፍጠር፡፡

**ተግባር 4፡** በኤጀንሲው የአገልግሎት ዕርካታ 100% መድረሱን ማረጋገጥ፡፡

**ግብ ሦስት፡ የልማትና የለውጥ ሥራዎቻችንን ውጤታማነት የሚያፋጥን የጥራት ሥራ አመራር ሥርዓት በቋሚነት ተተግብሮ በዘርፉ የጥራት ሥራ አመራር የብቃት ሰርተፊኬት እንዲገኝ ይደረጋል፡፡**

**ተግባር 1፡** የISO 9001:2008 የጥራት ሥራ አመራር ሥርዓት ትግበራ ቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን በማጠናቀቅ ሪፖርት ማቅረብ፣

**ተግባር 2፡** የISO 9001፡2008 የጥራት ሥራ አመራር ማስተግበሪያ 2 ሰነዶች ማዘጋጀት፣

**ተግባር 3፡** የISO 9001፡2008 የጥራት ሥራ አመራር ሥርዓት ማልማትና ትግበራ በማካሄድ ሪፖርት ማዘጋጀት፣

**ተግባር 4፡** የISO 9001፡2008 የጥራት የውስጥ ኦዲት ማካሄድ፣

**ተግባር 5፡** የISO 9001፡2008 የጥራት ሰርተፍኬት ለማግኘት ዝግጅት በማጠናቀቅ የውጭ ኦዲት ለማካሄድ ጥሪ ማስተላለፍ እና ሪፖርት ማዘጋጀት፣

**ተግባር 6፡** የISO 9001፡2008 የጥራት የውጭ ኦዲት በማካሄድ የብቃት ሰርተፊኬት ማግኘት፡፡

**ግብ አራት፡ በዘርፉ ጠንካራ የለውጥ ትግበራ ክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስ ስርዓት በመዘርጋት የለውጥ ሂደቱ በዓመቱ መጨረሻ ላይ ዘላቂና በማይቀለበስ ደረጃ ላይ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡**

**ተግባር 1፡** ሳምንታዊ የፈጻሚዎች ውጤት ተኮር ዕቅድ ክፍፍል፣ ዕለታዊ የአፈጻጸም መረጃ ምዝገባና ሳምንታዊ የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ፣

**ተግባር 2፡** ሳምንታዊ የልማትና የለውጥ ቡድን ዕርስ በርስ የመማማር ሂደት በእያንዳንዱ የለውጥ መሣሪያዎች ላይ ያለውን አፈጻጸም አጠናክሮ እንዲገመገም ማድረግ፣ ችግሮችና መንስኤቸው እንዲለይና መፍትኤም የሚያስቀምጥበት ሥርዓት መዘርጋት፣

**ተግባር 3፡** በየደረጃው በየወሩ፣ በየሩብ ዓመቱና በግማሽ ዓመት የውጤት ተኮር ዕቅድና ራስን የማብቃት ዕቅድ ትግበራና ዙሪያ መለስን ጨምሮ ግምገማና ምዘና በማካሄድ ማረጋገጥ፣

**ተግባር 4፡** የመወሰን ኃላፊነት ከተጠያቂነት ጋር (Empowerment) በየደረጃው እስከ ፈጻሚ ድረስ መውረዱን ማረጋገጥ፣

**ተግባር 5፡** በዘርፉ የለውጥ ሥራዎች አፈጻጸም ግምገማ ከልማት ሥራዎች አፈጻጸም ግምገማ ጋር በማቀናጀት በዓመት ሁለት ጊዜ ማካሄድ፣

**ተግባር 6፡** የውጤት ተኮር ሥርዓት ደረጃ ዘጠኝን ለማስፈጸም የተዘጋጁ የሰው ኃይል ልማት፣ የተቋማትና የሰራተኞች ምዘና፣ ጥቅማ ጥቅምና ማበረታቻ መመሪያዎች መተግበር፣

ተግባር 7፡ የ2006 በጀት ዓመት ውጤት ተኮር ዕቅድ እስከ ፈጻሚ እንዲወርድና በየደረጃው መግባቢያ ሰነድ እንዲፈረም ማድረግ፣

ተግባር 8፡ የለውጥ ኮሙኒኬሽን ዕቅድ አተገባበር ላይ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፡፡

## 2. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ሥራዎች

**ጥቅል ዓላማ፡** **የተቀናጀ ድጋፍ በመስጠት፣ ሰፊ የሥራ ዕድል በመፍጠር ድህነትን በመቀነስ፣ ተወዳዳሪና ለኢንዱስትሪው ልማት አስተማማኝ መሰረት የሚጥል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ማስፋፋት ነው፡፡**

**ጥቅል ግብ፡** **ከዘርፉ የ5 ዓመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ከተያዘው ዕቅድ ውስጥ በ2005 በጀት ዓመት በመደበኛ ለ618,832 ስራ ፈላጊ ዜጎችና በመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች 1.107 ሚሊዮን በድምሩ 1,718,832 የሥራ ዕድል ይፈጠራል፤ ለ550,396 አንቀሳቃሾች የብር 5 ቢሊዮን የአገር ውስጥ ገበያ እና ለ22,127 አንቀሳቃሾች የ23 ሚሊዮን ዶላር የውጭ አገር የገበያ ዕድል ይፈጠራል፤ ለነባር እና አዲስ ወደ ሥራ ለሚገቡ 2.38 ሚሊዮን አንቀሳቃሾች የአመለካከትና ክህሎት ሥልጠና በመስጠት የልማት ሠራዊት ይገነባል፡፡**

### 2.1. የክልሎች አቅም ግንባታ ሥራ

**ዓላማ፡** **የአነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ልማት የመደገፍ ሥራ ተቋማዊና ዘላቂ ይሆን ዘንድ ከክልል እስከ አንድ ማዕከል በአደረጃጀት፣ በአሠራር፣ በሰው ኃይል ለተልዕኮ ስኬት የሚረባረቡ እንዲሁም ለውጤት የሚተጋ ተቋም ለመፍጠር ነው፡፡**

**ግብ፡** **በ2005 የዕቅድ ዘመን የዘርፉን አስፈጻሚ አካላትና የክልሎችን የማስፈፀም አቅም ለማሳደግ ለ6,288 አመራር አካላትና ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ሥልጠና መስጠት እና ለ677,521 ነባር አንቀሳቃሾችና ወደ ሥራ ለሚገቡ አዲስ 1.7 ሚሊዮን አንቀሳቃሾች በድምሩ ለ2.38 ሚሊዮን የአመለካከትና ክህሎት ሥልጠና በመስጠት የልማት ሰራዊት ይገነባል፡፡**

**ዝርዝር ተግባራት**

ተግባር 1፡ ቀጣይነትና ተከታታይነት ያለው የሥራ አፈጻጸም ግምገማ ሥርዓት በመዘርጋት ለልማት ዝግጁነትና ተነሳሽነት ያለው የልማትና የለውጥ ሠራዊት ለመፍጠር በየሩብ ዓመቱ ግምገማዊ ሥልጠና በማካሄድ ግብረ-መልስ መስጠት፣

ተግባር 2፡ የጥቀቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል ካለበት 45.6 በመቶ (8,786) ወደ 90 በመቶ (17,572) በቅጥር እንዲያድግ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

**ተግባር 3፡** ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ የስልጠና ዕድሎችን በማፈላለግ 60 ለሚሆኑ የዘርፉ አስፈጻሚ አካላት ባለሙያዎች አቅም መገንባት፣ በዚህም የሴቶች ተጠቃሚነት 50 ከመቶ ማድረስ፣

**ተግባር 4፡** በየክልሉ በየደረጃው የሚገኙ 20,000 የሚሆኑ የዘርፉ የሶስቱም አስፈፃሚ አካላት አመራሮችና ባለሙያዎች በልማታዊ አስተሳሰብ እንዲገነቡ ማድረግ፣ የሴቶች ተሳትፎም 50 ከመቶ እንዲሆን ማድረግ፣

**ተግባር 5፡** በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፐራይዝ አንቀሳቃሾች ላይ የሚታየውን የአመለካከትና የክህሎት ችግሮችን ለመፍታት ለ677,521 ነባርና አዲስ ወደ ሥራ ለሚገቡ 1.7 ሚሊዮን አንቀሳቃሾች በየደረጃው ችግር ፈቺ የአመለካከትና የቴክኒክ ክህሎት ሥልጠና በመስጠት ሰፊ የህዝብ ንቅናቄ መፍጠር፣ የሴቶች ተጠቃሚነት 50 ከመቶ ማድረስ፣

**ተግባር 6፡** በየደረጃው ለሚገኙ ለ6,288 አመራር አካላትና ፈጻሚ ባለሙያዎች በዘርፉ ላይ ያላቸውን የአመለካከትና የክህሎት ችግር የሚፈታ እና በቀጣይም ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሥልጠና መስጠት የሚያስችል የአሰልጣኞች ሥልጠና መስጠት፣ የሴቶች ተጠቃሚነት 50 ከመቶ ማድረስ፣

**ተግባር 7፡** በየደረጃው ለሚገኙ 6,288 አመራሮችና ባለሙያዎች በኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ፣ በከተማ ልማት ፖሊሲ እና በዘርፉ ልማት ስትራቴጂና በድጋፍ ማዕቀፎች[1] ላይ ቀጣይነት ያለው የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፣ የሴቶች ተጠቃሚነት 50 ከመቶ ማድረስ፣

**ተግባር 8፡** የጥ/አ/ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍን አቅም ለመገንባት የአገር ውስጥ እና የውጭ ተሞክሮዎችን በመቀመር ለማስፋት የሚያስችሉ 12 ሠነዶችን ማዘጋጀት፣

**ተግባር 9፡** በየክልሎች ለሚገኙ 800 የዘርፉ አስፈጻሚ አካላት ባለሙያዎች በኢንተርፕርነርሺፕና በንግድ ልማት አገልግሎት አሰጣጥ (BDS) የአሰልጣኞች ስልጠና በመስጠት ኢንተርፕራዞች የተቀናጀ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎትን ማሳደግ፤ የሴቶች ተጠቃሚነት 50 ከመቶ ማድረስ፤

**ተግባር 10፡** ልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎች የሚገኙ የዘርፉ አስፈጻሚ አካላት አመራሮችና ባለሙያዎችን አቅም በመገንባት በክልሎቹ በሚገኙ ከተሞች የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት መስፋፋት አሁን ያለበትን ደረጃ በጥናት በመወሰን በመቶ ወደ 20 በመቶ እንዲያድግ ድጋፍ መስጠት፤

**ተግባር 11፡** ለ2,074 የዘርፉ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ጣቢያ ባለሙያዎች በሂሳብ አያያዝና በኦዲት ሥራ ላይ የአሠልጣኞች ሥልጠና መስጠት፣ የሴቶች ተጠቃሚነት 50 ከመቶ ማድረስ፡፡

---

[1] የድጋፍ ማዕቀፎች = የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ የማምረቻና የመሸጫ ቦታ አጠቃቀምና አስተዳደር፣ የብድርና ቁጠባ አገልግሎት አሰጣጥ፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት፣ የገበያ ልማትና ግብይት፣ የሰው ኃይል ልማት፣ የመሳሪያዎች ሊዝ መመሪያዎች፣ የሞዴል ኢንተርፕራይዞች ምርጥ ተሞክሮ ቅመራና ማስፋት ማንዋል ናቸው፡፡

2.2. የካይዘን ሥራ አመራር ሥርዓት ትግበራ አፈጻጸምና ክትትል ሥራ

**ዓላማ፡** የአነስተኛ እና የጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን የሚያመርቱት ምርት ወይም የሚያቀርቡት አገልግሎት ጥራት፣ ዋጋ እና ምርታማነት በቀጣይነት ማሻሻል (continuous improvement) እንዲችሉ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓትና ባህል ለመገንባት ነው፡፡

**ጥቅል ግብ፡** በካይዘን ሥራ አመራር 1,060 አሠልጣኞችን እና 15,000 አንቀሳቃሾችን በማሠልጠን በጥራት እና ዋጋ ማሻሻያ ሠርክል ቡድን አደራጅቶ ካይዘን ሥርዓት እንዲሆን ይደረጋል፡፡

**ዝርዝር ግቦችና ተግባራት**

**ግብ አንድ፡** ካይዘንን ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ በአንቀሳቃሾች ላይ የሚታዩ የአመለካከት ክፍተቶችን በመለየት ለመፍታት የሚያስችል ሰነድ በማዘጋጀት፤ ለ15,000 አንቀሳቃሾች የአመለካከት ክፍተቶች መሙያ ስልጠና በመስጠት እና ያመጣውን ለውጥ በመገምገም ግብረ-መልስ ይሰጣል፤ የሴቶች ተሳትፎ 50% መሆኑ ይረጋገጣል፡፡

**ተግባር 1፡** ከካይዘን ጋር በተያያዘ ያሉ የአመለካከት ክፍተቶችን በመለየት ክፍተቶቹን ሊሞላ የሚያስችል ሰነድ ማዘጋጀት፣

**ተግባር 2፡** በአመለካከት ስልጠናው ላይ የሚሳተፉ 15,000 የአነስተኛ ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾችን በመለየት ስልጠናውን መስጠት፣

**ተግባር 3፡** የአመለካከት ክፍተቶች መሙያ ስልጠናው ያመጣውን ለውጥ በመገምገም ግብረ-መልስ መስጠት፡፡

**ግብ ሁለት፡** ከፌደራል የቴ/ሙ/ት/ስ/ኤጀንሲና ከኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲቲዩት ጋር በቅንጅት በመስራት ከትግራይ፣ ከአማራ፣ ከኦሮሚያ፣ ከደቡብና ከሐረሪ ክልሎች እና ከአዲስ አበባና ከድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች የጥ/አ/ኢ/ል/ኤጀንሲዎች ወይም ቢሮዎች፣ ጽ/ቤቶች፣ አንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ለሚመለመሉ 1,060 ፈጻሚዎች በካይዘን ጽንሰ ሃሳብና አተገባበር ላይ ስልጠና ይሰጣል፣ የሴቶች ድርሻ 50% ይሆናል፡፡

**ተግባር 1፡** በካይዘን አፈጻጸም ትግበራ ላይ የፈጻሚዎችን የአቅም ክፍተቶች ለመለየት የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፣

**ተግባር 2፡** ለስልጠና የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን መለየትና የስልጠና መርሃ-ግብር ማዘጋጀት፤

**ተግባር 3፡** ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ከሚያመቻቹ ፈጻሚዎች በበጀት ዓመቱ የካይዘን ስልጠና የሚሰጣቸውን 1,060 ፈጻሚዎችን በመለየት ስልጠና መስጠት፣

**ግብ ሦስት፡ በትግራይ፣ በአማራ፣ በኦሮሚያና በደቡብ ክልሎችና በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣ በቆዳ፣ በእንጨትና ብረታ ብረትና በምግብ ዝግጅት ንዑሳን ዘርፎች ተሰማርተው ለሚገኙ** 11,000 **አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የካይዘን ስራ አመራር ስርዓት ስልጠና በመስጠት የቡድን አደረጃጀት በቅድሚያ ፈጥረው ካይዘን ይተገበራል፣ የሴቶች ተጠቃሚነት 50% ይሆናል፡፡**

**ተግባር 1፡** ከፌዴራል የቴ/ሙ/ት/ስ/ኤጀንሲ እና ከኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲቲዩት ጋር በጋራ ለአፈጻጸም የሚያግዝ ዝርዝር ዕቅድ በማዘጋጀትና በመተግበር አፈጻጸሙን በየሩብ ዓመቱ በጋራ መገምገም፣

**ተግባር 2፡** ጥ/አ/ኢንተርፕራይዞች የሚመቻቸውን የቡድን አደረጃጀት በመፍጠር የካይዘን ሥራ አመራር ስርዓትን ለመተግባር ፍላጎት እንዲኖራቸው በማድረግ [redacted] ኢንተርፕራይዞች መለየት፣

**ተግባር 3፡** ለተመረጡ 11,000 ኢንተርፕራይዞች ስልጠና እና የማማከር አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ፤

**ተግባር 4፡** በድርጅት ቡድን አማካይነት የአፈጻጸም ትግበራውን እየተከታተሉ ድጋፍ ማድረግ፤

**ተግባር 5፡** በካይዘን የተገኘውን ውጤት ለመለካት የሚያስችሉ መረጃዎችን መሰብሰብና ማደራጀት፣ በዶክመንተሪ ፊልም የተደገፉ በማድረግ በተለይ ለማነቃ አፈታት የተለየ ትኩረት መስጠትና የማስፋት ስትራቴጂ ነድፎ መተግበር፡፡

**ግብ አራት፡ በፌዴራል የጥ/አ/ኢ/ል/ኤጀንሲ ካሉ ዳይሬክቶሬቶች 75% በሚሆኑት የካይዘን ሥራ አመራር ሥርዓት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡**

**ተግባር 1፡** የዳይሬክቶሬቶችን የክፍተት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፤

**ተግባር 2፡** ከሌሎች የለውጥ መሣሪያዎች ጋር የተቀናጀና የተናበበ የካይዘን ስራ አመራር ስርዓት የትግበራ ማኑዋል ማዘጋጀት፤

**ተግባር 3፡** ከሌሎች የለውጥ መሣሪያዎች ጋር ያለው መስተጋብር ከተገነዘቡ በኋላ ካይዘን የሚተገበርባቸውን 6 ዳይሬክቶሬቶች መለየትና ስልጠና መስጠት፤

**ተግባር 4፡** ከሌሎች የለውጥ መሣሪያዎች ጋር የተጣጣመ ዕቅድ በማዘጋጀት ወደ ትግበራ መገባቱን ማረጋገጥና ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤

**ተግባር 5፡** በካይዘን እና ከሌሎች የለውጥ መሣሪያዎች ጋር በቅንጅት ተተግብሮ የተገኘውን መሻሻል ለመለካት የሚያስችሉ መረጃዎችን መሰብሰብና ማደራጀት እና ተሞክሮውን ማስፋት፡፡

**ግብ አምስት፡ በክልል ደረጃ ካሉ የፐ/አ/ኢ/ል/ኤጀንሲዎች ውስጥ 63% በሚሆኑት የካይዘን የስራ አመራር ስርዓት እንዲተገበር ይደረጋል፡፡**

**ተግባር 1፡** የክፍተት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፤

**ተግባር 2፡** የካይዘን ስራ አመራር ስርዓት የትግበራ ማኑዋል ማዘጋጀት፤

**ተግባር 3፡** ተቋማትን መለየትና ስልጠና መስጠት፤

**ተግባር 4፡** ወደ ትግበራ መገባቱን ማረጋገጥና ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤

**ተግባር 5፡** በካይዘን የተገኘውን መሻሻል ለመለካት የሚያስችሉ መረጃዎችን መሰብሰብና ማደራጀት፣

**ተግባር 6፡** የካይዘን ትግበራን አፈፃፀም ለመገምገም የሚያስችሉ የውጤት መለኪያዎችን በማዘጋጀት የካይዘን ትግበራ 63% መድረሱን በመገምገም ግብረ-መልስ መስጠት፡፡

**ግብ ስድስት፡ በትግራይና በአዲስ አበባ ከTVET ጋር በመቀናጀት 10 የካይዘን ትግበራ ምርጥ ተሞክሮ በመቀመርና በማስፋፋት ሞዴል ኢንተርፕራይዞች ይፈጠራሉ፡፡**

**ተግባር 1፡** በትግራይና በአዲስ አበባ ከTVET ጋር በመቀናጀት የካይዘን ትግበራ 10 ተሞክሮዎችን መቀመርና ሰነድ ማዘጋጀት፤

**ተግባር 2፡** በተቀመሩ ተሞክሮዎች ላይ ለፈጻሚ አካላት ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ስልጠና ለ1,060 አመራርና ፈጻሚ መስጠት፤

**ተግባር 3፡** ኢንተርፕራይዞችን መለየትና የማስፋት ስልጠና በማካሄድ፣ በአተገባበሩ ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፤

**ግብ ሰባት፡ የካይዘንን ጽንሰ ሃሳብና ጠቀሜታ አስመልክቶ ከአገር አቀፍ ሚዲያዎች ጋር በመተባበር 2 የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች ይዘጋጃሉ፡፡**

**ተግባር 1፡** የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም እና ማኑዋል የሚያዘጋጅ አካል በመለየት የውል ስምምነት መፈጸም፤

**ተግባር 2፡** የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም እና ማኑዋል ማዘጋጀት፤

**ተግባር 3፡** በተዘጋጀው ማኑዋል መሰረት ስለካይዘን ጽንሰ ሃሳብና ጠቀሜታ 2 ፕሮግራሞችን አዘጋጅቶ ግንዛቤ ማስጨበጥ፡፡

## 2.3. የጨርቃ ጨርቅ፣ ቆዳና ቆዳ ውጤቶች ሥራ

**ዓላማ፡** **በጨርቃ ጨርቅና ቆዳ በተመረጡ ግን በብዛት ገበያ ውስጥ ገብተው ከውጭ የሚገቡትን የጨርቃ ጨርቅና የቆዳ ውጤቶች ላይ በማተኮር ለቀጣይ መስፋፋት መሠረት የሚጥልና ሰፊ የሥራ ዕድል የሚፈጥር ዘርፍ መሆኑን በተጨባጭ እና በተግባር በማሣየት ተነሳሽነት (confidence)ለመፍጠር ነው፡፡**

**ግብ፡** **በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት 56,059 እና በቆዳና ቆዳ ውጤቶች 24,000 በድምሩ ለ80,059 አዲስ ሥራ ፈላጊ ዜጎች የሥራ ዕድል እንዲፈጠር በማድረግ እና ተገቢውን ክህሎት በመፍጠር በዓመቱ መጨረሻ ላይ ለምርጥ ተሞክሮነት ለማስላት የሚሆን ስኬት ይመዘገባል፡፡**

**ዝርዝር ተግባራት**

**ተግባር 1፡** በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት 56,059 እና በቆዳና ቆዳ ውጤቶች 24,000 በድምሩ ለ80,059 አዲስ ሥራ ፈላጊ ዜጎች የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ሙያዊ ድጋፍ በማድረግ ከነዚህ ውስጥ 50% ሴቶች ማድረግ፤

**ተግባር 2፡** በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት 7,000 እና በቆዳና ቆዳ ውጤቶች 3,000 የጥቃቅንና አነስተኛ አንቀሳቃሾች ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር በተለዩ የምርት ዓይነቶችና በግብዓት አቅርቦት እንዲተሳሰሩ ድጋፍ ማድረግ፣ ከነዚህ ውስጥ 50% ሴቶች ማድረግ፤

**ተግባር 3፡** በጨርቃ ጨርቅና የቆዳ ውጤቶች ዘርፍ የተጠኑ 3 (ሽመና፣ አልባሳት እና የቆዳ ውጤቶች) የዕሴት ሰንሰለቶችን ተግባራዊ እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት መስራት፤

**ተግባር 4፡** በጨርቃ ጨርቅና የቆዳ ውጤቶች ዘርፍ 13,000 (በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት 12,000 እና በቆዳና ቆዳ ውጤቶች 1,000) የሚሆኑ ነባር ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ቀጣይነት ለማረጋገጥ ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፤

**ተግባር 5፡** የጨርቃ ጨርቅና ቆዳ ውጤቶች የሚገኙ የሞዴል ኢንተርፕራይዞችን ምርታማነትና የምርት ጥራት ማሻሻል የማስፋት ስራ ከመሰራቱ በፊት የ3 የሽመና፣ 6 የልብስ ስፌት እና 4 የቆዳ ውጤቶች ላይ የተሰማሩ ባጠቃላይ የ10 ኢንተርፕራይዞችን ሞዴልነት ከአመለካከት ጥራትና ካፒታል እድገት ጋር የተያያዘ መሆኑን በማረጋገጥ ምርጥ ተሞክሯቸውን በአመለካከቱ፣ በካፒታል እድገቱ እንዲሁም ተጠቃሚነታቸው ሳይነጣጠል በጥንቃቄ እንዲቀመር ማድረግ፡፡

**ተግባር 6፡** በሽመና ምርት 1 የውጭ ሀገር ተሞክሮ ሰነድ ማዘጋጀት፡፡

2.4. የእንጨትና ብረታ ብረት ኢንጅነሪንግ ሥራ

**ዓላማ፡** በእንጨትና ብረታ ብረት በተመረጡ ግን በብዛት ገበያ ውስጥ ገብተው ሌላውን ዘርፍ በማስፋፋት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው ላይ በማተኮር እና በተነፃፃሪነት የተሻለ የሥራ ዕድል በሚፈጥሩ የምርት ዓይነቶች ውጤታማ መሆናቸውን በተጨባጭ እና በተግባር በማሳየት ለማስፋፋት እና የሙያ ምዘናው በአግባቡ እንዲፈጸም ማድረግ ነው፡፡ (ለምሳሌ፡- ቀርከሃ ለአትክልት ቤት ግንባታ (Green House) በማዋል በከተሞች ለምግብ ዋስትና እና የሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ ያለው ፋይዳ ማሳየትና ማስፋፋት ነው፡፡)

**ግብ፡** የተሟላ ድጋፍ በመስጠት (በብረታ ብረት እና ኢንጅነሪንግ) በብረታ ብረት ለ33,138፣ በእንጨት ለ17,000 አና በቀርከሃ ለ4,000 በድምሩ ለ54,138 እንዲሁም በመንግሥት ግዙፍ ፕሮጀክቶች ግንባታ በብረታ ብረት ሥራዎች 36,500 ሥራ ፈላጊ ዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር በዕቅድ የተያዘው የምዘና ውጤት እንዲሣካ ይደረጋል፡፡

**ዝርዝር ተግባራት**

**ተግባር 1፡** የተሟላ ድጋፍ በመስጠት (በብረታ ብረት እና ኢንጅነሪንግ) በብረታ ብረት ለ33,138፣ በእንጨት ለ17000 አና በቀርከሃ ለ4,000 በድምሩ ለ54,138 ሥራ ፈላጊ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር፣ ከዚህ ውስጥ 50% ሴቶች ማድረግ፣

**ተግባር 2፡** የተሟላ ድጋፍ በመስጠት በመንግሥት ግዙፍ ፕሮጀክቶች ማለትም በስኳር ፋብሪካዎች፣ በማዳበሪያ ፋብሪካዎች ግንባታ፣ በኮንስትራክሽን መሳሪያዎች፣ በባቡር ኔትዎርክና በኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ሥራዎች በብረታ ብረት ሥራዎች በድምሩ ለ36,500 ሥራ ፈላጊ ዜጐች የሥራ ዕድል መፍጠር፡፡ ከዚህ ውስጥ 50% ሴቶች ተጠቃሚ ማድረግ፣

**ተግባር 3፡** ከቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ጋር በመቀናጀት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ምርታማነትን የሚያግዙ የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚካሄድባቸው 439 ፕሮቶታይፖች ማዘጋጀት፣

**ተግባር 4፡** በእንጨትና በብረታ ብረት የሥራ ዘርፍ ለተሰማሩ ነባር 500 ኢንተርፕራይዞች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት፣

**ተግባር 5፡** በብረታ ብረትና በእንጨት የሥራ ዘርፍ ከተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች መካከል ብቃት ያላቸውን 20 ኢንተርፕራይዞች የምዘና ማዕከል ሆነው ማገልገል እንዲችሉ ዕውቅና እንዲያገኙ ማድረግ፣

**ተግባር 6፡** በብረታ ብረትና በእንጨት ዘርፍ ከተሰማሩ ነባር ኢንተርፕራይዞች መካከል 200 መሪ መዛኞችን ማፍራት፣

**ተግባር 7፡** የኢንተርፕራይዞችን ምርትና ማርታማነት ለማሳደግ የዕሴት ሰንሰለት ጥናት የተካሄደባቸውን የብረታ ብረት፣ የእንጨትና የቀርከሃ የምርት ዓይነቶችን በማስተዋወቅ ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ፣

**ተግባር 8:** በእንጨትና በብረታ ብረት የሚገኙ የሞዴል ኢንተርፕራይዞችን ምርታማነትና የምርት ጥራት ማሻሻል ማስፋት ስራ ከመሰራቱ በፊት የ10 ሞዴል ኢንተርፕራይዞች ከአመለካከት፣ ከምርታማነት፣ ከምርት ጥራትና ከካፒታል እድገት ጋር ተያይዞ በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት የተሻለ ተሞክሮዎችን በመቀመር እንዲስፋ ማድረግ፣

**ተግባር 9:** ጃካርድ፣ ኢንኩቤተር የካርትሪጅ ቀለም መሙያ እና 3 የብሪኬት ማምረቻ መሳሪያዎች ፕሮቶታይፕ ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር እንዲመረቱ ማድረግ፣

**ተግባር 10:** በአዲስ አበባ ከተማ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ሥራ ፈላጊዎች ወደ ስራ ለማስገባት ድጋፍ በማድረግ የተገኘውን ተሞክሮ ቀምሮ ወደ ሌሎች ክፍለ ከተሞችና ክልሎች እንዲሰፋ ማድረግ።

## 2.5. የኮንስትራክሽን ልማት ሥራ

**ዓለማ:** **በGTP የተያዙ የግንባታ ዕቅዶችም ይሁኑ ሌሎቹ በጥራት፣ በተመጣጣኝ ዋጋ እና በወቅቱ ይጠናቀቁ ዘንድ የሙያ ምዘናው በአግባቡ እንዲፈጸምና አጠቃላይ ኢንዱስትሪው አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞችን ይዞ ተወዳዳሪ እንዲሆን ማስቻል ነው።**

**ግብ:** **በመደበኛ በአግሮ ፕሮሰሲንግና ምግብ ዝግጅት፣ በኮንስትራክሽን ዘርፍ እና በከተማ ግብርና ዘርፍ በአጠቃላይ 322,819 እና በመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች 1.107 ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር በዕቅድ የተያዘው የምዘና ውጤት እንዲሣካ ይደረጋል። ከዚህ ውስጥ 50% ሴቶች ይሆናሉ።**

**ዝርዝር ተግባራት**

**ተግባር 1:** የተሟላ ድጋፍ በመስጠት በኮንስትራክሽን ዘርፍ ለ181,288፤ በአግሮ ፕሮሰሲንግና ምግብ ዝግጅት 70,329፤ በከተማ ግብርና ዘርፍ ለ71,202 በአጠቃላይ ለ322,819 አዲስ ሥራ ፈላጊ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር፣ ከዚህ ውስጥ 50% ሴቶች ተጠቃሚ ማድረግ፣

**ተግባር 2:** የተሟላ ድጋፍ በመስጠት በመንግሥት ግዙፍ ፕሮጀክቶች ማለትም በቤቶች ልማት/ በ10 ዩኒቨርሲቲዎች (182,335)፣ በ9 የስኳር ፋብሪካዎች (48,662)፣ በ8 የማዳበሪያ ፋብሪካዎች ግንባታ (37,077)፣ በመንገድ ልማት (382,713)፣ በባቡር ኔትዎርክ (131,040)፣ በኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ሥራዎች (121,114)፣ በኮብልስቶንና ሌሎች የከተማ መሰረተ ልማት (120,622)፣ በውሃና መስኖ ልማት ሥራዎች (48,662) በድምሩ ለ1.107 ሚለዮን ሥራ ፈላጊ ዜጐች የሥራ ዕድል መፍጠር። ከዚህ ውስጥ 50% ሴቶች ተጠቃሚ ማድረግ፤

**ተግባር 3:** በኮንስትራክሽን፣ በአግሮ ፕሮሰሲንግ፣ በከተማ ግብርናና በማዕድን ልማት ለተሰማሩ ለ224,951 አዲስ አንቀሳቃሾች የኢንተርፕረነርሽፕና ስራ አመራር እንዲሁም ለ97,868 የቴክኒክ ስልጠና (በአጠቃላይ በሁለቱም መስክ ለ322,819 ስልጠናው ይሰጣል) በቴክኒክና

ሙያ ሥልጠና ተቋማትና በተለያዩ ተቋማት ሥልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣ ከነዚህ ውስጥ 40% ሴቶች ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ፤

**ተግባር 4፡** በሁለት የከተማ አስተዳደርና በ9 ክልሎች ወደ ሥራ ለሚገቡ 618,000 አንቀሳቃሾች አገልግሎት የሚውል 6,429 ሄክታር ቦታ በማዘጋጀት 9,205 ሼዶችና 354 ህንፃዎች በብር 2 ቢልዮን እንዲገነባ ማድረግ፣ ከተጠቀሰው ቦታ/ህንጻ አቅርቦት ውስጥ ሴቶች 50% ተጠቃሚ ማድረግ፤

**ተግባር 5፡** በኮንስትራክሽን (በብሎኬትና ፕሪካስት ቢም ምርት፣ በኤሌክትሪክና ሳኒተሪ ኢንስታሌሽን) እና በአግሮፕሮስሲግ (በማንጎ፣ በበርበሬ፣ በእንጀራ፣ በምጥን፣ በማርና ጅንጅብል ምርቶች) ዘርፍ ለተሰማሩ ኢንተርፕራይዞችን ምርትና ማርታማነት ለማሳደግ የዕሴት ሰንሰለት መሰረት በማድረግና ቀደም ሲል ጥናት የተካሄደባቸውን 10 የምርት ዓይነቶችን ቀጣይ የማስተዋወቅ ተግባርና ኢንተርፕራይዞች በምርት ወይም በአገልግሎታቸው ተግባራዊ ማድረጋቸውን ማረጋገጥ፣

**ተግባር 6፡** በኮንስትራክሽን 7፣ በማዕድን 1፣ በከተማ ግብርና 2 እና በአግሮ-ፕሮስሲግ 3 ሞዴል ኢንተርፕራይዞች ከአመለካከት፣ ከምርታማነት፣ ከምርት ጥራትና ከካፒታል እድገት ጋር የተያያዘ በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት የተሻለ ተሞክሮዎችን በመቀመር እንዲሰፋ ማድረግ፣

**ተግባር 7፡** በአዲስ አበባ ከተማ በጉለሌ ክፍለ ከተማ በኮንስትራክሽን የስራ ዘርፍ በቤቶች ልማት ፕሮጀክት፣ በኮብል እስቶን መጥረብና ማንጠፍ እና በክፍለ ከተማው በሚገነቡ ግንባታዎችን የመንግስትና የግል ሕንጻዎች 16,357 ስራ ፈላጊዎችን በማሰልጠን ተጠቃሚ ማድረግ፣

**ተግባር 8፡** በኮንስትራክሽን የሥራ ዘርፍ ከተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች መካከል ብቃት ያላቸውን 20 ኢንተርፕራይዞች የምዘና ማዕከል ሆነው ማገልገል እንዲችሉ ዕውቅና እንዲያገኙ ማድረግ፣

**ተግባር 9፡** በኮንስትራክሽንዘርፍ ከተሰማሩ ነባር ኢንተርፕራይዞች መካከል 200 መሪ መዛኞችን ማፍራት፡፡

## 2.6. የገበያ ልማትና ግብይት ሥራ

**ዓላማ፡** **በመንግስት የሚሰጥ የገበያ ማፈላለግ ድጋፍ ዋነኛ ዓላማው ተቋማቶቹን ወደ ዘርፉ እንዲሠማሩ ለማስቻልና አዳዲስ የሥራ ዕድሎች ወደ ኢኮኖሚው እንዲገቡ እንዲሁም የኢምፖርት ሰብስቲትዩሽን ተልዕኮ ለመወጣት ነው፡፡**

**ግብ፡** **በተመረጡ የምርት ዓይነቶች ላይ በማተኮር ለ550,396 አንቀሳቃሾች በቆዳ፣ በጨርቃ ጨርቅ፣ በቀርከሃና በብረታ ብረት የ5 ቢሊዮን ብር የሃገር ውስጥ የገበያ ትስስር**

እንዲፈጠር እንዲሁም ለ300 ኢንተርፕራይዞች በምግብ ዝግጅት፣ በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣ በቆዳና ቆዳ ውጤቶችና የእደ ጥበብ ውጤቶች በመላክ 23 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ሃገር የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ በገበያ ትስስሩ የሴቶች ተጠቃሚነት 50% እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

**ዝርዝር ተግባራት፡**

**ተግባር 1፡** የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የገበያ ዕድል ለማስፋት የሚያግዙ 4 የግብይት ሥርዓቶች (ሰብ-ኮንትራክቲንግ፣ የአውትሶርሲንግ፣ ፍራንቻይዚንግና አውትግሮወር) ላይ ዝርዝር የአሰራር መመሪያ፣ የገበያ ቦታዎች አጠቃቀምን የተመለከተ Guidline እና የኤግዚቢሽን አዘገጃጀት ማንዋል በማዘጋጀት ለክልሎች ማሰራጨት፣ አፈጻጸሙ ላይ ክትትል በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 2፡** ለ550,396 ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አንቀሳቃሾች የ5 ቢሊዮን ብር የሃገር ውስጥ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ በገበያ ትስስሩ የሴቶች ተጠቃሚነት 50% እንዲደርስ ማድረግ፣

**ተግባር 3፡** የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የገበያ እድል የሚያሰፋ በአዲስ አበባ በሚገኙ የተመረጡ የሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት የገበያ ማዕከል አጠቃቀም ላይ ጥናት በማካሄድ የተሻለ ተሞክሮ መቀመር፣ የተገኘውን ተሞክሮ በ6 ክልሎች ለማሰራጨት ሚያስችል የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ማስፋት፣

**ተግባር 4፡** ብቃት ባላቸው 70 ሞዴል ኢንተርፕራይዞች የሚመረቱ በጥራትና በዋጋ ተወዳዳሪ የሆኑ ምርቶችን በኤጀንሲው ኢምፖሪየም በማስተዋወቅ የብር 1,497,961 ሽያጭ በማካሄድ የኢንተርፕራይዞችን የገበያ እድል እንዲሰፋ ማድረግ፣ የሴቶች ተጠቃሚነት 50% ማድረግ፣

**ተግባር 5፡** ብቃት ያላቸው 20 ኢንተርፕራይዞች ዕድገት/ዘርፍ ተኮር በሆኑ ምርቶች የሚሳተፉበት ባዛር በየወሩ መጨረሻ ማካሄድ፣ ከተሳታፊዎቹ ውስጥ 50% ሴቶች ማድረግ፣

**ተግባር 6፡** የኢንተርፕራይዞችን የገበያ ተወዳደሪነት ለማሳደግና የገበያ ችግራቸውን ለመፍታት ደረጃ ላልወጣላቸው ለ5 ዋና ዋና የዘርፉ ምርቶች ደረጃ እንዲወጣላቸው ማድረግ፡፡

**ተግባር 7፡** በየጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ምርትና አገልግሎቶቻቸውን የሚያስተዋውቁበትና የሚሸጡበት በክልልና በወረዳ ደረጃ የሚዘጋጁትን 1000 ኤግዚቢሽኖችና ባዛሮች ክትትልና ድጋፍ በማድረግና 2 አገር አቀፍ ኤግዚቢሽን በማዘጋጀት የገበያ ዕድላቸው እንዲሰፋ ማድረግ፣ በእነዚህ ኤግዚቢሽኖች የሴቶች ተሳትፎ 50% ማድረስ፣

**ተግባር 8፡** ለ300 የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ምርት ላኪዎች በሚሰጥ የውጭ ሀገር ገበያ ትስስር ድጋፍ በምግብ ዝግጅት፣ በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣ በቆዳና ቆዳ ውጤቶችና የእደ ጥበብ ውጤቶች በመላክ 23 ሚሊዮን ዶላር ገቢ እንዲያገኙ ማድረግ፡፡

**ተግባር 9፡** ኤክስፖርትን ለማሳደግ የኤጀንሲውን ድረ-ገጽ በመጠቀም የኢንተርፕራይዞች ምርትና አገልግሎቶች መረጃ 12 ጊዜ ወቅታዊ ማድረግ፣ 1 ዳይሬክተሪና 1 ካታሎግ ተዘጋጅቶ ማሰራጨት፣ በተጨማሪም በኤክስፖርት ለተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ከኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽንና ቴክኖሎጅ ሚ/ር ጋር በመተባበር ዌብ ፖርታል ተዘጋጅቶ ጥቅም ላይ እንዲዉል ማድረግ፣

**ተግባር 10፡** የኤክስፖርተሮችን ዓለም አቀፍ የገበያ ግንዛቤ ለማስፋትና የጥሬ ዕቃ አቅርቦትንና ትስስርን ለማጠናከር የሚያስችሉ 2 መድረኮች በየስድስት ወሩ በማዘጋጀትና በሩብ ዓመት አንድ ጊዜ ወቅታዊ የገበያ ነክ መጣጥፎችን በማሰራጨት የገበያ ተወዳደሪነታቸውን በማሳደግ የገበያ ችግራቸውን መፍታት፣ የሴቶች ተሳትፎ 50% ማድረግ፣

**ተግባር 11፡** 50 የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ምርትና አገልግሎቶቻቸውን የሚያስተዋውቁበትና የሚሸጡበት ከአጋር አካላት ጋር በመቀናጀት በምግብ ዝግጅት፣ በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣ በቆዳና ቆዳ ውጤቶችና የእደ ጥበብ ውጤቶች የሚያስተዋውቅ 1 ዓለም አቀፍ ኤግዚቢሽን በማዘጋጀትና በዉጭ አገር በሚካሄዱ ኤግዚቢሽኖች ላኪ ኢንተርፕራይዞችን በማሳተፍ ልምድ እንዲያገኙ በማስቻል የገበያ ዕድላቸው እንዲሰፋ ማድረግ፣ የሴቶች ተሳትፎ 50% ማድረግ፡፡

## 2.7. የአንድ ማዕከል አገልግሎቶች ክትትልና ድጋፍ ሥራ

**ዓለማ፡** **የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ለአገልግሎቶች ከአንዱ ቢሮ ወደ ሌላ ቢሮ በመንከራተት የሥራ ጊዜያቸውን ከሚያባክኑ የልማታዊ መንግሥታችን ለተቋማቱ የሚያስፈልጉ ሕጋዊ የቅድመ ሥራና የድጋፍ ማዕቀፎች በአንድ ቢሮ በተደራጀ አኳኃን በፍጥነት እንዲያገኙ ለማስቻል ነው፡፡**

**ጥቅል ግብ፡** **ከፌዴራል እስከ አንድ ማዕከል ድረስ ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት የሚያስችሉ 4 መመሪያና ጋይድላይኖች በማዘጋጀት፣ የድጋፍ የአገልግሎቶች ማዕቀፎች እና የተደራጀ የአገልግሎት ፓኬጅ (Tool kit) ተዘጋጅቶ ሥልጠና በመስጠት፣ እንዲሁም ነባር 1037 ማዕከላትን በማጠናከር እና አዲስ 130 ማዕከላትን በማቋቋም የአገልግሎት አቅርቦት ሥርዓቱ 90 በመቶ ማድረስ፡፡**

**ግብና ዝርዝር ተግባራት፡**

**ግብ አንድ፡** በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች ጥራት ያላቸውና ቀልጣፋ እንዲሆኑ ለማስቻል የአንድ ማዕከል አገልግሎቶች ክትትልና ድጋፍ አሰጣጥ ጋይድላይን፣ የኢንተርፕራይዞች ተወዳዳሪነት ጋይድላይን፣ ዜጎች ወደ ተለያዩ ሀገራት ለስራ ፍለጋ ከሚሰደዱ በሀገራቸው በልዩ ልዩ የስራ መስኮች መሰማራት የሚያስችል

ጋይድላይን እና የኢንተርፕራይዞች ሕብረት መመስረቻ መመሪያ በአጠቃላይ 3 ጋይድላይኖች እና 1 መመሪያ ይዘጋጃሉ፡፡

**ተግባር 1፡** ለማኑዋሎቹ ዝግጅት የሚያገለግሉ ጠቃሚ መረጃዎችን፣ ዶክመንቶችንና ፅሁፎችን ማሰባሰብ፤

**ተግባር 2፡** 4 ረቂቅ ሠነድ ማዘጋጀትና ለባለድርሻ አካላት በማሰራጨት፣ የማጠናከሪያ ሀሳቦችን በማሰባሰብ ሠነዱን ማዳበርና ማፀደቅ፤

**ተግባር 3፡** የጸደቁ 3 ጋይድላይኖች እና 1 መመሪያ ለክልሎች ማሰራጨትና አፈፃፀማቸውን መከታተልና ድጋፍ መስጠት፡፡

**ግብ ሁለት፡ በተለያዩ ዘርፎች ለ1,718,832 አዲስ ሥራ ፈላጊ ዜጎች የሥራ ዕድል እንዲፈጠር በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች አስፈላጊው ድጋፍ መሰጠቱ ይረጋገጣል፡፡ ከተጠቃሚዎች ውስጥ 50% ሴቶች ይሆናሉ፡፡**

**ተግባር 1፡** የተሟላ ድጋፍ በመስጠት በአገልግሎት ዘርፍ ለ124,128 እና በንግድ ዘርፍ ለ37,688 በአጠቃላይ ለ161,816 ሥራ ፈላጊ ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩን መከታተልና መደገፍ፣

**ተግባር 2፡** ሥራ ፈላጊ ወጣቶችና ሴቶች የራሳቸውን ሥራ እንዲፈጥሩ በተለያዩ መድረኮች ቅስቀሳ በማካሄድ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ መሰራቱን በየሩብ ዓመቱ ማረጋገጥ፣

**ተግባር 3፡** በቀበሌ በጎጥና በሌሎችም አደረጃጀቶች በመጠቀም ቤት ለቤት በማሰስ ሁሉንም የሥራ ፈላጊዎች የመመዝገብ ንቅናቄ መፈጠሩን መረጃው በአንድ ማዕከል አገልግሎት በተገቢው መዝገብ መመዝገቡን እና የተሟላ መረጃ መያዙን በየሩብ ዓመቱ ማረጋገጥ፣

**ተግባር 4፡** ሥራ ፈላጊዎች ሊሰማሩባቸው በሚችሉት የሥራ መስኮች ላይ መግለጫ መሰጠቱንና በራሳቸው ምርጫ የሥራ መስካቸውን እንዲመርጡ መደረጉን በየሩብ ዓመቱ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

**ተግባር 5፡** የአደረጃጀት አማራጮችን በማቅረብ እንዲመርጡ የሚያግዝ መግለጫ በባለሙያ መሰጠቱንና /በግል፣ በንግድ ማህበር፣ በህብረት ስራ/ በሕጋዊ አደረጃጀት እና በግብር ከፋይነት መመዝገባቸውን በየሩብ ዓመቱ ማረጋገጥ፣

**ተግባር 6፡** በመረጡት የሥራ መስክ የአዋጭነት ጥናት (Business plan) አዘጋጅተው ወደ ሥራ እንዲገቡ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ጋር በመተባበር የንግድ ሥራ አመራር እና የክህሎት ክፍተት ሥልጠና ማግኘታቸውን በየሩብ ዓመቱ ማረጋገጥ፤

**ተግባር 7፡** ኢንተርፕራይዞቹ የማምረቻና የመሸጫ ቦታ፣ የቁጠባ አገልግሎትና የፋይናንስ ድጋፍ ማግኘታቸውን ማረጋገጥና በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ተመጣጣኝ እርምጃ መወሰዱን በዓመት 2 ጊዜ ማረጋገጥና ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 8፡** በነባርና በአዲስ ኢንተርፕራይዞች የተፈጠሩ የስራ እድሎች መረጃ ተለይቶ መያዙን ማረጋገጥ፣

**ተግባር 9፡** የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች በሁሉም የስራ ዘርፎች ለተሰማሩ 2 ሚሊዮን አንቀሳቃሾች የሚሰጠው አገልግሎት 90% የድጋፍ ማዕቀፎችን፣ የኢንተርፕራይዞችን ፍላጐትና የእድገት ደረጃ መሠረት ባደረገ መልኩ መሰጠቱን ማረጋገጥ። ከተጠቃሚዎች ውስጥ 50% ሴቶች መሆናቸውን ማረጋገጥ።

**ግብ ሦስት፡ ከዩኒቨርሲቲዎችና በደረጃ III እና IV ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ለተመረቁ 343,766 ሥራ ፈላጊዎች በተለያዩ የሥራ ዘርፎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ይሰጣል፤**

**ተግባር 1፡** 343,766 ሥራ ፈላጊ ምሩቃን የራሳቸውን ሥራ እንዲፈጥሩ በ1,146 መድረኮች ቅስቀሳ በማካሄድ፣ በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች በመመዝገብ፣ የሚፈልጉትን የሥራ መስክ እንዲመርጡ መደረጉን በየሩብ ዓመቱ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ማረጋገጥ፣

**ተግባር 2፡** ለሥራ ፈላጊ ምሩቃን የአደረጃጀት አማራጮችን /በግል፣ በንግድ ማህበር፣ በህብረት ስራ/ በማቅረብ እንዲመርጡ የሚያግዝ መግለጫ በባለሙያ መሰጠቱን እና በ147,819 ኢንተርፕራይዝ በሕጋዊ አደረጃጀት መደራጀታቸውን እንዲሁም በግብር ከፋይነት መመዝገባቸውን በየሩብ ዓመቱ ማረጋገጥ፣

**ተግባር 3፡** በመረጡት የሥራ መስክ የአዋጭነት ጥናት /Business plan/ አዘጋጅተው ወደ ሥራ እንዲገቡ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ጋር በመተባበር የንግድ ሥራ አመራር እና የክህሎት ክፍተት ሥልጠና 343,766 ሥራ ፈላጊ ምሩቃን መሰጠቱ ማረጋገጥ፣

**ተግባር 4፡** ለተደራጁት 147,819 ኢንተርፕራይዞች የማምረቻና የመሸጫ ቦታ፣ የቁጠባና ብድር አገልግሎት እና የገበያ ትስስር ድጋፍ ማግኘታቸውን በየሩብ ዓመቱ ማረጋገጥ።

**ግብ አራት፡ በመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው በኢንተርፕራይዝ ያልታቀፉ ባለሙያዎችና 485,259 የቀን ሠራተኞችን በኢንተርፕራይዞች በማቋቋም እንዲሸጋገሩ አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል። ከተጠቃሚዎች ውስጥ 50% ሴቶች ይሆናሉ።**

**ተግባር 1፡** በመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች እስካሁን የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸውን በኢንተርፕራይዝ ያልታቀፉ ሥራ ፈላጊ ባለሙያዎችና የቀን ሠራተኞች ሊሰማሩባቸው በሚችሉት መስኮች ላይ ቅስቀሳ በማካሄድ፣ በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች በመመዝገብ፣

የሚፈልጉትን የሥራ መስክ እንዲመርጡ መደረጉን በየሩብ ዓመቱ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ማረጋገጥ፣

**ተግባር 2፡** የአደረጃጀት አማራጮችን /በግል፣ በንግድ ማህበር፣ በህብረት ስራ/ በማቅረብ እንዲመርጡ የሚያግዝ መግለጫ በባለሙያ መሰጠቱንና በ166,214 ኢንተርፕራይዞች በሕጋዊ አደረጃጀት መደራጀታቸውን እና በግብር ከፋይነት መመዝገባቸውን በየሩብ ዓመቱ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ማረጋገጥ፣

**ተግባር 4፡** በመረጡት የሥራ መስክ የአዋጭነት ጥናት /Business plan/ አዘጋጅተው ወደ ሥራ እንዲገቡ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ጋር በመተባበር የንግድ ሥራ አመራር እና የክህሎት ክፍተት ሥልጠና ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፤

**ተግባር 5፡** ለተደራጁት 166,214 ኢንተርፕራይዞች የማምረቻና የመሸጫ ቦታ፣ የቁጠባና ብድር አገልግሎት እና የገበያ ትስስር ድጋፍ ማግኘታቸውን በየሩብ ዓመቱ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ማረጋገጥ፣

**ግብ አምስት፡ ለጥ/አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጡትን አገልግሎቶች ተደራሽ ከማድረግ አንፃር ነባር 1,037 የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ይጠናከራሉ።**

**ተግባር 1፡** በሁሉም የአንድ ማዕከል አገልግሎት ጣቢያዎች የሚመለከታቸው አካላት በሰው ኃይልና በመገልገያ መሣሪያ በተሟላ ሁኔታ መግባታቸውንና ባለሙያዎችም ሥልጠና ማግኘታቸውን ማረጋገጥና ግብረ መልስ መስጠት፤

**ተግባር 2፡** በሁሉም የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች የመንግስት ድጋፍ አቅርቦትን ለማስፈፀም የወጡ መመሪያዎችና ማኑዋሎች መሟላታቸውን ፈፃሚዎችም የተሟላ ግንዛቤ መጨበጣቸውን ማረጋገጥና ግብረ መልስ መስጠት፤

**ተግባር 3፡** በ1037 የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይዞች ልማትን በተመለከተ የተጠናከረ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት መዘርጋቱንና ጥቅም ላይ መዋሉን ማረጋገጥና ግብረ መልስ መስጠት እንዲሁም የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎችን አጠቃላይ መረጃ ማሰባሰብ፤

**ተግባር 4፡** አንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥ በተዘጋጀው ማንዋል መሠረት መሆኑን በየወሩ በከተማ ደረጃ፣ በየሶስት ወሩ በክልል ደረጃ እንዲገመገም ማድረግ፤ በየስድስት ወሩ በሀገር አቀፍ ደረጃ ወካይ ናሙና በመውሰድ አፈጻጸሙን መገምገምና ግብረ-መልስ መስጠት፤

**ተግባር 5፡** በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች 50 በመቶ የሴቶችን ተጠቃሚነት ያረጋገጡ እንዲሆኑ ክትትል ማድረግ።

**ግብ ስድስት፡ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጡትን አገልግሎቶች ተደራሽ ከማድረግ አንፃር አዲስ 130 የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች እንዲቋቋሙ ይደረጋል፡፡**

**ተግባር 1፡** የአንድ ማዕከል አገልግሎት ህንጻ ግንባታ በሁሉም ክልሎች ስታንዳርዱን በጠበቀ መልኩ ለማከናወን የተዘጋጀውን ዲዛይን በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እንዲፀድቅ በማድረግ ወደ ክልሎች ማውረድ፣

**ተግባር 2፡** ክልሎችም በተላከላቸው አዲስ ዲዛይን መሰረት ማዕከላቱን ለመገንባት ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ማፀደቃቸውንና የቦታ ርክክብ ቅድመ ሁኔታዎችን ማጠናቀቃቸውን ማረጋገጥ፣

**ተግባር 3፡** በጥናት ላይ ተመስርተው አዲስ 130 የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች መቋቋማቸውንና አገልግሎት መጀመራቸውን በማረጋገጥ በየሩብ ዓመቱ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤

**ግብ ሰባት፡ የማምረቻና መሸጫ ህንፃዎችን፣ ክላስተር ማዕከላትንና ሼዶችን የሚያስተዳድር ኢንተርፕራይዝ በየክልሉና ከተሞች እንዲደራጅ ይደረጋል፡፡**

**ተግባር 1፡** የማምረቻና መሸጫ ህንፃዎችን፣ ክላስተር ማዕከላትንና ሼዶችን የሚያስተዳድር ኢንተርፕራይዝ ለማደራጀት የሚያስችል ሠነድ በማዘጋጀት፣ የአፈጻጸም መመሪያ በማዘጋጀት ለክልሎች በማሰራጨት መመሪያውን መሠረት በማድረግ ኢንተርፕራይዞቹ መደራጀታቸውን ማረጋገጥ፣

**ተግባር 2፡** ነባር እና አዳዲስ የተጠናቀቁ ህንፃዎች፣ ክላስተር ማዕከላትና ሼዶች መረጃ በመሰብሰብ የማምረቻና መሸጫ ህንፃ፣ የክላስተር ማዕከልና ሼዶች ችግር ያለባቸውን ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በመለየት የቴክኖሎጂ፣ የጥሬ ዕቃና የጋራ መሣሪያዎች ትስስር ለማድረግ በሚያስችል መልኩ አገልግሎቱ በግልፅነትና በጥራት መሰጠቱን ማረጋገጥ፤

**ተግባር 3፡** ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ለሶስተኛ ወገን የተላለፉ ክላስተር ማዕከላትና ሼዶችን በመለየት አገልግሎቱን ማግኘት ለሚገባቸው ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መተላለፉን ማረጋገጥ፡፡

**ግብ ስምንት፡ በአገልግሎት 5 እና በንግድ 2 ሞዴል ኢንተርፕራይዞች ከአመለካከት፣ ከምርታማነት፣ ከምርት ጥራትና ከካፒታል እድገት ጋር የተያያዘ በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት የተሻለ ተሞክሮዎችን በመቀመር እንዲሰፋ ይደረጋል፣**

**ተግባር 1፡** በአገልግሎትና በንግድ የስራ ዘርፎች አስቀድሞ በተለዩ መመዘኛዎች መሰረት 7 ሞዴሎችን በመምረጥ መቀመር፤

**ተግባር 2፡** የተቀመረው ተሞክሮ ለሌሎች በተመሳሳይ ዘርፍ ለተሰማሩ 161,816 ኢንተርፕራይዞች ማስፋት፣

**ተግባር 3፡** ክልሎች የማስፋት ስራውን እየፈጸሙ መሆናቸውን መከታተል፣ መደገፍና ግብረ-መልስ መስጠት፡፡

**ግብ ዘጠኝ፡ በ2004 በጀት ዓመት ከተቀመሩ 19 የፀደቁትና በ2005 በጀት ዓመት የሚቀመሩ አዲስ 43 በድምሩ የ62 ሞዴል ኢንተርፕራይዞች የተሻሉ ተሞክሮዎች እንዲሰፉ ይደረጋል፤ ክልሎችም በየደረጃው የተሻለ ተሞክሮን የመቀመር፣ የማስፋፋትና ውጤቱንም የመገምገም ተግባር እንዲያከናውኑ ክትትልና ድጋፍ ይደርጋል፡፡**

**ተግባር 1፡** በ2004 የተቀመሩትን 19 እና በ2005 የሚቀመሩትን 43 በድምሩ 62 የተሻሉ ተሞክሮ ሰነዶችን መረከብና በመመሪያው መሰረት በማዘጋጀት እንዲዳብር ማድረግ፣

**ተግባር 2፡** የተሞክሮ ማስተላለፊያ ዘዴዎችን በመምረጥ የተሻሉ ተሞክሮዎችን በሁሉም ከተሞች ለሌሎች በተመሳሳይ ዘርፍ ለተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች እንዲሰፉ ማድረግ፤

**ተግባር 3፡** ክልሎች የምርጥ ተሞክሮ ቀመራና የማስፋት ስራውን እየፈጸሙ መሆናቸውን በየሩብ ዓመቱ በመከታተል መደገፍና ግብረ-መልስ መስጠት፡፡

**ግብ አሥር፡ ከትግራይና ከአዲስ አበባ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ድጋፍ አሰጣጥና የሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ 2 የተቀመሩ የተሻሉ ተሞክሮዎች ለሌሎች ክልሎች ይሰራጫሉ፡፡**

**ተግባር 1፡** የተቀመሩትን 2 የተሻሉ ተሞክሮ ሰነዶችን መረከብና በመመሪያው መሰረት መዘጋጀቱን ማረጋገጥ፤

**ተግባር 2፡** ከየክልሉና ከተማ አስተዳደሮች ለተመረጡ የሚመለከታቸው ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የተቀመሩ የተሻሉ ተሞክሮዎችን ማስገንዘብና ክልሎች እርስ በርስ የሚማማሩበት አንድ መድረክ መፍጠር፤

**ተግባር 3፡** የተሞክሮ ማስተላለፊያ ዘዴዎችን በመምረጥ የተሻሉ ተሞክሮዎችን በሁሉም ዞኖች/ ወረዳዎችና ከተሞች እንዲሰፉ ማድረግ፤

**ተግባር 4፡** ክልሎች የተሻለ ተሞክሮ የማስፋት ስራውን እየፈጸሙ መሆናቸውን በየሩብ ዓመቱ በመከታተል፣ መደገፍና ግብረ-መልስ መስጠት፡፡

**ተግባር 5፡** በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉለሌ ክፍለ ከተማ ከሚገኙ 10 የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ የተሻለውን ማዕከል በመለየት የአንዱ ተሞክሮ መቀመርና እንዲሰፋ ማድረግ፣

**ግብ አሥራ አንድ፡ በበጀት ዓመቱ ካሉት ነባርና አዲስ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መካከል 1.5% (35,945) ወደ ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዝነት እንዲሸጋገሩ ይደረጋል፡፡**

**ተግባር 1፡** የኢንተርፕራይዞችን የእድገት ደረጃ መሰረት ያደረገ የድጋፍ አሰጣጥ መመሪያ ማዘጋጀትና መተግበሩን በክትትል ማረጋገጥ፤

**ተግባር 2፡** ከነባር እና ከአዲስ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መካከል 1.5% (35,945) ወደ ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዝነት የሚሸጋገሩትን መለየት፣

**ተግባር 3፡** ለተለዩት ኢንተርፕራይዞች ከዕድገት ደረጃቸው አንፃር የሚፈልጉትን የድጋፍ ዓይነቶችን በመለየት ድጋፉን የሚሰጡ አካላትን ማቀናጀትና ደረጃውን የጠበቀ ድጋፍ መስጠቱን በየሩብ ዓመቱ ማረጋገጥ፤

**ተግባር 4፡** ከየክልሉ ወደ ታዳጊ መካከለኛ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች በመመሪያው መሠረት በማረጋገጥ በሀገር አቀፍ ደረጃ ዕውቅና እንዲሰጣቸው ማድረግ፤

**ግብ አሥራ ሁለት፡ በንግድና በአገልግሎት ዘርፍ ላይ የተሰማሩትን 161,816 ኢንተርፕራይዞች ዝርዝር ሁኔታ በማጥናት የዕድገት ደረጃን ታሳቢ ያደረጉ ድጋፍ የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸትና በሂደትም 5% (8,090) ከአገልግሎት ዘርፍ ወደ አምራች ኢንዱስትሪ እንዲሸጋገሩ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡ ከተጠቃሚዎች ውስጥ 50% ሴቶች ይሆናሉ፡፡**

**ተግባር 1፡** በንግድና አገልግሎት ዘርፍ የሚገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማትና ተወዳዳሪነት እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን በጥናት በመለየት እንቅፋቶች ሊወገዱ የሚችሉበትን አማራጭ መፍትሄዎች ለይቶ በመተግበር አፈፃጸማቸውን መከታተልና ድጋፍ ማድረግ፤

**ተግባር 2፡** በንግድና በአገልግሎት ዘርፍ ላይ ከተሰማሩት ኢንተርፕራይዞች ውስጥ 5% (8,090) ከአገልግሎት ዘርፍ ወደ አምራች ኢንዱስትሪ እንዲሸጋገሩ መለየትና አስፈላጊውን ድጋፍ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣

**ተግባር 3፡** ኢ-መደበኛ (Informal) የንግድ አሰራር ስርዓት የሚከተሉትን ኢንተርፕራይዞች በመለየት ከኢ-መደበኛ ወደ መደበኛ የንግድ አሰራር ስርዓት እንዲመጡ ለማድረግ ስለንግድ ስራ ፈቃድና ምዝገባ ጥቅም በተለያዩ ሚዲያዎች ግንዛቤ ማስጨበጥና በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ህጋዊ ሰውነት በማግኘት ሕጋዊ ሆነው መንቀሳቀሳቸውን ማረጋገጥ፤

**ተግባር 4፡** የሚሰጠው ድጋፍ 50 በመቶ የሴት ኢንተርፕርነሮችን ፍላጐትና የእድገት ደረጃ ታሳቢ ያደረገ እንዲሆን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፡፡

**ግብ አሥራ ሦስት፡** **በበጀት ዓመቱ ወደ ሥራ ለሚገቡ ለአዲስ 812,000 እና ለነባር 128,000 አንቀሳቃሾች የብር 3.63 ቢሊዮን የብድር አገልግሎት እንዲመቻች ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል:: ከተጠቃሚዎች ውስጥ 50% ሴቶች ይሆናሉ።**

**ተግባር 1፡** ለነባር 128,000 እና ለአዲስ 812,000 አንቀሳቃሾች የብር 3.63 ቢሊዮን የብድር አገልግሎት እንዲመቻች በየሩብ ዓመቱ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ማረጋገጥ፣

**ተግባር 2፡** አገር አቀፍ ንቅናቄ በማካሄድ በበጀት ዓመቱ ብር 2.54 ቢሊዮን በአንቀሳቃሾች፣ በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲቆጠብ በየሩብ ዓመቱ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ማረጋገጥ፣

**ተግባር 3፡** በበጀት ዓመቱ የተሰራጨውን ብድር ሙሉ በሙሉ (100%) ተመላሽ እንዲሆን በየሩብ ዓመቱ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ማረጋገጥ፣

**ተግባር 4፡** ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር በጋራ የጀመረውን የመሣሪያዎች ሊዝ ጥናት አጠናቆ በሁሉም ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የመሣሪያዎች ሊዝ ሥርዓት ሥራ ላይ እንዲውል በየሩብ ዓመቱ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ማረጋገጥ፣

**ተግባር 5፡** ክልሎች የብድር ዋስትና ፈንድ ማቋቋማቸውን እና መተግበራቸውን በየሩብ ዓመቱ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ማረጋገጥ።

## 2.8. የዘርፉ ዕቅድና የመረጃ ልማት ሥራ

**ዓላማ፡** **በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ሴክተር በአስፈጻሚው ያለው አቅም፣ የሥራ ዕድል ፈጠራ ዓይነታቸውና የመነሻ መረጃቸው (Base-line) የሚሰጡ ድጋፎችና የመነሻ መረጃቸው (Base-line) በመረጃ መረብ በማደራጀት በእያንዳንዱ ሊደረስበት የታሰበው ዕቅድ (Benchmark) በማዘጋጀት አፈጻጸሙን በተከታታይ በመተንተን ለፖሊሲ አውጪዎች ከውሳኔ ሃሳብ ጋር አቅርቦ የሴክተሩ ልማት እንዲፋጠን ለማገዝ ነው።**

**ግብ፡** **5 ሃብት ማፈላለጊያ ፕጀክቶችን በመቅረጽና በመተግበር የሴክተሩን ማስፈጸም አቅም በመገንባት፤ መረጃዎችን በወረዳ መረብ (woreda net) ማደራጀት፣ የመነሻ መረጃ (Base-line) ማሰባሰብ፣ መቀመር እና ማሰራጨት የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት በመዘርጋት የጠራ ዕቅድ በማዘጋጀት ይተገበራል።**

**ዝርዝር ተግባራት**

**ተግባር 1፡** የነባር ፕሮጀክቶች (WED Project, LED Project, Project of Bamboo Housing, and Project of Bamboo Charcoal) አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ በማካሄድ ግብረ-መልስ መስጠት፤

**ተግባር 2፡** የዘርፉን ልማት ለመደገፍ የሚረዱ 5 የሃብት ማፈላለጊያ ፕሮጀክቶች[2] ማዘጋጀት/ ማጸበር፤

**ተግባር 3፡** ከክልሎች ጋር የዘርፉን ልማት የሚያፋጥን ቀልጣፋ የአሰራርና የአገልግሎት አሰጣጥ እንዲኖር የሚያስችል የመረጃ ልውውጥ ስርዓት መዘርጋት፣

**ተግባር 4፡** በዘርፉ ልማት ላይ ያተኮሩ መረጃዎች (የሥራ ፈላጊ፣ የሥራ ዕድል ፈጠራ፣ የብድር አቅርቦት፣ የቁጠባ፣ የብድር አመላለስ፣ የገበያ ትስስር፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት፣ የማምረቻና መሸጫ ቦታ፣ የቴክኖሎጂ/ፕሮቶታይፕ፣ የኤንደስትሪ ኤክስቴሽን፣ የሥልጠናና ሊሎች ድጋፎች) በተቀናጀ የዳታቤዝ ሲስተም ማስተዳደር፣

**ተግባር 5፡** የመረጃ አሰባሰቡ ደረጃውን የጠበቀና በአገር አቀፍ ደረጃ ተመሳሳይ (standardized) እንዲሆን በማድረግ፤ ለፖሊሲ ውሳኔ ሊጠቅሙ የሚችሉ በዘርፉ ልማት ላይ ያተኮሩ መረጃዎችን ማሰባሰብ፣ መቀናበር እና ማሰራጨት፣

**ተግባር 6፡** የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት አገር አቀፍ ጉባኤ ሁለት ጊዜ ማካሄድ፣

**ተግባር 7፡** ለ54 ክልሎችና ለአስፈጻሚ አካላት በመረጃ፣ በዕቅድ እና በአፈጻጸም ሪፖርት ዝግጅት ዙሪያ ስልጠና አንድ ጊዜ መስጠት፣

**ተግባር 8፡** ወቅቱን የጠበቀ የጠራ ዕቅድ በማዘጋጀትና የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ በማካሄድ ግብረ-መልስ መስጠት፡፡

## 2.9. የቴክኖሎጂ ምርት ማሻሻያና ማበልፀጊያ ልማት ሥራ

**ዓላማ፡** **በተለያዩ የቴክኖሎጂ ፈጠራና አሰባሰቢ አካላት የተሰባሰቡ ቴክኖሎጂዎች ወደ ኢኮኖሚው ከማስገባት አንጻር ያለው መስተጓጎል (Procrastination) በማስቀረት ቴክኖሎጂዎችን በአጣዳፊነት (Sense of urgency) ወደ ምርታ በስፋት ማስገባት ነው፡፡**

**ግብ፡** **ከ81 የማያንሱ ቴክኖሎጂዎች ዲዛይናቸውና ፕሮቶታይፓቸው ተሠርቶ ወደ ገበያ እንዲገቡ ይደረጋል፡፡ ለቀርካሃ፣ ለልብስ ስፌት፣ ቆዳ ጫማ፣ የጫጩት መፈልፈያ፣ ለአትክልት ልማት ቤት (Green House) ቅድሚያ ይሰጣል፡፡**

**ዝርዝር ተግባራት**

**ተግባር 1፡** 8 የማምረቻ መሣሪያዎች (በሽክላ ፤በሽመና በቀርክሃ፤ በእንጨት) በኩረጃ መስራት፤

**ተግባር 2፡** ኃላቀር የነበሩ ስድስት የማምረቻ መሣሪያዎችን አሻሽሎ መስራት፤

**ተግባር 3፡** በማዕከል ባሉት10 የሥራ ክፍሎች ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ ለተሸጋገሩት15 እና ለ10 ሞዴል ኢንተርፕራይዞች የቴክኒክ አገልግሎት መስጠት፤

---

[2] (Establishment of Data Exchange Project between FeMSEDA and ReMSEDAs, Project of ToT for MSE Agencies Employees on Entrepreneurship and BDS,A Project collaboration with TICA, Project Proposal for Strengthening Common Facility Centers in Selected Towns, and Establishment of Technology Development Center Project)

ተግባር 4፡ በበጀት ዓመቱ በ7 የሥራ ክፍሎች/ቀርክሃ፣ ሽመና ሥጋጃ፣ጋርመንት፣ጌጣጌጥ፣ ጨርቃ ጨርቅ ማቅለም ህትመትና ሽክላ /73 የምርት ናሙናዎች ሰርቶ ማውጣት፤

ተግባር 5፡ በኤጀንሲው ባሉ 7 የሥራ ክፍሎች የካይዘን ፕሮግራም ትግበራ ማካሄድ፣

ተግባር 6፡ የተፈጥሮ ቅጠል ቀለም /Natural dye staff/ ላይ አንድ ጥናት ማካሄድ፤

ተግባር 7፡ በልብስ ስፌት መሣሪያዎች ጥገና በልብስ ፓተርን ዲዛይን በጨርቃ ጨርቅ ማቅለም ህትመት በጌጣጌጥ በሽመና በቀርክሃ በሸክላ በተሰሩ ፕሮቶታይፕና ከእያንዳንዱ ሙያ ዘርፍ 6 ለቴ/ሙ/ሥ/ኮ መምህራን በ4 ዙር የተግባር ስልጠና መስጠት፡፡

## 3. የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ሥራዎች

**ጥቅል ዓላማ፡** በከተሞች የማስፋፊያ አካባቢዎችና የደቀቁ እና ከደረጃ በታች አገልግሎት ላይ የዋሉ አካባቢዎች ፍትሐዊ የልማት ተነሺ መስተንግዶ ሥርዓት በመዘርጋት፣ የመሰረተ ልማት አቅርቦት ቅንጅት በመፍጠር እና በመዘርጋት፣ የተዘጋጀዉን መሬት በመረጃ ባንክ ገቢ በማድረግ እንዲሁም ለዝግጅት የወጣዉን ወጪ በማስመለስ ቀጣይነት ያለው በቂ የመሬት አቅርቦት እንዲኖር በማድረግ የከተማ ልማትን ማፋጠን እንዲሁም የመሬትና መሬት ነክ የንብረት ባለቤትነት በዘመናዊ መረጃ በማደራጀት ዋስትናውን ለማረጋገጥ ነው፡፡

**ጥቅል ግብ፡** በሀገራችን የከተሞች ልማትና ማኔጅመንት ሥራ ተቋማዊ በሆነ መንገድ በመምራት አደረጃጀቱ ወጥ ሆኖ፣ መሠረታዊ አሠራሮች ተዘርግተው፣ በዘርፉ የሰው ኃይል ሙያ ተሰጥቶ እና ስልጠና ጀምሮ በዓመቱ መጨረሻ ላይ ለተፋጠነ የከተማ ልማት የመሬት አቅርቦት ሥርዓትን ግልጸኝነት ለማላበስ የመሬት አጠቃቀም ፕላንን ሥርዓት ለማስያዝ የዘመናዊ የመሬት መረጃ ሥርዓት አዲስ አበባ ላይ የጀመረው ትግበራ በክልሎች ለማስፋፋት ቅድመ ሁኔታዎች እንዲጠናቀቁ ይደረጋል፡፡

### 3.1. የከተሞች የመሬት አጠቃቀም ፕላን ሥራዎች

#### 3.1.1. የከተሞች ፕላን አፈጻጸም ክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስ ሥራ

**ዓላማ፡** ከተሞች የመሬት አጠቃቀማቸውን እንዲያከብሩና የሚያፋልሱ ሲኖሩ የሚጠየቁበት ሥርዓት መፍጠር ነው፡፡

**ጥቅል ግብ፡** በ618 ከተሞች የፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም አቅም ለማሳደግ 7 የተለያዩ የሕግ ማዕቀፎችን እና የአሠራር ማኑዋሎችን በማዘጋጀት፣ ለ220 የግል የከተማ ፕላን አማካሪ ድርጅቶች እና 86 የካርታና ቅየሳ አሃዶችን እንዲደራጁ በማድረግ አፈጻጸማቸው ላይ ክትትልና ግምገማ በማካሄድ ግብረ-መልስ ይሰጣል፡፡

**ዝርዝር ግቦችና ተግባራት**

**ግብ አንድ፡** **በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ የከተማ ፕላን ተቋማት እና ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸምን በተሟላ መልኩ ለማከናወን የሚያስችላቸውን አቅም ለማጎልበት 9 የተለያዩ የሕግ ማዕቀፎች እና የአሠራር ማኑዋሎች ይዘጋጃሉ፤ ትግበራቸውም ላይ ክትትልና ግምገማ በማካሄድ ግብረ-መልስ ይሰጣል፡፡**

**ተግባር 1፡** የከተማ ፕላን ዝግጅት ሥራዎች በተሟሉ የህግ ማዕቀፍ እና ማኑዋሎች መሠረት እንዲከናወን የተለያዩ 7 የጥናት ሰነዶች[3] ማዘጋጀትና በሥራ ላይ ስለመዋላቸው ክትትል በማድረግ የጽሁፍ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 2፡** የሃገር አቀፍ የልማት ቀጠና እና የልማት ማዕከላትን ታሳቢ ያደረገ የከተማ ልማት ስኪም (National Urban Development Scheme) እና የአዲስ አበባ ከተማን ተወዳዳሪ ሆኖ ማስቀጠል የሚያስችል ጥናት እንዲዘጋጅ ማድረግ እና ወደ ተግባር ማስገባት፤

**ተግባር 3፡** በ7 ከተሞች የማስፋፊያ አካባቢ ልማት ፕላን እና የከተማ ዲዛይን ፕላን ማዘጋጀት፣ ለዚህም የሚረዳ የከተማ ዲዛይን ማኑዋል ማዘጋጀት እና ተግባራዊነቱን ክትትል ማድረግ፡፡

**ግብ ሁለት፡** **በክልሎችና ከተሞች ለሚገኙ የከተማ ፕላን ተቋማት እና 220 የግል የከተማ ፕላን አማካሪ ድርጅቶች ድጋፍና ክትትል በማድረግ እና አቅም በመገንባት የከተሞችና የግሉ ዘርፍ የፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም አቅም ይጎለብታል፡፡**

**ተግባር 1፡** የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈፃፀም በከተማ ፕላን አዋጅ፣ ስትራቴጂ፣ ማኑዋል እና ስታንዳርድ መሠረት ስለመሆኑ አዲስ በሚዘጋጁ የ150 የአነስተኛ ከተሞች ፕላን እና ከዚህ በፊት በተዘጋጀላቸው 468 አነስተኛ ከተሞች ፕላን አፈጻጸም ላይ የክትትልና የግምገማ በማካሄድ የጽሑፍ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 2፡** በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ ደረጃ የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም እንዲሁም 86 የካርታና የቅየሳ አሀዶች (Units) እንደየከተሞቹ የዕድገት ደረጃ ተቋማዊ አደረጃጀት መፍጠሩን፣ ለአደረጃጀቱም ሰነድ መዘጋጀቱን በየሩብ ዓመቱ የጋራ መድረኮችና የክትትል ሥራዎችን በማከናወን የአፈጻጸም ምልከታ ማካሄድ እና የጽሑፍ ግብረ-መልስ መስጠት፤

**ተግባር 3፡** ለፕላን ዝግጅት ግብዓት እንዲሆን የ80 ከተሞች መሠረታዊ መረጃዎችን (Urban Profile) በማሰባሰብና በማደራጀት በድረ-ገጽ እንዲለቀቅ ማድረግ፣

[3] 7ቱ የጥናት ሠነዶች፡- የከተማ ፕላን አዋጅ ክለሳ፣ የከተማ ፕላን ሞዴል ደንብ ክለሳ፣ የመሬት አጠቃቀም ለውጥና የመሬት አጠቃቀም ጥሰት ሞዴል መመሪያ ማዘጋጀት፣ የከተማ ፕላን የተሳትፎ ማንዋል (Participation Manual) ክለሳ፣ እያቆጠቆጡ ላሉ የገጠር ቀበሌ ማዕከላት የፕላን አዘገጃጀት ማንዋል ማዘጋጀት፣ የከተሞች ድንበር አከላለልና አወሳሰን ጋር በተያያዘ ማንዋል ማዘጋጀት እና የከተማ ፕላን የስትራቴጂክ አካባቢ ግምገማ ጋይድ ላይን ማዘጋጀት ናቸው፡፡

ተግባር 4፡ 220 የግል የከተማ ፕላን ዝግጅት አማካሪ ድርጅቶችን አቅም በመገንባት ወደ መስኩ እንዲገቡ ማድረግ፣

ተግባር 5፡ በ9 ክልሎችና በ2ቱ ከተማ አስተዳደሮች የከተማ ፕላን ዝግጅት ተቋማት የፕላን ጥራት ቁጥጥር ሥርዓት ስለመኖሩ እንዲሁም ወጥ የሆነ የመረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀትና ልውውጥ ስርዓት ስለመዘርጋቱ በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት የመስክ ኢንስፔክሽን በማካሄድ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ እና የጽሑፍ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ግብ ሦስት፡ በክልሎችና በከተሞች በሚዘጋጁ 150 መሰረታዊ ካርታና ፕላን፣ 24 መዋቅራዊና 62 አካባቢ ልማት ፕላኖች እንዲሁም በከተሞች ለሚቋቋሙ 10 የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች፣ 10 ዩኒቨርስቲዎች እና 11 የማዳበሪያ ፕሮጀከቶች የመዋቅራዊና አካባቢ ልማት ፕላኖች ላይ በየሩብ ዓመቱ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ ይሰጣል፡፡**

ተግባር 1፡ የመሠረታዊ ካርታ ለሚዘጋጅላቸው 150 አነስተኛ ከተሞች አስፈላጊውን ድጋፍ፣ ክትትልና ግምገማ በየሩብ ዓመቱ በማካሄድ የጽሁፍ ግብረ-መልስ መስጠት፣

ተግባር 2፡ የመሠረታዊ ፕላን ለሚዘጋጅላቸው 150 አነስተኛ ከተሞች በየሩብ ዓመቱ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የጽሁፍ ግብረ-መልስ መስጠት፣

ተግባር 3፡ በ24 ከተሞች በሚዘጋጁ መዋቅራዊ ፕላኖች ላይ በየሩብ ዓመቱ ክትትል በማድረግ የጽሁፍ ግብረ-መልስ መስጠት፣

ተግባር 4፡ በከተሞች በሚዘጋጁ 62 የአካባቢ ልማት ፕላኖች ላይ በየሩብ ዓመቱ ክትትል በማድረግ የጽሁፍ ግብረ-መልስ መስጠት፣ ከእነዚህ ውስጥ ለ15ቱ የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ፣

ተግባር 5፡ 10 የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች፣ 10 ዩኒቨርስቲዎች እና 11 የማዳበሪያ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ በሚሆኑባቸው ከተሞች በሚዘጋጁ መዋቅራዊና የአካባቢ ልማት ፕላኖች ላይ በየሩብ ዓመቱ ክትትል በማድረግ የጽሁፍ ግብረ-መልስ መስጠት፡፡

### 3.1.2. የከተማ መሬት አጠቃቀም ፕላን ሥልጠና ሥራ

**ዓላማ፡ የመሬት አጠቃቀም ፕላን ዝግጅት ክህሎት ለማዳበር እና የፕላን ዝግጅትን ስታንዳርድ ለማስጠበቅ የሚያስችል ስልጠና በመስጠት በሀገራችን ተቀራራቢ የከተሞች የመሬት አጠቀቀም ሥርዓት እንዲዘረጋ ለማስቻል ነው፡፡**

**ግብ፡ በከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም ዙሪያ በተለያዩ መስኮች በዘርፉ ለተሠማሩ አስፈጻሚ አካላት ለ220 የከተማ ፕላን አማካሪ ድርጅቶች፣ 564 ከንቲባዎች፣ ሥራ አስኪያጆችና ባለሙያዎች እንዲሁም 552 ባለሙዎች በልዩ ልዩ ርዕሰ ጉዳዮች ሥልጠና በመስጠት የሙያ ብቃታቸው ያድጋል፡፡**

**ዝርዝር ተግባራት**

ተግባር 1፡ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በፓይለት ደረጃ የመሬት ላይ የቅየሳ ዘዴን በመጠቀም ከከተማው ለተውጣጡ 150 የቅየሳ ባለሙያዎችን በአማካሪነት /በአሃድ/ በ50 ቡድኖች እንዲደራጁ ማድረግና ስልጠና ተሠጥቷቸው የሙያ ብቃታቸው በሚመጥኑት ደረጃ ሰርቲፋይድ ማድረግ፡፡

ተግባር 2፡ 220 የግል የከተማ ፕላን ዝግጅት አማካሪ ድርጅቶች ወደ መስኩ እንዲገቡ ሥልጠና መስጠት፣

ተግባር 3፡ በፕላን ዝግጅት እየተሳተፉ ከሚገኙ 15 የግል አማካሪ ድርጅቶች በፕላን ዝግጅት ጋር በተያያዘ የልምድ ልውውጥ ማካሄድ፣

ተግባር 3፡ በ24 ከተሞች አመራሮች ኀላኖችን በአግባቡ ተገንዝበው የተቀናጀ መሠረተ-ልማት ለማቅረብ የሚያስችል እንዲሁም የከተሞቹ እድገትና የልማት ቅደም ተከተልን መሠረት አድርገው ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ለማስቻል ከየከተሞቹ ለተውጣጡ 120 አስፈጻሚዎች ሥልጠና መስጠት፣ ዕቅድ ዝግጅቱ ላይ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

ተግባር 4፡ ለ564 ከተማ ከንቲባዎች፣ ሥራ አስኪያጆችና ባለሙያዎች ስለከተማ ፕላን አዘገጃጀትና አተገባበር የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፣ በተለይ ባለሙያዎቹ የሙያ ምዘና ተካሄዶላቸው ሠርቲፋይድ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡

ተግባር 5፡ በክልሎች በሚዘጋጁ የከተማ ፕላን ዝግጅቶች ላይ በመሳተፍ 6 የመስክ የሥራ ላይ ሥልጠና ማካሄድ፣

ተግባር 6፡ በመንግስት የፕላን ዝግጅት ተቋማት ለሚሠሩ 552 ባለሙዎች በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚ፣ ፊዚካል፣ ስፓሻል እና ጂ.አይ.ኤስ ሙያ ዘርፍ ስልጠና መስጠት፡፡

## 3.2. የመሬት ልማትና አስተዳደር ሥራዎች

**ዓላማ፡** **በከተሞች የመሬት ልማትና አስተዳደር ሥራዎች የዓለም ዓቀፍ ሥርዓት የተከተለና ለፈጠነ ልማታችን አጋዥ በሆነ መንገድ መምራት የሚያስችል ተቋማዊ አቅም መፍጠር ነው፡፡**

**ጥቅል ግብ፡** **የከተሞችን የመሬት አቅርቦት፣ ግብይት እና አስተዳደር ሥርዓት በማሻሻል ከተሞቻችን በልማት እና መልካም አስተዳደር እንዲጎለብቱ ይደረጋል፡፡**

### 3.2.1. የመሬት ልማትና ከተማ ማደስ ሥራ

**ዓላማ፡** **በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ መሠረት የከተሞች መስፋፍያ፣ መልሶ ማደስ ወይም የከተሞቹ ማሻሻል በሥርዓትና የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት በሚያረጋገጥና የፈጣን ልማታችን ሂደት በሚያግዝ መልኩ እንዲደገፍ ማድረግ ነው፡፡**

**ጥቅል ግብ:** በመሬት ልማት እና ከተማ ማደስ ዙሪያ 3 የአሠራር ማኑዋል በማዘጋጀት እና 2 ጥናቶችን በማካሄድ፣ ከሁሉም ክልሎች፣ ከአዲስ አበባ ከተማ እና ከድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ለተውጣጡ 2000 አመራሮችና ፈጻሚዎች ሥልጠና በመስጠት፣ እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ በተመረጠ ክፍለ ከተማ ላይ በተግባር በመፈተሽ ተሞክሮ እንዲቀመር ይደረጋል፡፡

**ዝርዝር ግቦችና ተግባራት**

**ግብ አንድ:** በሁሉም ክልሎች፣ በአዲስ አበባ ከተማ እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ቀጣይነት ያለዉ የመሬት ዝግጅት እና መልሶ ማልማት እንዲኖር የሚያስችሉ 3 የአሠራር ማኑዋል በማዘጋጀት እና አንድ ጥናት በማካሄድ፣ 2,000 ፈጻሚዎችና አመራሮችን በማሰልጠን የመሬት አቅርቦት ሥርዓት ወጥ እና ተቋማዊ ይዘት እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

**ተግባር 1:** የመሬት ዝግጅት እና የመሬት ባንክ የአሰራር እና አደረጃጀት ማኑዋል በማዘጋጀት ለሁሉም ክልሎች፣ ለአዲስ አበባ ከተማ እና ለድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች በማሰራጨት ተግባራዊነቱ ላይ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 2:** የመሬት ዝግጅት የፋይናንስ አቅርቦት ሥርዓት ጥናት በውጭ አማካሪ እንዲከናወን በማድረግ እና ወደ ተግባር ለማስገባት የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት፣

**ተግባር 3:** የመሬት ባንክ በሁሉም ከተሞች ላይ መደራጀቱን ለማረጋገጥ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መሰጠት፣

**ተግባር 4:** በመሬት ዝግጅት፣ በመሬት ባንክ እና በመልሶ ማልማት አሠራር ላይ ለክልል፣ ለአዲስ አበባ እና ለድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች 2000 አመራሮች እና ፈጻሚዎች ስልጠና መስጠት፣

**ግብ ሁለት:** በሁሉም ክልሎች እና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚዉል 8,651 ሄክታር መሬት በአዋጁ መሰረት ደረጃዉን ጠብቆ መዘጋጀቱ እና ወደ መሬት ባንክ መግባቱ በየሩብ ዓመቱ ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ ይረጋገጣል፡፡

**ተግባር 1:** በስታንዳርዱ መሠረት 8,651 ሄክታር መሬት ወደ መሬት ባንክ መግባቱን ማረጋገጥና አፈጻጸሙ ላይ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 2:** ወደ መሬት ባንክ የገባ መሬት የዝግጅት ደረጃውን መገምገም እና የአሰራር ክፍተት ካለ እንዲስተካከል ድጋፍ በማድረግ የጽሑፍ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 3:** በአዲስ አበባ፣ በድሬዳዋ እና በክልል ከተሞች ቀደም ሲል የተጀመሩ የመልሶ ማልማት ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም በመገምገም፣ በበጀት ዓመቱ እንዲጠናቀቁ ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ፡፡

**ግብ ሦስት፡ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች 30 አዲስ የኢንዱስትሪ ዞኖች ለመከለል እና ቀደም ሲል የተከለለውን 4,145.6 ሄክታር የኢንዱስትሪ ዞኖች እንዲጠናቀቁ እንዲሁም የተነሺ መስተንግዶ እንዲጠናቀቅ ተገቢው ክትትል እና ድጋፍ ይደረጋል፡፡**

ተግባር 1፡ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች 30 አዲስ የኢንዱስትሪ ዞኖች መከለሉንና መቀየሱን በመከታተል እና በመደገፍ ማረጋገጥ እና በአፈጻጸሙ ደረጃ ላይ የጽሑፍ ግብረ-መልስ መስጠት፣

ተግባር 2፡ የኢንዱስትሪ ዞን የተነሺ መስተንግዶ መጠናቀቁን በየሩብ ዓመቱ በመከታተል እና በመደገፍ ማረጋገጥና በአፈጻጸሙ ላይ የጽሑፍ ግብረ-መልስ መስጠት፣

ተገባር 3፡ ቀደም ሲል ለኢንዱስትሪ ዞን ልማት በአዲስ አበባ 425 ሄክታር መሬት፤ በትግራይ 873.6 ሄክታር በድሬዳዋ 1,050 ሄክታር መሬት በኦሮሚያ 1,191 ሄክታር መሬት፤ በአማራ 606 ሄክታር በድምሩ 4,145.6 ሄክታር መሬት ተከልሎ በሂደት ላይ የሚገኙትን የኢንዱስትሪ ዞኖች የአፈጻጸም ደረጃ በመገምገም እና በመደገፍ መጠናቀቁን ማረጋገጥ፡፡

**ግብ አራት፡ በአዲስ አበባ ከተማ በተመረጡ ክፍለ ከተሞች በመሬት ዝግጅት እና ባንክ ተቋም የተመደቡ ባለሙያዎችን የክህሎት ክፍተት በመፈተሽ፣ በ3 ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ለ100 ባለሙያዎች ስልጠና በመስጠት እና በተግባር በመደገፍ አቅም በመፍጠር ተሞክሮዉ እንዲቀመር ይደረጋል፡፡**

ተግባር 1፡ በአዲስ አበባ ከተማ በተመረጡ ክፍለ ከተሞች በመሬት ዝግጅት እና ባንክ ተቋም ለተመደቡ ባለሙያዎች በተለያዩ 3 ርዕሰ ጉዳዮች (የካሳ ግምት እና ልኬት፣ የመሬት ቅየሳ እና ሽንሽና እንዲሁም የተዘጋጀ መሬት ባንክ ምዝገባ እና አስተዳደር) ላይ የቲዮሪ እና የተግባር ስልጠና ለ100 ባለሙያዎች መስጠትና ሠርቲፋይ ማድረግ፣

ተግባር 2፡ በመሬት ዝግጅት እና ባንክ ተቋም የተመደቡ ባለሙያዎችን የተግባር አፈጻጸም ላይ ድጋፍ በማድረግ ሥራው በአግባቡ መከናወኑን በማረጋገጥ ምርጥ ተሞክሮውን መለየት፣

ተግባር 3፡ የተለየውን ተሞክሮ ለክልሎችና ከተሞች ለማስፋት እንዲቻል መቀመር፡፡

**ግብ አምስት፡ የዘመናዊ ኢንዱስትሪ ዞን ልማት ፕላን፤ ዲዛይን ዝግጅት እና አሰራር ማኑዋል ጥናት በማጠናቀቅ በአዲስ አበባ ከተማ በተመረጠ ክፍለ ከተማ ላይ ለተመደቡ 100 ባለሙያዎች ስልጠና በመስጠት እና በተግባር በመደገፍ ለቀጣይ ለክልሎችና ከተሞች ለማስፋት ተሞክሮ ይቀመራል፡፡**

ተግባር 1፡ ከኢንዱስትሪ ሚ/ር እና ሌሎች የሚመለከታቸዉ አካላት የኢንዱስትሪ ዞን ልማት ልምድ በመቅሰም ፕላኑን፤ ዲዛይኑን እና የአሰራር ማኑዋሉን በማጠናቀቅ ለ100 ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት፣

ተግባር 2፡ በአዲስ አበባ ከተማ በተመረጠ ክፍለ ከተማ በተመረጠ አንድ የኢንዱስትሪ ዞን ልማት ድጋፍ እና ክትትል በማድረግ አፈጻጸሙን ማረጋገጥና የጽሑፍ ግብረ-መልስ መስጠት፣

ተግባር 3፡ በአዲስ አበባ ከተማ በተመረጠ ክፍለ ከተማ የተለየውን ተሞክሮ መቀመር፡፡

**ግብ ስድስት፡ በአዲስ አበባ በተመረጠ ክፍለ ከተማ አንድ ዘመናዊ የገበያ ማዕከል ግንባታ ፕላን፤ ዲዛይን ዝግጅት እና አሰራር ሥርዓት ጥናት በማጠናቀቅ እና ለ100 ባለሙያዎች ስልጠና በመስጠት የመሬት ዝግጅቱን በተግባር በመደገፍ ለክልሎችና ከተሞች ለማስፋት ተሞክሮ ይቀመራል፡፡**

ተግባር 1፡ የከተማ ዘመናዊ የገበያ ማዕከል ግንባታ አሰራር ጥናት ሰነድ ማጠናቀቅ፣ የፕላኑ፣ የዲዛይኑ እና የአሰራር ማኑዋል ዝግጅት በማጠናቀቅ ለ100 ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት፣

ተግባር 2፡ በአዲስ አበባ ከተማ በተመረጠ ክፍለ ከተማ በሚገኙ አንድ የገበያ የማዕከል የመሬት ዝግጅት ፕሮጀክት ላይ ተገቢዉን ድጋፍ እና ክትትል በማድረግ የጽሑፍ ግብረ-መልስ መስጠት፣

ተግባር 3፡ ለክልሎችና ከተሞች ለማስፋት እንዲቻል ተሞክሮ በመለየት መቀመር፡፡

**ግብ ሰባት፡ በአዲስ አበባ፤ በኦሮሚያ እና በሐዋሳ ከተሞች በ3 ነባር የኢንዱስትሪ ዞኖች ዝግጅት እና አጠቃቀም ደረጃ ግምገማ ለማከናወን ስታንዳርድ በማዘጋጀት፣ በስታንዳርዱ መሠረት በመገምገም ዎርክሾፕ በማዘጋጀት ፈጻሚዎችና አመራሮች ግንዛቤ እንዲጨብጡ ይደረጋል፡፡**

ተግባር 1፡ የነባር ኢንዱስትሪ ዞን መገምገሚያ የስታንዳርድ ሰነድ ማዘጋጀት፣

ተግባር 2፡ በተዘጋጀው ስታንዳርድ መሠረት በ3ቱ ነባር የኢንዱስትሪ ዞኖች ላይ ግምገማ በማከናወን ዉጤቱን እና የማስተካከያ ውሳኔ ሀሳብ የሚያመላክት ሠነድ ማዘጋጀት፣

ተግባር 3፡ ወርክሾፕ በማዘጋጀት የማስተካከያ ግንዛቤ ማስጨበጥ እና ለሚመለከታቸው ከተሞች የጽሑፍ ግብረ-መልስ መስጠት፡፡

### 3.2.2. የመሬት ግብይት፣ አሰጣጥ እና የሊዝ አስተዳደር ሥራ

**ዓላማ፡ ለሁሉም አይነት አገልግሎቶች መሬት በበቂ መጠን በግልጸኝነት፣ ተጠያቂነት ባለውና ቀልጠፋ በሆነ አሠራር የሚቀርብበት ሥርዓት አስተማማኝ በሆነ መንገድ በመዘርጋት ፈጣን ልማታችን እንዲቀጥል ማድረግ ነው፡፡**

**ጥቅል ግብ፡** በከተሞች 8,651 ሄክታር መሬት ለተለያዩ አገልግሎቶች ግልጸኝነት በተላበሰ አሠራር እንዲቀርብ ለማድረግ የሊዝ አስተዳደርን ለማጠናከር የሚያስች የአሠራር ማኑዋል በማዘጋጀት አፈጻጸሙ ላይ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡

**ዝርዝር ግቦችና ተግባራት**

**ግብ አንድ፡** በከተሞች የመሬት ግብይት እና ይዞታ አስተዳደር ሥርዓትን ለማጠናከር የሚያስችሉ …… የአሠራር ማኑዋሎችን በማዘጋጀት፣ 3 ጥናቶችን በማካሄድ፣ 2 ሶፍትዌሮችን በመቅረጽ፣ በ450 ከተሞችን ወደሊዝ ሥርዓት እንዲገቡ በማድረግ 2,000 አመራሮችን እና ባለሙያዎችን በማሰልጠን ሥርዓቱ እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡

**ተግባር 1፡** በከተሞች የመሬት ጨረታ እና ግብይት ሥርዓቱ ግልፅ እና ቀልጣፋ ለማድረግ የሚያስችል የጨረታ ሶፍትዌር እና የመሬት ግብይት ዌብሳይት በማዘጋጀት ተግባራዊነቱ ላይ ተገቢውን ድጋፍና ክትትል በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 2፡** በክልሎች ወደሊዝ ያልገቡ 450 ከተሞች ወደሊዝ የሚገቡበትን መስፈርት በጥናት ማዘጋጀት እና በማሰራጨት ወደ ሊዝ ሥርዓት መግባታቸውን ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ ማረጋገጥ፣

**ተግባር 3፡** ወደሊዝ አዲስ ለሚገቡ 450 ከተሞች የሊዝ ጨረታ መነሻ ዋጋ ጥናት ዝግጅትን በመደገፍ እና በመከታተል መተግበሩን ማረጋገጥ፣

**ተግባር 4፡** የከተሞችን የሊዝ ዋጋ ለማረጋጋት አቅጣጫ ለማስቀመጥ የሚያስችል የሊዝ ዋጋ ኢንዴክስ በየስድስት ወሩ በማሳተም ለሚመለከታቸው እንዲሰራጭ ማድረግ፣

**ተግባር 5፡** የከተሞች የመሬት ኪራይ እና የቤት ግብር ትመና የሚያገለግል ጥናት በማከናወን ለክልሎችና ለከተሞች በማሰራጨት ተግባራዊነቱ ላይ በመደገፍ እና በመከታተል ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 6፡** በክልሎችና ከተሞች የጸደቀ የሊዝ ደንብ እና መመሪያ በማሰባሰብ እና ከሞዴል ሠነዶቹ ጋር ያላቸውን አንድነት እና ልዩነት እንዲሁም የተደረጉ ተገቢ ማስተካከያዎችን በመፈተሽ የጽሁፍ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 7፡** በመሬት ግብይት እና ይዞታ አስተዳደር …….. የአሰራር ማኑዋሎችን በማዘጋጀት ከክልሎችና ከተሞች ለተውጣጡ 2000 ፈጻሚዎች እና አመራሮች ስልጠና መስጠት፣

**ግብ ሁለት፡** በሁሉም ክልሎች እና በሁለቱ ከተሞች ለ618 ሺ አንቀሳቃሾች አገልግሎት የሚውል 6,429 ሄክታር ቦታ፤ በአዲስ አበባ እና በክልሎች በ40/60 ፕሮግራም ለሚገነቡ 10 ሺህ ቤቶች የሚዉል 16 ሄክታር መሬት፤ በከተሞች አነስተኛ ገቢ ላላቸዉ የህብረተስብ ክፍሎች የሚዉሉ 35 ሺህ ቤቶች ግንባታ የሚዉል 105 ሄክታር መሬት፤ በሁሉም

**ክልሎች እና በሁለት ከተሞች ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚዉሉ 2,101 ሄክታር በድምሩ 8,651 ሄክታር መሬት በአዋጁ መሠረት መተላለፉ ይረጋገጣል፡፡**

**ተግባር 1፡** አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ጨምሮ በሁሉም ክልሎች ወደ ሊዝ ለገቡ የ23 ናሙና ከተሞች የመሬት አሰጣጥ እና ግብይት የአሰራር ሥርዓት ላይ ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ በአፈጻጸሙ ላይ የጽሑፍ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 2፡** ወደሊዝ ያልገቡ የ15 ናሙና ከተሞች የመሬት አሰጣጥ አሰራር ክትትል እና ግምገማ ማድረግና በአፈጻጸሙ ላይ የጽሑፍ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 3፡** በክልሎችና ከተሞች የመሬት አሰጣጥ እና ግብይት የአሰራር ሂደት ላይ ግምገማ በማካሄድ የግምገማ ውጤቱን ግብረ-መልስ ጽሑፍ ለሁሉም ከተሞች እና ለሚመለከታቸው አካላት ማስተላለፍ፣

**ተግባር 4፡** በአዋጁ መሰረት 8,651 ሄክታር መሬት ለመንግስት የተለያዩ ልማቶች እና ለተለያዩ ተጠቃሚዎች እንዲተላለፍ ድጋፍ እና ክትትል በማድረግ ወቅታዊ የጽሑፍ ሪፖርት ማቅረብ፣

**ተግባር 5፡** በከተሞች ለተለያዩ አገልግሎቶች ከሚቀርበው 8,651 ሄክታር መሬት ውስጥ ለጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፐራይዞች 20%፣ ለመኖሪያ ቤትና ተያያዥነት ላላቸው /ለሪል እስቴት ...ወዘተ/፣ 45%፣ ለመሠረተ ልማት 25%፣ ለመዝናኛና ሌሎች አገልግሎቶች 10% መቅረቡን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ማረጋገጥ፡፡

**ግብ ሦስት፡ በክልሎች እና በከተሞች የሊዝ መብት ማስተላለፍ እና በዋስትና ማስያዝ የሚያስችል ሶፍትዌር በማዘጋጀት፣ በአዋጁ መሠረት ከኪራይ ሰብሳቢነት ድርጊት ነጻ ሆኖ መፈጸሙን በመከታተል ግብረ-መልስ በመስጠት በሊዝ የተመዘገበ ይዞታ መጠን 60 በመቶ መሆኑ ይረጋገጣል፡፡**

**ተግባር 1፡** የሊዝ መብት ማስተላለፍ እና የሊዝ ይዞታ መረጃ ለማደራጀት የሚያስችል ሶፍትዌር በማዘጋጀት ተግባራዊነቱ ላይ ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 2፡** ወደ ሊዝ ሥርዓት የገቡ ከተሞች የሊዝ መብት ማስተላለፍና በዋስትና ማስያዝ በአዋጁ መሰረት መፈጸሙን እና ከኪራይ ሰብሳቢነት ድርጊት ነጻ መሆኑን በመከታተል እና በመደገፍ በየሩብ ዓመቱ ግብረ-መልስ በጽሑፍ መስጠት፣

**ተግባር 3፡** ወደ ሊዝ የገቡ ከተሞች የልማት እና የውል ክትትል ሥርዓት መዘርጋቱን በመከታተል እና ወቅታዊ የክትትል ሥርዓት መኖሩን ማረጋገጥ፣

**ተግባር 4፡** ሊዝ ተግባራዊ በሆነባቸው ከተሞች በሊዝ የተመዘገበ ይዞታ መጠን 60 በመቶ እንዲደርስ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፡፡

**ግብ አራት፡** **በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ያለፈቃድ የተያዙ እና ሰነድ አልባ ይዞታዎችን ሥርዓት ለማስያዝ የሚያስችል የአሰራር ማኑዋል በማዘጋጀ፣ ለ2,000 ፈጻሚዎች ስልጠና በመስጠት ሰነድ አልባ ከሆኑ ይዞታዎች ውስጥ 75 በመቶ የሚሆኑት ሰነድ እንዲያገኙ እንዲሁም ያለፈቃድ የተያዙ ይዞታዎች 50 በመቶ ሥርዓት እንዲይዙ ይደረጋል፡፡**

**ተግባር 1፡** በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ያለፈቃድ የተያዙ እና ሰነድ አልባ ይዞታዎችን ሥርዓት ለማስያዝ የሚያስችል የአሰራር ማኑዋል ማዘጋጀት፣

**ተግባር 2፡** በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ያለፈቃድ የተያዙ እና ሰነድ አልባ ይዞታዎችን ሥርዓት ለማስያዝ የሚያስችል የአሰራር ማኑዋል ላይ ለ2,000 ፈጻሚዎች ስልጠና በመስጠት ተግባራዊነቱ ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 3፡** በከተሞች ሰነድ አልባ ከሆኑ ይዞታዎች 75 በመቶ የሚሆኑት ሰነድ እንዲያገኙ ተገቢዉ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ፣

**ተግባር 4፡** በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ያለፈቃድ የተያዙ ይዞታዎች ሥርዓት ለማስያዝ የሚያስችል የአሰራር ማኑዋል በማዘጋጀት በከተሞች 50 በመቶ ያለፈቃድ የተያዙ ይዞታዎች ሥርዓት እንዲይዙ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፡፡

**ግብ አምስት፡** **በአዲስ አበባ በተመረጡ 2 ክፍለ ከተሞች በመሬት ግብይት እና የሊዝ ባለመብቶች የተሟላ መረጃ በዘመናዊ መንገድ ለማደራጀት የሚያስችል ስልጠና ለ100 ባለሙያዎች ይሰጣል፣ ተግባራዊ ይደረጋል፤ ለይዞታ ማህደር ደህንነት እና አገልግሎት አሰጣጥ አመቺ የሆነ ዘመናዊ የይዞታ አስተዳደር አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ በማዘጋጀት እና ሥርዓቱ መዘርጋቱን በማረጋገጥ የተገኘው ተሞክሮ ይቀመራል፡፡**

**ተግባር 1፡** በአዲስ አበባ ከተማ በተመረጡ 2 ክፍለ ከተሞች የመሬት ግብይት ላይ ለተመደቡት 100 ባለሙያዎች ከጨረታ አፈጻጸም እስከ ክትትል ያለበትን የክህሎት ክፍተት በመፈተሽ የቲዮሪ እና የተግባር ስልጠና በመስጠት ተሞክሮ መቀመር፣

**ተግባር 2፡** በአዲስ አበባ ከተማ በተመረጠ ክፍለ ከተማ የሊዝ ባለመብቶችን የተሟላ መረጃ በዘመናዊ መንገድ በማደራጀት፣ ለ100 ባለሙያ ስልጠና በመስጠት፣ ትግበራው ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ አሠራሩ መዘርጋቱን በማረጋገጥ ተሞክሮ መቀመር፣

**ተግባር 3፡** በአዲስ አበባ ከተማ በተመረጡ 2 ክፍለ ከተሞች ለይዞታ ማህደር ደህንነት እና አገልግሎት አሰጣጥ አመቺ የሆነ የፋይል ካቢኔት እና የደህንነት ሲስተም እንዲሁም የማህደር ክፍል ዲዛይን በማዘጋጀት እና 10 ፋይል ካቢኔት ሞዴል በማሰራት እና የደህንነት ሥርዓት በመዘርጋት ርክክብ ማድረግ፣

**ተግባር 4፡** በአዲስ አበባ ከተማ በተመረጡ 2 ክፍለ ከተሞች ዘመናዊ የይዞታ አስተዳደር አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ በማዘጋጀት፤ የአገልግሎት መስጫ ማዕከል በማስተካከል፤ 10ሩን

ፋይል ካቢኔቶች በመጠቀም ዘመናዊ የይዞታ ማህደር በማደራጀት እና ዘመናዊ የአገልግሎት መስጫ ፋሲሊቲ በማቅረብ ቀልጣፋ፤ ግልጽ እና ዘመናዊ የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋቱን በማረጋገጥ የተገኘውን ተሞክሮ መቀመር፡፡

3.2.3. **የከተማ መሬት መረጃ ሥራ**

**ዓላማ፡** **የመሬት አጠቃቀም ፕላን፣ የውዝፍ ይዞታ መጠን፣ የህግ ወጥ ይዞታ መጠን፣ የህጋዊ ይዞታ መጠን በማን እንዴት ምን ያህል ተያዘ የሚል የተደራጀ መረጃ ለፖሊሲ ውሳኔ ለመራው አካል በማቅረብ ለልማት አጋዥ የሆኑ ውሳኔዎች በወቅቱ እንዲሰጡ ማስቻል ነው፡፡**

**ጥቅል ግብ፡** **በ86 ከተሞች የመሬት ሃብት ቆጠራ እና ምዝገባ በማከናወን፣ የመሬት መረጃ ባንክ ተደራጅቶ የከተማ መሬት መረጃ ሥርዓት ተስፋ በሚሰጥ ደረጃ በከተሞች የተደራጀ መረጃ ማግኘት የሚቻልበት ሁኔታ ይፈጠራል፤ የመረጃ ሽፋኑም 100 በመቶ በማድረስ ሥርዓቱ ግልጽ መሆን ይጀምራል፡፡**

**ዝርዝር ግቦችና ተግባራት**

**ግብ አንድ፡** **ለክልሎች እና ለከተሞች የአስተዳደር ወሰን ለመከለል እና የመሬት ኢንቨንተሪ እና ምዝገባ ለማድረግ የሚያስችል የከተማ መሬት ሃብት አስተዳደር ሞዴል ደንብ በማዘጋጀት እና የመሬት መረጃ ባንክ አደረጃጀት ሥርዓት በመዘርጋት በአሠራሩ ላይ ለ400 ፈጻሚዎች ሥልጠና በመስጠት ሥርዓቱ እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡**

**ተግባር 1፡** ለክልሎች እና ለከተሞች የአስተዳደር ወሰን ለመከለል እና የመሬት ኢንቨንተሪ እና ምዝገባ ለማድረግ የሚያስችል የከተማ መሬት ሃብት አስተዳደር ሞዴል ደንብ ማዘጋጀትና ለሚመለከታቸው ማሠራጨት፤

**ተግባር 2፡** ለክልሎች እና ለከተሞች የአስተዳደር ወሰን ለመለየት እና የመሬት ኢንቨንተሪ እና ምዝገባ ለማድረግ የሚያስችል አደረጃጀት መፈጠሩን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠቱን ማረጋገጥ፣

**ተግባር 3፡** ለ400 ፈጻሚዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፡፡

**ግብ ሁለት፡** **በፌዴራል ደረጃ የመሬት መረጃ ባንክ ሶፍትዌር በማዘጋጀት በመረጃ አደረጃጀቱ ላይ ለ100 ፈጻሚዎች ስልጠና በመስጠት የተጠናከረ የመሬት መረጃ ባንክ ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል አቅም በመፍጠር የመሬት መረጃ ሽፋኑ 100 በመቶ መድረሱ በጥናት ይረጋገጣል፡፡**

**ተግባር 1፡** የመሬት መረጃ ባንክ ሶፍትዌር አማካሪ በመቅጠር እንዲዘጋጅ ማድረግ፣

**ተግባር 2፡** በመሬት መረጃ ባንክ ሶፍትዌር 100 ባለሙያዎችን እንዲሰለጥኑ ማድረግና የሙያ ደረጃቸውን በምዘና ማረጋገጥ፣

**ተግባር 3፡** የከተሞች የመሬት መረጃ ማዕከል አደረጃጀት መፈጠሩን እና የመሬት መረጃ ማዕከል ሆኖ እያገለገለ መሆኑን መከታተልና በአፈጻጸሙ ላይ የጽሑፍ ግብረ-መልስ መስጠት፡፡

**ተግባር 4፡** በክልሎችና በከተሞች የተሰበሰበ የመሬት መረጃ ሽፋን 100% መድረሱን በጥናት ማረጋገጥ፡፡

**ግብ ሦስት፡ በአራቱ ክልሎች (ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ እና ትግራይ) በተመረጡ 4 አነስተኛ ከተሞች ላይ የመሬት መረጃ የማኑዋል ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል የከተሞች የማኑዋል መረጃ አደረጃጀት ስታንዳርድ በማዘጋጀት እና ለ40 አመራሮችና ፈጻሚዎች ሥልጠና በመስጠት በትግበራዉ ላይ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ተሞክሮ ይቀመራል፡፡**

**ተግባር 1፡** የከተሞች የማኑዋል መረጃ አደረጃጀት ስታንዳርድ ማዘጋጀትና በማጸደቅ ሥራ ላይ እንዲውል ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

**ተግባር 2፡** ከክልል አመራሮች ጋር በጋራ 4 አነስተኛ ከተሞችን በመለየት ከተመረጡት ከተሞች አመራሮች ጋር የጋራ ዕቅድ ማዘጋጀት፣

**ተግባር 3፡** ለተመረጡት 4 ከተሞች 40 አመራርና ፈጻሚዎች ስልጠና መስጠትና የሙያ ደረጃቸውን በምዘና ሠርቲፋይ በማድረግ ማረጋገጥ፣

**ተግባር 4፡** የከተሞች የማኑዋል መረጃ ማደራጃ ማዕከል አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን እንዲሟላ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

**ተግባር 5፡** መረጃዉ ተሰብስቦ እንዲደራጅ ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ የጹሑፍ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 6፡** የመሬት መረጃ የማኑዋል ሥርዓት ላይ ተሞክሮ መቀመር፡፡

**ግብ አራት፡ በአዲስ አበባ የመሬት ኢንቨንተሪ ምዝገባ እና የመረጃ ባንክ አሰራር ላይ ለ20 ፈጻሚዎች ስልጠና በመስጠት እና በተመረጡ 2 ወረዳዎች ላይ የትግበራ ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ ሥርዓቱ መዘርጋቱን በማረጋገጥ ተሞክሮ ይቀመራል፡፡**

**ተግባር 1፡** በመሬት ኢንቨንተሪ፤ ምዝገባ እና መረጃ ባንክ አሰራር ላይ ለ20 ፈጻሚዎች ስልጠና በመስጠት ወደ ሥራ እንዲገቡ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

**ተግባር 2፡** ለሞዴልነት በተመረጡ 2 ወረዳዎች ላይ በመሬት ኢንቨንተሪ፤ ምዝገባ እና መረጃ ባንክ አሰራር ትግበራን ማጠናቀቅና በአፈጻጸሙ ላይ የጹሑፍ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 3፡** በተመረጡ 2 ወረዳዎች ላይ በመሬት ኢንቨንተሪ፤ ምዝገባ እና መረጃ ባንክ አሰራር ላይ ተሞክሮ መቀመር፡፡

**ግብ አምስት፡ የአስተዳደር ወሰናቸዉ በአግባቡ ባልተለዩ 86 ከተሞች የአስተዳደር ወሰን በመከለልና በካርታ እንዲመላከት ይደረጋል፡፡**

**ተግባር 1፡** በ86 ከተሞች የአስተዳደር ወሰን ማመላከቻ ነጥብ /Reference Point/ እንዲቀመጥ እና በካርታ እንዲመላከት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

**ተግባር 2፡** አፈጻጸሙን ተከታትሎ የጹሑፍ ግብረ-መልስ መስጠት፡፡

**ግብ ስድስት፡ በ86 ከተሞች በክፍትነት የሚገኙ፣ በጊዜያዊ ሊዝ በተያዙ እንዲሁም ለእርሻ እና ለግጦሽ የዋሉ 25,000 ሄክታር ስፋት ያላቸዉ ቦታዎች ኢንቨንተሪ በማድረግ መረጃቸዉ እንዲደራጅ እና በጊዜያዊ ሊዝ ለተያዙት እና ለአርሶ አደር ይዞታዎች 5,635 ጊዜያዊ መጠቀሚያ ሰነድ እንዲሰጥ ድጋፍ እና ክትትል ይደረጋል፡፡**

**ተግባር 1፡** በ86 ከተሞች ክልል ውስጥ ለእርሻ፣ ለግጦሽ እና ለአትክልት ልማት የዋሉትን፣ በጊዜያዊ ሊዝ እና ፈቃድ ለማዕድን ልማት፣ ለአነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋማት የተሰጡትን፣ በመንግስት አስተዳደር እና በከተሞች አስተዳደር በኪራይ አግባብ አገልግሎት የሚሰጡ የቀበሌ ቤቶች እና የመንግስት ህንጻዎች የሚገኙባቸዉን 25,000 ሄክታር መሬት ቆጠራ እንዲካሄድ ክትትል ማድረግ፤

**ተግባር 2፡** እንደየከተሞቹ አቅምና ደረጃ ቆጠራ የተካሄደባቸው 86 ከተሞች የመሬት መረጃ በዳታ ቤዝ እንዲደራጅ እና በካርታ ላይ እንዲመላከት ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

**ተግባር 2፡** እንደየከተሞቹ አቅምና ደረጃ ቆጠራ የተካሄደባቸው 86 ከተሞች ውስጥ ለአርሶ አደር ይዞታዎች 5,635 ጊዜያዊ መጠቀሚያ ሰነድ እንዲሰጥ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

**ተግባር 3፡** በበጀት ዓመቱ 2 ጊዜ ቆጠራ የተካሄደበትን 25,000 ሄክታር መሬት በዳታ ቤዝ መደራጀቱን እና ጊዜያዊ መጠቀሚያ ሰነድ መሰጠቱን የመስክ ጉብኝት በማድረግ ተግባራዊ አፈጻጸሙን ተከታትሎ የጽሑፍ ግብረ-መልስ መስጠት፡፡

**ግብ ሰባት፡ በ33 ከተሞች የተተከሉ እና የተስፋፉ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች በማመላከት አስተማማኝ የደህንነት ጥበቃ ስርዓት መዘርጋቱ እና መከላከያ መገንባቱ ክትትል በማድረግ ይረጋገጣል፡፡**

**ተግባር 1፡** በ33 ከተሞች የተተከሉ ወይም የተስፋፉ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች በመለየት፣ በካርታ ማመላከት እና መረጃዉን በዳታቤዝ እንዲደራጅ ማድረግ፣

**ተግባር 2፡** በ33 ከተሞች በተተከሉ እና በተስፋፉ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ላይ የደህንነት ጥበቃና የመከላከያ ግንባታ እንዲኖር ማድረግ፣

ተግባር 3፡ በበጀት ዓመቱ 2 ጊዜ የከተሞችን የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች መረጃ አያያዝ እና የደህንነት ጥበቃ ተግባራዊነት በከተሞች በመገኘት ማረጋገጥና በጽሑፍ ግብረ-መልስ ማካሄድ፡፡

## 3.3. የከተማ መሬት የጂኦስፓሻል እና የይዞታ መረጃ ማደራጀትና ሥርዓት ዝርጋታ ሥራዎች

**ጥቅል ዓላማ፡ መሬትና መሬት ነክ መረጃ ለመሰብሰብ፣ ለማደራጀት፣ ለመተንተንና ለማቅረብ ጥቅም ላይ የሚውለው የቴክኖሎጂ ውጤት ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ፣ ከሌሎች ሲስተሞች ጋር የሚናበብ፣ የመረጃ ደህንነትን በአስተማማኝ ሁኔታ የሚያረጋግጥ፣ በተፈለገ ጊዜ ለማሳደግ የሚያመች የመረጃ ስርዓት በመላው ሀገሪቱ ከተሞች ወጥ በሆነ መንገድ እንዲዘረጋ በማድረግ ለልማቱ አጋዥ የሆነ ሥርዓት ለመዘርጋት ነው፡፡**

**ጥቅል ግብ፡-**

**ሀ. ዘመናዊ ተቋማዊ አደረጃጀትና የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋትና የአንድ ቋት መረጃ አጠቃቀም ማዕከል በመገንባት በፌደራል፣ በክልሎች እና በከተሞች ዘመናዊ የመሬት መረጃ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት እንዲኖር ይደረጋል፡፡**

**ለ. የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን በመትከል፣ የአየር በረራ እና የሳታላይት ምስል በመጠቀም የመሬትና መሬት ነክ መረጃን መሰብሰብ፣ ማደስ፣ ማደራጀትና ደረጃቸውን የጠበቁ የመሠረታዊ፣ የአድራሻ ሥርዓትና የካደስተር ካርታዎችን ዝግጅት የሚያፋጥን የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት በከተሞች ተግባራዊ ይደረጋል፡፡**

**ሐ. የመሬት ልማት እና ማኔጅመንት መረጃ ዝርጋታ ስርዓቱን የሚያስጀምር ሥልጠናና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምዘና በማካሄድ በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ሃይል የማፍራት ሂደት ይጀመራል፡፡**

**መ. ቀድሞ ወደ ሥራ ከገቡት ከተሞች መልካም ተሞክሮ በመውሰድና በመቀመር በሌሎች ክልሎችና ከተሞች ላይ በመተግበር ለዘመናዊ የመሬት መረጃ አያያዝና አጠባበቅ ሥርዓት ዝርጋታ እገዛ ይደረጋል፡፡**

**ሠ. በተንዛዛ፣ በዘልማድና ወጥነት በጎደለው መንገድ ተሰርቶ ተከማችተው ያሉትን የመሬትና መሬት ነክ ይዞታ ማሳያ ሰነዶችና ካርታዎች በማኑዋል የአሰራር ሥርዓት ተደራጅተው አገራዊ ስታንዳርድና ደህንነታቸው የተጠበቀ መረጃ እንዲኖር መሠረት ይጣላል፡፡**

### 3.3.1. የሲስተም ልማትና አተገባበር ሥራ

ዓላማ፡ በአምስት ክልሎች (አማራ፤ ትግራይ፤ ኦሮሚያ፤ ደቡብና ሐረሪ) እና በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የመሬትና መሬት ነክ መረጃ ስርዓት ዝርጋታ አጠቃላይ አተገባበር አስፈላጊው ክትትልና ድጋፍ ማድግ ነው፡፡

ግብ፡ የ23 ከተሞች የሲስተም ልማትና ትግበራን ወጥ በሆነ መልኩ ለማስጀመር እንዲቻል በአዳማ፣ በሐዋሳ፣ በባህር ዳር፣ በመቀሌ እና በድሬደዋ ከተሞች የመሬትና መሬት ነክ መረጃ ስርዓት ለመዘርጋት 3 ሶፍትዌሮችን እንዲዘጋጁና ተግባራዊ እንዲሆኑ ለ115 አመራሮችና ባለሙያዎች ሥልጠና በመስጠት ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል።

**ዝርዝር ተግባራት**

ተግባር 1፡ በ23 ከተሞች ላይ የሚደረገውን የሲስተም ልማትና ትግበራን ወጥ በሆነ መልኩ ለማስጀመር እንዲቻል በአዳማ፣ በሐዋሳ፣ በባህር ዳር፣ በመቀሌ እና በድሬደዋ ከተሞች ላይ የመሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ የመረጃ ሲሰተም ለማልማት አማካሪ ድርጅት በመቅጠር ሲስተም እንዲዘጋጅ ማድረግ፣

ተግባር 2፡ የ23 ከተሞች የሲስተም ልማትና ትግበራን ወጥ በሆነ መልኩ ለማስጀመር እንዲቻል በአዳማ፣ በሐዋሳ፣ በባህር ዳር፣ በመቀሌ እና በድሬደዋ ከተሞች የመሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ መረጃ ሥርዓት ዝርጋታውን ጥራት የሚቆጣጠር ተቆጣጣሪ ድርጅት መቅጠር፣

ተግባር 3፡ የፌዴራል የመሬትና መሬት ነክ ኤጀንሲን ከአዳማ፣ ከሐዋሳ፣ ከባህር ዳር፣ ከመቀሌ እና ከድሬደዋ ከተሞች ጋር በሚዘረጋው የመሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ መረጃ ሥርዓት የሚያስፈልገውን የኔትወርክ መሰረተ ልማት እንዲዘረጋ ማድረግ፣

ተግባር 4፡ በ23 ከተሞች ላይ የመሬት ላይ መቆጣጠሪያ ነጥቦች (Ground Control Point/GCP) የመረጃ አያያዝ ስርዓት ለመዘርጋት የተዘጋጀውን ሶፍትዌር በተመረጡ ሁለት ከተሞች በመሞከር ወደ ሌሎች 21 ከተሞች ማስፋት፣

ተግባር 5፡ በአዲስ አበባ ከተማ የሚደረገውን የአሃዛዊ የመሬትና መሬት ነክ መረጃ ሥርዓት የትግበራ ተሞክሮን በመቀመርና ሰነድ በማዘጋጀት ወደ ሌሎች 23 ከተሞች ማስፋት፣

ተግባር 6፡ በከተሞች የሚገኙ ክፍት ቦታዎችን መዝግቦ የሚይዝ የመረጃ ሥርዓት እና የሊዝ ይዞታ መረጃ ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል ሶፍትዌር የሚያዘጋጅ አማካሪ ድርጅት በመቅጠር በ2 ከተሞች ሙከራ በማካሄድና በማረጋገጥ ወደ ሌሎች 23 ከተሞች ማስፋት፣

ተግባር 7፡ ሲስተሙ ለሚተገበርባቸው በተመረጡ 23 ከተሞች እና በሲስተም ልማት እና ትግበራ፣ በቢጋርና ቅድመ ዝግጅት ላይ ስልጠና ለ115 አመራሮችና ባለሙያዎች በመስጠት በትግበራዉ ላይ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

ተግባር 8፡ ለመሬትና መሬት ነክ ተቋማት የተዘጋጀው ዌብ ሳይት ከህብረተሰቡና ከባለድርሻ አካላት በሚሰጠው አስተያየት መሠረት 4 ጊዜ ማሻሻል።

### 3.3.2. የሰው ኃይል ልማት ሥራ

**ዓላማ:** **ለተቀናጀ የመሬት ልማትና ማኔጅመንት የሚሆን በቴክኒክና ሙያ፣ በዲግሪ፣ በሁለተኛ ዲግሪና በሦስተኛ ዲግሪ ተመርቆና የሙያ ደረጃው በምዘና ተረጋግጦ የሴክተሩ ራዕይ ማሳካት የሚችል ሥርዓትና የሰው ኃይል በአስተማማኝ ደረጃ መፍጠር ነው፡፡**

**ግብ:** **የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ሥራዎችን ለመምራትና ለመፈጸም እንዲቻል በ35 የትምህርት መስኮችሥርዓተ ትምህርት በመቅረጽ በአጭር፣ በመካከለኛና በረጅም ጊዜ በአጠቃላይ 7,075 አመራሮችና ባለሙያዎች ሥልጠና በመስጠትና ምዘና በማካሄድ በዘርፉ ብቁ የሰው ኃይል የሚፈጠርበት ሥርዓት ይዘረጋል፡፡**

**ዝርዝር ተግባራት**

**ተግባር 1:** በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ስልጠና ላይ ላሉ 255 ሰልጣኞች በ12 የሴክተሩ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ስልጠና መስጠት፣

**ተግባር 2:** ከመሬት ልማትና ማኔጅመንት እንዲሁም ከትምህርት ተቋማት ከሚውጣጡ 60 አመራሮችና ባለሙያዎች ጋር በዘርፉ የሰው ኃይል ልማት ሥራዎች ላይ የምክክር መድረክ ማካሄድ፣

**ተግባር 3:** ለመሬት እና መሬት ነክ ዘርፍ ተጨማሪ 2 የሙያ ደረጃ ምደባ፣ ሥርዓተ-ስልጠናና 2 የምዘና መሳሪያዎችን ማዘጋጀት፣

**ተግባር 4:** ለዘርፉ ከተዘጋጁት ሙያ ደረጃዎች አንጻር የባለሙያዎችን የክህሎት ክፍተት ጥናት በማካሄድ የመሪ መዛኝነትና የትብብር አሰልጣኝነት ሥልጠና እና ምዘና ለ260 ባለሙያዎች መስጠት፣

**ተግባር 5:** ቀድመው ከሚተገበሩ የመረጃ ሥርዓቶች ውስጥ 2 ተሞክሮዎችን በመለየት ቀምሮ ለክልሎች ማስፋት፣

**ተግባር 6:** ለ10 የሙያ ደረጃዎች ሥርዓተ ስልጠናውን መሠረት ያደረገ 100 የሥልጠና ማቴሪያል /TTLM/ ተዘጋጅቶ ለስልጠና ተቋማት ማሰራጨት፣

**ተግባር 7:** ከተለያዩ የስልጠና ተቋማት እና ከክልል ፕሮጀክት ጽ/ቤቶች ጋር በመተባበር የመሬት መረጃ ዝርጋታ ሥርዓቱን ለማስጀመርና ለማከናወን የሚያስችል በ22 የሥልጠና ዓይነቶች ላይ ለ500 ባለሙያዎች የመካከለኛ ጊዜ ስልጠና መስጠት፣

**ተግባር 8:** በ7 የክልል ፕሮጀክት ጽ/ቤቶች እና በተለያዩ የስልጠና ተቋማት ትብብር ለመሬት መረጃ ዝርጋታ ሥርዓቱ አጋዥ የሆነ የሰው ኃይል ለማፍራት የሚያስችል የአጭር ጊዜ ስልጠና ለ2,500 ባለሞያዎች በሚሰጥበት አግባብ ላይ ክትትልና ድጋፍ ማደረግ፣

**ተግባር 9:** በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አስተባባሪነት የተሰጡ ስልጠናዎች እያስገኙት ያለው ውጤት ላይ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፣

ተግባር 10፡ በ7 ተቋማት ተዛማጅ የትምህርት ዝግጅትና የሥራ ልምድ ያላቸው 1000 ባለሙያዎች በምዘና ብቃታቸውን በማረጋገጥ የመሬት የመረጃ ሥርዓት ትግበራውን የሚቀላቀሉበት መንገድ ማመቻቸት፣

ተግባር 11፡ የመሬት እና መሬት ነክ መረጃ ሥርዓቱን መሠረት ባደረጉ የሙያ ደረጃዎች ለ3,500 ሰልጣኞች በ7 ክልሎች በሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ስልጠና እንዲካሄድ ክትትል ማድረግ፣

ተግባር 12፡ በ10 ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በተለያየ የትምህርት ደረጃ (BSc, MSc, PhD) በመሬትና መሬት ነክ ዘርፍ ላይ ሥርዓተ ትምህርት ቀርጸው የማስተማርና የምርምር ሥራ ለማስጀመር ምክክር በማድረግ ስምምነት ላይ መድረስ፣

ተግባር 13፡ ለዘርፉ በተለዩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በ5 የስልጠና መስኮች ተመራቂዎች ብቃት የሚረጋገጥበት ሥርዓት መዘርጋት፣

ተግበር 14፡ በኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ኤጀንሲ እየተካሔደ ባለው የ19 ባለሙያዎች ስልጠና ምዘና ለማካሄድ አንድ የምዘና መሳሪያዎች ፓኬጅ ማዘጋጀት፣

### 3.3.3. የቴክኖሎጂ አቅርቦትና አሠራር ሥርዓት ዝርጋታ ሥራ

**ዓላማ፡** **የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት በተለይ የመሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ /Legal Cadester/ የዓለም የደረጃዎች ምደባ ስታንዳርድ በአሟላ ሥርዓት ለማካሄድ የሚያስችል የተሻሻለ የማኑዋል የአሰራር ሥርዓት ለመዘርጋት ነው።**

**ግብ፡** **የመሬት መረጃን ለማሰባሰብ፣ ለማደራጀትና ለማስተዳደር የሚያስችል የተሻሻለ የማኑዋል የአሰራር ሥርዓት እንዲጠና በማድረግ፣ የሕግ ማዕቀፎች (ደንብ፣ መመሪያና ማኑዋል)፣ አደረጃጀት በመፍጠር ለ78 የክልል አመራሮችና ባለሙያዎች ሥልጠና በመስጠት ተግባራዊ ማድረግ ይጀመራል።**

**ዝርዝር ተግባራት**

ተግባር 1፡ ለመሬት መረጃ ሥርዓት ለመጠቀም የተገዙ 63 ISO ስታንዳርዶችን በክልልና በከተማ ደረጃ የሚገኙ የመሬት ተቋማት እንዲተገብሩት ለ78 አመራሮችና ፈጻሚዎች ሥልጠና በመስጠት ሥራ ላይ እንዲውል ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

ተግባር 2፡ በ5 ክልሎችና በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ የመሬትና መሬት ነክ መረጃ ተቋማት የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ የጋራ መድረክ በማዘጋጀት፣ ተሞክሮ ቀምሮ በክልሎች እንዲተገበር ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

ተግባር 3፡ በከተሞች የተጀመረው የመሬትና መሬት ነክ መረጃ የአሰራር ስርዓት ዝርጋታ አተገባበር የሚያሳይ የስራ ፍሰት ሠነድ በማዘጋጀት ለክልሎች ማሰራጨትና እንዲተገበር ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

**ተግባር 4፡** በ5 ክልሎች በሚገኙ 23 ከተሞች የሚገነቡትን የመሬት ነክ ተቋማት ሕንጻ ግንባታ ተግባራዊነት 3 ጊዜ በመከታተልና በድጋፍ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 5፡** በ5 ክልሎችና ድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ የፕሮጀክት ጽ/ቤቶችን አደረጃጀት 2 ጊዜ የመስክ ክትትልና ድጋፍ በማድረግና ግብረ-መልስ በመስጠት የተሻሻለ አደረጃጀት መፍጠር፣

**ተግባር 6፡** የኪራይ ሰብሳቢነትን አማራጮችን የሚዘጋ የመሬት መረጃን ለማሰባሰብ፣ ለማደራጀትና ለማስተዳደር የሚያስችል የተሻሻለ የማኑዋል የአሰራር ሥርዓት በአማካሪ እንዲጠና በማድረግ፣ ለ78 የክልል አመራሮችና ባለሙያዎች ሥልጠና በመስጠት እንዲሁም የሕግ ማዕቀፎች (ደንብ፣ መመሪያና ማኑዋል) በማዘጋጀት በ2 ከተሞች የሙከራ ትግበራ ሂደት ላይ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

### 3.3.4. የመረጃ ማሰባበሰብ፣ ማደራጀትና ማደስ ሥራ

**ዓላማ፡** **የከተማ የይዞታ መረጃ አስተማማኝ በሆነ መንገድና ሥርዓት አረጋጋጦ የፖለቲካል ኢካኖሚው እንቅስቃሴ አካል ማድረግና በየከተሞቹ እያንዳንዱ ቁራሽ መሮት ምን ያህል፣ በምን አገልግሎት ማን እንደያዘ ደህንነቱ የተረጋገጠ የመረጃ ሥርዓት ለመዘርጋት ነው፡፡**

**ግብ፡** **የአየር በረራ እና የሳታላይት ምስል በመጠቀም የመሬትና መሬት ነክ መረጃን መሰብሰብ፣ ማደስ፣ ማደራጀትና ደረጃቸውን የጠበቁ የመሠረታዊ፣ የአድራሻ ሥርዓትና የካደስተር ካርታዎችን ዝግጅት የሚያፋጥን የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት በ23 ከተሞች ተግባራዊ ይደረጋል፡፡**

**ዝርዝር ተግባራት**

**ተግባር 1፡** ከ23 ከተሞች ውስጥ የአየር ፎቶግራፍ በረራ ሥራ ባልተከናወነባቸው 11 ከተሞች እንዲከናወን ክትትልና ድጋፍ በማካሄድ ርክክብ ማድረግ፣

**ተግባር 2፡** በ23 ከተሞች የፎቶግራሜትሪ ሥራዎች ለማካሄድ የትሪአንጉሌሽን አጀስትመንት እና የከፍታ መረጃ (DTM) ሥራዎችን በማከናወን የመሠረታዊ ካርታ ለሚያዘጋጅ አካል ማስረከብ፣

**ተግባር 3፡** የ23 ከተሞች አየር ፎቶግራፍና ፎቶግራሜትሪ ስራዎች ጥራት ቁጥጥር በአማካሪ ድርጅት ለማከናወን የሚያስችል የጥራት መለኪያዎችና ፕሮሲጀር በማዘጋጀት ጥራት ቁጥጥሩን ማካሄድ፣

**ተግባር 4፡** በኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ኤጀንሲ የ23 ከተሞች መሠረታዊ ካርታ እንዲዘጋጅ በማድረግ ለክልሎች ማስረከብ፣

**ተግባር 5፡** ለ49 ከተሞች የመሬት መቆጣጠሪያ ነጥቦችን በመሥራት በሳተላይት ስቴሪዮ ምስል መሰረታዊ ካርታ በአማካሪ ድርጅቶች እንዲዘጋጅ በማድረግ ለክልሎች ማስረከብ፣

**ተግባር 6፡** ለ23 ከተሞች ካዳስተር ልኬት ለማከናወን የተከላ የመስፈርት እና መመሪያ በማዘጋጀት ለካዳስተር ልኬት መነሻ የሚሆኑ የቅየሳ ነጥቦች ተከላና ማባዛት በ23 ከተሞች ማከናወን፣

**ተግባር 7፡** የ10 አነስተኛ ከተሞች መሰረታዊ ካርታ እንዲዘጋጅ በማድረግ ለክልሎች ማስረከብ፣

**ተግባር 8፡** የአድራሻ ሥርዓትን ለመተግበር የሚስፈልግ ስታንዳርድ እና ጋይድላይን በማዘጋጀት በ6 ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ለተውጣጡ 30 አመራሮችና ፈጻሚዎች ሥልጠና በመስጠት ለትግበራ ማስተላለፍ፣

**ተግባር 9፡** ከኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ኤጀንሲ ጋር በጋር የ18 ከተሞች የፎቶ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ቅየሳ ልኬት ማከናወን፡፡

### 3.4. የከተማ መሬትና መሬት ነክ ቋሚ ንብረት ምዝገባ ሥራዎች

**ጥቅል ዓላማ፡** በክልሎችና ከተሞች የሚቋቋሙት የከተማ የመሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ተቋማት አገራዊ ተናባቢነትና መደጋገፍ እንዲፈጥሩ የአሰራርና አደረጃጀት ትስስር ከፌዴራል እስከ ክልልና ከተሞች ድረስ መፍጠር ነው፡፡

**ጥቅል ግብ፡** በፌዴራል ደረጃ የከተሞችን የህጋዊ ካዳስተርና የመሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ መረጃ ለመመዝገብ የሚረዳ ስርዓት እና ተቋም በመገንባት፣ አገራዊ ማዕከላዊ የህጋዊ ካዳስተር እና የመሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ መረጃ ቋት በመገንባት ለ23 ከተሞች የመሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ አስተዳደር ላይ እገዛ ይደረጋል፣ በሃገራዊ የህጋዊ ካዳስተር መረጃ እንደሁም መሬትና መሬት ነክ የንብረት ምዝገባን አለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ እየተራመደ መሆኑ ይረጋገጣል፡፡

**ዝርዝር ግቦችና ተግባራት**

**ግብ አንድ፡** በ5 ክልሎች፣ በ2 ቻርተርድ ከተሞች እና በ21 ክልላዊ ከተሞች ተናባቢና ወጥ የሆነ የካዳስተር፣ የመሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ አሠራርና መዋቅር በመገንባት በ6 ከተሞች ላይ ለ20,500 የከተማ ማህበረሰብ፣ ባለሃብትና ባለሙያዎች ግንዛቤ ይፈጠራል፡፡

**ተግባር 1፡** በ5 ክልሎች፣ በ2 ቻርተርድ ከተሞች እና በ21 ክልላዊ ከተሞች ተናባቢና ወጥ የሆነ የመሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ አስተዳደር መዋቅር መዘርጋት፣

**ተግባር 2፡** በ5 ክልሎች እና በ2 ቻርተርድ ከተሞች የከተማ የመሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ተቋም በየእርከኑ በማደራጀት የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት፣

**ተግባር 3፡** የመሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ ስትራቴጂን ለማስፈጸም የሚያስችሉ የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት ለ20,500 የከተማ ማህበረሰብ፣ ባለሃብትና ባለሙያዎች ሥልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፡፡

ግብ ሁለት፡ በ23 የክልል ከተሞች የካዳስተር ካርታ ሥራ መነሻውን ከከተሞቹ ያደረገ 208 የፎቶ መቆጣጠሪየ ነጥቦች ተዘጋጅተው ለመሬትና መሬት ንክ ንብረት ምዝገባ ፕሮግራም አገልግሎት ዝግጁ እንዲሆኑ ይደረጋል፣ ለካዳስተር ወሰን ቅየሳ የሚያገለግሉ 1,548 የጂኦደቲክ መቆጣጠሪ ነጥቦች ተከላ ቢያንስ በአንድ ካ.ሜ. መካሄዱን ብሎም የወሰን ቅየሳ በሃገራዊ ስታንዳርድ መከናወኑ ይረጋገጣል፡፡

ተግባር 1፡ በ23 የክልል ከተሞች በ1፡2000 መስፈርት ደረጃ የካዳስተር ካርታ ሥራ መነሻውን ከከተሞቹ ያደረገ 208 የፎቶ መቆጣጠሪየ ነጥቦችን ማዘጋጀት፣

ተግባር 2፡ የ23 ከተሞች ደረጃውን የጠበቀ የካዳስተር ካርታ ዝግጅትን ላይ የ1,548 የጂኦደቲክ ቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች የማስፋፋት ሥራን ማስተባበር እና ትግበራውን በመመዘን ማረጋገጥ፣

ተግባር 3፡ በ23 ከተሞች በሚዘጋጁ የካዳስተር ካርታና መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ ሥርዓት ግንባታ ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

ተግባር 4፡ በአዲስ አበባ ከተማ ደረጃውን የጠበቀ የካዳስተር ወሰን ቅየሳ መከናወኑን የማረጋገጥ፣ ድጋፍና ክትትል የማድረግ ሥራ መስራት ግብረ-መልስ በጹሑፍ መስጠት፡፡

ግብ ሦስት፡ ዘርፉ የተቀመጠለትን አገራዊ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ማሳካቱን ከወዲሁ ሊያመላክት የሚችል ሥርዓት ለመገንባት የሚያስችሉና ጥናትን መሰረት ያደረጉ 7 መመሪያዎችና 5 ስታንዳርዶች እና 3 ማኑዋሎች በማዘጋጀት ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

ተግባር 1፡ 7 የካዳስተር የይዞታ መብት ምዝገባ፣ የይዞታ መብት ማረጋገጫ፣ የመረጃ ደህንነት መመሪያዎችን በማዘጋጀት እንዲጸድቁ ማድረግ እና ተግባራዊነቱ ላይ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

ተግባር 2፡ 5 የካዳስተር ካርታ፣ የይዞታ መብት ምዝገባ፣ የይዞታ መብት ማረጋገጫ ስታንዳርድ ዝግጅት ማከናወንና ሲፀድቅ ተግባራዊነቱ ላይ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

ተግባር 3፡ የከተማ የሕጋዊ ካዳስተር እና የመሬትና መሬት ነክ ንብረት መረጃ ምዝገባ 2 ማኑዋል ማዘጋጀት እና ተግባራዊነቱ ላይ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

ተግባር 4፡ የከተማ የሕጋዊ ካዳስተር የመብት ምዝገባ አንድ የአሠራር ማኑዋል ማዘጋጀት እና ተግባራዊነቱ ላይ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፡፡

ግብ አራት፡ በአዲስ አበባ ከተማ አተገባበር መሰረት የ23 ከተሞችን የወረቀት ይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ሥርዓት ቀርጾ የተመረጡ የይዞታ ሰነዶችን ዲጅታይዝ በማድረግ ከአዲሱ የዲጅታል ካዳስተር ካርታ ጋር እንዲተሳሰሩ ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፡፡

ተግባር 1፡ በ23 ከተሞች ነባር የይዞታ ሰነዶችን ዲጂታል ማድረግ እና ካዳስተር ካርታ ላላቸው የማስተሳሰር ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

ተግባር 2፡ በአዲስ አበባና በ23 ከተሞች ነባር የይዞታ ማረጋገጫ ሰነዶች ዲጂታል ከሆኑ በኃላ ከካዳስተር ካርታ ጋር የማስተሳሰር ሥራ እንዲሰራ ድጋፍ ማድረግ እና የጹሑፍ ግብረ መልስ ማድረግ፡፡

## 4. የመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመንግስት ህንጻዎች ኮንስትራክሽን ሥራዎች

**ጥቅል ዓላማ፡** የከተማ ነዋሪዎችን የቤት ችግር በቤቶች ልማት ፕሮግራም አማካይነት ለማቃለል በሚደረገው እንቅስቃሴ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በማስፋፋት በከተሞች የሚታየውን የሥራ አጥነት ችግር ለመቅረፍ የህብረተሰቡን የቁጠባ ባህል ለማዳበር እና የመንግስት ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው መርሃ-ግብር እንዲከናወኑ ለማስቻል ነው፡፡

**ጥቅል ግብ፡** በአዲስ አበባ ከተማ የተጀመሩ 83,895 ቤቶች ግንባታይጠናቀቃል፣ በ2006 ለሚጀመሩ 35ሺ ቤቶች ቅድመ ዝግጅት ይደረጋል፣ በ40/60 ቁጠባ ቤቶች ፕሮግራም 10ሺ ቤቶች እንዲጀመሩ ይደረጋል፣ በስኳር፣ በማዳበሪያ፣ በዩኒቨርሲቲ እና ኢንዱስትሪ ዞን ልማቶች ላይ ድጋፍ ይሰጣል፣ በቤት ልማት ፕሮግራሙ 130 ሺ የሥራ ዕድል ይፈጠራል፡፡

### 4.1. የቤቶችና የሕንጻ ስትራቴጂና ሕግ ጉዳዮች ሥራ

ዓላማ፡ በሀገራችን የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ፖሊሲና ስትራቴጂ እንዲኖረው፣ የህግ ማዕቀፍ እንዲዘጋጅለት እንዲሁም አነስተኛ እና መካከለኛ ገቢ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የመንግስት ድጋፍ አግኝተው የቤት ተደራሽነት ለማረጋገጥ ነው፡፡

ግብ፡ በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ የሚካሄደው የቤት ልማት ህግና ሥርዓት ይዞ እንዲለማ ለማድረግ የተዘጋጀውን የቤት ፖሊሲና ስትራቴጂ ተግባራዊ በማድረግ፣ የተለያዩ 17 የሕግ ማዕቀፍ ሰነዶች (ደንቦችና መመሪያዎች) በማዘጋጀት፣ እና በ14 መድረኮች ስልጠናዎችን በመስጠትና እንዲተገበር በማድረግ በአገር አቀፍ ደረጃ የቤት ልማት እንዲስፋፋ ይደረጋል፡፡

**ዝርዝር ተግባራት**

ተግባር 1፡ የከተማ ቤት ፖሊሲና የስትራቴጂ ሰነድ በተሟላ ሁኔታ ወደ ትግበራ እንዲሸጋገር የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በማዘጋጀት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

ተግባር 2፡ ቁጠባን መሠረት ያደረጉ በግልና በቤት ህብረት ሥራ ማኅበራት ለሚገነቡ ቤቶች ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል አንድ ደንብ በማዘጋጀት ሥራ ላይ እንዲውል ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

**ተግባር 3፡** ቀደም ሲል ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ የዋለው የጋራ ህንጻ ባለቤትነት አዋጅ በተሟላ መልኩ ወደ ትግበራ እንዲሸጋገር ክትትልና ድጋፍ ማድረግ በግኝቱም ላይ የጹሑፍ ግብረመልስ መስጠት፣

**ተግባር 4፡** በመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲና በቀበሌ አስተዳደሮች የሚከራዩ ቤቶችን አስተዳደርና አጠቃቀም ለማሻሻል የሚረዱ አንድ የጥናት ሰነድ እና 2 መመሪያዎችን በማዘጋጀት በትግበራው ላይ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

**ተግባር 5፡** አነስተኛ ገቢ ላላቸው የከተማ ነዋሪዎች የቤት ልማት ፕሮግራም አፈጻጸም የሚረዱ የህግ ማዕቀፎች (አንድ ሞደል ደንብና አንድ መመሪያ) በማዘጋጀት በትግበራው ላይ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

**ተግባር 6፡** የቤት ፋይናንስና አቅርቦትን ለማሻሻል የሚያስችል የስትራቴጂ ሰነድ ማዘጋጀትና በሚመለከተው አካል አቅርቦ ማፀደቅና ወደ ትግበራ ማሸጋገር፣

**ተግባር 7፡** በከተማ ቤት ፖሊሲና ስትራቴጂ ላይ በክልሎችና በአዲስ አበባ ከተማ የማስተዋወቂያ ዘዴዎችን በመምረጥ 7 የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች እንዲዘጋጁ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

**ተግባር 8፡** በአነስተኛ ገቢ ላላቸው የከተማ ነዋሪዎችና በ40/60 ቁጠባ ቤቶች ልማት ፕሮግራሞች ላይ በክልሎችና በአዲስ አበባ 7 የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች እንዲዘጋጁ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

**ተግባር 9፡** በክልሎች በ40/60 ቁጠባ ቤቶች ልማት ፕሮግራም ለማስጀመር በጥናት ላይ የተመሠረተ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ማዘጋጀትና አዋጪ በሆኑት ላይ ለመንግስት አቅርቦ ማስወሰን፣

**ተግባር 10፡** በክልሎች አነስተኛ ገቢ ላላቸው ነዋሪዎች የቤቶች ልማት ፕሮግራም ለማካሄድ በጥናት ላይ የተመሠረተ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ማዘጋጀትና አዋጪ በሆኑት ላይ ለመንግስት አቅርቦ ማስወሰን፣

**ተግባር 11፡** በህንፃ ኘሮጀክቶች ላይ እየተሳተፉ የሚገኙ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ተሞክሮ እንዲቀመር ማድረግና የማስፋት ስትራቴጂ ቀይሶ የማስፋት ሥራ መስራት፣

**ተግባር 12፡** የሪል ስቴት አዋጅ በመንግስት እንዲጸድቅ እና ወደ ትግበራ እንዲሸጋገር ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

**ተግባር 13፡** በሁሉም ክልሎች ከቤት ልማት ፕሮግራሙ ጋር በተያያዘ 6 መመሪያዎችና የአሠራር ማኑዋሎች እንዲዘጋጁ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

**ተግባር 14፡** በከተሞች ያሉትን ያረጁና የተጨናነቁ ቤቶች በ42 በመቶ መቀነሱን ትንተና በማካሄድ በዓመቱ መጨረሻ በሪፖርት ማረጋገጥ፣

4.2. የቤቶችና ህንጻ ዲዛይን ዝግጅትና ትግበራ ክትትል ሥራ

ዓላማ፡ በአነስተኛ ወጪ እና ተመጣጣኝ ጥራት ያለው ዲዛይን በወቅቱ ለመንግስት ሕንጻዎች በማዘጋጀት የልማት ዕቅዶች እንዲሳኩ ድጋፍ ማድረግ ነው፡፡

ግብ፡ ወጪ ቆጣቢ የሆኑ እስከ 92 የሚደርሱ አዳዲስ፣ የተሻሻሉና በቁጠባ ላይ በተመሠረተ በመልሶ ማልማት እና በገጠር አካባቢዎች፣ በስኳር ልማት፣ በማዳበሪያ ፋብሪካዎችና በኢንዱስትሪ ዞን ልማት ለሚገነቡ መኖሪያና መኖሪያ ያልሆኑ ቤቶችና አገልግሎቶች እንዲሁም በዩኒቨርስቲዎች ግንባታ እና የመንግሥት ሕንፃዎች ሥራ ላይ የሚውሉ የተለያዩ ስታንዳርድ ዲዛይኖች እንዲዘጋጁ ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፡፡

ዝርዝር ተግባራት

ተግባር 1፡ የኅብረተሰቡን የቁጠባ ባሕል በማዳበር 40% የቅድሚያ ቁጠባ በማድረግ በቁጠባ ላይ በተመሠረተ ለሚገነቡ ቤቶች 3 የተለያዩ የሕንፃ ዲዛይኖች (G+8፣ G+10 እና G+14) ማዘጋጀት፣ ስለአፈጻጸሙ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

ተግባር 2፡ 2 የተሻሻሉ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የንግድና አገልግሎት ማዕከላት (G+3 እና G+4) ዲዛይኖች ማዘጋጀት፣ ስለአፈጻጸሙ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

ተግባር 3፡ በማዳበሪያ ፋብሪካዎች ለሚገነቡ 8 ቤቶች እና 13 መኖሪያ ያልሆኑ አገልግሎት የሚውሉ ለሚገነቡ በድምሩ 21 ዓይነት የመኖሪያ ቤት ዲዛይኖች ማዘጋጀት፣

ተግባር 4፡ አነስተኛ ገቢ ላላቸው የአዲስ አበባ ከተማ፣ የ2ኛ ደረጃ ከተሞች፣ የ3ኛ ደረጃ ከተሞች የከተማ ነዋሪዎች የቤት ተደራሽነት የሚያረጋግጥ 3 ዓይነት የመኖሪያ ቤት ዲዛይኖች ማዘጋጀት፣

ተግባር 5፡ በገጠር ማዕከላትና በገጠር አካባቢዎች ለሚገኙ ከፍተኛ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የገጠር ነዋሪዎች ለሚገነቡ መኖሪያ ቤቶች 3 ዓይነት ዲዛይኖች ማዘጋጀት፣

ተግባር 6፡ በሥራ ላይ ያሉ የመንግሥት ሕንፃዎችና የሕዝብ መገልገያ ተቋማት ዓይነቶችን ለመለየት 30 ዲዛይኖች እንዲሰባሰቡ ማድረግ፣

ተግባር 7፡ በፌዴራል መንግሥት የሚገነቡ 10 የተለያዩ ፕሮጀክቶች የዲዛይን ማረጋገጥና ድጋፍ የመስጠት ሥራ ማከናወን፣

ተግባር 8፡ በትላልቅ የሃገሪቱ ከተሞች ለሚገነቡ የኢንዱስትሪ ዞኖች የሚገነቡ የፋብሪካ ሼዶች፣ የመኖሪያና መኖሪያ ያልሆኑ የአገልግሎት ተቋማት 20 ዲዛይኖችን ማዘጋጀት፣

ተግባር 9፡ በከተሞች ደረጃና እርከን ላይ የተመሠረተ የቦታና የቤት ስፋ 9 ስታንዳርድ ዲዛይኖች ተዘጋጅቶ ለተግባራዊነቱ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ በአፈጻጸሙም ላይ የጽሑፍ ግብረ መልስ ማድረግ፣

ተግባር10፡ በ2004 የበጀት ዓመት በክ/ል/ከ/ሚ/ር የተዘጋጁ 67 የግንባታ ዲዛይኖች ሥራ ላይ ስለመዋላቸው አፈጻጸሙ ተረጋግጦና ዝንባሌአዊ ትንተና ተሠርቶ ለበላይ አመራር ሪፖርት ማቅረብና ለሚመለከታቸው አካላት የጽሑፍ ግብረ-መልስ ማድረግ፣

**4.3. የቤቶች፣ የህንጻ ልማት፣ አቅርቦትና አቅም ግንባታ ሥራ**

**ዓላማ፡ ለሕንፃ ግንባታ የሚሆኑ ግብዓቶች በቅድሚያ የሚዘጋጁበት ሁኔታ ማመቻቸት፣ ባለሚናዎችን ኃላፊነታቸውን በወቅቱ በማስገንዘብ የግንባታ መርሃ-ግብሮች በወቅቱና በታቀደው መሠረት እንዲፈጸም ለማስቻል ነው።**

**ጥቅል ግብ፡ በመንግስት ለሚከናወኑ የቤቶችና የህንጻዎች ግንባታ የሚያስፈልጉ የተለያዩ የኮንስትራክሽን ግብዓቶች እንዲቀርቡ ትስስር መፍጠር እና የተለያዩ ሥልጠናዎች እንዲሰጡ ይደረጋል። በፕሮጀክቶቹ ላይ በሚሳተፉ 1,000 ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች፣ ሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች እና የፕሮጀክት ባለቤቶች አማካይነት 130ሺ አዲስ የሥራ ዕድል መፈጠሩ ይረጋገጣል።**

**ዝርዝር ግቦችና ተግባራት**

**ግብ አንድ፡ በቤት ልማትና ትስስር ባላቸው ፕሮጀክቶች ግንባታ ላይ ከአስፈፃሚ ባለቤቶች፣ ከአማካሪዎች እና ከሥራ ተቋራጭ ኢንተፕራይዞች ለሚውጣጡ 1,078 አመራርና ባለሙያዎች በዲዛይን እና ግንባታ ኮንትራት አስተዳደር የክህሎት ስልጠና ይሰጣል።**

ተግባር 1፡ የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም በሚካሄድባቸው ፕሮጀክቶች (አዲስ አበባ) የሚሣተፉ ከአስፈፃሚ ባለቤት፣ ከሥራ ተቋራጭ እና ከአማካሪ ኢንተርፕራይዞች ለተውጣጡ 314 አመራሮችና ባለሙያዎች የክህሎት ስልጠና መስጠት፣

ተግባር 2፡ በ10 አዲስ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ለሚሣተፉ ከአስፈፃሚ ባለቤት፣ ከስራ ተቋራጭ እና ከአማካሪ ኢንተርፕራይዞች ለተውጣጡ 118 አመራሮችና ባለሙያዎች የክህሎት ስልጠና መስጠት፣

ተግባር 3፡ በማዳበሪያ ፋብሪካ የቤቶች ግንባታ ለሚሣተፉ ከአስፈፃሚ ባለቤት፣ ከስራ ተቋራጭ እና ከአማካሪ ኢንተርፕራይዞች ለተውጣጡ 31 አመራሮችና ባለሙያዎች የክህሎት ስልጠና መስጠት፣

ተግባር 4፡ በስኳር ልማት የቤቶች ግንባታ ለሚሣተፉ ከአስፈፃሚ ባለቤት፣ ከሥራ ተቋራጭ እና ከአማካሪ ኢንተርፕራይዞች ለተውጣጡ 295 አመራሮችና ባለሙያዎች የክህሎት ስልጠና መስጠት፣

ተግባር 5፡ በምህንድስና ሙያ አዲስ ተመራቂ የሆኑ 200 ባለሙያዎችን በአስፈላጊው የምዝገባ፣ የመለየት እና የሙያዊ ክህሎት ሥልጠና ሂደት እንዲያልፉ በማድረግ በቤቶች ልማትና ትስስር ባላቸው የመንግስት ግንባታ ፕሮጀክቶች እና በ40/60 የቁጠባ ቤቶች ልማት

ፕሮጀክቶች ላይ የሥራ ትስስር ተፈጥሮላቸው እንዲሰማሩ በማድረግ አፈፃፀሙንም በሪፖርት ማረጋገጥ፣

**ተግባር 6፡** በኢንዱስትሪ ዞን የቤቶች ግንባታ ለሚሣተፉ ከአስፈፃሚ ባለቤት፣ ከሥራ ተቋራጭ እና ከአማካሪ ኢንተርፕራይዞች ለተውጣጡ 76 አመራሮችና ባለሙያዎች የክህሎት ስልጠና መስጠት፣

**ተግባር 7፡** ለ11 ከተሞች የተሰራጩትን የአፈር ምርምራና የግንባታ ማቴሪያል ጥራት መፈተሻ መሳሪያዎች አስፈላጊው አደረጃጀት፣ የሰው ኃይል እና በጀት እንዲያሟሉ ክትትል በማድረግ መሳሪያዎቹን ለሚያንቀሳቅሱ 44 ባለሙያዎች የሥልጠና ድጋፍ መስጠት፣

**ተግባር 8፡** በቤት ልማትና ትስስር ባላቸው ፕሮጀክቶች ላይ በሚሳተፉ 1,000 ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች፣ ሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች እና የፕሮጀክት ባለቤቶች አማካኝነት 130 ሺ አዲስ የሥራ ዕድል መፍጠሩን ማረጋገጥ።

**ግብ ሁለት፡ በመንግስት ለሚከናወኑ የቤቶችና የህንጻዎች ግንባታ የሚያስፈልጉ የተለያዩ የኮንስትራክሽን 466.8 ሺ ቶን ሲሚንቶ፣ 46,600 ቶን የአርማታ ብረት፣ እና ሌሎች ግብዓቶች እንዲቀርቡ ትስስር በመፍጠር በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ እንዲቀርቡ ድጋፍና ክትትል ይደረጋል።**

**ተግባር 1፡** ለመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመንግስት ህንፃ ግንባታ ፕሮጀክት የሚያስፈልግ 466,800 ቶን ሲሚንቶ ከሃገር ውስጥ አምራቾች እየቀረበ መሆኑን ክትትል በማድረግ፣ መረጃ በመያዝ አፈፃፀሙ ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 2፡** ለመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመንግስት ህንፃ ግንባታፕሮጀክት የሚያስፈልግ 46,600 ቶን የአርማታ ብረት ከሃገር ውስጥ አምራቾችና ከውጭ ከሚገባው እንዲቀርብ ትስስር በመፍጠር አፈፃፀሙ ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 3፡** ለ83,895 ቤቶች የሚሆኑ የተለያዩ የሣኒተሪና የኤሌክትሪክ ዕቃዎች እንዲቀርብ ሁኔታዎች ማመቻቸት ከግዢ ፈጻሚ አካል ጋር እንዲተሳሰር በማድረግ የግዥና አቅርቦት አፈፃፀሙ ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 4፡** ለ83,895 ቤቶች የሚሆኑ ትራንስፎርመር እና ቆጣሪ እንዲቀርብ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ አፈፃፀሙ ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 5፡** ለመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመንግስት ህንፃ ፕሮጀክት የሚያስፈልግ 600,000 አግሮስቶን ፓኔል ከሃገር ውስጥ አምራቾች እንዲቀርብ ትስስር በመፍጠር አፈፃፀሙ ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 6፡** ለ4 የአግሮስቶን ማምረቻ ፋብሪካዎች የሚያስፈልጉ የተለያዩ ማሽነሪዎች፣ ሞልዶችና መለዋወጫዎች በሃገር ውስጥ እንዲመረት ሁኔታዎች እንዲመቻች በማድረግ ቀሪው

ከውጭ እንዲቀርብ በማድረግ አፈፃፀሙ ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 7፡** በሃገር ውስጥ የማግኒዚየም ክሎራይድ ፋብሪካ እንዲቋቋም ኃላፊነት ለተሰጠው አካል ተገቢውን ድጋፍ በማድረግ አፈፃፀሙ ላይ ክትትል በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 8፡** የማግኒዝየም ኦክሳይድ ፋብሪካ በሙሉ አቅሙ እንዲሰራ በማድረግ በዓመት 30ሺ ቶን Mgo እንዲያመርት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

**ተግባር 9፡** ለአግሮስቶን ማምረቻ ማዕከላት የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃ ግብዓቶች ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገር እንዲሟሉ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ አፈፃፀሙ ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 10፡** በ40 ከተሞች የአግሮስቶን ማምረቻ ማዕከላት እንዲቋቋሙ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

**ተግባር 11፡** ለልዩ ልዩ ፕሮጀክቶች የሚያስፈልጉ የተለያዩ የኮንስትራክሽን ማሽነሪዎች አቅርቦት ለማሟላት ክትትልና ድጋፍ በማድረግ አፈፃፀሙ ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት።

## 4.4. የኮንስትራክሽን ኮንትራት አስተዳደርና ውጤታማነት ክትትል ሥራ

**ዓላማ፡** የመንግስት የኮንስትራክሽን ሥራዎች የኮንትራት አስተዳደራቸው ግልጸኝነትና ተጠያቂነት ባለው አሠራር እየተፈጸመ መሆኑን ማረጋገጥና ለኮንስትራክሽን የሚወጣው ገንዘብ /Value for money/ ከውጤቱ ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው።

**ግብ፡** የመንግሥት ፕሮጀክቶችና የመኖሪያ ቤቶች በተያዘላቸው መርሃ-ግብር ማለትም ጊዜን፣ ወጪንና ጥራትን ባገናዘበ መልኩ እንዲጠናቀቁ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን አሠራር በማጠናከር ቀልጣፋና ውጤታማ የግንባታ አስተዳደርና የጥራት ቁጥጥር ሥርዓት እንዲኖረው ይደረጋል።

**ዝርዝር ተግባራት**

**ተግባር 1፡** ወቅታዊ የግንባታ ዋጋ ጥናት በማድረግ በመንግሥት የህንጻ ፕሮጀክቶች ውስጥ የሚያገለግል 4 ነጠላ ዋጋ እና 4 የዋጋ ኢንዴክስ በየሩብ ዓመቱ ማዘጋጀት፣

**ተግባር 2፡** በዕድገትና ትራንስፎርሜሽኑ ዘመን የታቀዱ 10 የፌዴራል የህንጻ ፕሮጀክቶችን መረጃ በማደራጀት ፕሮጀክቶቹ በተያዘላቸው የዋጋ፣ የጥራት፣ ደረጃና የጊዜ ሠሌዳ መሠረት መሠራታቸውን በማረጋገጥ አፈፃፀሙ ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 3፡** በአዲስ አበባ ከተማ እየተገነቡ ያሉ የመኖሪያ ቤት ፕሮጀክቶች ውስጥ በየካ አባዶ የሚገኙ 3 ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ዋጋ፣ ጥራት፣ ጊዜና ዘመናዊ የኮንትራት አስተዳደር ሥራ መሠራቱን በማረጋገጥ አፈፃፀሙ ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

ተግባር 4፡ የስኳር ልማት ፕሮጀክት ቤቶችና ፋብሪካ ግንባታ በተያዘላቸው ዋጋ፣ ጥራት፣ ጊዜና እና ዘመናዊ የኮንትራት አስተዳደር ሥራ መሠራቱ ማረጋገጥ፣

ተግባር 5፡ የ10 አዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ በተያዘላቸው ዋጋ፣ ጥራት፣ ጊዜና እና ዘመናዊ የኮንትራት አስተዳደር ሥራ መሠራቱን በማረጋገጥ 5 የሪፖርት ሰነዶችን ማቅረብ፣

ተግባር 6፡ የውስን ነጠላ ዋጋ አዘገጃጀት አንድ የጥናት ሰነድ እና አንድ ማኑዋል በማዘጋጀት ለክልሎችና ከተሞች በማሰራጨት ተግባራዊነቱ ላይ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

ተግባር 7፡ በ2005 በጀት ዓመት በ9 ክልሎች፣ በአዲስ አበባና ድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮች ከሚገነቡት የመንግስት ግንባታዎች ውስጥ 11 የኮንትራት ውሎችንና የኮንትራት አስተዳደር ሥራዎች ላይ ድጋፍ ማድረግ፣

ተግባር 8፡ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ከተያዙት ዋና ዋና ኘሮጀክቶች ውስጥ 10 ያህል ኘሮጀክቶች በተገባላቸው ውል መሠረት እየተፈፀመ መሆኑን በማረጋገጥ ግብረ-መልስ መስጠት፡፡

## 4.5. የቤት ልማት ፋይናንስና ማስተላለፍ ሥራ

**ዓላማ፡** **የተገነቡ ቤቶችን በአግባቡ በማስተላለፍ ጥቅም ላይ የዋለውን የቦንድ ሽያጭ ብድር እንዲመለስ ለማድረግና ለቤትልማት አስተማማኝ የፋይናንስ አቅርቦት ለማመቻቸት የህብረተሰቡን የመቆጠብ ባህል ማዳበርና ሌሎች የፋይናንስ ምንጮችን ለማፈላለግ ነው፡፡**

**ግብ፡** **ባለፉት ዓመታት የተጀመሩ 61,625 ቤቶች እንዲሁም በአዲስ አበባ በ2003 በጀት ዓመት 17,171 ቤቶች እና በ2004 የተጀመሩ 42,829 ቤቶች ግንባታን በማጠናቀቅ ለተጠቃሚዎች መተላለፉን በሪፖርት ይረጋገጣል፡፡ ቀደም ብለው ለተጀመሩት ማጠናቀቂያና በ2005 በጀት ዓት አዲስ ለሚጀመሩ 30,000 ቤቶች የሚያስፈልግ ቦንድ ብድር 6 ቢሊዮን የቦንድ ሽያጭ ሥራ ላይ የዋለ መሆኑን ክትትል በማድረግ በሪፖርት ይረጋገጣል፡፡**

**ዝርዝር ተግባራት**

ተግባር 1፡ የህብረተሰቡን የቁጠባ ባህል በማዳበር በ40/60 የቁጠባ ቤቶች ልማት ፕሮግራም ፋይናንስ አቅርቦት በአዲስ አበባ ለሚገነቡ 10ሺ ቤቶች 636.5 ሚሊዮን ብር በቁጠባ እንዲገኝ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ማረጋገጥ፣

ተግባር 2፡ የተዘረጋውን የቤቶች ማስተላለፍና የፋይናንስ ሥርዓት በማጠናከር ቀደም ሲል ከቦንድ ሽያጭ ወጪ የተደረገውን ብር 15 ቢሊዮን ብድር አመላለስ ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ማረጋገጥ፣

ተግባር 3፡ በአዲስ አበባ በተቀናጀ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ፕሮግራም ለሚገነቡ 83,895 ቤቶች እና አዲስ ለሚጀመሩ 11,105 ቤቶች ቅድመ ዝግጅት ብር 4.75 ቢሊዮን በ40/60 ቁጠባ የቤት

ልማት ፕሮግራም 10ሺ የሚገነቡ ቤቶች ብር 1.25 ቢሊዮን በአጠቃላይ ብር 6 ቢሊዮን የቦንድ ሽያጭ በመርሃ ግብሩ መሠረት ጥቅም ላይ እንዲውል ክትትል በማድረግ ማረጋገጥ፣

**ተግባር 4:** ለቤቶች ልማትና ትስስር ላላቸው ፕሮጀክቶች የሚያስፈልግ የውጭ ምንዛሬ 162 ሚሊዮን USD በስራ ላይ እንዲውል ክትትል በማድረግ ማረጋገጥ፣

**ተግባር 5:** በተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም ቀደም ሲል በክልሎችና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የተገነቡ ቤቶች እንዲሁም በአዲስ አበባ የሚገነቡ 30ሺ ቤቶች ለተጠቃሚዎች እንዲተላለፉ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ማረጋገጥ፣

**ተግባር 6:** በተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም የቦንድ አወጣጥ፣ አጠቃቀምና አመላለስ እና በመኖሪያ ቤት ቁጠባ ፕሮግራም የቁጠባ አሰባሰብና ብድር አሰጣጥ እና የቤቶች ማስተላለፍ መረጃ በተቀናጀ መልኩ ለመከታተልና ግብረ-መልስ ለመስጠት የሚያስችል ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት እንዲዘረጋ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ማረጋገጥ፣

**ተግባር 7:** በክልሎች ለኮንዶምኒየም ቤቶች ግንባታ በሀገር ውስጥ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ እንዲሆን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ማረጋገጥ፣

**ተግባር 8:** ለቤቶች ልማትና ትስስር ላላቸው የመንግስት ፕሮጀክቶች በጀት መመደቡን በማረጋገጥ ለፕሮጀክቶቹ የዋለው በጀት አፈጻጸም ላይ ክትትል በማድረግ ማረጋገጥ፣

**ተግባር 9:** በአገር አቀፍ ደረጃ አንድ ዘመናዊና የተሟላ የቤት መረጃ ዳታቤዝ እንዲደራጅ ማድረግ፣

**ተግባር 10:** በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የቤት ተጠቃሚዎች ምዝገባ መስፈርት በማዘጋጀት ቀደም ሲል የተመዘገቡ 453,287 ቤት ፈላጊዎችን ለማጣራት እንዲሁም በ3 ንዑስ ፕሮግራሞች የቤት ፈላጊዎች ምዝገባ ለማካሄድ በሚዘጋጁ መመሪያዎችና የተለያዩ ሠነዶች ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በትግበራው ላይ ግብረ-መልስ መስጠት፣

## 4.6. የኮንስትራክሽን ግብዓት ጥናትና ድጋፍ ሥራ

**ዓላማ:** በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ለሚከናወኑ የኮንስትራክሽን ሥራዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በጥናት ላይ በመመስረት እንዲሟሉ በማድረግ የመንግሥት ኘሮጀክቶች እና የግሉን ዘርፍ አፈፃፀም ውጤታማ ለማድረግ ነው።

**ግብ:** የተለያዩ 7 ጥናቶችን በማካሄድ ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚያስፈልጉ ግብዓቶች አስተማማኝ እና ቀጣይነት ባለው መልኩ መቅረባቸውና የተፈለገው ውጤት እየተገኘ መሆኑ ይረጋገጣል።

**ዝርዝር ተግባራት**

**ተግባር 1፡** በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመኑ ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚያስፈልግ የሲሚንቶ መጠን እንዲጠና ማድረግ፣

**ተግባር 2፡** በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመኑ ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚያስፈልግ የብረት መጠን እንዲጠና ማድረግ፣

**ተግባር 3፡** በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመኑ ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚያገለግሉ የአካባቢ ግብዓቶች ፍላጎት እና ምንጮች እንዲጠኑ ማድረግ፣

**ተግባር 4፡** በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመኑ ለሚገነቡ ቤቶች የሚያገለግሉ የአግሮስቶን እና ሌሎች ፕሪፋብሪኬትና ምርቶች የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎች ፍላጐት እንዲጠና ማድረግ፣

**ተግባር 5፡** በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመኑ ለሚሰሩ ግንባታዎች የሚያስፈልጉ ትራንስፎርመሮች፣ ቆጣሪዎችና የሳኒተሪ ዕቃዎች ፍላጎቶች እንዲጠኑ ማድረግ፣

**ተግባር 6፡** በዕቅድና ትራንስፎርሜሽን ዘመኑ ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚያገለግሉ/ የሚያስፈልጉ ማሽነሪዎች ፍላጎቶች እንዲጠኑ ማድረግ፣

**ተግባር 7፡** በሀገር ውስጥ ያለውን የሲሚንቶ አቅርቦት መሠረት ያደረገ ሲሚንቶ በስፋት መጠቀም የሚያስችሉ ፕሮጀክቶችና ምርቶች ለመለየት ጥናት በማካሄድ ሲሚንቶ በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ፡፡

## 4.7. የቤቶችና የህንጻ ፕሮጀክቶች ክትትልና ግብረ-መልስ ሥራ

**ዓላማ፡** **በተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራምና በመንግስት የተለያዩ የህንፃ ፕሮጀክቶች አስፈላጊውን ክትትል፣ ግምገማና ድጋፍ በማድረግ በቀጣይ መሟላት ወይም መስተካከል የሚገባቸውን ጉዳዮች በመለየት ለፕሮጀክቶች አስፈላጊ የክትትል ስርዓት በመዘርጋት ለመደገፍ ነው፡፡**

**ግብ፡** **በተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም ቀደም ሲል የተጀመሩ የጋራ መኖሪያ ቤቶች፣ በአዲስ አበባ ከተማ የሚጀመሩ ቤቶች፣ የስኳር ፋብሪካ ግንባታ፣ የማዳበሪያ ፋብሪካ ቤቶች ግንባታ፣ የአዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ፣ አነስተኛ ገቢ ያላቸው ዜጎች የመኖሪያ ቤት ፕሮግራም ቤቶች ግንባታ፣ የ40/60 ፕሮግራም ቤቶች ግንባታ እና የተለያዩ የመንግስት ህንፃ ፕሮጀክቶች ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግንባታዎች በተያዘላቸው መርሃ-ግብር እንዲጠናቀቁ ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፡፡**

### ዝርዝር ተግባራት

**ተግባር 1፡** በአዲስ አበባ ቀደም ሲል የተጀመሩ እና በ2005 የሚጀመሩ 83,895 ሺህ ቤቶች እንዲጠናቀቁ እንዲሁም በ2006 በጀት ዓመት የሚጀመሩ 35 ሺህ ቤቶች ቅድመ ዝግጅት እንዲጠናቀቅ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ማረጋገጥ፣

**ተግባር 2፡** በአዲስ አበባ በ40/60 ቁጠባ ቤቶች ልማት ፕሮግራም የሚገነቡ 10ሺ ቤቶች 40% ግንባታ እንዲከናወን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ማረጋገጥ፣

**ተግባር 3፡** በአዲስ አበባ አነስተኛ ገቢ ላላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የመኖሪያ ቤት ልማት ፕሮግራም 35ሺ ቤቶች ግንባታ አፈፃፀም ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ማረጋገጥ፣

**ተግባር 4፡** ከስኳር ኢንዱስትሪ ጋር በተያያዘ በጣና በለስ፣ በደቡብ ኦሞ እና ወልቃይት በግንባታ ሂደት ላይ በሚገኙት 3461 ቤቶች ከነመገልገያቸው በ2005 እንዲጠናቀቁና በ2005 ወደ 1700 ቤቶች ግንባታ አፈጻጸም ቢያንስ 60% እንዲደርስ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 5፡** በ10 አዲስ ዩኒቨርስቲዎች ቀደም ሲል ግንባታቸውን የጀመሩት እንዲጠናቀቁና አዲስ የሚገነቡ 475 የመኖሪያና የመማሪያ ህንፃዎች ግንባታ ላይ በክትትልና ድጋፍ በማረጋገጥ ግብረ መልስ መስጠት፣

**ተግባር 6፡** በማዳበሪያ ፋብሪካ የሚገነቡ 530 ቤቶች ግንባታ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

**ተግባር 7፡** የኢንዱስትሪ ዞን ልማት ፕሮግራሞች በመርሃ-ግብሩ መሠረት እየተፈፀሙ መሆኑን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

**ተግባር 8፡** የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የማምረቻ እና የመሸጫ ማዕከላት ተግባራዊነት በመከታተልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 9፡** በየካ አባዶ ቤቶች ግንባታ ልዩ ድጋፍ በማድረግ በኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሻለ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ልምድ መቀመር፣

**ተግባር 10፡** እስከ 20 ለሚደርሱ ለተለያዩ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሚገነቡ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ወደ ግንባታ ለመግባት የሚያስችላቸው ልዩ ልዩ ድጋፍ በመስጠት በፕሮጀክት አፈፃፀም ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 11፡** በግሉ ዘርፍ የሚካሔድ ግንባታ በ7 ከተሞች ክትትል በማድረግ ለከተማ አስተዳደሮች ግብረ-መልስ መስጠት፡፡

### 4.8. የፌዴራል መንግስት ቢሮ ግንባታ ሥራ

**ዓላማ፡** **በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የሚሠሩ የተለያዩ የፌዴራል መንግስት ቢሮዎች ግንባታ ሥራዎች አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች የሚሞከርበት፤ በዘመናዊ መልክ የተደራጁ የግብዓት አቅርቦት ማኔጅመንት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ የሚደረግበት ወቅታዊ የነጠላ የዋጋ ተከላ** (Unit rate build up) **ሥርዓት በመተግበር ፍትሃዊ የሆነ የግዥ ሂደት ግምገማ ሥርዓት እንዲኖር የሚሠራበት፤ ከወጪ ቆጣቢነት አንፃር በጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጀ ማህበራት ተሳትፎ ያረጋገጠ መሆን ያለበት፣ የ**(Application software) **በመጠቀም**

የኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ እና ማኔጅመነት የሚሞከርበት፤ በአጠቃላይ የምርጥ ተሞክሮ ማዕከል (center of excellence) እንዲሆኑ ለማድረግ ነው፡፡

**ጥቅል ግብ፡** በፌዴራል መንግስት ቢሮዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ዘመናዊ የኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂና ማኔጅመንት ሥርዓት የሚተገበርበት እና የምርጥ ተሞክሮ ማዕከል (center of excellence) እንዲሆን በማድረግ በፌዴራል መንግስት በተለያየ የግንባታ አፈጻጸም ደረጃ ላይ የሚገኙትን 14 የመንግስት ሚኒስቴር ጽ/ቤቶችና ኤጀንሲዎች ያሉባቸውን ያልተመቻቸ የሥራ አካባቢ በማስወገድ ደረጃውን የጠበቀ የቢሮ ግንባታ እስከ ሙሉ ፋሲሊቲዎች ዝግጁ ይደረጋል፡፡

**ዝርዝር ተግባራት**

ተግባር 1፡ ኘሮጀክቶችን በዘመናዊ መልክ ለመምራት የሚያስችል የዘመናዊ ኘሮጀክት ማኔጅመንት ሥርዓት እንዲዘረጋ በማድረግ የግንባታ ኘሮጀክቶች COE ሆነው እንዲያገለግሉ ማድረግ፣

ተግባር 2፡ ለፌዴራል መንግሥት ቢሮዎች ግንባታ የሰው ኃይል፣ የአሠራር ማኑዋል እንዲሟሉና የሎጂስቲክስ ሥርዓቱን በመዘርጋት የበጀት አጠቃቀሙ 100% እንዲሆን ማድረግ፣

ተግባር 3፡ የመጀመሪያ ደረጃ ርክክብ የተፈጸመባቸው የውጭ ጉዳይ እና የግብርና ሚኒስቴር ህንፃዎች የመጨረሻ ርክክብ መፈጸም፣

ተግባር 4፡ የፍትህ ሚኒስቴር ቢሮ ግንባታ ቀሪ 25% ግንባታ በማጠናቀቅ የመጀመሪያ ርክክብ እንዲፈፀም ማድረግ፣

ተግባር 5፡ የሦስት ቢሮዎች (ስታስቲክስ፣ ኘሬስ፣ ገቢዎችና ጉምሩክ) ቀሪ 40% ግንባታ በማጠናቀቅ ርክክብ እንዲፈፀም ማድረግ፣

ተግባር 6፡ የሦስት ቢሮዎች (ፌዴራል ማረሚያ ቤቶች፣ ኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን እና ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚ/ር) ቢሮ ግንባታ ቀሪ 80% ግንባታ በማጠናቀቅ ርክክብ መፈፀም፣

ተግባር 7፡ የመረጃ ደህንነት ቢሮ ቀሪ 20% የህንፃ ግንባታ በማጠናቀቅ ርክክብ እንዲፈፀም ማድረግ፣

ተግባር 8፡ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ቢሮ ህንፃ የመጀመሪያ ምዕራፍ ቀሪ 90% ግንባታ ውስጥ 60% የሚሆነው በበጀት ዓመቱ እንዲጠናቀቅ ማድረግ፣

ተግባር 9፡ የሦስት ቢሮዎች ግንባታ (ፌዴራል ዋና ኦዲተር፣ ሲቪል ሰርቪስ እና ኢንዱስትሪ ሚ/ር ህንፃዎች) ቀሪ 90% ግንባታ በማጠናቀቅ ርክክብ መፈጸም፣

ተግባር 10፡ አዳዲስ ተጨማሪ 5 ቢሮዎች ግንባታ ማከናወን የሚያስችል የቅድመ ዝግጅት እንዲከናወን ማድረግ፣

ተግባር 11፡ ለቢሮዎች ግንባታ አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ ግብዓቶች እንዲሟሉ እና የተለያዩ ንዑስ ሥራ ተቋራጮች እንዲመረጡ ማድረግ፣

ተግባር 12፡ ለቢሮዎች ግንባታ ለተለያዩ ሥራ ተቋራጮች የሥራ ትስስር እንዲፈጠር ማድረግ፡፡

## 5. የከተሞች የመሠረተ ልማት ግንባታና ማኔጅመንት(ጥገና) ሥራዎች

**ጥቅል ዓላማ:** ለከተሞች ልማት የሚውል ፈንድ በማፈላለግና በማመቻቸት እና የከተሞች የተቀናጀ የመሠረተ ልማት አቅርቦት ሥርዓት በመዘርጋት ከተሞች ለነዋሪዎቻቸው ምቹና ቀጣይነት ያለው የልማት ማዕከልነታቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡

**ጥቅል ግብ:** ለከተሞች ልማት የሚውል ፈንድ በማፈላለግና በማመቻቸት እና የከተሞች የተቀናጀ የመሠረተ ልማት አቅርቦት ሥርዓት በመዘርጋት በከተሞች በ3 ቢሊዮን ብር እና ክልሎች በሚመድቡት በጀት ሰፊ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ይካሄዳሉ፡፡

### 5.1. የፕሮጀክት ዝግጅት፣ ፋይናንሲንግ አፈጻጸም ክትትልና ድጋፍ ሥራ

**ዓላማ:** ከተለያዩ አበዳሪና ለጋሽ ድርጅቶች የፋይናንስ ምንጮችን በማፈላለግና በማመቻቸት 3 ቢሊዮን ብር ለከተሞች ልማት እንዲውል ማድረግ ነው፡፡

**ግብ:** 6 ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ከተለያዩ አበዳሪና ለጋሽ ድርጅቶች የፋይናንስ ምንጮችን በማፈላለግና በማመቻቸት 3 ቢሊዮን ብር ለከተሞች መሠረተ ልማት እንዲውል ይደረጋል፡፡

**ዝርዝር ተግባራት**

**ተግባር 1:** የተለዩ የትኩረት አቅጣጫዎችን መሰረት በማድረግ 6 የፕሮጀክት ሰነድ ማዘጋጀት፣

**ተግባር 2:** የተዘጋጁ የፕሮጀክት ሰነዶችን ለሚመለከታቸው አካላት በማቅረብ እና በማግባባት 3 ቢሊዮን ብር ማስገኘት፣

**ተግባር 3:** የተዘጋጁትን የፕሮጀክት ሰነዶች መነሻ በማድረግና በሚደረገው ስምምነት መሠረት ለ3 ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ሰነድ ማዘጋጀት፣

**ተግባር 4:** በተዘጋጁት 3 የፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ሰነዶች ላይ ለ62 ፈጻሚዎችና አመራሮች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፤

**ተግባር 5:** በ31 ከተማ አስተዳደሮች ለሚገኙ ለ62 አመራሮችና ባለሙያዎች በፕሮጀክት ሥራ አመራር ላይ ስልጠና፣

**ተግባር 6:** በከተሞች ልማትና መልካም አስተዳደር ላይ የሚያማክሩ የ23 አማካሪዎችን ግዥ መፈጸም፣

**ተግባር 7:** በከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ አማካይነት 35 የተለያዩ የቢሮ መገልገያ ዕቃዎች እና 20 ተሽከርካሪዎችን በዓለም አቀፍ ግዥ መፈጸም፣

**ተግባር 8:** የተለያዩ 11 የአለም አቀፍ ግዥዎችን በሌተር ኦፍ ክሬዲት (L/C) እንዲፈጸም ማድረግ፣

**ተግባር 9:** ከመደበኛ ከብድርና ከእርዳታ የተገኘውን ፈንድ የበጀት እቅድ በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል እንዲቀርብ ማድረግ፣

**ተግባር 10፡** የተጀመሩት 3 ፕሮጀክቶች በፋይናንሻል ማኔጅመንት እና በብድርና እርዳታ ስምምነቱ መሰረት እንዲፈጸም ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤

## 5.2. የከተሞች የተቀናጀ መሰረተ ልማት አቅርቦት ሥራ አመራር ሥራ

**ዓላማ፡** የከተሞች የተቀናጀ መሰረተ ልማት አቅርቦት ስትራቴጂን ለማስፈጸም የሚያስችል አደረጃጀት በየደረጃው እንዲፈጠር በማድረግ የከተሞችን የማስፈጸም አቅም መገንባት ነው፡፡

**ጥቅል ግብ፡** ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የከተሞች የተቀናጀ መሰረተ ልማት አቅርቦት ስትራቴጂን መሠረት በማድረግ በየደረጃው አደረጃጀት በመፍጠር እና በጀት በመመደብ ከተሞች ለነዋሪዎቻቸው ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ መሠረተ ልማቶችንና አገልግሎቶችን እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡

**ዝርዝር ግቦችና ተግባራት**

**ግብ አንድ፡** የከተሞች የተቀናጀ መሰረተ ልማት አቅርቦት ስትራቴጂን ለማስፈጸም የሚያስችል አደረጃጀት በየደረጃው እንዲፈጠር በማድረግ የከተሞችን የማስፈጸም አቅም ይገነባል፡፡

**ተግባር 1፡** የከተሞች የተቀናጀ የመሠረት ልማት አቅርቦት ስትራቴጂ ለማስፈፀም የሚስችል አደረጃጀት በየደረጃዉ እንዲፈጠር ድጋፍና ክትትል በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 2፡** የከተሞች የተቀናጀ የመሠረት ልማት አቅርቦት ስትራቴጂና ስልት እንዲተገበር ለ122 የከተማ አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት፣

**ተግባር 3፡** የከተሞች የተቀናጀ የመሠረት ልማት አቅርቦት ስትራቴጂና ስልት በ31 ከተሞች እንዲተገበር ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 4፡** በካፒታል ኢንቨስትመንት ዕቅድ፣ በአሴት ማኔጅመንት ዕቅድ፣ በከተሞች በአካባቢ ጥበቃና ማህበራዊ ደህንነት፣ በገቢ ማሳደጊያ ዕቅድ፣ በግዥ ዕቅድ እንዲሁም በኮንትራት አስተዳደር አዘገጃጀትና አተገባበር የተገኘ የአፈፃጸም በአጠቃላይ 6 ተሞክሮዎችን በመቀመር እንዲሰፋፉ ማድረግ፣

**ተግባር 5፡** ለ31 ከተሞች አገልግሎት የሚዉል 3 ስታንዳርድ ዲዛይን እንዲዘጋጁ ማድረግ፣

**ተግባር 6፡** በፌዴራልና ክልል መንግስታት የማዘጋጃቤታዊ መሰረተ ልማት ድጎማ (MIG) ሞዴል መመሪያ እንዲሁም በከተሞች የመሰረተ ልማት አቅርቦት በተቀናጀ ሁኔት ለማስፈፀም የሚያስችል መመሪያ በማዘጋጀት በሁሉም ክልሎች እንዲተገበር ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 7፡** በተዘጋጀዉ የከተሞች የተቀናጀ የመሰረተ ልማት አቅርቦት መመሪያ በከተሞች ተፈፃሚ እንዲሆን ለ62 አመራሮችና ባለሙያዎች ሥልጠና በመስጠት አተገባበሩ ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 8፡ በከተሞች የመሰረት ልማት አቅራቢ ተቋማት ቅንጅታዊ ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል መመሪያ ማዘጋጀት፣**

**ግብ ሁለት፡ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድን ከማሳካት አኳያ የከተሞች የተቀናጀ መሰረተ ልማት አቅርቦት ስትራቴጂን መሠረት በማድረግ ክልሎችና ከተሞች የተለያዩ የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን ለመገንባት በጀት በመመደብ ግንባታዎች ማካሄዳቸው ይረጋገጣል፡፡**

**ተግባር 1፡** በክልሎችና በከተሞች በጀት ተመድቦ 1,677 ኪ.ሜ የውስጥ ውስጥ መንገድ /በኮብልስቶን/ መገንባታቸውን በመከታተል ማረጋገጥ፣

**ተግባር 2፡** በክልሎችና በከተሞች በጀት ተመድቦ 1,630 ኪ.ሜ የጎርፍ እና የዝናብ ውሃ ማስወገጃ መገንባታቸውን በመከታተል ማረጋገጥ፣

**ተግባር 3፡** በክልሎችና በከተሞች በጀት ተመድቦ 192 የደረቅ ቆሻሻ መጣያ ቦታዎች መገንባታቸውን በመከታተል ማረጋገጥ፣

**ተግባር 4፡** በክልሎችና በከተሞች በጀት ተመድቦ 134 የፍሳሽ ቆሻሻ መድፊያ ቦታዎች መገንባታቸውን በመከታተል ማረጋገጥ፣

**ተግባር 5፡** በክልሎችና በከተሞች በጀት ተመድቦ 165 ዘመናዊ ቄራዎች መገንባታቸውን በመከታተል ማረጋገጥ፣

**ተግባር 6፡** በክልሎችና በከተሞች በጀት ተመድቦ 971 የኢንዱስትሪ ዞኖች መገንባታቸውን በመከታተል ማረጋገጥ፣

**ተግባር 7፡** በክልሎችና በከተሞች በጀት ተመድቦ 59 መሸጫ ቦታዎች መገንባታቸውን በመከታተል ማረጋገጥ፣

**ተግባር 8፡** በክልሎችና በከተሞች በጀት ተመድቦ 10,030 የማምረቻ ሼዶች መገንባቱን በመከታተል ማረጋገጥ፣

**ተግባር 9፡** በክልሎችና በከተሞች በጀት ተመድቦ 569 የገበያ ማዕከላት መገንባታቸውን በመከታተል ማረጋገጥ፡፡

### 5.3. የከተሞች መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮጀክት (ULGDP)

**ዓላማ፡** **የከተሞች መሰረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮጀክት (ULGDP) ተግባራዊ በሚሆንባቸው ከተሞች የልማት ፕሮጀክቶችን የመፈጸም አቅም እንዲጎለብት ማድረግ ነው፡፡**

**ግብ፡** **የከተሞች መሰረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮጀክት (ULGDP) ተግባራዊ በሚሆንባቸው 19 ከተሞች የልማት ፕሮጀክቶችን የማቀድና የመፈጸም አቅም እንዲጎለብት ይደረጋል፡፡**

**ዝርዝር ተግባራት**

ተግባር 1፡ በካፒታል ኢንቨስትመንት እቅድ ዝግጅት፣ በግዥ ስርዓት፣ በአሴት ማኔጅመንት፣ በአከባቢና ማህበራዊ ደህንነት ላይ ለ256 የክልልና የከተማ ስራ አመራርና ባለሙያዎች ስልጠና በመስጠት በቂ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ማድረግ፣

ተግባር 2፡ በ19 ከተሞች የግዥ ስርዓትና የኮንትራት አስተዳደር ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለው ሁኔታ እንዲፈጸም ድጋፍና ክትትል በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

ተግባር 3፡ በከተሞቹ የፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት እንዲረጋገጥ አፈጻጸሙ ላይ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

ተግባር 4፡ ከከተሞች መሰረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮጀክት (ULGDP) በተገኘው ፈንድ ተጠቃሚ በሆኑ 19 ከተሞች የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች (90.3 ኪ.ሚ የድንጋይ ንጣፍ፣ 181.06 ኪ.ሜ የጎርፍና የውሃ ማስወገጃ መስመሮች፣ 11 የደረቅ ቆሻሻ መጣያ ቦታዎች፣ 1 የፍሳሽ ቆሻሻ መድፊ ቦታ እና 5 የኢንዱስትሪ ዞኖች) እንዲገነቡ በየሩብ ዓመቱ ክትትል በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

ተግባር 5፡ በ19 ከተሞች ለሚከናወኑ ግዢዎች የግዥ ዕቅድ ዝግጅት እና የአማካሪና የግንባታ ሥራ ጨረታ ላይ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

ተግባር 6፡ በአፈጻጸም ድጋፍ በጀት ለሚከናወኑ ግዢዎች የግዢ ዕቅድ ዝግጅት እንዲሁም ለብሔራዊና ለዓለም አቀፍ ግዥዎች ድጋፍና ክትትል በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፡፡

## 5.4. ያልተማከለ የከተሞች አስተዳደር ፕሮጀክት (UGDP)

**ዓላማ፡** **የከተሞችን ሁለንተናዊ አቅም በመገንባት ከተሞች ፍትሃዊና ቀጣይነት ያለው የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሠረተ ልማት አገልግሎት በማቅረብ ነዋሪዎቻቸውን የልማቱ ቀጥተኛ ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግ ነው፡፡**

**ግብ፡** **የከተሞች ያልተማከለ መልካም አስተዳደር ፕሮጀክት (UGDP) ተግባራዊ በሚሆንባቸው 8 ከተሞች የተለያዩ የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶችን የማቀድና የመፈጸም አቅም እንዲጎለብት ይደረጋል፡፡**

**ዝርዝር ተግባራት**

ተግባር 1፡ በ8 ከተሞች የፕሮጀክቶች ማስጀመሪያ ፕሮፖዛሎችን በመገምገም፣ በስትሪንግ ኮሚቴ በማፀደቅ 4 የማስፈፀሚያ ሰነዶችን[4] ማዘጋጀት፣

ተግባር 2፡ በ8 በከተሞች ለሚከናወኑ 8 ፕሮጀክቶች የጥናትና ዲዛይን ሥራዎች በተሟላ መንገድ እንዲከናወኑ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

[4] /operational manual, project cycle management guidelines and procedures, and project management information systems, environmental management and social framework/

**ተግባር 3፡** በ8 ከተሞች ለሚከናወኑ ፕሮጀክቶች የኮንትራክተር ግዢዎች እንዲፈፀሙ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

**ተግባር 4፡** በ3 ከተሞች (በይርጋለም 1.5 ኪ.ሜ፣ በአድዋ 2 ኪ.ሜ እና በጋምቤላ 1.0 ኪ.ሜ) የፋይናንስ አቅርቦት፣ የድጋፍና የክትትል ሥርዓት በማመቻቸት በዕቅድ ዘመኑ የማኅበራዊና አካባቢ ደኅንነትን መሠረት ያደረገና የጥራት ደረጃውን የጠበቀ በድምሩ 4.5 ኪ.ሜ የኮብልስቶን መንገድ እንዲገነባ ማድረግ፣

**ተግባር 5፡** በ4 ከተሞች (በይርጋለም 1.5 ኪ.ሜ፣ በአድዋ 4.3 ኪ.ሜ፣ በአሶሳ 4.5 ኪ.ሜ እና በጂጂጋ 5 ኪ.ሜ) የፋይናንስ አቅርቦት፣ የድጋፍና የክትትል ሥርዓት በማመቻቸት በዕቅድ ዘመኑ የማኅበራዊና አካባቢ ደኅንነትን መሠረት ያደረገና የጥራት ደረጃውን የጠበቀ በድምሩ 15.5 ኪ.ሜ የጎርፍ ማስወገጃ ቦይ እንዲገነባ ማድረግ፣

**ተግባር 6፡** የኢኮኖሚ የማኅበራዊና የአካባቢ ደኅንነትን መሠረት ያደረጉ 2 ቄራዎች በጋምቤላና ነቀምት ከተሞች ጥራታቸው ተጠብቆ እንዲገነቡ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

**ተግባር 7፡** የኢኮኖሚ የማኅበራዊና አካባቢ ደኅንነትን መሠረት ያደረጉ 2 የደረቅ ቆሻሻ ፕሮጀክቶች በደብረ-ማርቆስ እና በሰመራ ከተሞች ጥራታቸው ተጠብቆ እንዲገነቡ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

**ተግባር 8፡** የኢኮኖሚ የማኅበራዊና ከባቢያዊ ደኅንነትን መሠረት ያደረጉ አንድ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ፕሮጀክት በደብረ-ማርቆስ ከተማ እና አንድ የገበያ ማዕከል በነቀምት ከተማ ጥራታቸው ተጠብቆ እንዲገነቡ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

**ተግባር 9፡** ለቆሻሻ አወጋገድ የአገልግሎት መስጫ 6 ተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች እንዲገዙ ማድረግ፣

**ተግባር 10፡** በ8 ከተሞች ለሚከናወኑ ፕሮጀክቶች የኮንትራት አስተዳደር ሥርዓትን መሠረት ያደረገ የአማካሪ ድርጅቶችና የኮንትራክተሮች ክፍያ መፈጸም፣

**ተግባር 11፡** በድሃ ተኮር ፕሮጀክት (LUSUP) የሚደገፉ የ8 ከተሞች ልማት ፕሮጀክቶችን በራስ ኃይል ደሃውን ባሳተፈ መልኩ ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ፣

**ተግባር 12፡** የድሃ ተኮር ፕሮጀክቶች ትግበራ የተሻለ አፈጻጸም ያላቸው 4 ከተሞች እውቅናና ማበረታቻ እንዲያገኙ በማድረግ ቀጣይ ድሃ ተኮር የሆኑ ፕሮጀክቶች እንዲተገበሩ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

**ተግባር 12፡** በሀገሪቱ ባለው እውቀትና አዳዲስ ፈጠራዎች መካከል ያለውን ክፍተት ለማጥበብና አዳዲስ ፈጠራዎችንም ለማበረታታት ጥናት በማካሄድ በከተሞች የሚታዩ ተግዳሮቶችን የሚፈቱ የፕሮጀክት ሃሳቦችና ግለሰቦች/ቡድኖች እንዲበረታቱ ማድረግ፡፡

## 6. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ሬጉላቶሪ ሥራዎች

ጥቅል ዓላማ:የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ለሃገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት መፋጠን ተገቢውን ሚና እንዲጫወት ለማድረግ እና የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ለማሳደግ ነው።

ጥቅል ግብ፡ የዓለም አቀፍ ግዢ በሚጠይቁ ግንባታዎች ላይ የተወዳዳሪነት አቅም ያላቸው 10 የአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮች እና 3 አማካሪዎች እንዲፈጠሩ፣ 3,000 መለስተኛ የግንባታ ባለሙያዎች የሚመዘኑበትና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚያገኙበት ሥርዓት በመዘርጋት ብቃታቸው እና ለልማት ያላቸው አስተዋፅኦ እንዲያድግ ይደረጋል፣ 27 አዲስ የኮንስትራክሽን መሳሪያ አከራዮችን እንዲደራጁ እንዲሁም በዕቅድ ዘመኑ 2 አዲስ የግንባታ ዕቃዎችና 12 የአገነባብ ቴክኖሎጂ ላይ ጥናት በማካሄድ የሀገር ውስጥ የግንባታ ዕቃዎች የማቅረብ አቅም እንዲያድግ ይደረጋል።

### 6.1. የአሠራር ሥርዓት ማሻሻያና የግሉ ዘርፍ አቅም ግንባታ (የሕግ ዝግጅትና ማስፈጸም) ሥራ

ዓላማ፡ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ወጥ በሆነ ሬጉላቶሪ ሥርዓት እንዲመራ ለማድረግ የሚያስችሉ መሪ ሠነዶችን ማዘጋጀትና የማስፈፀሚያ ሥርዓት ዘርግቶ በሥራ ላይ መዋሉን በክትትልና ቁጥጥር ማረጋገጥ ነው።

ጥቅል ግብ፡ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ወጥ በሆነ ሬጉላቶሪ ሥርዓት እንዲመራ ለማድረግ የሚያስችሉ 26 ያህል መሪ ሠነዶችን (ሕጎች፣ ደንቦች፣ ስታንዳርዶች፣ ማንዋሎችና መመሪያዎች) ማዘጋጀትና የማስፈፀሚያ ሥርዓት ዘርግቶ በሥራ ላይ መዋሉን በክትትልና ቁጥጥር ይረጋገጣል። በዘርፉ የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት 50 በመቶ ይደርሳል።

ዝርዝር ግቦችና ተግባራ

ግብ አንድ፡ ከአጋር አካላት ጋር በመሆን የሀገር ውስጥ ባለሃብቶችና ኢንተርፕራይዞች የሚሳተፉበት በባቡር፣ በመንገድና ለሃይል ማመንጫ የመወዳደሪያ መስፈርት ይዘጋጃል፣ በ3ቱ ዘርፎች የሚሳተፉ ሥራ ተቋራጮች ቁጥር 76 እና አማካሪ ድርጅቶች ቁጥር 39 እንዲደርስ ይደረጋል። በዘርፉ የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት 50 በመቶ ይደርሳል።

ተግባር 1፡ ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን፣ ከኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና ከኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን ጋር በቅንጅት በመስራት ለመንገድ፣ ለባቡር መስመር እና ለሃይል ማመንጫ የግንባታ ግዥ የሀገር ውስጥ ተቋራጮች የውድድር ዕድል እንዲያገኙ በ3ቱ ዘርፎች የሚጠየቁ የመወዳደሪያ መስፈርት ተሻሽሎ እንዲዘጋጅ ማድረግ፤

ተግባር 2፡ ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን፣ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና ከኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን ጋር በቅንጅት በመስራት በመንገድ፣ በኃይል እና

ባቡር ዘርፍ የሚሳተፉ ሥራ ተቋራጮች 76 እና አማካሪ ድርጅቶች 39 እንዲደርስ መከታተልና መደገፍ፣

**ተግባር 3፡** በዘርፉ የአቅም ግንባታ ኘሮጀክት አፈጻጸም በ50 በመቶ የሴቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማሳደግ የሚያበረታቱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

**ተግባር 4፡** ለመሣሪያ መግዣ ገንዘብ የሚቆጥቡ 300 ሥራ ተቋራጮች የማሚያ ብድር ከባንኮች የሚያገኙባቸው ሁኔታዎች ማመቻቸት፣

**ተግባር 5፡** አለም አቀፍ ተወዳዳሪነት አቅም ያላቸው 10 ሥራ ተቋራጮችን እና 3 አማካሪዎች እንዲፈጠሩ ማድረግ፣

**ግብ ሁለት፡ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን አሠራር የሚያሳልጡ የተለያዩ 26 የሕግ ማዕቀፎች እንዲዘጋጁና እንዲሻሻሉ ይደረጋል።**

**ተግባር 1፡** በውጭ ኃይል የሚዘጋጁ 15 ያህል የማስፈፀሚያ ሠነዶች ዝግጅት ሥራ ተጠናቆ እና ፀድቆ ወደ አፈፃፀም እንዲገባ ክትትል ማድረግ፣

**ተግባር 2፡** በመሥሪያ ቤቱ አቅም የሚዘጋጁ የማስፈፀሚያ 6 ሠነዶች[5] ዝግጅት ሥራ ተጠናቆ እና ፀድቆ በሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፤

**ተግባር 3፡** ለኢንዱስትሪው አስፈላጊ የሆኑ በጥናት የሚለዩ ተጨማሪ 5 የማስፈፀሚያ ሰነዶች በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ፣

**ተግባር 4፡** በጅምር ላይ የሚገኘው የንዑስ ሥራ ተቋራጭነት፣ የተባባሪ (Local Counterpart) እና የሽሙር (Joint Venture) አሰራር ሥርዓት ጥናት በማጠናቀቅ እና የሕግ ማዕቀፍ በመቅረፅ በሥራ ላይ እንዲውል በማድረግ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

**ተግባር 5፡** አማራጭ ያለመግባባት አፈታት ዘዴዎች እንዲተዋወቁ እና በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ከግልግል ተቋም ጋር የጋራ ዕቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ፣

**ተግባር 6፡** በአገሪቱ ያለው የግዥ አፈፃፀም ሥርዓት ወጥ ለማድረግ የሚያስችል መመሪያ/ማኑዋል ከመንግስት ግዥ ኤጀንሲ ጋራ በጋራ አዘጋጅቶ ተግባራዊ በማድረግ አፈጻጸሙን መከታተል።

**ግብ ሦስት፡ የሕንጻ አዋጁ ተግባራዊ በሚደረግባቸው በ271 ከተሞች የግንባታ እና የመጠቀሚያ ፈቃድ መመሪያዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ክትትል ይደረጋል።**

**ተግባር 1፡** የሕንፃ አዋጁ፣ ደንቡ እና ተጓዳኝ መመሪያዎች ተግባራዊ እንዲደረጉ በየሩብ ዓመቱ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤

---

[5] (የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ም/ቤት ማቋቋሚያ ደንብ፣ የተጨማሪ የስራ መደቦች የምዝገባ መስፈርት መመሪያ፣ የመሠረተ-ልማትና ቅንጅታዊ አሠራር ረቂቅ ደንብ፣ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች የኪራይ አገልግሎት ረቂቅ መመሪያ፣ ጊዜያዊ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ጤናና ደህንነት መመሪያ እና የአሠሪ፣ ሥራ ተቋራጭና የፋይናንስ ተቋማት የሶስትዮሽ የብድር አሠጣጥ መመሪያ ናቸው)

**ተግባር 2፡** ከክልሎች ጋር በጋራ በመስራት የሕንፃ አዋጁ ተግባራዊ በሚሆንባቸው 271 ከተሞች አስፈላጊውን አደረጃጀት እንዲፈጠር እና ወደ አፈፃፀም እንዲገባ የተጀመረው ሥራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረግ፤

**ተግባር 3፡** የሕንፃ አዋጁ ተፈፃሚ በሚሆንባቸው 271 ከተሞች የሚገነቡ 12,000 የሚገመቱ ሕንፃዎች በአዋጁ መሠረት የግንባታ ፈቃድ እንዲያገኙ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣

**ተግባር 4፡** የሕንጻ ህጉ በሚፈጸምባቸው 271 ከተሞች ውስጥ የሚጠናቀቁ 3,000 ሕንጻዎች የመጠቀሚያ ፈቃድ እንዲያገኙ ማድረግ።

## 6.2. የሰው ኃይል ልማትና ደረጃዎች ዝግጅት ሥራ

**ዓላማ፡** **ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የሚያስፈልግ ወቅታዊ የሰው ሀይል መረጃ በመሰብሰብ፣ በመተንተንና የሰው ሀይል ፍላጎት ጥናት በማድረግ ለአጠቃቀም ዝግጁ ማድረግ፣ የስልጠና ፍላጎትን በዓይነትና በደረጃ መለየት፣ የአፈጻጸም መመሪያዎችን ማዘጋጀት፣ አማራጭ ስልቶችን መቀየስ፣ የምዘና ሂደቶችን መከታተል፣ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የሰው ሀይል ልማት ዕቅድ ማዘጋጀት፣ የባለድርሻ አካላት ሚናን ለይቶ ማሳወቅ፣ የምክክር መድረኮችን ማመቻቸት እና ለተጠቃሚው አካል የተዘጋጀውን መረጃ ማሰራጨት ነው።**

**ግብ፡** **በኮንስትራክሽን ዘርፍ የሚገኙትን 250,000 ዝቅተኛ፣ መለስተኛና ከፍተኛ የግንባታ ባለሙያዎች የሚመዘኑበት የሙያ ዓይነቶችና ደረጃዎች ተዘጋጅቶ በምዘና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚያገኙበት ሥርዓት በመዘርጋት ብቃታቸው እና ለልማት ያላቸው አስተዋፅኦ ያድጋል።**

### ዝርዝር ተግባራት

**ተግባር 1፡** ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በቅንጅት በመስራት 250,000 ዝቅተኛና መለስተኛ ባለሙያዎች በምዘና ማዕከላት አማካኝነት በልዩ ልዩ መስክ ምዘና በማካሄድ ሰርቲፋይ እንዲሆኑ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

**ተግባር 2፡** ምዘናውን ማለፍ ይሳናቸዋል ተብሎ ለሚገመቱ ለ64,000 ዝቅተኛና መለስተኛ ባለሙያዎች የክህሎት ማሚያ የኩባንያና የትብብር ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣

**ተግባር 3፡** ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት አስፈላጊ የሆኑ የየዓመቱን የብቁ ሙያተኛ ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ በሙያ ዓይነት፣ በደረጃና በመጠን መለየት፤

**ተግባር 4፡** ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ የሰው ኃይል ልማትን ለመምራት የሚያስችሉ 3 መመሪያዎችን አዘጋጅቶ ስራ ላይ እንዲውል ማድረግና ተፈፃሚነታቸውን መከታተል፣

**ተግባር 5፡** በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ያለው የሰው ኃይል ልማትን በተመለከተ የሚካሄዱ የለውጥ ስራዎችን 2 መድረክ በማዘጋጀት እና 2 የህትመት ጽሁፍ በማዘጋጀት (የቅድመ-ምዘና

ምዝገባ፣ ምዘና፣ ድህረ-ምዘና ምዝገባ፣ ስልጠና ወዘተ) ለህብረተሰቡ[6] እንዲተዋወቁ ማድረግ፣

**ተግባር 6፡** የገበያ ክፍተት በሚታይባቸው ዘርፎች በልዩ ልዩ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች በመስራት ላይ የሚገኙ ባለሙያዎች ድጋፍ በማድረግ በሥራ ተቋራጭነት እና በአማካሪነት እንዲደራጁ ለማድረግ እንዲቻል በ8 መስሪያ ቤቶች ላይ የክፍተት ዳሰሳ ጥናት ማድረግ፤

**ተግባር 7፡** የምህንድስና የትምህርት ክፍሎች ያሏቸውን 31 የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት/ዩኒቨርሲቲዎች/ የምክር አገልግሎት ሥራዎች ላይ እንዲሳተፉ ለማድረግ ያላቸውን አቅም በጥናት ማረጋገጥ፣

**ተግባር 8፡** የመንግስትና የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ አጋርነት ለማጠናከር እንዲሁም በኢንዱስትሪው ሊያበረክቱ የሚችሉትን አስተዋጽኦ እንዲያሳድጉ ማድረግ የሚያስችል በዘርፉ ከተደራጁ የሙያ ማህበራት ጋር የጋራ ዕቅድ በማዘጋጀት መተግበር፤

**ተግባር 9፡** በኢንዱስትሪው የሚገኙ የሙያ ማህበራት የላቀ ተሞክሮ ካላቸው የውጭ የሙያ ማህበራት የክህሎት ሽግግር ማድረግ እንዲቻል ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከማህበራቱ ጋር የጋራ የመግባቢያ ሠነድ በማዘጋጀት እንዲተገበር ማድረግ፣

**ተግባር 10፡** በቤት ልማት እና በተለያዩ በመንግስት ፕሮጀክቶች ከሚሰማሩት የግል አማካሪዎች እና ሥራ ተቋራጮች ውስጥ ለ20 በመቶ (330) ለሆኑት የተለያዩ ድጋፎችን በመስጠትና ምዘና በማካሄድ የጥራት ማረጋገጫ እንዲያገኙ ማድረግ። (ከቤቶች የተዛወረ)

## 6.3. የግንባታ ዕቃዎች እና የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች አቅርቦት አቅም ግንባታ ሥራ

**ዓላማ፡** የኢንዱስትሪውን ልማት ለማሳደግ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር በግንባታ ዕቃዎች፣ በቴክኖሎጂዎች ሽግግር፣ በአማራጭ ዲዛይኖች እና በመሳሪያዎች አቅርቦት (በቴክኖሎጂ ሽግግር የሚገኙ) እና በአገነባብ ዘዴዎች ላይ ጥናትና ምርምር በማድረግ ሥራ ላይ እንዲውል ማደረግ ነው።

**ግብ፡** የኢንዱስትሪውን ልማት ለማሳደግ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር በግንባታ ዕቃዎች፣ በቴክኖሎጂዎች ሽግግር፣ በአማራጭ ዲዛይኖች እና በመሳሪያዎች አቅርቦት (በቴክኖሎጂ ሽግግር የሚገኙ) እና 12 በአገነባብ ቴክኖሎጂዎች ላይ ጥናትና ምርምር በማድረግ ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል። በ20 የግንባታ ዕቃዎችም የጥራትና ደረጃ ቁጥጥር ይደረጋል።

**ዝርዝር ተግባራት**

[6] (በህንጻ ንዑስ ዘርፍ የተሠማሩ ባለሙያዎች ማለትም ግንበኛ፣ አናጺ፣ ቀለም ቀቢ፣ ለሳኝ፣ የሳኒቴሪ እና ኤሌክትሪካል መስመር የሚዘረጉ ባለሙያዎች)

ተግባር 1፡ በፌዴራል ደረጃ የአካባቢ የግንባታ ግብአቶች ላይ ምርምርና ስርፀት ለማካሄድ የሚያስችል የምርምር ማዕከል ማቋቋም፣

ተግባር 2፡ በአካባቢ የግንባታ ግብአቶች ላይ ምርምርና ስርፀት ለማካሄድ ከ5 ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የትብብርና የውል ስምምነት ሠነድ መፈራረምና አተገባበሩን መከታተል፤

ተግባር 3፡ የተመረጡ ዩኒቨርስቲዎች በ16 አዳዲስ እና የተሻሻሉ ወጪ ቆጣቢ የአካባቢ ግንባታ ግብአቶች ላይ የሚያደርጉት ምርምር ውጤታማ እንዲሆን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤

ተግባር 4፡ 12 አዳዲስና የተሻሻሉ ወጪ ቆጣቢ ግንባታ ቴክኖሎጂዎች በዩኒቨርስቲዎቹ ተዘጋጅተውና በደረጃዎች ዝግጅት ኤጀንሲ ደረጃ ወጥቶላቸው ወደ ትግበራ እንዲሸጋገሩ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤

ተግባር 5፡ በ20 የግንባታ ዕቃዎች ላይ የጥራትና ደረጃ ቁጥጥር እንዲደረግ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

ተግባር 6፡ በክልሎች የሚዘጋጁ የአካባቢ ግብዓት ካባዎች የተሻለ አሠራርና አጠቃቀም ስርዓት መመሪያ ሥራ ላይ እንዲውል ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

ተግባር 7፡ ከሁሉም ክልሎች ለስፋት ግዥ አገልግሎት የሚውሉ የፍላጎት መረጃዎች ማጠናቀርና ለሚመለከተው አካ ማስተላለፍ፣

ተግባር 8፡ ወጪ ቆጣቢና ተስማሚ የግንባታ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ፍትሃዊ የመኖሪያ ቤት ተደራሽ የሚያደርግ ጥናት በማካሄድ ተግባራዊ እንዲደረግ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

ተግባር 9፡ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ነባራዊ ሁኔታ ትንተና በማካሄድ የጥናት ሠነድ ማዘጋጀት፣

ተግባር 10፡ በልማት ፕሮጀክቶች ውስጥ ለሚሳተፉ 100 ሥራ ተቋራጮች እና 50 አማካሪዎች የተለያዩ ድጋፎች ተደርጐላቸው የISO9001፡2008 ስታንዳርድ አደረጃጀት እንዲኖራቸው ማድረግ፡፡

6.4. *የሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች ባለሙያዎችና የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ምዝገባ ሥራ*

ዓላማ፡ የስራ ተቋራጮች፣ ባለሙያዎች፣ አማካሪዎች እና የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ምዝገባ ስራ በቅልጥፍና፣ በውጤታማነት፣ በግልጽነትና በተጠያቂነት መንፈስ እንዲከናወን ለማድረግ ነው፡፡

ግብ፡ ግንባታዎች በተፈቀደላቸው ዲዛይንና የጥራት ደረጃ እንዲገነቡና አስተማማኝ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ 1,000 ፐራክቲሲንግ፣ 7,000 ባለሙያዎች፣ 2,300 ሥራ ተቋራጮችን፣ 230 አማካሪዎች፣ የ12,600 የኮንስትራክሽን መሳሪያዎችና ተያያዥ አገልግሎቶች እንዲሁም ለ500 የንግድ ድርጅቶችና ግለሰቦች የብቃት ማረጋገጫ በመስጠት ምዝገባ ይከናወናል፡፡

**ዝርዝር ተግባራት**

**ተግባር 1፡** የ1,000 የፕራክቲሲንግ እና የ7,000 ባለሙያዎች አመታዊ ምዝገባዎች ማከናወን፤

**ተግባር 2፡** የ2,300 ሥራ ተቋራጮችን እና 230 አማካሪዎችን ዓመታዊ ምዝገባ ማከናወን፣

**ተግባር 3፡** የ13,100 የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች እና ተያያዥ አገልግሎቶች መስጠት፤

**ተግባር 4፡** በመ/ቤታችን የብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጥባቸዉ ለተወሰኑት 500 የንግድ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ መስጠት፤

**ተግባር 5፡** ወደ አገር ዉስጥ የሚገቡ ያገለገሉ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች በቂ የአገልግሎት ጊዜ እንዳላቸዉ የሚያረጋግጥ የአሠራር ሠነድ ተቀርጾና አደረጃጀት ተፈጥሮ የመሳሪያዎች ደህንነትና ምርታማነት እንዲረጋገጥ ማድረግ፣

**ተግባር 6፡** የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች የግምት መመሪያ ማዘጋጀትና በሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ፤

**ተግባር 7፡** ከደረጃ 4 በታች ያሉ ሥራ ተቋራጮችና ባለሙያዎች ምዝገባ በየክልሉ እንዲሰጥ ለማድረግ አስፈላጊው ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣ግበረ

**ተግባር 8፡** የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ምዝገባ አዋጅ እና ደንብ ዝግጅት ማጠናቀቅ፤ የሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች፣ ባለሙያዎች እና የኮንስትራክስን መሣሪያ ምዝገባ መመሪያ ማጠናቀቅ፤ እንዲሁም ከሌሎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ የብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጣቸው ለተወሰኑ የንግድ የሥራ መደቦች መስፈርት ዝግጅት በማጠናቀቅ ተግባራዊ እንዲሆኑ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

**ተግባር 9፡** አዲስ 1,701 አነስተኛና መካከለኛ ሥራ ተቋራጮች፣ 20 አማካሪዎች እና 27 የኮንስትራክሽን መሣሪያ አከራዮች ተደራጅተው የተለያዩ ድጋፎች ተሰጥቷቸው ወደ ሥራ መሰማራታቸውን ማረጋገጥ፡፡

## 7. የከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ሥራዎች

**ጥቅል ዓላማ፡** የከተሞች አገልግሎት ዓለም አቀፍ ስታንዳርድን መሰረት በማድረግና የመልካም አስተዳደር መርህን ተከትሎ እንዲቀርቡ በመደገፍ፣ የህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄን በማጠናከር፣ ከተሞች ለነዋሪዎቻቸው ምቹ የመኖሪያ፣ የልማትና የመልካም አስተዳደር ማዕከላት እንዲሆኑ የማስፈጸም አቅማቸውን ለማጎልበት ነው፡፡

**ጥቅል ግብ፡** የከተሞችን የሠለጠና የሰው ኃይል በየደረጃው እንዲያድግ በማድረግ የህዝብን ንቅናቄ በማቀጣጠል ህብረተሰቡ በልማትና መልካም አስተዳደር ያለውን ሁሉን አቀፍ ተሳትፎና ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ በማድረግ ከተሞች ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት ለመስጠት እንዲችሉና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በመደገፍ በከተሞች መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ይደረጋል፡፡

7.1. የከተሞችና የክልሎች የሰው ኃይል ልማትና ስታንዳርዳይዜሽን ሥራ

ዓላማ፡ በአጭር በመካከለኛና የረዥም ስልጠና ፕሮግራም በየደረጃው የሚገኙ ፈጻሚ አካላትን በማብቃት የከተሞችን የሰው ኃይል ፍላጎት ለማሟላት ነው፡፡

ጥቅል ግብ፡ በዘርፉ አዲስ ለሚሰማሩ እና በሥራ ላይ ያሉ አመራሮችና ፈጻሚዎች የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ስልጠና ፕሮግራም በማዘጋጀት፣ ሥልጠና በመስጠትና ምዘና በማካሄድ የከተሞችን የሰው ኃይል ፍላጎት እንዲያድግ ይደረጋል፡፡ እንዲሁም በ8 የከተሞች የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች ላይ 50,000 አዳዲስ ባለሙያዎችን በማፍራትና ለ10,000 ነባር ባለሙያዎች ምዘና በማካሄድ ለነዋሪዎቻቸው ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

ዝርዝር ተግባራት

ግብ አንድ፡ የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ስልጠና ፕሮግራም በማዘጋጀት እና ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በቅንጅት በመስራት የዘርፉ የሰው ኃይል ፍላጎት እንዲሟላ ይደረጋል፡፡

ተግባር 1፡ በ2004 በተዘጋጀውና በፀደቀው የሙያ ደረጃና ስርዓተ ትምህርት መሰረት ተጀምረው ያልተጠናቀቁ 555 የመምህራን ማስተማሪያና መማሪያ መሳሪያዎችን/TTLM/ ባለሙያዎችን በመጋበዝ ማዘጋጀት፣

ተግባር 2፡ በማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች ሥልጠና፣ ምክርና የምርምር አገልግሎት የሚሰጥ የልህቀት ማዕከላት /Center of Excellency/ በፌደራል ደረጃ ለማቋቋም የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ እንዲቋቋም ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

ተግባር 3፡ በከተማ ልማት ዘርፍ በከፍተኛ ደረጃ ባለሙያችን ለማፍራት በተለያዩ አዲስ የትምህርት ፕሮግራሞች በማስትሬት ዲግሪ ደረጃ የሰው ኃይል ማሰልጠን እንዲቻል ከዩኒቨርሲቲዎችና ከዘርፉ ባለሙያዎች ጋር በመሆን የባለሙያዎች/ተመራቂዎች/ ፕሮፋይል እና ስርዓተ ትምህርት እንዲዘጋጅ ማድረግ፣

ተግባር 4፡ በከተማ ልማት ዘርፍ ሥርዓተ ትምህርቶች ለተዘጋጀላቸው አዲስ የማስትሬት ዲግሪ ደረጃ የትምህርት ፕሮግራሞች የማሰልጠኛ ማቴሪያሎች በዩኒቨርሲቲዎችና በዘርፉ ኢንዱስትሪዎች ትብብር እንዲሟሉ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

ተግባር 5፡ በ8 ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች በዝቅተኛና መካከለኛ ደረጃ የሙያ ስታንዳርድ ለተዘጋጀላቸው ሙያዎች በመጀመሪያ ዲግሪ ስልጠና ለመጀመር የስልጠና መስክ መለየትና የተመራቂዎች ፕሮፋይል እንዲዘጋጅ በማድረግ ሥርዓተ ትምህርት እንዲቀረጽ ማድረግ፣

ተግባር 6፡ በተዘጋጀና በፀደቀው 4 የሙያ ደረጃዎች (በግብይት አስተዳደር፣ ቤቶች ልማት፣ ቁራ አስተዳደርና አሴት ማኔጅመንት) ላይ የሙያ ስታንዳርድና የሥልጠና ሥርዓተ ትምህርት እንዲዘጋጅ ማድረግ፣

**ተግባር 7:** በተለያዩ የከተማ ልማት ነክ ሙያዎች (በከተማ ስራ አመራር፣ በከተማ አካባቢ አጠባበቅ፣ በመሰረተ ልማት አቅርቦትና በመሳሰሉት) ላይ በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ 2,019 ባለሙያዎች በማስትሬት ዲግሪ ደረጃ እንዲሰለጥኑ ድጋፍ ማድረግ፣

**ተግባር 8:** በተለያዩ የከተማ ልማት ነክ ሙያዎች (በከተማ ስራ አመራር፣ በከተማ አካባቢ አጠባበቅ፣ በመሰረተ ልማት አቅርቦትና በመሳሰሉት) በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በማስትሬት ዲግሪ ስልጠና እየወሰዱ ለሚገኙት 209 ሰልጣኞች ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

**ተግባር 9:** በፌዴራል፣ በክልልና ከተማ ያሉ አመራሮችና ባለሞያዎች በተለያዩ የከተማ ነክ አገልግሎቶችና ሞያዎች 3 የልምድ ልውውጥና አጫጭር ስልጠናዎች በውጭ ሀገር እንዲያገኙ ማድረግ፣

**ተግባር 10:** በሰው ኃይል ልማትና ስታንዳርዳይዜሽንና ምዘና ስትራቴጂ እንዲሁም በስትራቴጂው ማስፈጸሚያ ማንዋሎች ላይ 200 የከተማ አመራሮችና ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት፣

**ተግባር 11:** በ8ቱ የማዘጋጃቤታዊ ሙያዎች ላይ 130 መሪ መዛኞችን በመለየትና በማፍራት ለመዛኝነት ማዘጋጀት፣

**ተግባር 12:** በ2ቱም ደረጃዎች (C, B) በቀጣይ ሦስት ዓመታት የሚያስፈለገውን የመምህራን ፍላጎት በመለየት 80 መምህራንን በማሰልጠን ሰነ ዘዴ /ሜቶዶሎጂ/ ከክልሎች ጋር በመሆን ስልጠና በመስጠት ለሥራ ማዘጋጀት፡፡

**ተግባር 13:** ባለፉት አራት ተከታታይ ዙሮች በከተማ ሥራ አመራር ድህረ ምረቃ ፕሮግራም የሰለጠኑ 2,094 አመራሮችና ባለሙያዎች ስምሪትና በሥራ ላይ ያመጡትን ለውጥ በመስክ በመገኘት የተጽኖ ግምገማ ማድረግ፡፡

**ግብ ሁለት፡ ክልሎችና ከተሞች በተለዩት 8 የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት የሙያ ስታንዳርዶች ላይ 50,000 አዳዲስ ባለሙያዎች በማፍራትና ለ10,000 ነባር ባለሙያዎች የብቃት ምዘና በማካሄድ ለነዋሪዎቻቸው ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲሰጡ ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፡፡**

**ተግባር 1:** የሙያ ደረጃ በተዘጋጀላቸውና በፀደቀላቸው 8 ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች ክልሎች 50,000 አዳዲስ ባለሙያዎችን በዝቅተኛና በመካከለኛ ደረጃ እንዲያፈሩ ተከታታይ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

**ተግባር 2:** በ8ቱ ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች[7] የሙያ ማረጋገጫ ሳያገኙ ስራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ 10,000 ነባር ሰራተኞች በብቃት ምዘና እየተመዘኑና ብቃታቸው እየተረጋገጠ ስራ ላይ እንዲሰማሩ ለክልሎች ድጋፍና ክትትል በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

---

[7] 8ቱ አገልግሎቶች = ዘላቂ ማረፊያ፣ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ፣ የህብረተሰብ ተሳትፎ፣ የእሳትና ድንገተኛ አደጋ መከላከል፣ የከተሞች አረንጓዴ፣ ደንብ ማስከበር፣ የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ እና የውሃ አቅርቦትና ስርጭት የሚሉት ናቸው፡፡

**ተግባር 3፡** በክልሎች አዲስም ሆኑ ነባር ባለሙያዎች በ8 ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች የሚመዘኑበት የብቃት ምዘና 50 ጣቢያዎችን በማደራጀትና እንዲቋቋሙ ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፣

**ተግባር 4፡** ልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎች ለሚገኙ 64 አመራርና ባለሙያዎች በ8ቱ ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች የሙያ ስታንዳርዳይዜሽን ሥልጠና መስጠት፣

**ተግባር 5፡** ኮዲፋይድ በሆኑ 4 ሙያዎች (በግብይት አስተዳደር፣ ቤቶች ልማት፣ ቁራ አስተዳደር እና አሴት ማኔጅመንት) ለሚዘጋጁ የሙያ ደረጃዎች ለ50 አመራሮችና ባለሙያዎች ሥልጠና መስጠት፡፡

## 7.2. የሕዝብ ተሳትፎና ያልተማከል አስተዳደር ማሻሻያና ማጠናከሪያ ሥራ

**ዓላማ፡** **ቀጣይነት ያለው የከተሞች ልማትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ያልተማከለ አስተዳደርን ማጠናከርና የህዝብ ተሳትፎን ማረጋገጥ ነው፡፡**

**ጥቅል ግብ፡** **ቀጣይነት ያለው የከተሞች ልማትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ያልተማከለ አስተዳደርን በማጠናከር እንዲሁም የልማት አጀንዳዎችን በመቅረጽ የህዝብ ባለቤትነት እና ተሳትፎ ይረጋገጣል፡፡**

**ዝርዝር ግብና ተግባራት**

**ግብ አንድ፡** **በክልሎችና በከተሞች መልካም አስተዳደር እንዲሰፍንና ህዝቡም ተጠቃሚ እንዲሆን 7 የልማት አጀንዳዎች እና 3 የአሠራር ማኑዋሎችን በማዘጋጀት እና እንዲተገበር በማድረግ ሕዝቡ በከተማ አጀንዳዎች ላይ ተሳታፊና ባለቤት እንዲሆን ይደረጋል፡፡**

**ተግባር 1፡** በበጀት አመቱ መጨረሻ የከተማ የሕዝብ ተሳትፎና ንቅናቄን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር የሚያስችሉ 3 የአሰራርና የአደረጃጀት ሰነዶች እንዲዘጋጁ በማድረግ በከተሞች የአሰራርና የአደረጃጀት ለውጥ እንዲመጣ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

**ተግባር 2፡** በበጀት አመቱ መጨረሻ ወቅታዊ የሆኑ 7 የከተማ አጀንዳዎች በሚመለከታቸው ቢሮዎች እንዲቀረጹ ማድረግና 4 የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በመፍጠር በየደረጃው የሚገኙ የከተማ አመራሮች፣ ፈጻሚዎችና ህዝቡ አቅማቸውና ግንዛቤያቸው እንዲያድግ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

**ተግባር 3፡** በፌዴራል ደረጃ ከሚመለከታቸዉ ጋር በመሆን በከተሞች የህዝብ ተሳትፎንና ንቅናቄን የሚያስተባብሩ የህዝብ አደረጃጀቶች በክልሎችና በ72 ከተማ አስተዳደሮች እንዲመሰረቱና እንዲጠናከሩ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

**ተግባር 4፡** በ9 ክልሎችና በ2ቱ ከተማ አስተዳደሮች ለሚገኙ 208 አመራሮች፣ ፈጻሚዎችና የከተማ ምክር ቤት ተመራጮችን በህዝብ ተሳትፎና ንቅናቄ ሰነዶች እና አጀንዳዎች ላይ የአሰልጣኞች ስልጠና በመስጠት ንቅናቄው ላይ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

**ተግባር 5፡** በህዝብ ተሳትፎ ንቅናቄ ዙሪያ ያሉ አንድ የውጭ እና አንድ የሀገር ዉስጥ ተሞክሮዎችን በመለየት ከከተማ ሥራችን ጋር በሚጣጣም መልኩ በመቀመር ሰነድ ተዘጋጅቶ በሁሉም ከተሞች እንዲስፋፉ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፡፡

**ግብ ሁለት፡ የከተሞች ሳምንት በሕዝብ ንቅናቄ እንዲከበር በማድረግ ከተሞችና አጋሮቻቸው የልማትና የመልካም አስተዳደር ስራዎቻቸውን በማስተዋወቅ እውቅና እንዲያገኙና ተሞክሮዎቻቸውን እንዲለዋወጡ ይደረጋል፡፡**

**ተግባር 1፡** የከተሞች ሳምንት አከባበርን አስመልክቶ የሚመሩ አካላትና በማደራጀት፣ አንድ መሪ ዕቅድ እና 12 ማስፈጸሚያ መመሪያዎችን በማዘጋጀት ሥራው በተደራጀና በተቀናጀ መንገድ እንዲፈጸም ማድረግ፣

**ተግባር 2፡** ለከተሞች በዓል ዝግጅት ማስፈጸሚያ ከስፖንሰርና ከመንግስት ብር 6 ሚሊዮን በማሰባሰብ ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ በሆነ መንገድ አገልግሎት ላይ እንዲውል ማድረግ፣

**ተግባር 3፡** በበዓሉ ላይ ከ100 በላይ ከተሞችና ድርጅቶች እንዲሳተፉ በማድረግ የከተሞች ሳምንት በህዝብ ንቅናቄ እንዲከበር ማድረግ፣

**ተግባር 4፡** የላቀ የልማትና የመልካም አስተዳደር አፈጻጸም ያላቸው ክልሎች፣ ከተሞችና የልማት ኃይሎች በልዩ በልዩ ርዕሰ ጉዳዮች እውቅና በመስጠት ከተሞችና የልማት ኃይሎች የውድድር መንፈስ እንዲያድግ ማድረግ፣

**ተግባር 5፡** በተለያዩ 12 ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ለ5 ቀናት በ3 መድረኮች የፓናል ውይይት በማድረግ ተሳታፊ ክልሎች፣ ከተሞችና ባለድርሻ አካላት በከተማ አጀንዳዎች ዙሪያ ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ፡፡

**ግብ ሦስት፡ በከተሞች ያልተማከለ አስተዳደርን ለማጠናከር 9 ማስፈጸሚያና የአሰራር ማንዋሎችን በማዘጋጀት እና ሥራ ላይ በማዋል የከተማ አገልግሎቶች ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡**

**ተግባር 1፡** በከተሞች ያልተማከለ አስተዳደር ስርዓትን ለማጠናከርና ለማሻሻል የሚያስችሉ 9 ማስፈጸሚያና የአሰራር ማንዋሎች እንዲዘጋጁና በረቂቅ ደረጃ ላይ ያለው ያልተማከለ አስተዳደር ማስፈጸሚያ ሰነድ ጸድቆ ሥራ ላይ እንዲውል ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

**ተግባር 2፡** 170 የገጠር የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት መስፈርት ወጥቶላቸው በህዝቦች ቀጥታ ተሳትፎ ህጋዊ የከተማነት ዕውቅና እንዲያገኙ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

**ተግባር 3፡** ወጥ የከተሞች ፎርጅና የከተሞች አስተዳደር እርከኖች የአደረጃጀት መስፈርት በማዘጋጀትና 100 ከተሞች የአደረጃጀት ለውጥ እንዲያገኙ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

**ተግባር 4፡** 200 የከተማ ምክር ቤት አባላት ኃላፊነታቸውን በሚገባ ለመወጣት እንዲችሉ በ4 ዙር ስልጠና መስጠት፣

**ተግባር 5፡** ያልተማከለ አስተዳደር ስርዓት በከተሞች ለማጠናከር የሚያስችል 1 የዉጭና 1 የሀገር ዉስጥ ተሞክሮዎችን በመለየት ከከተማ ሥራችን ጋር በሚጣጣም አግባብ መቀመርና በሁሉም ከተሞች እንዲስፋፋ ማድረግ፡፡

## 7.3. የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት ስታንዳርዳይዜሽንና የአፈጻጸም ምዘና ሥራ

**ዓላማ፡** **ከተሞቻችን ግልፅ፣ ውጤታማና ተጠያቂነት ያለውና ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ለመስጠት የሚችል ስርዓት በመዘርጋት አፈጻጸማቸውን በመመዘንና ግብረ-መልስ በመስጠት ብቁና ተወዳዳሪ ከተሞችን ለመፍጠር ነው፡፡**

**ግብ፡** **ከተሞቻችን ግልፅ፣ ውጤታማና ተጠያቂነት ያለውና ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቁ 14 የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚያስችል ሥርዓት በመዘርጋት ለ359 አመራሮችና ፈጻሚዎች ሥልጠና በመስጠት እና በ100 ከተሞች በመተግበር አፈጻጸማቸውን በመመዘን ግብረ-መልስ ይሰጣል፡፡**

**ዝርዝር ተግባራት፡**

**ተግባር 1፡** በማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተሻለና ምርጥ ተሞክሮ ያላቸውን ከተሞች መነሻ (Bench mark) በማድረግና የተገኘውን ምርጥ ተሞክሮ በመቀመር ለ14 ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች ስታንዳርዶችን ማዘጋጀት፣

**ተግባር 2፡** ለተዘጋጁት 14 የአገልግሎት ስታንዳርዶች ትግበራ የድርጅታዊ አቅም፣ የቴክኖሎጂ አቅርቦትና የአሠራር ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችሉ 7 የማስፈጸሚያ ማኑዋሎችን ማዘጋጀት፣

**ተግባር 3፡** የአገልግሎት ስታንዳርዶችን ለመተግበር የሚያስችል እና በአገልግሎቶቹ የአፈፃፀም ምዘና ሥርዓት ላይ ግንዛቤ ለማስጨበጥ እንዲቻል ከፌዴራል፣ ከክልሎችና ከከተሞች ለተውጣጡ ለ122 ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት፣

**ተግባር 4፡** ለ14 ማዘጋጃቤታዊ አገልገሎቶች ስታንዳርድ ትግበራ መነሻ የሚሆን ጥናት (Baseline Survey) ማካሄድ፣

**ተግባር 5፡** በ27 ከተሞች የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች ስታንዳርዶች ትግበራ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 6፡** የከተማ አገልግሎት አፈጻጸም ምዘና ለማካሄድ የሚያስችል አንድ የምዘና መለኪያ መስፈርቶች እና አንድ የማስፈጸሚያ ማኑዋል ሠነድ ማዘጋጀት፣

**ተግባር 7፡** በተዘጋጀው የምዘና መለኪያና ማኑዋል መሰረት በ100 ከተሞች የአገልግሎት አፈጻጸም ምዘና ማካሄድ፣

ተግባር 8፡ በማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች ላይ 3 ምርጥ ተሞክሮዎች ተቀምረው በ100 ከተሞች እንዲሰፉ ማድረግ፡፡

## 8. የከተሞች ጽዳትና ውበት ሥርዓት ማሻሻያ ሥራዎች

**ጥቅል ዓላማ፡ የክልሎችን፣ ከተሞችንና የግሉን ዘርፍ አቅም በመገንባት ከተሞች ጽዱና ውብ ሆነው በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ለነዋሪዎቻቸው ምቹ እንዲሁም ተፎካካሪ እንዲሆኑ ለማድረግ ነው፡፡**

**ጥቅል ግብ፡ ክልሎች፣ ከተሞችና የግሉ ዘርፍ የከተሞች ጽዳትና ውበት ሥራዎችን በተሟላ መልኩ ለማከናወን የሚያስችላቸዉን የአቅም ግንባታና የቴክኒክ ድጋፍ በመስጠት የማስፈጸም አቅማቸው እንዲያድግ ይደረጋል፡፡**

### 8.1. የከተማ ጽዳትና ውበት ጥናትና ምርምር ሥራ

**ዓላማ፡ በከተማ ጽደዳትና ውበት ዙሪያ የክልሎችንና የከተሞችን እንዲሁም የግሉን ዘርፍ አቅም ለመገንባት የተለያዩ የጥናት ሰነዶች፣ የሕግ ማዕቀፎች፣ ማኑዋሎች፣ ወዘተ በማዘጋጀት ድጋፍ ማድረግ ነው፡፡**

**ግብ፡ በከተማ ጽዳትና ውበት ዙሪያ ለክልሎች፣ ለከተሞች እና ለግሉ ዘርፍ አቅም ግንባታ የሚያገለግሉ የተለያዩ 7 የሕግ ማዕቀፎች፣ ማኑዋሎችንና ስታንዳርዶችን በማዘጋጀት ወደ ትግበራ እንዲሸጋገሩ ይደረጋል፡፡**

**ዝርዝር ተግባራት**

ተግባር 1፡ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት ለማሻሻል የሚስችል ጥናት በማካሄድ የአደገኛ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ማንዋል በማዘጋጀት፣ ተግባራዊ እንዲሆኑ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

ተግባር 2፡ የፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓትን ለማሻሻል ጥናት በማድረግ የአደገኛ ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ማንዋል በማዘጋጀት፣ ተግባራዊ እንዲሆኑ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

ተግባር 3፡ 5 የውበትና አረንጓዴ ልማትን የተመለከተ የጥናት ሠነዶች /የከተሞች ውበትና አረንጓዴነት ልማት አዋጅ፣ የከተሞች የአረንጓዴ ቦታዎች ተስማሚ እጽዋት አያያዝ ጋይድላይን፣ በአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ጉዳይ ጥናት፣ የአዲስ አበባ ከተማ ወንዝ ዳርቻ የተቀናጀ ላንድ ስኬፕ አያያዝ ጥናት እና የአረንጓዴ መሰረተ ልማት ስታንዳርድ በማዘጋጀት ተግባራዊ እንዲሆኑ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፡፡

8.2. የከተማ ጽዳትና ውበት ስልጠና ሥራ

ዓለማ፡ ከተሞች ጽዱና ዉብ እንዲሆኑ የአስፈጻሚ አካላትን አቅም በመገንባት ከተሞች የተሻለ የልማት ማዕከላት እንዲሆኑ ማጠናከር ነው፡፡

ግብ፡ በከተማ ጽዳትና ውበት ዙሪያ ለ58 ከተሞች ሞዴል አደረጃጀት በመፍጠር፣ በተለያዩ መስኮች በዘርፉ ለተሠማሩ ለ122 አስፈፃሚ አካላት ሥልጠና በመስጠትና ድጋፍና ክትትል በማድረግ አቅማቸው እንዲጎለብት ይደረጋል::

ዝርዝር ተግባራት

ተግባር 1፡ በደረቅ እና በፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እንደ ከተሞቹ ተጨባጭ ሁኔታ ለ58 ከተሞች ሞዴል አደረጃጀት በመቅረፅ ተግባራዊ እንዲሆኑ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

ተግባር 2፡ በደረቅ እና በፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ዙሪያ ለ122 አመራሮችና ፈጻሚ አካላት የተቀናጀ የግንዛቤ መፍጠር ወይም አመለካከትን የማሳደግ ስራ በ122 ከተሞች ለመሥራት የሚያስችሉ ሁኔታዎች ማመቻቸትና ስልጠናም እንዲሰጥ ማድረግ፣

ተግባር 3፡ በፌዴራል ደረጃ በከተሞች አረንጓዴነት ልማት ዙሪያ ሞዴል የአደረጃጀት ሰነድ ማዘጋጀት በ58 ከተሞች ወጥ የሆነ አደረጃጀት በመቅረጽ ተግባራዊ እንዲሆኑ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

ተግባር 4፡ በ122 ከተሞች በአረንጓዴነት ልማት ዙሪያ ለ122 አመራሮችና ፈጻሚ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እንዲሰጥ ማድረግ፣

8.3. የከተሞች ጽዳትና ውበት ሕግና ስታንዳርድ የአፈጻጸም ክትትልና ግብረ-መልስ ሥራ

ዓላማ፡ ክልሎች፣ ከተሞችና የግሉ ዘርፍ የከተሞች ጽዳትና ውበትን በተመለከተ ሕግና ስታንዳርድን መሰረት አድርገው እንዲመሩና እንዲሁም ተያያዥ/ተጓዳኝ የክትትልና ግምገማ ሥራዎችን በተሟላ መልኩ ለማከናወን የሚያስችላቸውን የአቅም ግንባታና የቴክኒክ ድጋፍ በመስጠት የማስፈጸም አቅማቸውን ማሳደግ ነው፡፡

ጥቅል ግብ፡ ከተሞች ጽዱ፣ ውብና አረንጓዴ ሆነው በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አካባቢያቸው ምቹና ተፎካካሪ እንዲሆኑ ሕግና ስታንዳርድን መሰረት አድርገው እንዲንቀሳቀሱ የድጋፍ፣ የክትትልና ግምገማ ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡

ዝርዝር ተግባራት

ግብ አንድ፡ በደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ላይ ጉለሌ ክፍለ ከተማን በሞዴልነት በመውሰድ መልካም ተሞክሮ በመቀመር ወደ ሌሎች ክፍለ ከተሞችና የክልል ከተሞች እንዲሰፉ ይደረጋል፡፡ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ 192 ቦታዎች በ70 ከተሞች እንዲሁም የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ 134 ቦታዎች በ50 ከተሞች እንዲዘጋጁ በማድረግ ለ4017 ዜጎች የሥራ ዕድል ይፈጠራል፡፡ ከዚህ ውስጥ ሴቶች 50% ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

**ተግባር 1:** ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ጋር በተያያዘ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ሕብረተሰቡንና ሌሎች የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ ሞዴል ክፍለ ከተማ በመፍጠር ለ179 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር፣ ተሞክሮውን በመቀመር ወደ ሌሎች ክፍለ ከተሞች እና ከተሞች እንዲስፋፉ ማድረግ፣ በአፈጻጸሙም ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 2:** በከተሞች ሕብረተሰቡንና ሌሎች የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ የተቀናጀ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ፤ መልካም ተሞክሮ ተቀምሮ እንዲስፋፉ ማድረግ፣ በአፈጻጸሙም ላይ በ15 ከተሞች ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 3:** በከተሞች የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝ፣ አወጋገድና መልሶ መጠቀም የሚያስችሉና የሚያግዙ የኮምፖስት፣ የብሪኬትና የፕላስቲክ መልሶ መጠቀም ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመለየት በዕቅድ እንዲያካትቱ በማድረግ በተግባራዊነቱ ላይ በ15 ከተሞች የክትትል፣ ድጋፍና ግብረ-መልስ ስራ ማከናወን፣

**ተግባር 4:** በከተሞች ከደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ጋር በተያያዘ በስራ ላይ እንዲውሉ በፌዴራል፣ ክልሎችና ከተሞች የወጡ ህጎችና ስታንዳርዶች በአግባቡ እየተተገበሩ ስለመሆኑ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ስራዎችን በ15 ከተሞች በማከናወን ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 5:** ከደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ጋር በተያያዘ ሕብረተሰቡንና ሌሎች የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ በ15 ከተሞች 3,838 የሥራ ዕድል መፍጠር፣ ከሚፈጠረውም የሥራ ዕድል 50% ሴቶችን ተጠቃሚ ማድረግ፣ በአፈጻጸሙም ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 6:** ሕብረተሰቡንና ሌሎች የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ ዘመናዊና ወጪ ቆጣቢ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ 192 ቦታዎች በ70 ከተሞች እንዲሁም የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ 134 ቦታዎች በ50 ከተሞች እንዲዘጋጁ ማድረግ እና በአፈጻጸሙ ላይ ክትትልና ድጋፍ ስራ ማከናወን፣

**ተግባር 7:** ከአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በቅንጅት በመስራት በከተሞች የሚገኙ ኢንዱስትሪዎችና የህክምና ተቋማትን በመለየት አግባብነት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ የቅድመ ማጣራት ሥራዎችን /Pre-treatment Facilities/ እንዲሰሩና አዳዲስም ሆኑ ነባር ኢንዱስትሪዎች የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት እንዲያካሂዱ ማድረግ፣ ለተግባራዊነቱም ድጋፍና ክትትል በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ግብ ሁለት:** **በውበትና አረንጓዴነት ልማት ላይ ጉለሌ ክፍለ ከተማን በሞዴልነት በመውሰድ መልካም ተሞክሮ በመቀመር በሌሎች ከተሞች እንዲስፋ ይደረጋል:: በከተሞች የአረንጓዴነት**

**መሰረተ-ልማት አይነቶችን በመለየት የአረንጓዴነት ልማት ዕቅድ ተዘጋጅቶ እንዲተገበር በማድረግ 700 ሄክታር እንዲለማ ይደረጋል፡፡ በዚህም ለ969 ዜጎች የሥራ ዕድል ይፈጠራል፡፡ ከዚህ ውስጥ ሴቶች 50% ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡**

**ተግባር 1፡** ከውበትና አረንጓዴነት ልማት ጋር በተያያዘ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ህብረተሰቡንና ሌሎች የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ ሞዴል ክፍለ ከተማ በመፍጠር ለ193 ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር እና ተሞክሮውን በመቀመር ወደ ሌሎች ክፍለ ከተሞች እና ከተሞች እንዲስፋፉ ማድረግ፣ በአፈጻጸሙ ላይ ክትትል፣ ድጋፍና ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 2፡** ከከተማ ውበትና አረንጓዴ ቦታዎች ጋር በተያያዘ በስራ ላይ እንዲውሉ የወጡ ህጎችና ስታንዳርዶች በአግባቡ እየተተገበሩ ስለመሆኑ በ15 ከተሞች ላይ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ስራዎችን በማከናወን ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 3፡** ከተሞች የአረንጓዴነት ልማት ዕቅድ እንዲያዘጋጁ በማድረግ የመንገድ ፓርኮች፣ ፕላዛና ክብረ-በዓል ቦታዎች፣ የመንገድ ዳርና አካፋይ መሰረተ-ልማት ሥራዎችን በ700 ሄክታር ለከተሞች ውበት በሚሰጥ መልኩ እንዲለሙ ማድረግ፣ ለተግባራዊነቱም በ15 ከተሞች የክትትል፣ ድጋፍ እና ግብረ-መልስ ሥራ ማከናወን፣

**ተግባር 4፡** በከተሞች የሚገኙ የወንዝ እና የሐይቅ ዳርቻዎች እንዲሁም የከተማ ዳርቻ በ700 ሄክታር ተፋሰስ ቦታዎች እንዲለሙና እንዲጠበቁ እንዲሁም የከተማ ግብርና ደረጃውን በጠበቀ መንገድ እንዲለማ ማድረግ፣ በአፈጻጸሙ ላይ በ15 ከተሞች የክትትል፣ ድጋፍ እና ግብረ-መልስ ስራ ማከናወን፣

**ተግባር 5፡** በከተሞች የሚከናወኑ የልማት ስራዎች የአካባቢ ጥበቃ መርህን እና የአየር ንብረት ለውጥን ታሳቢ ያደረጉ መሆኑን በ15 ከተሞች ግምገማ በማካሄድ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 6፡** በመንግስት እና በኃይማኖት ድርጅቶች የሚተዳደሩ ዘላቂ ማረፊያዎች ወደ መታሰቢያ ፓርክነት እንዲቀየሩ ስታንዳርድ በማዘጋጀት ለተግባራዊነቱም በ15 ከተሞች የክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 7፡** በከተሞች ከውበትና አረንጓዴነት ልማት ጋር በተያያዘ ለ776 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር፣ ከሚፈጠረውም የሥራ ዕድል 50% ለሴቶች እንዲሆን ማድረግ፤ ለተግባራዊነቱም በ15 ከተሞች የክትትል፣ ድጋፍ እና ግብረ-መልስ ስራ ማከናወን፡፡

## 9. የትምህርትና ልማታዊ ኮሚዩኒኬሽን ሥራዎች

**ጥቅል ዓላማ፡ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ዋና ዋና የትኩረት መስኮች ለጋራ መግባባትና ለተቋማዊ ገጽታ ግንባታ የሚረዳ ትክክለኛ፣ ወቅታዊና ጥራት ያለው የኮሚዩኒኬሽንና የመረጃ አሰባሰብ፣ አዘገጃጀትና አሰረጫጨት ሥርዓት በመዘርጋት፣ መረጃን በቀጣይነት በመስጠት ህዝብን**

**በማሳወቅ፣ በማሳመንና ወደ ተግባር በማስገባት ተሳትፎውን በማጎልበት በዘርፉ ለተያዘው ግብ ውጤታማነት መስራት፡፡**

**ጥቅል ግብ፡** **በተቋሙና በሕብረተሰቡ መካከል ቀልጣፋና ውጤታማ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት በመዘርጋት በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋሙ ለማከናወን ባቀዳቸው ዋና ዋና ተግባራት ዙሪያ ሰፊ የህዝብ ንቅናቄ በመፍጠር ሕብረተሰቡና ባለድርሻ አካለት ጉልህ አስተዋጽኦ ማበርከት እንዲችሉና የተቋሙ ተልዕኮ ስኬታማ እንዲሆን ያስቻለ የህዝብ ግንኙነትና ኮሚዩኒኬሽን ስርዓት ይፈጠራል፡፡**

**ዝርዝር ግቦችና ተግባራት**

**ግብ አንድ፡** **የዘመናዊ ኤሌክትሮኒክ ሚዲያ በመጠቀም በ84 የቴሌቪዥንና ሬድዮ ፕሮግራሞች፣ በ8 ዶክምንተሪ ፊልሞች እና በሌሎች ስልቶች በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ዙሪያ በሕብረተሰቡ እና በባለድርሻ አካላት ዘንድ ሰፊ የህዝብ ንቅናቄ ለመፍጠር የሚያስችል ግንዛቤ መፍጠር፡፡**

**ተግባር 1፡** በተቋሙ በተለዩት የትኩረት መስኮች የስራ እንቅስቃሴ ዙሪያ በአመት 8 ዶክመንተሪ ፊልሞች ማዘጋጀት፣

**ተግባር 2፡** በተቋሙ የትኩረት መስኮችና ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ዙሪያ በሳምንት አንድ፣ በአመት 48 የሬዲዮ ፕሮግራም ከሚዲያ ተቋማት ጋር በመተባበር ማዘጋጀት፣

**ተግባር 3፡** በተቋሙ የትኩረት መስኮችና ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ዙሪያ በወር ሁለት፣ በአመት 24 የቴሌቭዥን ፕሮግራም ከሚዲያ ተቋማት ጋር በመተባበር ማዘጋጀት፣

**ተግባር 4፡** ከተቋሙ ተልዕኮ አፈጻጸም ጋር ተያያዥነት ባላቸው ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ከክልልና ከተጠሪ ተቋማት ጋር በመተባበር በክልል በሚገኙ ሚዲያዎች 12 የቴሌቭዥን ፕሮግራም ማዘጋጀት፣

**ተግባር 5፡** የተቋሙን የስራ እንቅስቃሴ የተመለከቱ ልዩ ልዩ መረጃዎች በየሳምንቱ 1 ጊዜ በፖርታልና ድህረ-ገፅ ላይ በመጫን፣ በመከታተልና ወቅታዊ በማድረግ የውስጥና የውጪ አካላት በተቋሙ አፈጻጸም ዙሪያ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣

**ተግባር 6፡** በተቋሙ ልዩ ልዩ የስራ ክንውኖች ዙሪያ በየሁለት ወሩ አንድ፣ በአመት ስድስት ጊዜ የዜና መግለጫ ማዘጋጀት፣

**ተግባር 7፡** የሚዲያ አካላት ለሚያነሱት ጥያቄዎች 100% ምላሽ መስጠት /የሚዲያ ኢንኳየሪ/ ስራ ማከናወን፣

**ተግባር 8፡** የሚኒስቴር መቤቱን የሥራ እንቅስቃሴ በሚመለከቱ የሚዲያ ሞኒተሪንግ ስራ በየዕለቱ ማከናወን፣

**ተግባር 9፡** በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቅጥር ግቢ ለሚዘጋጀው ሶኒ ስክሪን የማስታወቂያ ማሳያ የሚሆኑ የምስልና የጽሁፍ መረጃዎችንና መልዕክቶች ተዘጋጅተው በሳምንት አንድ ጊዜ እንዲተላለፉ ማድረግ፣

**ተግባር 10፡** የተቋሙ አበይት የስራ ክንውኖች በየሳምንቱ በመከታተል በፎቶግራፍና የቪዲዮ ቀረፃ በማከናወን በዶክመንትነት እንዲያዙ ማድረግ፣

**ግብ ሁለት፡ የተለያዩ የህትመት ውጤቶች በመጠቀም (በመጽሔት፣ ጋዜጣ፣ በራሪ ጽሁፎች እና በመሳሰሉት) በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ዙሪያ በሕብረተሰቡ እና በባለድርሻ አካላት ዘንድ ሰፊ የህዝብ ንቅናቄ ለመፍጠር የሚያስችል ግንዛቤ መፍጠር፡፡**

**ተግባር 1፡** ልማተ-ከተማ መፅሔትን በአመት 4 ጊዜ በ2000 ኮፒ በማዘጋጀት በተቋሙ የትኩረት መስኮችና ተያያዥነት ባላቸው ርዕሶች ዙሪያ መረጃዎች ማሰራጨት፣

**ተግባር 2፡** ‹‹የከተሞች ልሳን›› ጋዜጣን በአመት 12 ጊዜ በ5000 ኮፒ በማዘጋጀት በተቋሙ የትኩረት መስክ፣ በተልዕኮ አፈፃፀሙና ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ዙሪያ መረጃዎች ማሰራጨት፣

**ተግባር 3፡** በዘርፉ የተያዘውን ዕቅድ ለማሳካት የሚያስችሉና ህብረተሰቡን ለተግባር በማነሳሳት ተሳትፎውን የሚያጎለብቱ በየ2 ወሩ አንድ በራሪ ፅሁፍና አንድ ብሮሸር በአመት 6 በራሪ ጽሁፍና 12 ብሮሸር ተዘጋጅተው ማሰራጨት፣

**ተግባር 4፡** የሚኒስቴር መ/ቤቱንና የስራ ሂደቶችን የሚያንጸባርቁ አንድ አመታዊ አጀንዳ፣ አንድ ፖስተርና አንድ ካላንደር ማዘጋጀት፣

**ግብ ሦስት፡ የተለያዩ ህብረተሰቡን በቀጥታ ማግኘት የሚያስችሉ ስልቶችን በመጠቀም (በሚዲያ ቱር፣ በፕሬስ ኮንፈረንስ፣ በአውደ ርዕይ እና በመሳሰሉት) በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ዙሪያ በሕብረተሰቡ እና በባለድርሻ አካላት ዘንድ ሰፊ የህዝብ ንቅናቄ ለመፍጠር የሚያስችል ግንዛቤ መፍጠር፡፡**

**ተግባር 1፡** የተቋሙን አበይት የስራ አፈፃፀሞች በመለየት አንድ ጊዜ የሚዲያ ተቋማት የመስክ ጉብኝት /ሚዲያ ቱር/ እንዲያደርጉና ለህብረተሰቡ የስራዎቹን ውጤት እንዲያሳውቁ ማድረግ፣

**ተግባር 2፡** የተቋሙን የስራ እንቅስቃሴዎች ከሀገር አቀፍና አለም አቀፍ ሁነቶች ጋር በማያያዝ 6 ሁነቶች እንዲከበሩ ማድረግ፣

**ተግባር 3፡** በተቋሙ አጠቃላይ የስራ ክንውኖችና ተልዕኮ አፈጻጸም ዙሪያ በየሩብ ዓመቱ ፕሬስ ኮንፈረንስ ማዘጋጀት፣

**ተግባር 4:** በተቋሙ አጠቃላይ የስራ ክንውኖች እና ወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ 2 ጊዜ የክፍለ ህዝብ አስተያየት በመሰብሰብ ግብረመልስ መስጠት፣

**ተግባር 5:** በተቋሙ ተልዕኮ አፈፃፀምና በተገኙ ውጤቶች ዙሪያ የፎቶና የቪዲዮ አውደ ርዕይ አንድ ጊዜ ማዘጋጀት፣

**ተግባር 6:** የመረጃ ጥያቄ ለሚያቀርቡ የተቋሙ ደንበኞችና ተገልጋዮች በመረጃ ዴስክ በኩል በየሳምንቱ ተደራጅቶ ተገቢው ምላሽ መስጠት::

## 10. የባለ ፈርጀ ብዙ ሥራዎች

**ዓላማ:** **በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሥር በተዋቀሩ ቢሮዎች፣ በተጠሪ ተቋማት፣ በክልሎች እና አዲስ አበባና ድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮች የከተማ ልማት እና የኮንስትራክስን ዘርፍ ተቋማት ሴቶችና ወጣቶች፣ አረጋውያን፣ የአካል ጉዳተኞች እንዲሁም ታዳጊ ክልሎች የዘርፉ ልማት ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ ነው:: እንዲሁም የከባቢያዊ ጉዳዮች በልማት ሥራዎች ላይ ታሳቢ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው::**

**ጥቅል ግብ:** **የከተማ ልማት እና የኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት በሚያካሂዷቸው የልማት ሥራዎች የአካባቢ ብክለትን በመጠበቅ ሴቶችን፣ ወጣቶችን፣ አረጋውያን፣ የአካል ጉዳተኞች እንዲሁም ታዳጊ ክልሎች ቀጥተኛ ተሳታፊና ተጠቃሚ መሆናቸው ይረጋገጣል::**

**ዝርዝር ግቦችና ተግባራት**

**ግብ አንድ:** **በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ፣ በተጠሪ ተቋማት፣ በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፎች የሥርዓተ ፆታ፣ የወጣቶች፣ የኤ.ች.አይ.ቪ/ኤድስ የአረጋውያን፣ የህጻናት፣ የአካል ጉዳተኞች እና የአካባቢ ደህንነት ጉዳዮች ተቋማዊ የሆነ ይዘት እንዲኖረውና እንዲካተት በማድረግ የሴቶች እኩልነት ይረጋገጣል::**

**ተግባር 1:** በተካሄዱ የሥራ ዕድል ፈጠራ፣ በኮንዶሚኒየም ቤቶች ማስተላለፍ፣ እንዲሁም በሴቶችና በወጣቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ዙሪያ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ክፍተቶች እንዲለዩና መፍትሔ እንዲያገኙ ማድረግ፣

**ተግባር 2:** በዕቅድ ዘመኑ በሚወጡ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶችና ዕቅዶች ውስጥ የሥርዓተ ፆታ፣ የወጣቶች እና የኤ.ች.አይ.ቪ/ኤድስ ጉዳዮች የተካተቱና ግምት ውስጥ የገቡ መሆኑን ከአፈጻጸም ሪፖርቶች በመመልከትና የዝንባሌ ትንተና በማከናወን እንዲረጋገጥ ማድረግ፣

**ተግባር 3:** በእቅድ ዘመኑ በሚከበሩ 4 በዓላት ላይ የሥርዓተ ፆታ፣ የወጣቶች እና የኤ.ች.አይ.ቪ/ ኤድስ ጉዳዮች ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች እንዲሰጡ ማድረግ፣

**ተግባር 4:** በእቅድ ዘመኑ በWEDP፣ በአለም ባንክና በጀርመን ባንክ (KFW) እንዲሁም በULGDP በሚደገፉ ፕሮጀክቶች ሴቶችና ወጣቶች ተጠቃሚ መሆናቸውን፣ እንዲሁም በጥቃቅንና

አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ ከሚፈጠሩ የሥራ አድሎች ውስጥ 50% ያህሉ ሴቶች መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

**ተግባር 5:** በአቅድ ዘመኑ የልዩ ድጋፍ እርምጃዎችን (Affirmative Action) በማጠናከርና በዘርፉ ሴቶች የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ተሳትፎአቸው 50% እንዲሆን በማድረግ፣ የአፈጻጸም ክፍተቶች እንዲጠቡና ተሳታፊና ተጠቃሚነታቸው እንዲረጋገጥ ማድረግ፣

**ተግባር 6:** ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከሚፈጠረው የሥራ ዕድል ውስጥ 50 በመቶ ሴቶች መሆናቸውን ክትትል በማድረግ በሪፖርት ማረጋገጥ፣

**ተግባር 7:** ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከሚቀርቡ የተለያዩ ድጋፎች (በማምረቻና መሸጫ ቦታ፣ በብድር፣ በስልጠና፣ በገበያ) 50 በመቶ ሴቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረጉን ክትትል በማድረግ በሪፖርት ማረጋገጥ፣

**ተግባር 8:** የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ተጠቃሚ ከሚሆኑት ውስጥ 50% ሴቶች መሆናቸውን ክትትል በማድረግ በሪፖርት ማረጋገጥ።

**ተግባር 9:** **በዕቅድ ዘመኑ በሚወጡ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶችና ዕቅዶች ውስጥ የአረጋውያንና፣ የህጻናት፣ የአካል ጉዳተኞች እና የአካባቢ ደህንነት ጉዳዮች በሁሉም ዘርፎች የተካተቱና ግምት ውስጥ የገቡ መሆኑን ከአፈጻጸም ሪፖርቶች በመመልከትና የዝንባሌ ትንተና በማከናወን እንዲረጋገጥ ማድረግ፣**

**ግብ ሁለት: የታዳጊ ክልሎች የማስፈጸም አቅም እንዲጎለበት ይደረጋል።**

**ተግባር 1:** ለታዳጊ ክልሎች ራሱን የቻለ ዓመታዊ የልዩ ድጋፍ ዕቅድ እንዲዘጋጅ በማድረግ የአፈፃፀም ድጋፍ፣ ክትትልና ግብረ-መልስ ማከናወን፣

**ተግባር 2:** በአራቱ ታዳጊ ክልሎች የሚደረገውን ሁሉን አቀፍ የልማትና መልካም አስተዳደር ስራዎችን ለመደገፍ የሚያስችል አንድ የልዩ ድጋፍ አሰጠጥ ማኑዋል እንዲዘጋጅ ማድረግ፣

**ተግባር 3:** በታዳጊ ክልሎች ከሚገኙ ከተሞች አንድ ከተማ ከውጭ አገር ከተማ እንዲሁም 4 ታዳጊ ከተሞች ከ4 የሀገር ዉስጥ እህት ከተሞች ጋር ትስስር በመፍጠር ልምድ እንዲለዋወጡ ማድረግ፣

**ተግባር 4:** በታዳጊ ክልሎች የሚገኙ 40 የዘርፉ አስፈጻሚ አካላት አመራሮችና ባለሙያዎችን ሥልጠና በመስጠት በክልሎቹ በሚገኙ ከተሞች የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማትን ማስፋፋት።

## 11. የጥናትና ምርምር፣ የዕቅድ ዝግጅት እና የፖሊሲና ፕሮግራም የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ሥራዎች

ጥቅል ዓላማ፡ የከተማ ልማትና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዘርፎች ክፍተቶችን በለመየትና የፖሊሲ አቅጣጫዎችን በማመላከት እንዲሁም ጠንካራ የክትትል፣ የድጋፍና የግብረ-መልስ ሥርዓት በመዘርጋት የዘርፉን አፈጻጸም ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ የበኩሉን ለመወጣት ነው፡፡

ጥቅል ግብ፡ የከተማ ልማትና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዘርፎችን ክፍተቶች በለመየትና የፖሊሲ አቅጣጫዎችን በማመላከት ዘርፎች በተሟላና ግልጽ በሆኑ ፖሊሲዎች፣ የሕግ ማዕቀፎች፣ ስትራቴጂዎችና የልማት ፕሮግራሞች እንዲዘጋጁ በማድረግና ጠንካራ የክትትል፣ የድጋፍና የግብረ-መልስ ሥርዓት በመዘርጋት ዘርፎቹ በዕቅድ እንዲመሩ ይደረጋል፡፡

### 11.1. የዕቅድ ዝግጅት፣ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ሥራ

ዓላማ፡ የጠራ፣ ግልጽና ተፈጻሚነት ያለው የሚኒስቴር መ/ቤቱን የበጀት ዓመቱን ዕቅድ በማዘጋጀት እና ወቅታዊ ክትትልና ግምገማ በማድረግ በፕሮግራሞች የተጣሉ ግቦች ተግባራዊነት ለማረጋገጥ ነው፡፡

ጥቅል ግብ፡ የጠራ፣ ግልጽና ተፈጻሚነት ያለው የሚኒስቴር መ/ቤቱን የበጀት ዓመቱን ዕቅድ በማዘጋጀት እና ወቅታዊ ክትትልና ግምገማ በማድረግ በፕሮግራሞች የተጣሉ ግቦች ተግባራዊነት ለማረጋገጥ ነው፡፡

ዝርዝር ግቦችና ተግባራት

ግብ አንድ፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚይዛቸው ግቦች እውን ለማድረግ የሚከናወኑ ተግባራት ግልጽ፣ ተነሳሽነትና የባለቤትነት ስሜትን የሚፈጥሩ እና ተጠያቂነትን የሚያስከትሉ ሆነው በአግባቡ እንዲፈጸሙ ይደረጋሉ፡፡

ተግባር 1፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የ2005 በጀት ዓመት ዕቅድ 300 ኮፒ አሳትሞ ለባለድርሻ አካላት ማሰራጨት፣

ተግባር 2፡ የ2005 በጀት ዓመት መሪ ዕቅድ ላይ ሁሉም በየደረጃው የሚገኙ በዘርፉ የተሰማሩ ባለድርሻ አካላት አመራሮች እና ፈጻሚዎች የጠራ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ፣

ተግባር 3፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የ2005 በጀት ዓመት ዕቅድ በግማሽ ዓመቱ መከለስ፣

ተግባር 4፡ የተጠሪ ተቋማት፣ የክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የ2005 በጀት ዓመት ዕቅድ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚገኙ ቢሮዎች ጋር በተናበበ ሁኔታ መዘጋጀቱን ማረጋገጥ፣

ተግባር 5፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የ2006 በጀት ዓመት መሪ ዕቅድ ማዘጋጀት፣

**ግብ ሁለት፡** **በሚኒስቴር መ/ቤቱ አስተባባሪነት በዘርፉ በበጀት ዓመቱ ለማከናወን የታቀዱ ሥራዎችና ተግባራት በተቀመጠላቸው መርሃግብር መሠረት መከናወናቸውን በሪፖርት ይረጋገጣል፡፡**

**ተግባር 1፡** የዘርፉን የ2004 የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በአማርኛና በእንግሊዝኛ በማዘጋጀት ለገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መላክ፣

**ተግባር 2፡** የ2004 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በሐምሌ ወር በማዘጋጀት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማቅረብ፣

**ተግባር 3፡** በበጀት ዓመቱ የሚኒስቴር መ/ቤቱ 8 ወርሃዊ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ሰነዶች ማዘጋጀት፣

**ተግባር 4፡** የበጀት ዓመቱ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት፣ የግማሽ ዓመትና የዘጠኝ ወር ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ሰነዶች በጥቅምት፣ በጥርና በሚያዚያ ወራት ማዘጋጀት፡፡

## 11.2. የክልሎች ድጋፍና ክትትል ኢንስፔክሽን ሥራ

**ዓላማ፡** **በሚኒስቴር መ/ቤቱ በበጀት ዓመቱ ለማከናወን የታቀዱ እና በፕሮግራሞች የታቀፉ ተግባራት በተያዘላቸው ዕቅድ መሠረት መከናወናቸውን በመገምገምና በመመዘን ግብረመልስ ለመስጠት ነው፡፡**

**ግብ፡** **በሚኒስቴር መ/ቤቱ በበጀት ዓመቱ ለማከናወን የታቀዱ እና በፕሮግራሞች የታቀፉ ተግባራት በተያዘላቸው ዕቅድ መሰረት በአግባቡ ይከናወናሉ፡፡ በዘርፉ በበጀት ዓመቱ ለማከናወን በታቀዱ ሥራዎች እና ተግባራት የሚጠበቁ ውጤቶች መገኘታቸውን በመገምገም እና ፈጻሚዎችን በመመዘን ግብረ መልስ ይሰጣል፡፡**

**ዝርዝር ተግባራት**

**ተግባር 1፡** በፌዴራል፣ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የተከናወነው የዕቅድ ማናበብ ስራ በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱ መሰረት መሆኑንና ተግባራዊነቱን በመስክ አንድ ጊዜ ክትትል በማድረግ ማረጋገጥ፣

**ተግባር 2፡** የክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት መነሻ በማድረግ በየሩብ ዓመቱ በመስክ (Inspection) በማረጋገጥ የተሻሉ ተሞክሮዎችን መለየት፣ ከህዝብ ግንኙነት ጋር በመሆን መቀመር፣

**ተግባር 3፡** በከተሞችና በክልሎች የሚካሄዱ ድጋፎች በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት (Information Technology Infrastructure) የታገዙ እንዲሆኑ ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና ዳታ ቤዝ ልማት ቢሮ ጋር በትብብር መስራት፣

**ተግባር 4፡** በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በእቅድና በአፈጻጸም መካከል ያለውን ልዩነት (Gap) በመለየት በስልጠና እና በማቴሪያል ድጋፍ ማድረግ፣

**ተግባር 5፡** የየበጀት ዓመቱ የመጀመሪያው ሩብ ዓመትና የሶስተኛው ሩብ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ የቪድዮ ኮንፍረንስ ከክልሎችና ከተሞች ጋር በጥቅምትና ሚያዚያ ወራት ማካሄድ፣

**ተግባር 6፡** የየበጀት ዓመት የመጀመሪያው እና የሁለተኛው ግማሽ ዓመት በመስክ የሴክተር ተቋማት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ለማድረግ በጥቅምት እና በግንቦት ወር ቅድመ ዝግጅት ማድረግ፣

**ተግባር 7፡** ያለፈው በጀት ዓመት የሁለተኛው ግማሽ አመት እና የያዝነው በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት በመስክ የሴክተር ተቋማት የዕቅድ አፈጻጸም ምዘና በሐምሌ እና በጥር ወራት ማካሄድ፣

**ተግባር 8፡** ከክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች በመቀበል በአፈጻጸም ላይ በታዩ ጠንካራ እና መሻሻል የሚገባቸውጉዳዮች ተለይተው በየሩብ ዓመቱ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 9፡** የክትትል፣ግምገማ፣ ግብረ-መልስና ሽልማት መመሪያ በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ፡፡

### 11.3. የከተማ ልማት ዘርፍ እና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ፖሊሲና ፕሮግራም አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ሥራ

**ዓላማ፡** በከተማ ዘርፍ የሚታዩ ክፍተቶች እንዲለዩና የፖሊሲ አቅጣጫዎች እንዲቀመጡላቸው፣ ዘርፉም በተሟላና ግልጽ በሆኑ ፖሊሲዎች፣ህጎች ስትራቴጂዎችና ዕቅዶች እንዲመራ የተሟላ የአሰራር ሥርዓት እንዲዘረጋለት እና ለሃገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መፋጠን ተገቢውን ሚና እንዲጫወት ማድረግ የሚያስችል ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ነው፡፡

**ግብ፡** በከተማ ልማት ዘርፍና በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የሚታዩ ክፍተቶች እንዲለዩና የፖሊሲ አቅጣጫዎች እንዲቀመጡላቸው፣ ዘርፉም በተሟላና ግልጽ በሆኑ ፖሊሲዎች፣ ህጎች ስትራቴጂዎችና ዕቅዶች እንዲመራ የተሟላ የአሰራር ሥርዓት እንዲዘረጋለት እና ለሃገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መፋጠን ተገቢውን ሚና እንዲጫወት ማድረግ የሚያስችል ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡

**ዝርዝር ተግባራት**

**ተግባር 1፡** የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የልማት ፕሮግራም የማጠናቀቂያ ዘመን የአፈጻጸም ፋይዳ ግምገማ ማካሄድ፣

**ተግባር 2፡** በ10 ቢሮዎች/የሥራ ክፍሎች (58 መምሪያዎች) ከGTP አንጻር 120 ወርሃዊ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የአፈጻጸም ግምገማ መድረኮችን ማመቻቸት፣

ተግባር 4፡ የ10 ቢሮዎች/የሥራ ክፍሎችን 12 ወርሃዊ፣ 4 የሩብ ዓመት፣ የግማሽ ዓመት፣ የዘጠኝ ወራትና ዓመታዊ የአፈጻጸም ሪፖርቶችን በማሰባሰብ፣ ትሬንድ አናሊሲስ በመስራት የጽሑፍ ግብረ-መልስ መስጠት፡፡

ተግባር 3፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱና በሥሩ የሚገኙ ቢሮዎች/የሥራ ክፍሎችን በ5 ክልሎች/የከተማ አስተዳደሮች ከሚገኙ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፎች ተጓዳኝ የስራ ክፍሎች ጋር ዓመታዊ እቅዶችን በጋራ ማሳካት የሚያስችሉ ስምምነቶች ማፈራረም፡፡

## 11.4. የፕሮግራም በጀት ዝግጅት፣ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ሥራ

**ዓላማ፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱን ፕሮግራሞች ለማስፈጸም የሚረዳ ሀብት በማፈላለግ፣ ውጤት ላይ መሠረት ያደረገ የፕሮግራም በጀት በማዘጋጀት፣ ተፈጻሚነቱን በመከታተልና ግብረመልስ በመስጠት ውጤታማ የበጀት አጠቃቀምን እንዲጎለብት ለማድረግ ነው፡፡**

**ጥቅል ግብ፡ የፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ ሀብትን በማፈላለግ፣ ውጤት ላይ መሠረት ያደረገ የፕሮግራም በጀትን በማዘጋጀትና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ በመጠቀም እና የበጀት አጠቃቀም ጥናት በማካሄድ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተያዙት ግቦችና ዓላማዎች እንዲሳኩ ይደረጋል፡፡**

**ዝርዝር ግቦችና ተግባራት**

**ግብ አንድ፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱን ፕሮግራሞች ለማስፈጸም የሚረዳ ሀብት በማፈላለግ፣ ውጤት ላይ መሠረት ያደረገ የፕሮግራም በጀት በማዘጋጀት፣ ተፈጻሚነቱን በመከታተልና ጥናት በማካሄድ ውጤታማ የበጀት አጠቃቀምን እንዲጎለብት ይደረጋል፡፡**

ተግባር 1፡ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ብር 5 ቢሊዮን ማፈላለግ፣

ተግባር 2፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱን የ2006 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት ዕቅድ ማዘጋጀት፣

ተግባር 3፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፊዚካል ዕቅድ ከፋይናንስ ዕቅድ ጋር መናበቡን ማረጋገጥ፣

ተግባር 4፡ የገንዘብ ፍሰት ዕቅድና የፕሮግራም በጀት የሥራ መርሃ ግብር ማዘጋጀት፣

ተግባር 5፡ በፕሮግራም በጀት አፈጻጸም ሂደት የበጀት እጥረት በታየባቸው ውጤቶች ሥር የሚገኙ የበጀት አርዕስት የበጀት ዝውውር ማካሄድና ተጨማሪ በጀት ለሚያስፈልጋቸው ስራዎች በጀት ማስፈቀድ፣

ተግባር 6፡ በጸደቀው የፕሮግራም በጀት መሠረት ቢሮዎች በጀታቸውን ወደ መምሪያና ግብ እንዲያወርዱ ማድረግ፡፡

**ግብ ሁለት፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱን የፕሮግራም በጀት አጠቃቀም በየጊዜው በማጥናት የበጀት አፈጻጸሙ ውጤታማ እንዲሆን ይደረጋል፡፡**

**ተግባር 1፡** በዘርፉ ለሚከናወኑ የልማት ስራዎች የበጀት ምንጭ (ፈንድ) ለማፈላለግ የሚረዳ ጥናት ማካሄድ፣

**ተግባር 2፡** የሚ/ር መ/ቤቱ ወርሃዊ፣ የሩብ ዓመት እና ዓመታዊ የፕሮግራም በጀት ዕቅድ አፈጻጸም ማዘጋጀት፣

**ተግባር 3፡** በፕሮግራም በጀት አሠራር ላይ በየጊዜው የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመለየትና የመፍትሔ ሃሳብ በማስቀመጥ አሰራሩ በተሟላ መልኩ እንዲተገበር ማድረግ፣

**ተግባር 4፡** ቢሮዎች የመ/ቤቱን የመረጃ መረብ “Portal“እና የ”IBEX” ስርዓትን በቀጥታ በመጠቀም ወቅታዊ የበጀት አፈጻጸም መረጃ የሚያገኙበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲመቻች ማድረግ፣

**ተግባር 5፡** የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የፕሮግራም በጀት አጠቃቀም ሁኔታን አስመልክቶ ግምገማ በማካሄድ ወቅታዊ የመፍትሔ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ሰነድ እንዲዘጋጅ ማድረግ፡፡

## 11.5. የስታትስቲክስ፣ ጥናትና ምርምር ሥራ

**ዓላማ፡ በከተማ ዘርፉ መሠረታዊ የስታቲስቲክስ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን ለፕሮግራሞች ውጤት፣ ስኬትና ፋይዳ ግምገማ የመረጃ ምንጭ እና የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ የጥናትና ምርምር ማዕከል መሆን ነው፡፡**

**ግብ፡ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ በተከናወኑትና በመከናወን ላይ ያሉ የልማት ስራዎች በከተማ ነዋሪው ህዝብ ኑሮ እና በሃገሪቱ ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ላይ ያመጡትን ፋይዳ፣ ለመገምገምና የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ለማስቀመጥ የሚያስችሉ መረጃዎችን የመሰብሰብ የማጠናቀር እና በበጀት ዓመቱ በዘርፉ ሁለት የተለያዩ የጥናትና የምርምር ስራዎችንና አንድ የስታቲስቲካል አብስትራክት ዝግጅት ስራዎችን ማከናወን፡፡**

**ዝርዝር ተግባራት**

**ተግባር 1፡** የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ልማት ለኢትዮጲያ ኢኮኖሚ እድገት እያበረከተ ያለውን ሚና በሞዴል የታገዘ እንዲሆን ከኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪና ሬጉላቶሪ ቢሮ ጋር በመተባበር እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ ድረስ አንድ ጥናት ማከናወን፣

**ተግባር 2፡** በ2004 በጀት ዓመት በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ዙሪያ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በማደራጀት ለላቀ ጥናትና ትንተና ዝግጁ ማድረግ፣

**ተግባር 3፡** የከተሞች መሠረተ-ልማትና አገልግሎት አቅርቦትን እና ፍላጎትን የሚዳስስ አንድ ጥናት ማካሄድ፣

ተግባር 4፡ የዘርፉን የአምስት አመት የልማት ስራ ለመገምገም የሚያስችል የአብስትራክት (2000-2004) ሠነድ ተዘጋጅቶ እንዲሰራጭ ማድረግ፣

ተግባር 5፡ የከተማ መሬት ልማት ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እድገት ያለውን አስተዋጽኦ ለማጥናት የሚያስችል የአጠናን ስልት የሚያሳይ ተሞክሮ ተቀምሮ ለጥናት ዝግጁ ማድረግ፣

ተግባር 6፡ የከተማ መልካም አስተዳደር ሚና በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ያለው ተፅዕኖ ለማጥናት የሚያስችል ተሞክሮ መቀመር፣

ተግባር 7፡ ለ2006 በጀት ዓመት ለሚጠና አንድ ጥናት የፈንድ ማፈላለጊያ ፕሮፖዛል ማዘጋጀት፣ ፈንድም ማፈላለግ፣

ተግባር 8፡ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ በተዘረጋው መሠረታዊ የስታቲስቲክስ መረጃ ሥርዓት እና በተደራጀው የመረጃ ቋት መሠረት ክልሎች እና ከተሞች እየተጠቀሙና እየተተገበሩ መሆኑን ክትትል ማድረግ፡፡

## 12. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ዳታቤዝ ልማት ሥራዎች

**ጥቅል ዓላማ፡ የዘርፉን የአሠራር በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን በመደገፍ ፈጣንና ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ በሚደረገው ርብርብ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ማድረግ ነው፡፡**

**ጥቅል ግብ፡ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ የተቀናጀ የአፕሊኬሽንና ዳታቤዝ ሥርዓት በመገንባት፣ ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥና የኢንፍራስትራክቸር ደህንነትን በማስፈንና የኢ.ኮ.ቴን አጠቃቀምን በማጎልበት ለልማት ያለው አስተዋጽኦ እንዲረጋገጥ ይደረጋል**

### 12.1. የተቀናጀ የአፕሊኬሽንና ዳታ ቤዝ ልማት ሥራ

**ዓላማ፡ በዘርፉ አስተማማኝና የተቀናጀ የአፕሊኬሽንና ዳታቤዝ ሥርዓት እንዲኖር ማስቻል ነው፡፡**

**ግብ፡ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን አፕሊኬሽንኖች ዳታ ቤዞች እንዲለሙና የውጤት ተኮር የሥራ አፈጻጸም ምዘና አውቶሜት እንዲሆን ይደረጋል፡፡**

**ዝርዝር ተግባራት**

ተግባር 1፡ አንድ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ሬጉላቶሪ ቢሮ የኮንትራክተሮችን፣ ባለሙያዎችና ማሽነሪ ፈቃድና እድሳት የመረጃ ሥርዓት አቶሜት ማድረግ፣

ተግባር 2፡ በሚኒስቴር መስሪያቤቱ ሥር ያሉ ፕሮጀክቶችን በቀላሉ ማስተዳደር የሚያስችል የፕሮጀክት ማኔጀመንት ሶፍትዌር እንዲለማ ማድረግ፣

ተግባር 3፡ የተቀናጀ የንብረት አስተዳደር፣ የጠቅላላ አገልግሎትና የአቅርቦት የመረጃ ሥርዓት በሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዲዘረጋ ማድረግ፣

ተግባር 4፡ የ37 ከተሞች የመሬት አጠቃቀም ፕላን ስካንና ጂኦሪፈርንስ እንዲሆን ማድረግ፣

ተግባር 5፡ በመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሚከናወነው የኢሰርቪስ አገልግሎት ኦቶሜሽን በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተግባራዊ ማድረግ፣

ተግባር 6፡ የተጀመረውን የውጤት ተኮር ኦቶሜሽን ተጠናቆ እንዲተገበር ማድረግ፣

ተግባር 7፡ የተቀናጀ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መረጃ ስርዓት ለመዘርጋት ጥናት ማካሄድና በ4 ቢሮዎች የሴክተሩን ዳታቤዝ ማደራጀት።

## 12.2. ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስልጠና እና የአጠቃቀም ፖሊሲ ክትትልና ድጋፍ ሥራ

**ዓላማ፡** **የመስሪያ ቤቱ ሠራተኞች ስልጠናዎችን፣ የአጠቃቀም ማኑዋሎችንና ፖሊሲዎች አዘጋጅቶ በመስጠት ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን የሥራቸው ዋና አጋዥ እንዲያደርጉት ማድረግ ነው።**

**ግብ፡** **በዘርፉ ለሚገኙ ሠራተኞች ስልጠናዎችን፣ የአጠቃቀም ማኑዋሎችንና ፖሊሲዎች ተዘጋጅተው እንዲሰጡ ይደረጋል።**

**ዝርዝር ተግባራት**

ተግባር 1፡ ለ11 የክልል ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያዎች የSQL፣ GIS እና ORACLE ስልጠና መስጠት፣

ተግባር 2፡ በከተማ ልማትና በኮንስትራክሽን ዘርፍ በክልሎችና በተጠሪ ተቋማት የዳታቤዝና አፕሊኬሽን በተመለከተ በዓመት ሁለት ጊዜ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

ተግባር 3፡ በጂኦስፓሻል ዳታቤዝ ዘርፍ በአገር አቀፍ ደረጃ የፀደቁ የተለያዩ ስታንዳርዶችን ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ሊፀድቁ የሚገባቸውን መመሪያዎች/ስታንዳርዶች ማዘጋጀት፣

ተግባር 4፡ የከተማ የመሬት መረጃዎችን ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ የሚያስችል ድህረ-ገፅ ዝግጅት በማጠናቀቅ ተግባራዊ ማድረግ።

## 12.3. የኔትዎርክና ሴኪዩሪቲ ኢንፍራስትራክቸር ልማትና አስተዳደር ሥራ

**ዓላማ፡** **በዘርፉ ቀልጣፋና አስተማማኝ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ለማስቻል የመረጃ መረብ ኢንፍራስትራክቸር በመዘርጋትና በማስተዳደር ፈጣንና ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ በሚደረገው ርብርብ አስተዋጽኦ ማድረግ ነው።**

**ግብ፡** **በተቋሙና በዘርፉ ለሚኖር ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥና ፍሰት አስተማማኝ የመረጃ መረብ ኢንፍራስትራክቸር እንዲኖር ይደረጋል።**

**ዝርዝር ተግባራት**

**ተግባር 1፡** በ2004 በጀት ዓመት የተጀመረውን ከዋናው መ/ቤት አካባቢ ለተወሰኑ ቢሮዎች አገልግሎት እንዲሰጥ በተወሰነው ተጨማሪ ሕንጻ የሎካል ኤርያ ኔትወርክ በመዘርጋትና ከዋናው መ/ቤት ጋር በዋይድ ኤርያ ኔትወርክ የማገናኘት ሥራ በማጠናቀቅ በአጠቃቀሙ ላይ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

**ተግባር 2፡** በ2004 በጀት ዓመት የተጀመረውን የሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሦስቱ ተጠሪ ተቋማት፣ ከክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች ጋር በዋይድ ኤሪያ ኔትወርክ /WAN/ የማገናኘት ሥራ በማጠናቀቅ በአጠቃቀሙ ላይ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

**ተግባር 3፡** የሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎች ጋር የሚያደርገው የክትትልና ድጋፍ እንዲሁም ግብረ መልስ ሥርዓት 2 ጊዜ በቪዲዮ ኮንፈረንስ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ ማድረግ፣

**ተግባር 4፡** በኔትወርክና ሴኪዩሪቲ ሲስተም አጠቃቀም ዙሪያ 2 ማኑዋሎች (የፋይል ሴኪዩሪቲና የአንቲ ቫይረስ አጠቃቀም) ተዘጋጅተው ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣

**ተግባር 5፡** በክልሎችና በተጠሪ ተቋማት የኔትወርክና ሴኪዩሪቲ ኢንፍራስትራክቸር ልማትን በተመለከተ 2 ጊዜ ክትትልና ድጋፍ ተደርጎና አፈጻጸሙ ላይ ክትትል በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት፣

**ተግባር 6፡** በ2004 በጀት ዓመት የተጀመረውን ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ሬጉላቶሪ ቢሮ ለሚሰራው Queue Management System (QMS) የኔትወርክ ዝርጋታ በማጠናቀቅ በአጠቃቀሙ ላይ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

**ተግባር 7፡** በሚቀጥሉት 15 ዓመታት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያስፈልግ ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ኢንፍራስትራክቸር ፍላጎት (IP Telephony, Video Conference, CCTV, etc) እንዲጠና ማድረግ፡፡

## 13. የ2005 በጀት አመት የበጀት ዕቅድ

ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚ/ር ለ2005 በጀት ዓመት የጸደቀው ጠቅላላ በጀት ብር 973.03 ሚሊዮን ነው፡፡ የበጀቱ መጠን ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ እንደተመለከተው በመደበኛ በጀት ብር 67.735 ሚሊዮን ሲሆን በካፒታል በጀት ብር 838.97 ሚሊዮን ነው፡፡ ከመንግስት ትሬዠሪ፣ ከብድር እና ከዕርዳታ ከተገኘ ካፒታል ፈንድ በጀት የተያዘላቸው ፕሮግራሞች ከነተፈቀደላቸው በጀት መጠን በሠንጠረዥ 1 የተመለከተ ሲሆን በሠንጠረዥ 2 ለበጀት ዓመቱ የጸደቀው ጠቅላላ የመደበኛና የካፒታል በጀት መጠን በጀቱ በተያዘለት ፕሮግራም ተዘርዝሮ ቀርቧል፡፡ የካፒታል በጀቱ በተገኘበት ምንጭ በዝርዝር ሲታይ ከመንግስት ግምጃ ቤት ብር 257.69 ሚሊዮን፣ ከብድር ብር 90.99 እና ከዕርዳታ ብር 490.29 ሚሊዮን ነው፡፡

**ሠንጠረዥ 1፡ የ2004 በጀት ዓመት የጸደቀ ካፒታል በጀት በፕሮግራምና በንዑስ ፕሮግራም (በ'000' ብር)**

| ተ.ቁ. | ፕሮግራም/ንዑስ ፕሮግራም | ከመንግስት ግምጃ ቤት | ብድር | ዕርዳታ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| ጠቅላላ ድምር | | 257,689.60 | 90,996.10 | 490,288.70 | 838,974.40 |
| 1 | የመኖሪያ ቤቶችና የመንግስት ኮንስትራክሽን ልማት ፕሮግራም | 171,926.60 | | | 171,926.60 |
| 2 | የከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ፕሮግራም | 12,639.00 | 90,996.10 | 490,288.70 | 669708.34 |
| 3 | የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ፕሮግራም | 68,124.00 | | | 68,124.00 |
| 3.1 | የከተማ መሬት ልማት አቅርቦትና አስተዳደር ንዑስ ፕሮግራም | 5,124.00 | | | |
| 3.2 | የፌዴራል የተቀናጀ የመሬት መረጃ ስርዓት ዝርጋታ ንዑስ ፕሮግራም | 63,000.00 | | | |
| 4 | የጥናትና የዕቅድ ዝግጅት እና የፖሊሲ ፕሮግራም የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ፕሮግራም | 5,000.00 | | | 5,000.00 |

**ሠንጠረዥ 2፡ ለ2005 በጀት ዓመት የጸደቀ መደበኛና ካፒታል በጀት በፕሮግራምና በንዑስ ፕሮግራም**

| ተ.ቁ | ፕሮግራም/ንዑስ ፕሮግራም | ጠቅላላ ድምር | መደበኛ | ካፒታል | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ከመንግስት ግምጃ ቤት | ከመንግስት ግምጃ ቤት | ብድር | ዕርዳታ | ድምር |
| ጠቅላላ ድምር | | 973,033.41 | 67,735.61 | 257,689.60 | 90,996.10 | 490,288.70 | 838,974.40 |
| 1 | የሚ/ር መ/ቤቱ አመራርና አስተዳደር ፕሮግራም | 22,848.88 | 22,848.88 | | | | |
| 2 | የጥናትና የዕቅድ ዝግጅት እና የፖሊሲ ፕሮግራም የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ፕሮግራም | 9,354.74 | 4,354.74 | 5,000.00 | | | 5,000.00 |
| 3 | የመኖሪያ ቤቶችና የመንግስት ህንጻዎች ኮንስትራክሽን ልማት ፕሮግራም | 177,937.53 | 6,011.53 | 171,926.60 | | | 171,926.60 |
| 4 | የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አቅም ግንባታና ሬጉላቶሪ ፕሮግራም | 8,975.49 | 8,975.49 | | | | |
| 5 | የከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ፕሮግራም | 598,153.47 | 4,229.67 | 12,639.00 | 90,996.10 | 490,288.70 | 593,923.80 |
| 6 | የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ፕሮግራም | 75,945.00 | 9,621.00 | 68,124.00 | | | 68,124.00 |

| ተ.ቁ | ፕሮግራም/ንዑስ ፕሮግራም | ጠቅላላ ድምር | መደበኛ | ካፒታል | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ከመንግስት ግምጃ ቤት | ከመንግስት ግምጃ ቤት | ብድር | ዕርዳታ | ድምር |
| 6.1 | የከተማ መሬት ልማት አቅርቦትና አስተዳደር ንዑስ ፕሮግራም ፕሮግራም | 8,435.60 | 3,311.60 | | | | |
| 6.2 | የፌደራል የተቀናጀ የመሬት መረጃ አያያዝ ስርአት ዝርጋታ ንዑስ ፕሮግራም | 67,509.40 | 4,509.40 | | | | |
| 7 | የከተማ ፕላን፣ ጽዳትና ውበት ፕሮግራም | 3,873.30 | 3,873.30 | | | | |

ለበጀት ዓመቱ የተያዘው በጀት በቁጠባና ብክነትን ባስወገደ መልኩ ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ ለመዋል ከፍተኛ ርብርብ ይደረጋል፡፡ በጀቱ ከተፈቀደ በኃላ በዕቅዱና ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት በአግባቡና በወቅቱ ጥቅም ላይ ለታለመት ዓላማ እየዋለ መሆኑን ለማረጋገጥ የቅርብ ክትትል የሚደረግበት ይሆናል፡፡ በመሆኑም በየወሩ የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት ለፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ እየቀረበ የሚገመገም ይሆናል፡፡

# ክፍል አራት

# ለሥራችን አፈጻጸም የምንከተላቸው አቅጣጫዎች እና ስጋቶችና የመፍትሔ አቅጣጫዎች

## 1. ለሥራችን አፈጻጸም የምንከተላቸው አቅጣጫዎች

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዳችን ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሴክተር የተሰጡ ተልዕኮዎች በሀገራችን ለማምጣት ከምናስበው የፖለቲካል ኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን አንፃር ጉልህ አስተዋፅኦ ያለው ነው፡፡ ይህ ተልዕኮ በሚጠየቀው ልክ የሴክተሩ አመራር ጨብጦታል ማለት ያዳግታል፡፡ በከተሞች የፖለቲካል ኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን ለማምጣት በቅደም ተከተል መፈጸም አለብን ብለን ያስቀመጥናቸው የልማትና የለውጥ ሰራዊት ግንባታ፣ የሥራ ዕድል ፈጠራ፣ የመሬት ልማትና ማኔጅመንት፣ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ...ወዘተ አይደለም የአመራሩ መሰጠት ተጓሎበት ያለምንም ደባል አጀንዳ ሙሉ የአካልና የአስተሳሰብ መሰጠት ብናደርግም ፈታኝ ስራዎች ናቸው፡፡ የአመራሩ በአስተሳሰብና በተግባር ባለቤት ሆኖ ሥራዎቹን በአጣዳፊነት እንዳይመራ ደግሞ የራሱ የግል አጀንዳዎች ላይ ተጠምዶ የሚታየው አመራር ቁጥር ቀላል አይደለም፡፡ እሱን የሚመለከት የተወሰነ ጥቅማ ጥቅም ሲነሳ የሚነቃቃውን ያህል በተሰጠው ኃላፊነት በዚያው ልክ አይነሽጠውም፡፡ በግምገማም ይሁን በሪፖርት አብዛኛው አመራር ጉድለቱ እንድታሳየው ፍቃደኛ አይደለም፡፡ ካነሳህም ያኮርፋል አልያም አካባቢውን በሙሉ የሚበክል ወይም ቀደም ሲል የነበረውንም አፈጻጸም ወደ ኋላ የሚጎትት አዋራ ያነሳል፡፡ በዚህም ምክንያት የውስጠ ድርጅት ትግላችን የሰላ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ለሥራዎቻችን በታሰበው ልክ ያለመፈጸም ወይም አሁን ካስፈጸምነው መጠን በላይ እንዳናስፈጽም ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ በስራ ያሰማራነው አመራርና ፈጻሚ በሚያስመዘግበው ልክ መዝነን በየደረጃው ስለማናስቀምጥ፣ ብናስቀምጥም ወስነን የምናደርገው ማሽጋሸግም ይሁን ለውጥ ስለሌለ ነው፡፡ ይህ እዳናደርግ ደግሞ የሸበበን አድርባይነት እና መቻቻል ነው፡፡ መፍትሔውም አመራሩና ፈጻሚው የሚሰማራበት ግልጽ ተልዕኮና ግብ ማስቀመጥ ነው፡፡ የዚህ ተልዕኮና ግብ አፈጻጸም በተከታታይ የሚገመገምበት እና ግብረ መልስ የሚሰጥበት ሥርዓትና መድረክ መፍጠር ነው፡፡ በዚህ ሂደት ለሥራዎቹ ባለቤትነት እየፈጠርን በመሄድ በምክንያት የሚያምን፣ ለተልዕኮው የተነሳሳ፣ ለጋራ ራዕይና ተልዕኮ ራሱን የሰጠ አመራርና ፈጻሚ እየፈጠርንና እያሰፋን መሄድ እንችላለን፡፡ በሂደቱም ለችግሮች መፍትሔ የማስቀመጥ ብቃታችንም በዚያው ልክ ተደማሪ እየሆነ ይሄዳል፡፡ የልማትና የለውጥ ሰራዊቱም እየተገነባና መሠረት እየጣለ መሄዱ አይቀርም፡፡ ይህንን መሰረታዊ የአፈጻጸም አቅጣጫ ለማስተግበር የሚከተሉትን አቅጣጫዎች ይዘን እንሄዳለን፡፡

## 1.1. የለውጥና የልማት ሰራዊት ግንባታ ላይ ትኩረት ሰጥቶ የመስራት አቅጣጫ መከተል

የመስሪያ ቤታችን የሰራዊት ግንባታ አሀዶች በመሰረታዊነት ሁለት ቦታ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው በአመራሩና በፈጻሚው ዘንድ የሚፈጠረው የልማትና የለውጥ ኃይል ነው፡፡ በዚህ እረገድ ለልማትና ለውጥ መድረክነት የመረጥነው በመ/ቤታችን ያሉ ተጠሪ መ/ቤቶችንም ጨምሮ ከ60 በላይ የሆኑ ንዑስ የሥራ ሂደቶችን (ቡድኖችን) ነው፡፡ በእያንዳንዱ ቡድን ትይዩ በመንግስት መዋቅር የግንባር ቀደሞች አሀድ እንዲደራጅ እናደርጋለን፡፡ በድርጅት በኩል ደግሞ የድርጅት አባላት ያሉበት የህዋስ አደረጃጀት በትይዩ እንፈጥራለን፡፡ የበላይ አመራሩም በተለይ ለመንግስታዊ ቡድኑ በወር አንድ ጊዜ የዕቅድ ክንውን ግምገማ በማድረግ በፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ አማካይነት የጽሑፍ ግብረ መልስ እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡ በድርጅት በኩል ደግሞ የግል ዕቅዱን መሠረት ያደረገ የወርሃዊ የአፈጻጸም ግምገማና ግብረ-መልስ በህዋስዋ አማካይነት ይደረጋል፡፡ በየመምሪያም የእያንዳንዱ ሠራተኛ አፈጻጸም እየተገመገመ ግብረ-መልስ የሚሰጥበት ሥርዓት ይፈጠራል፡፡ ከእያንዳንዱ ሠራተኛ የወርሃዊ ምዘና ጋር በተያያዘ ያለው አፈጻጸም በለውጥ ቢሮ በኩል ክትትልና ድጋፍ ይደረግበታል፡፡ ይህ ስራ የበለጠ ግልጸኝነትና ተጠያቂነት እየተላበሰ፣ አመራሩና ፈጻሚው የበለጠ በውጤቱ እየተመዘነ፣ በቀጣይም በውጤቱ መሠረት ተጨባጭ ግብረ-መልስ እየተሰጠው የሚሄድበት ሥርዓት ስለሚሆን አጠናክረን መቀጠል ይኖርብናል፡፡ በመ/ቤታችን የልማትና የለውጥ ሰራዊት መፍጠሪያ መሠረታዊ አቅጣጫና መድረኮች ያልናቸው እነዚህ ስለሆኑ ተጠናክረው የሚቀጥሉ ይሆናሉ፡፡ ሁለተኛው የሰራዊት ግንባታ ክንፍ የሕዝብ አደረጃጀት ነው፡፡ በፌደራል ከመ/ቤታችን ጋር ግንኙት ካላቸው ማህበራት ጋር የምንሰራው ሥራ ትኩረት የምንሰጠው ይሆናል፡፡ ይህ በሰራዊት ግንባታ መልክ ሳይሆን ማህበራቶቹ ልማታዊ አስተሳሰብ ለመገንባት የልማት ዕቅዶቻችን በተፋጠነ መንገድ ለማስፈጸምና ድጋፋዊ አስተሳሰብ እንዲኖራቸው የሚሰራ ስራ ይሆናል፡፡ ለሕዝብ ተሳትፎ ከወረዳ ወይም ከከተማ ቀበሌዎች በታች ባለው አደረጀጀት ማለትም በሰፈርና በቀጠና የሚፈጠረው የሴቶች፣ የወጣቶችና የነዋሪዎች አደረጃጀት ለሰራዊት ግንባታ አንዱ የትኩረት መድረክ ተደርጎ ተለይቷል፡፡ ለዚህም ስትራቴጂ የማዘጋጀት፣ አጀንዳ የመቅረጽና የሕግ ማዕቀፍ የማዘጋጀት ሥራዎች እየተካሄዱ ሲሆን ሲፀድቁ በስፋት የምንገባበት ይሆናል፡፡

## 1.2. የሚመለከታቸው አካላትን በብቃት የማሳተፍ አቅጣጫ መከተል

ዕቅድ በምናዘጋጅበት ጊዜ ባለሚናዎችን ማሳተፍ አለብን፡፡ በድርጅት በኩል ከመቼውም በተሻለ ሁኔታ የከተማ ሥራችን የሚከታተል ክንፍ ተደራጅቷል፡፡ ከፌደራል እስከ ከተማ የመንግስትና የድርጅት ክንፉ ተናበውና ተቀናጅተው መሄድ አለባቸው፡፡ ከሴክተሩ ግንኙነት ያላቸው ተገልጋዮች በመጀመሪያ እራሳቸውን እንዲያደራጁ ማነሳሳት ያስፈልጋል፡፡ በቀጣይም በጋራ በሚሰሩ ሥራዎች ዙሪያ መደበኛ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ማስፈጸም ተገቢ ይሆናል፡፡ ዕቅዱን በማስፈጸም በኩል ፈርጀ ብዙ ሚና ያላቸው ብዙ የመንግስት መ/ቤቶች በዕቅዱ እና በአፈጻጸም ዙሪያ በጋራ ተናቦና ተቀናጅቶ የመስራት ተነሳሽነትና ዝግጁነት እንዲፈጠር አቅዶ መስራት ያስፈልጋል፡፡ በየደረጃው ካሉ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤትም ጋር

በቅንጅት መሠራት ያለባቸው ሥራዎች በቅድሚያ ለይቶ ተደማሪ ለውጥ በሚያመጣ መልኩ አቅዶ መስራት ይጠይቃል፡፡ ከመገናኛ ብዙኃን፣ ከመንግስት የኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት፣ አርቲስቶች፣ ከጋዜጠኞች፣ ስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን እና ሌሎችም ተቋማት ጋር በሚያቀናጁ አጀንዳዎች ዙሪያ ተናቦ መስራት ለዕቅዱ የላቀ አፈጻጸም ትርጉም ይኖረዋል፡፡

## 1.3. የሥራ ውጤትን የሁለም ነገር ማጠንጠኛ የማድረግ አቅጣጫ መከተል

የሴክተሩ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማስፈጸም በየደረጃው የተቀመጡ ግቦች ሊመዘኑ የሚችሉ፣ የጊዜ ገደብ የተቀመጠላቸው፣ ፈጻሚ የተለየላቸው ተግባራት (Deliverables) እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ ከስራችን ጋር አግባብነት ያላቸውም ባለሚናዎች በጋራ የምንሰራቸውና በተናጠል የምንሰራቸውን ሥራዎች (Deliverables) በወጉ የለየና መግባባት ላይ እንዲደረስባቸው ይደረጋል፡፡ በሕዝቡም እንዲፈጸሙ የምንፈልጋቸው ተግባራትም (Deliverables) በአግባቡና በወቅቱ ለይተን ለሕዝቡ ቀርበው ውይይት ከተካሄደባቸው በኂላ ስምምነት ላይ እንዲደረስባቸው ይደረጋል፡፡ በሴክተራችን የሚዘጋጀው ዕቅድ ወጥነት ያለውና የተናበበ እንዲሆን የላይኛው መዋቅር ለታችኛው መዋቅር ሞዴል ዕቅድ አዘጋጅቶ እንዲሰጥና የታችኛው መዋቅር የራሱን ዕቅድ አዘጋጅቶ ለላይኛው መዋቅር ሲያቀርብለት ዕቅዱን በዝርዝር ገምግሞ የጽሑፍ ግብረ መልስ እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡ በአፈጻጸም ሪፖርትም ላይ በተመሳሳይ ክትትል ይደረጋል፡፡ ከሪፖርቶች በተጨማሪም የመስክ ኢንስፔክሽን ተካሄዶ የተደራጀ የሰርቬይ ሪፖርት ይቀርባል፡፡ የመስክ ቅኝትና የአፈጻጸም ሪፖርቱን በመያዝ የግምገማ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ውይይትም ይደረግበታል፡፡ የተሻለ ተሞክሮዎች ትምህርት ይወሰድባቸውል፡፡ ድክመቶች የሚስተካከሉበት አቅጣጫና መስማማት ይፈጠራል፡፡ በዚህ ሁሉ ሂደት ማጠንጠኛው ውጤት እንዲሆን ይደረጋል፡፡

## 1.4. በግልጽ ቅደም ተከተል የመምራት አቅጣጫ መከተል

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዳችን ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሴክተር የተሰጡ ተልዕኮዎች በሚከተለው ቅደም ተከተል የሚፈጸሙ ይሆናሉ፡-

1ኛ) የለውጥና የልማት ሠራዊት ግንባታ
2ኛ) የሥራ ዕድል ፈጠራና የአነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ማስፋፋት
3ኛ) የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ሥርዓት ማዘመን (መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ)
4ኛ) የተቀናጀ የመኖሪያ ቤት ግንባታ
5ኛ) የከተሞች መሠረተ ልማት ማስፋፋት
6ኛ) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አቅም ግንባታ
7ኛ) የከተሞች ያልተማከለ አስተዳደር፣ የሕዝብ ተሳትፎ እና የማስፈጸም አቅም ግንባታ
8ኛ) የከተሞች የፅዳትና የአረንጓዴ ልማት … ወዘተ እያለ ይቀጥላል፡፡

እነዚህ ሥራዎች በታቀደው ፍጥነት እንዳይፈፀሙ ማነቆዎች መፈጠራቸው አይቀርም፡፡ እንደማነቆዎቹ አቅም እና ደረጃ እንዳንዴ ምንም ፈቀቅ ማለት በማይቻልበት ደረጃ እግር ተወርች አስሮ እስከማቆም ሊደርስ ይችላል፡፡ የችግር አፈታትና የሀብት አመዳደብ ቅደመ ተከተላችን ከፍ ብሎ በተቀመጠው አግባብ እንዲሆን በማድረግ እንሠራለን፡፡

## 1.5. የእርሰ በእርስ የመማማር ሥርዓት የመዘርጋትና የመተግባር አቅጣጫ መከተል፡፡

በድርጅት መድረኮች በህዋስ፣ በመሠረታዊ ድርጅት፣ በወረዳ ስብሰባዎች አመራሩና ፈፃሚው እርስ በእርሱ መማማር ይችል ዘንድ የተሻሉ ተሞክሮዎች እንዲቀርቡ መበረታታት ይኖርባቸዋል፡፡ በመንግስት የግንባር ቀደም መድረኮችም በተመሣሣይ ተልዕኮ ሊሰጠው ይገባል፡፡ ከሌሎች መ/ቤቶችም በተለይ በምክንያታዊ አስተሳሰብ ግንባታ (Rational thinking) እና የአስተሳሰብና የባህሪ ለውጥ (Attitude change) ላይ እንግዳ አቅራቢዎች ስልጠና የሚሰጡበት መድረኮች እንፈጥራለን፡፡ አመራሩና ፈፃሚው በዘወትር የአስተባሰበና የተግባር መሻሻል ምህዋር ውስጥ እንዲገባ ታቅዶ ይሠራል፡፡ ለውጡንም በውጤት ላይ በሚታየው መሻሻል ለመለካት ጥረት ይደረጋል፡፡ በልማታዊ የአስተሳሰብና የተግባር ዝንባሌና በኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብና የተግባር ዝንባሌ መካከል የሚደረግ ትግል መሆኑ ስለማይቀር የውስጠ ድርጅት አሰራራችን የተጠናከረ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

## 1.6. የመስሪያቤቱ እሴቶች የአመራሩና የፈፃሚው የዕለት ተዕለት ባህሪይ ይሆኑ ዘንድ የተለያዩ የማስረጽ አቅጣጫዎች መከተል

### 1.6.1. የሁሉም አመራርና ሠራተኛ የጋራ እሴቶች

- የግልጸኝነት፣ የእውነተኝነትና የተጠያቂነት አሠራር መርህ ተከትዬ እሰራለሁ፡፡
- ለውጤታማነትና ለቀልጥፍና ዘወትር እተጋለሁ፡፡
- ሁሌም በማያቋርጥ የመማርና የመማር ምህዋር ውስጥ መሆኔን እገነዘባለሁ፡፡

### 1.6.2. ከሠራተኞች የጋራ እሴቶች በተጨማሪ አመራሩን በተለይ የሚመለከቱ እሴቶች፡-

- ለሕዝብ ጥቅም ቅድሚያ መስጠት እንዳለብኝ አምናለሁ፡፡
- ሁሉን ሰው እኩል ማየትና የተለያዩ ሃሳቦችን በአግባቡ ማስተናገድ የአመራር ግዴታዬ መሆኑንን እገነዘባለሁ፡፡

እንዚህ እሴቶች የመ/ቤቱ ባህል እንዲሁኑ ተግቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡

## 2. ቁልፍ ስጋቶችና የመፍትሔ አቅጣጫዎች

በዕቅድ አፈፃፀም ሂደት የሚታየው መሠረታዊ ችግር ለስምሪት የተላከው አመራርና ፈፃሚ ችግር ለይቶ ሪፖርት ማቅረብ እንጂ ፈትቶ ሲመጣ አይታይም፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ከችግሮች ሁሉ የከፋው ችግር ደግሞ ማነቆዎቹን በአግባቡ መለየት ያለመቻል ችግርም ቀላላ አይደለም፡፡ በየተግባሩ የሚታዩ

የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብና ተግባር፣ የክህሎት ችግሮች፣ የግብዓት ያለመሟላት፣ የክትትልና ድጋፍ መቆራረጥ፣ የግምገማና ግብረ መልስ ሥርዓት መቆራረጥና ያለበቂ ዝግጅት ማካሄድ በተደጋጋሚ የሚስተዋሉ ችግሮች ናቸው፡፡ ድክመት ሲኖር ማስታወሻ ይዞ ክፍተቱን በፍጥነት ለመድፈን የሚያስችል ዝርዝር ኦፐሬሽናል ዕቅድ አዘጋጅቶ ወደ ተግባር ሲገባ አይታይም፡፡ አንድ ችግር በተደጋጋሚ ሲነሳና መፍትሔ ሳይሰጠው ለብዙ ጊዜ ሲንከባለል ይስተዋላል፡፡

አንድ ሥራ በጥራትና በፍጥነት ለማስፈፀም ዝርዝር ዕቅድ የማዘጋጀት፣ በዕቅዱ ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በብቃት ተወያይቶ መረዳዳት፣ ሥራው የሚያስፈልገው ባለሙያ የማስማራት፣ ለሥራው የሚያስፈልገው ግብዓት የማደራጀት፣ በአፈፃፀም ሂደት ሥራውን በቅርብ የመከታተልና ችግሮች ሲያገጥሙ በቅርብ ሆኖ የመደገፍ እና ችግር የመፍታት ጥበብን ይጠይቃል፡፡ በመቀጠልም መርሃ-ግብሩን በጠበቀ መልኩ ዕቅዱን መሠረት ያደረገ የአፈፃፀም ሪፖርት የመቀበል፣ አፈፃሙን በመስክ ተገኝቶ የማየትና ሪፖርት የማዘጋጀት እና በአፈፃፀሙ ሂደት በነበሩ ስኬቶችና ውድቀቶች አመራሩና ፈፃሚው ተገናኝቶ የሚገመገምበት ሥርዓት ይጠይቃል፡፡ መልሶ መላልሶ በቀጣይ ተግባር አፈፃፀም ሂደት ይህንኑ መድገም ይጠይቃል፡፡ ልማትና መልካም አስተዳደር ማሳለጥ ማለት ባልተቆራረጠ መንገድ እንዚህን ተግባራት በቀጣይነት በጠንካራ ዲስፕሊንና ባልተቀዛቀዘ ኃይል በመታገዝ መደጋገም ማለት ነው፡፡ አብዛኛው አመራራችን ከፍ ተብሎ እንደተጠቀሰው በዚህ ልክ ለመንቀሳቀስ የመንፈስም ይሁን የተግባር ዝግጁነት አይታይበትም፡፡ አመራሩ በተሟላ መንገድ በኃይል ተሞልቶ ካለተንቀሳቀሰ ፈፃሚውም የራሱን ችግር ታክሎበት እንቅስቃሴው በክፉ ማነቆ መተብተቡ አይቀርም፡፡ የመንግስት አመራርና ፈፃሚው ባለተንቀሳቀበሰበት ህብረተሰቡን ማንቀሳቀስ ደግሞ ከግብር ይውጣ ያልተናነሰ ስብሰባ ማካሄዳ ካልሆነ በተስተቀር በቂ ዝግጅት አድርጎና ለውጤት አነሳስቶ መሄድ አይቻልም፡፡

በመሆኑም ዋነኛ የርብርብ ማዕከላችን አመራሩን በማብቃትና በምክንያት የማመን አቅሙ ማጎልበት ላይ ትኩረት ሰጥተን እንሰራለን፡፡ በመንሰኤና ውጤት ትስስር ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲይዝ ይደረጋል፡፡ የአመራሩ መነቃነቅ ፈፃሚውን፤ የፈፃሚው መነቃነቅ ደግሞ የህብረተሰቡ ንቅናቄ እንደሚፈጠር ውይይት በማድረግ መግባባት ላይ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ በዚህ ሂደት መንገዋለል ያለበትም እንዲገዋለል ይደረጋል፡፡ ማደግ ያለበትም በተመሳሳይ ተገቢው ግብረ-መልስ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ቁልፍ ማጠንጠኛው በዚህ ላይ አድርገን ሌሎቹ ማነቆዎችም በተመሣሣይ እና በየደረጃቸው ትኩረት ሰጥተን እንሰራለን፡፡

# ክፍል አምስት

# የ2005 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስ ሥርዓት

በየደረጃው ያሉ የአመራር አካላት የዕቅድ አፈጻጸሞች በመደበኛነትና በቅርብ ሆነው በሚዛናዊ ውጤት ተኮር የምዘና ሥርዓት ጥናት እና የመሠረታዊ አሠራር ለውጥ ጥናት በሚያመለክቱት የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መሠረት መከታተል ይኖርባቸዋል፡፡ ለዚህም የሚከተሉት የክትትል መሣሪያዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## 1. መደበኛ የመረጃና የሪፖርት ልውውጥ

1) ቢሮዎች የእያንዳንዱን ሠራተኛ የዕለታዊ ሪፖርት በየመምሪያው በማጠናቀር ሣምንታዊ ሪፖርት ለቢሯቸው ያቀርባሉ፣የተጠቃለለ ወርሃዊ ሪፖርት በማዘጋጀት በፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ ለከተማ ልማት ዘርፍ የፖሊሲና ፕሮግራም አፈጻጸም ክትትል መምሪያ እና ለኮንስትራክሽን ዘርፍ የፖሊሲና ፕሮግራም አፈጻጸም ክትትል መምሪያ ይቀርባል፡፡ ሁለቱ መምሪያዎች የቀረበላቸው ሪፖርት ላይ ዝንባሌያዊ ትንተና በማካሄድ የየመምሪያዎቹም ወርሃዊ ሪፖርት በየወሩ ለዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸም ክትትል መድረክ ይቀርባል፣
2) በየቢሮው ሥራ አመራር ኮሚቴ ተገምግሞ የጸደቀ የእያንዳንዱ ቢሮ ወርሃዊ፣ የሩብ ዓመት፣ የግማሽ ዓመት፣ የዘጠኝ ወርና ዓመታዊ ዝርዝር የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ ለዕቅድ ዝግጅት፣ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ መምሪያ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ መምሪያውም ከየቢሮዎቹ የቀረቡለትን ሪፖርቶች በመጭመቅና በማጠቃለል ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ አመራሮችና ለሚኒ ካቢኔ አባላት ያቀርባል፣
3) የሪፖርቶች አቀራረብ የሴክቶራልና የተቋማዊ ዕቅድ አፈጻጸምን በማጣመር በበጀት ዓመት ዕቅዱ ላይ የተቀመጡትን ግቦችና ዋና ዋና ተግባራትን መሠረት ያደረገ ሆኖ ውጤቶች ላይ ያተኮረ መሆን ይኖርበታል፣
4) ሪፖርቱ በዕቅዱ የተቀመጡ ግቦችን ከአፈጻጸም ጋር በማነጻጸር ምን ያህል እንደተሳካ፣ ካልተሳካም ለምን እንዳልተሳካ የሚገልጽ፤
5) በዕቅድ አፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸውን የያዘ፤
6) የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች፣ የነበሩ መልካም ተሞክሮዎችንና ቀጣይነታቸውን ለማረጋገጥና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ወደ ሌሎች ለማስተላለፍ መከናወን ያለባቸውን ተግባራት እንዲሁም ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች ያመላከተ፤
7) በሪፖርት ማድረጊያ ጊዜ በጅምር ላይ ያሉ ሥራዎች የሚጠናቀቁበትን ጊዜ የሚጠቁም፤

8) የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች የተቋሙን የወቅቱን የአፈጻጸም ደረጃ የምዘና ውጤት የሚያሳይ መሆን ይኖርበታል፣

9) ወርሃዊ ሪፖርት በየግቡ ሥር እየተከናወኑ ባሉ ዋና ዋና ሥራዎች ላይ በማተኮር የተዘጋጀ አጭር ዘገባ ወሩ በተጠናቀቀ በመጀመሪያው ሳምንት ባሉ 5 ቀናት የሚቀርብ ይሆናል፣

10) የሩብ ዓመት፣ የግማሽ ዓመት፣ የዘጠኝ ወራት እና ዓመታዊ ሪፖርት ዘርዘር ያሉ የአፈጻጸም ሪፖርቶች ከነማብራሪያው በመያዝ የየሩብ/ግማሽ ዓመቱ ወይም የእቅድ ዘመኑ በተጠናቀቀ በአምስት ቀናት ውስጥ ተዘጋጅቶ መቅረብ ይኖርበታል፣

11) በየደረጃው ተገምግሞ በመጨረሻ መልኩ የሚወጣው የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ታትሞ በየሦስት ወሩ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር፣ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ለሚኒስትሮች ም/ቤት እና ለሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ይሰራጫል፣

12) እያንዳንዱ ሠራተኛ የግሉን የዕለት ተዕለት አፈጻጸም በመከታተል የረጅም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ እራስን የማብቃት ዕቅድ አፈጻጸም ደረጃ ይለካል፤ ለዚህም የእራስን ማብቃት ዕቅድ (Self development plan) ይኖረዋል፡፡ በመምሪያዎች የአሃድ ውይይቶች ላይ የአፈጻጸም ደረጃው ይገመገማል፡፡

## 2. የመስክ ጥናት

በበጀት ዓመቱ ዕቅድ የተቀመጡትን ሥራዎች አፈጻጸም በቀጣይነት ለመከታተል የምንጠቀምበት ሌላው መንገድ የመስክ ጥናት ነው፡፡ በመሆኑም አስፈጻሚ ቢሮዎች በእቅድ የተያዙ ፕሮግራሞችን አፈጻጸም በተመለከተ በመስክ በአካል ተገኝቶ መደበኛ የመስክ ክትትልና ግምገማ ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ በመስክ ግምገማው በየፕሮግራሞቹ ሥር የሚካሄዱ ፕሮጀክቶችን በመጎብኘት እና ስለአፈጻጸማቸው አግባብነት ካላቸው የክልልና የከተማ አስተዳደር አካላት ጋር አጠቃላይ ውይይት በማካሄድ ከማዕከል የሚጠበቀውን ድጋፍ መሰጠቱን የማረጋገጥ እና የመስክ ግምገማውን ሪፖርት የማዘጋጀት ተግባራት ይከናወናል፡፡

## 3. የሴክተር ተቋማት ምዘናና ግብረመልስ ማከናወን

በበጀት ዓመቱ በዕቅድ የያዝናቸው ሥራዎች አፈጻጸም ከምንከታተልባቸው ዘዴዎች መካከል አንዱ በዓመት ሁለት ጊዜ የሴክተር ተቋማትን እቅድ መሠረት አድርጎ በተዘጋጀ ቼክ ሊስት መሰረት በክልሎች/ከተሞች በመገኘት የዕቅድ የአፈፃፀም ምዘና ማከናወን ነው፡፡ ይህ ምዘና በፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ አስተባባሪነት ከሚመለከታቸው የፌደራል ተቋማት በተወጣጡ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተቋማት ባለሙያዎች አማካኝነት የሚከናወን ይሆናል፡፡ የምዘናው ውጤት ሪፖርት ተዘጋጅቶና ውይይት ተደርጎበት ከጸደቀ በኋላ የዘርፉ አፈጻጸም በሚገመገምበት የሴክተር ጉባኤ ላይ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበት ግብረ-መልስ ይሰጣል፡፡

## 4. የሴክተር ጉባኤ ማካሄድ

በፌደራል፣ በክልል እና በከተሞች መካከል የሚካሄድ የሴክተር ጉባኤ አንዱ የዕቅድ አፈጻጸም የምንገመግምበት ዘዴ ሲሆን በሁለት መንገዶች ማለትም መድረክ በማመቻቸት እና በቪዲዮ ኮንፍረንስ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በሚካሄድ የጋራ መድረክ አማካኝነት ይከናወናል፡፡ የጋራ መድረኩ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሥር የሚገኙ ቢሮዎችና ተጠሪ ተቋማት፣ ክልሎች፣ ከተሞች እና የከተማልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት በዕቅድ አፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙዋቸውን ችግሮች በተመለከተ መፍትሔ በጋራ ለማፈላለግ፤ ከማዕከል የሚጠበቁ ድጋፎችን በተገቢው መንገድ መሰጠታቸውን ለማረጋገጥ፤ ጉድለት በታየበት አካባቢ ለማጠናከር ግብረ-መልስ ለመስጠት እና የተሻሉ ተሞክሮዎችን ለይቶ በማውጣት ለመማማር የሚችሉበት ነው፡፡

## 5. ከክልሎችና ከሌሎች አካላት ጋር የሚደረግ መደበኛ የሪፖርት ልውውጥ

ለበጀት ዓመቱ የታቀዱት ሥራዎች በርካታ ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፉ ናቸው፡፡ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚ/ር አንዱ ሚና የነዚህን የባለድርሻ አካላትን ትስስርና ቅንጅታዊ አሰራሮችን ማስተባበር በመሆኑ በነዚህ አካላት የሚፈጸሙ ተግባራትን በመደበኛነት መከታተል ይጠበቅበታል፡፡ ስለሆነም የክልል እና የከተማ አስተዳደሮች የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት እንዲሁም ተጠሪ ተቋማት ስለ ሥራ አፈጻጸማቸው በመደበኛነት መረጃዎችንና ሪፖርቶችን እንዲልኩ በማድረግ ይከታተላል፡፡ ከፌደራል፣ ከክልልና ከከተማ አሰተዳደሮች የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት ጋር የሚኖረው የክትትል ሥርዓት በመደበኛ ስብሰባና በመስክ ጉብኝት የሚታገዝ ሲሆን ከዚህ የክትትል ሥርዓት የሚገኙትን መረጃዎች በማጠናቀር ለዕቅዱ አፈጻጸም መሻሻል የምንገለገልባቸው ይሆናል፡፡ በዚሁ መሠረት፡-

- ሀ. በሚ/ር መ/ቤቱ የሚገኙ ተቋማት በየክልሉና ከተማ አስተዳደሮች ከሚገኙ አቻ ተቋማት ጋር በተፈራረሙት ዕቅድ መሰረት የአፈጻጸም ሪፖርት በማሰባሰብ ግምገማ ያካሂዳሉ፣
- ለ. በየክልሉና ከተማ አስተዳደሮች የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮዎች የክልሉን የተጠቃለለ ሪፖርት አዘጋጅተው ለፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ በየሩብ ዓመቱ እንዲልኩ በማድረግ የዕቅድ ዝግጅት፣ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ መምሪያ የቀረበውን ሪፖርት የዝንባሌ ትንተና በማድረግ ለበላይ አመራሩ ያቀርባል፣ ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮችም ግብረ መልስ ይሰጣል፣

## 6. የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማና ግብረ-መልስ ሥርዓት

### 6.1. በዕቅዱ የተቀመጡትን ግቦች መሠረት ያደረገ ግምገማ ማካሄድ

ሀ) በዕቅዱ ላይ የተቀመጡት ዋና ዋና ሥራዎች ላይ ያተኮረ፤ በምን ያህል መጠን፣ በጀት እና ጊዜ እንደተከናወኑ የሚያሳይ መደበኛ የሥራ ግምገማ በየደረጃው እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡

ለ) በሚኒስቴሩ ሚኒ-ካቢኔ ደረጃ በየወሩ፣ በሩብ ዓመቱ፣ በግማሽ ዓመት እና በአመቱ መጨረሻ ላይ ዝርዝር የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ይካሄዳል፡፡ የየሩብ ዓመቱ የሚኒ ካቢኔ ግምገማ የመምሪያ ኃላፊዎችን የሚያሳትፍ ይሆናል፡፡ እያንዳንዱ ቢሮ በተመሳሳይ መልኩ ከሠራተኞች ጋር በመደበኛነት ግምገማ የሚያካሄድ ሲሆን ግምገማውም በተቋሙ ዕቅዶች ላይ ያተኮረ መሆን ይኖርበታል፡፡

ሐ) ግምገማውን ይበልጥ ለማዳበር የባለሙያዎች የሥራ ተነሳሽነት ለማሻሻል ሚኒስቴሩ ከጠቅላላ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኞች ጋር በዓመት ሁለት ጊዜ የዕቅድ አፈጻጸሙን በጋራ ይገመግማል፡፡

መ) ሚኒስቴር መ/ቤቱ የእቅድ አፈጻጸሙን ከክልል እና ከተማ አስተዳደሮች የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት ጋር በየሩብ ዓመቱ በቪዲዮ ኮንፈረንስ እንዲሁም በግማሽ ዓመትና በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በጋራ መድረክ ሴክተር ጉባኤ ላይ ይገመገማል፡፡ ይህም በዕቅዱ ላይ በተቀመጡ ግቦች ላይ ያተኮረ ይሆናል፡፡

ሠ) በልማት ሥራዎች ላይ እያንዳንዱ ፈጻሚ ቢሮ በመርሃ-ግብሩ የተቀመጠውን የጊዜ ገደብ በመጠበቅ ብቻ ሳይሆን የጊዜ ዝንፈት ሳይከሰት ወይም ከጊዜ ገደቡ በፊት በሚፈለገው የሥራ ጥራትና በተመደበው የበጀት መጠን መሠረት መፈጸሙን እያረጋገጡ ለመሄድ የሚያስችል የክትትልና የግምገማ ሥርዓት እንዲኖር ይደረጋል፡፡

ረ) የመምሪያዎች አፈፃፀም ግምገማ በሣምንት 2 ቀናት የሚካሄድ ሲሆን በየወሩ የሚካሄደው የሚኒ-ካቢኔ ግምገማ በወሩ መጨረሻ ለአንድ ቀን ይካሄዳል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሚያካሂደው የየሩብ ዓመቱና የዓመቱ ግምገማ ከ2-3 ቀናት በመመደብ የሚከናወን ይሆናል፡፡

## 6.2. ግምገማ በማካሄድ ግብረ-መልስ መስጠት

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሐምሌ 1 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን የ2005 በጀት ዓመት ዕቅዱን ለማሳካት ሥራዎችን በየዕለቱ፣ በየሳምንቱ፣ በየወሩ፣ በሩብ ዓመት፣ በግማሽ ዓመት፣ በዘጠኝ ወር እና በዓመት ለመገምገም እና የአፈጻጸም ደረጃዎችን በመመዘን ግብረመልስ መስጠት የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቷል፡፡ የክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮች፣ ተጠሪ ተቋማት፣ ቢሮዎችና መምሪያዎች በተዘጋጀው የተቋማት የውጤት ተኮር ዕቅድ መሰረት የዕቅድ አፈጻጸም ደረጃ ተመዝኖ በሚኖራቸው የምዘና ውጤት መሰረት በወቅቱ ግብረመልስ ይሰጣል፡፡ የፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮም የዚህን ፕሮግራም ተግባራዊነት ተከታትሎ በተደራጀ መልኩ ያስፈጽማል፡፡ በሌላ በኩል የሠራተኛውን የስራ ተነሳሽነት ለማሳደግ እና አፈጻጸሙን ለማሻሻል ግልጽና ዲሞክራሲያዊ በሆነ አግባብ ገምግሞ ዕውቅና መስጠት ተገቢ በመሆኑ፡-

ሀ) በፌደራል ደረጃ በሚገኙ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት ሥር የሚገኝ እያንዳንዱ ሠራተኛ የየዕለት ክንውኑን በየዕለቱ ከ11፡00 እስከ 11፡30 ሠዓት በሠራተኛ የራስ ማብቃት ዕቅድ መሰረት የዕለታዊ የአፈጻጸም ሂደቱን ይገመግማል፡፡ መምሪያዎች ከመምሪያዎቹ ሳምንታዊ ዕቅድ በመነሳት የመምሪያውን ሠራተኞች በሳምንት ሁለት ጊዜ ማክሰኞና ሐሙስ በመገምገም ደረጃ የሚሰጡ ሲሆን ይህንኑ ለቢሮው በየሳምንቱ ያቀርባሉ፡፡ በመምሪያው ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ የወጡ ኮከብ ሠራተኞችን ዕውቅና ይሰጣሉ፤ የመምሪያዎቹ ሳምንታዊ የሥራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባ ቀንና ሠዓት በተቋማቱ የስብሰባ መርሐ-ግብር መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፤

ለ) ቢሮዎቹም የመምሪያዎቹን ሳምንታዊ የሠራተኞች ውጤት ያሰባስባሉ፤ በየሳምንቱ በሚከናወነው የተቋማቱ የሥራ አመራር ስብሰባ የየመምሪያዎቹን አፈጻጸም መሠረት በማድረግ ያላፈውን ሳምንት እና የቀጣይ ሳምንት ሥራዎች ላይ ይወያያሉ፤ የሳምንቱ ቀን ኮከብ ሠረተኞችን ለይተው ይይዛሉ፤

ሐ) ቢሮዎቹ የስድስት ወር የኮከብ ሠራተኞቻቸውን ፎቶ እና የአፈጻጸም ደረጃ በተቋሙ ማስታወቂያ ቦርድ ላይ ይለጠፋሉ፤

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሚኒካቢኔ በየወሩ የቢሮዎቹ ያለፈው ወር አፈጻጸምና የቀጣይ ወር ዕቅድ የሚገመገም ሲሆን የቀጣይ ወር የትኩረት አቅጣጫ ያስቀምጣል፣
- ይህ በየሩብ ዓመቱ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሚኒ ካቢኔ ተገምግሞ የየተቋማቱ የኮከቦች ኮከብ ተለይተው ግብረመልስ ይሰጣል፤
- በስድስት ወር በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሚኒ ካቢኔ ተገምግሞ የየተቋማቱ የኮከቦች ኮከብ እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ ደረጃ ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ የወጡ ሠራተኞች ተለይተው ግብረመልስ ይሰጣል፤

ለዚህ አፈጻጸም ሁሉም ተቋማትና መምሪያዎቻቸው ጉልህ ድርሻ ያላቸው ሆኖ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የማስፈጸም አቅምና የለውጥ ሥራ አመራር ቢሮ አሠራር በመዘርጋት፤ ከየመምሪያዎቹ መረጃውን በማሰባሰብና አፈጻጸሙን በመከታተል እንዲያስፈጽም ይደረጋል፡፡

### 6.3. የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶችን ለበላይ አካላት በመደበኛነት ማቅረብ

ከላይ በተገለጸው መሠረት ተገምግሞ የሚዘጋጀው የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በመደበኛነት ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር፣ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ይቀርባል፡፡ ሚኒስቴሩ ሲጠራም በበላይ አመራሮቹ አማካይነት በአካል ቀርቦ ሪፖርቱን ያሰማል፡፡

## 6.4. ቀልጣፋና ውጤታማ አሰራርን የሚያረጋግጡ ቅንጅታዊ አሠራርና አደረጃጀቶችን መፍጠር

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለ2005 በጀት ዓመት ያቀዳቸው ሥራዎች በርካታ የፌደራልና የክልል አካላትን የሚያሳትፉ በመሆናቸው የዕቅዱ መሳካት የነዚህን አካላት የተሳለጠ ቅንጅታዊ አሠራር የሚጠይቅ ነው፡፡ በተጨማሪም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥር የተደራጁ ተቋማት ተናበውና ተደጋግፈው መንቀሳቀስ ለዕቅዱ መሳካት ወሳኝ ነው፡፡ ስለሆነም ባለፉት ዓመታት የተጀመረውን የቅንጅት ሥርዓት ይበልጥ ማጠናከር እጅግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በዚሁ መሰረት፡-

ሀ) የሚኒስቴሩ ሚኒ-ካቢኔ በተሟላ ሁኔታ ተግባሩንና ኃላፊነቱን በመወጣት ላA ያለ ሲሆን አዲስ ለተፈጠሩት የሥራ ሂደቶች የማኔጅመንት ኮሚቴዎችን በማቋቋም እና የሁሉም ተቋማት መምሪያዎችን ሥራ በየሳምንቱ የሚገመግምበትን ሥርዓት በማጠናከር ቀጣይነቱን ማረጋገጥ ፣

ለ) የመሠረታዊ አሠራር ለውጥ ጥናት ባመላከተው መሠረት የተፈጠሩት አደረጃጀቶች ቀልጣፋና ውጤታማ አሠራርን የሚያረጋግጡ መሆናቸውን በመፈተሽ ወቅታዊ ማሻሻያ ማድረግ፣

ሐ) ከክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ግንኙነት በየወቅቱ በመፈተሽ አስፈላጊ ማሻሻያዎችን ማድረግ፣

# 7. ምርጥ ልምዶችን የመለየትና የህዝብ ግንኙነት ሥራዎች

## 7.1 ምርጥ ልምዶችን /Best Practices/ የመቀመርና የማስተላለፍ ሥርዓት

ሀ) በሚካሄዱ ክትትሎችና ግምገማዎች በዋና ዋና ፕሮግራሞች ላይ በማተኮር ምርጥ ልምዶችን መለየት፤

ለ) የተለዩት ምርጥ ልምዶች በባለሙያ ቡድን በዝርዝር እንዲጠኑ ማድረግና ፋይዳቸው ከፍተኛ ሆኖ ሲገኝ ልምዶቹ እንዲቀመሩ ማድረግ፤

ሐ) በዓመታዊ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሴክተር ጉባኤ እንዲሁም የከተሞች የመልካም አስተዳደር ኮንፈረንሶችን በማዘጋጀት የተለዩትን ምርጥ ልምዶች ውይይት እንዲካሄድባቸውና የበለጠ እንዲዳብሩ ማድረግ፤

መ) በዚህ መልክ ዳብረው የሚወጡ ፋይዳቸው ልቆ የተቀመሩ ምርጥ ልምዶች ታትመው እንዲወጡ ማድረግ፤

ሠ) ምርጥ ልምዶችን በተለያዩ አግባቦች በሁሉም አካላት ዘንድ ማስተዋወቅና ማስረጽ፤

ረ) ምርጥ ልምዶቹ መመሪያዎችንና ሌሎች አሠራሮችን ለማሻሻል ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ ይሆናል፡፡

## 7.2 የህዝብ ግንኙነት ሥራ

ሀ) በከተሞች በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት፣ በመሬት ልማትና ማኔጅመንት፣ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ልማት፤ በመሠረተ ልማት ማስፋፋት፤ በመልካም አስተዳደርና በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ የተከናወኑ ስራዎችን ለህዝብ ማስተዋወቅ፤

ለ) ለከተማ ነዋሪዎችና ባለድርሻ አካላት ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ በመስጠት ለከተማ ልማታችን ስኬት መፋጠን የበኩላቸውን እንዲወጡ የማድረግ፣ የማሳወቅ፣ የማሳመን እና ለተግባር መነሳሳትን መሰረት ያደረጉ ወቅታዊና ጥራታቸውን የጠበቁ አብስትራክትና ህትመቶችን በማዘጋጀትና በማሰራጨት በትኩረት መስኮች ዙሪያ የጋራ መግባባትን መፍጠር፣

ሐ) የሚኒስቴር መ/ቤቱን የሩብ ዓመት፣ የግማሽ ዓመት የዘጠኝ ወር እና ዓመታዊ የስራ አፈጻጸሞችን ለህዝብ የሚያሳውቅና የሚገልጽ ቢያንስ 5 ፕሬስ ኮንፈረንስ ማዘጋጀት፤

መ) በኢትዮጵያ ከተሞች ቀን እና በተለያዩ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚከናወኑ መድረኮች የሚታተሙ ባነሮች እና ሌሎች ህትመቶችን ማሳተም፤

ሠ) ብሔራዊ፣ አህጉራዊና ዓለምአቀፋዊ በአላት ከከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት አጀንዳ ጋር ተያይዘው እንዲከበሩ ማድረግ፤

ረ) የሚኒስቴር መ/ቤቱን የማህበራዊ ኮሚቴ የአገርህን እወቅ ጉብኝት በልማት ክንውኖች እንዲያከብር የማስተባበር ተግባራት ማከናወን፣

ሰ) የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተቋማቶች ልዩ ልዩ የስራ ክንውን የኦዲየቪዥዋል ቀረጻና የፎቶ አውደ ርዕይ ማዘጋጀት፣

ቀ) የየሩብ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸሞችንና ተሞክሮዎችን የሚያሳውቅና ግንዛቤ የሚያስጨብጥ የዜና መጽሄት ማዘጋጀት ናቸው።

# ክፍል ስድስት

## ማጠቃለያ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአምስት ዓመቱን የሃገር አቀፍ እና የዘርፉን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ፣ በየንዑሳን ዘርፎቹ የተዘጋጁ ስትራቴጂዎችንና ፕሮግራሞችን እንዲሁም የ2004 በጀት ዓመት አፈጻጸምና የተገኙ ውጤቶችን ዳሰሳ መነሻ በማድረግ የ2005 በጀት ዓመት ዕቅድ አዘጋጅቷል፡፡

በቀጣይ የልማት ዕቅድ ዘመን በሁሉም ፕሮግራሞች ባለፉት ዓመታት የተገኙትን ውጤቶች ይበልጥ በማጐልበት፣ ሳይፈጸሙ የቀሩትን በተሟላ መልኩ በማከናወን እና ከወቅቱ ትኩረት አኳያ ተጨማሪ አዳዲስ ኘሮጀክቶችን በማካተት አጠቃላይ አፈጻጸም ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ በሚያስችል መልኩ ይህ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

በዚህ በጀት አመት እንዳለፉት በጀት ዓመታት የለውጥ እና የልማት ሠራዊት ግንባታ ሥራችን ቁልፍ ተግባር ሆኖ ይቀጥላል፡፡ ይህ በጀት ዓመት ባለፉት በጀት ዓመታት የተጀመሩ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተጠናቀው ወደ ትግበራ የተገባበት ማግስት በመሆኑ በ2004 በጀት ዓመት የተገኙ ጅምር ውጤቶችን አጠናክሮ በመቀጠል እንዲሁም በዘርፉ የሚታየውን የኪራይ ሰብሳቢነት ተግባርና አመለካከት በጽናት ለመታገል የሚችል አመራርና ባለሙያ በየደረጃው ከፌዴራል እስከ ታችኛው የዘርፉ መዋቅር ድረስ የለውጥና የልማት ሰራዊት ግንባታው ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ እንዲሁም ዋነኛው ስትራቴጂዊ ግባችን የሆነው የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ ሥራችን እንደ 2004 በጀት ዓመት አመርቂ አፈጻጸም ሁሉ በዚህም የዕቅድ ዘመን በተሻለ ደረጃ በመፈጸም ለዜጎቻችን በሚሊዮን የሚቆጠር የሥራ ዕድል ይፈጠራል፡፡ የመሬት ልማትና አስተዳደር፣ የመኖሪያ ቤት አቅርቦት፣ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ፣ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው አቅም ግንባታ፣ የከተሞች የመልካም አስተዳደር እና አቅም ግንባታ እና የከተሞች ጽዳትና ውበት ሥራዎቻችንን በትምህርታዊና ልማታዊ ኮሚዩኒኬክን ሥራዎች በማጀብ በላቀ ደረጃ ይፈጸማሉ፡፡

በተጨማሪም ዘርፉ ከሚጠበቅበት ሀገራዊ ተልዕኮ አንጻር በፌዴራል እና በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች መካከል ያለውን ልማታዊ ግንኙነት እና የአሰራር ሥርዓት ዘላቂነት ባለዉ መንገድ ለመምራት እንዲቻል የቅርብ ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ እቅዱን ከማስፈጸም በተጨማሪ የስርዓት ዝርጋታው ስራዉን እንደመሰረታዊ ምሶሶ በመያዝ መንቀሳቀስ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት ይከናወናል፡፡ በአጠቃላይ በዕቅዱ የተመለከቱትን ሥራዎች አፈጻጸም የአሰራርና የአመራር ሥርዓት በመዘርጋት የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡ በክትትልና ድጋፉ ወቅት ከሚገኙት እውነታዎችም በመነሳት

አስፈላጊው ግብረ-መልስ ይሰጣል፡፡ የተሻሉ ተሞክሮዎች የሚስፋፉበትና ጉድለቶች በግምገማ ነክ ሥልጠና ይሞላሉ፡፡

በመጨረሻም ይህ ዕቅድ መሪ ዕቅድ እንደመሆኑ መጠን ዕቅዱን መሠረት በማድረግ ሁሉም ክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮች፣ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተጠሪ ተቋማት እና ቢሮዎች የየራሳቸውን ዝርዝር ዕቅድ በማዘጋጀት መተግበርን ይጠይቃል፡፡ አስፈጻሚ አካላትም ሥራቸውን በተናጠል እንደሚሠሩ ሳይሆን ተመጋጋቢና ቅንጅታዊ የአሠራር ዘዴ በመከተል በየጊዜው የላቀ ውጤትን (Synergy) ማስመዝገብ በሚያስችል እና የጋራ የሆነውን ዓላማና ግቦች እንዲሁም ራዕይ ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ ታላሚ ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡